ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE



# ብሄራዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መተግበሪያ መመሪያ

ነሐሴ 2011 ዓ.ም
አዲስ አበባ



ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# ብሄራዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መተግበሪያ መመሪያ

## በአነስተኛ መስኖ ልማት ዳይሬክቶሬት እና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

ነሐሴ 2011 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ብሄራዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መተግበሪያ መመሪያ

## አዘጋጆች (በፊደል ቅደም ተከተል)


| | |
|---|---|
| አቶ መኮንን በቀለ ገ/ሥላሴ፡- | ከግብርና ሚኒስቴር የአነስተኛ መስኖ ልማት ዳይሬክቶሬት የምጣኔ ሀብት ባለሙያ |
| አቶ በለጠ በንቴሮ | በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የመስኖና ድሬይኔጅ ፕሮግራም ትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ስፔሻሊስት |
| አቶ ቡርቃ ቡላሾ ሻሻሞ፡- | ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት የአነስተኛ እና ጥቃቅን መስኖ ድጋፍ ሰጪ ፕሮጀክት ከፍተኛ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያ |
| አቶ ተሾመ ኃ/ገብርኤል ተ/ማርያም፡- | ከግብርና ሚኒስቴር የኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ የአፈርና ውሃ ጥበቃ እና ልማት ባለሙያ |
| አቶ ታጠቅ ገብረአብ ገብረጊዮርጊስ፡- | ከኦሮሚያ ክልል የአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ ድጋፍ ሰጪ ፕሮጀክት ከፍተኛ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያ |
| ዶ/ር አካሉ ተሾመ ፍሬው፡- | ከግብርና ሚኒስቴር የኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት የማህበራዊ ምጣኔ ከፍተኛ ተመራማሪ |
| አቶ ፈንታ ይማም ያሲን፡- | ከግብርና ሚኒስቴር የኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ የኤክስቴንሽን ኮሚዩኒኬሽን ባለሙያ |
| ኢ/ር ዘለቀ በላይ አድማሱ፡- | ከግብርና ሚኒስቴር የአነስተኛ መስኖ ልማት ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ የመስኖ መሃንዲስ |
| አቶ ይሁኔ አለምነህ ተገኝ፡- | ከግብርና ሚኒስቴር የአነስተኛ መስኖ ልማት ዳይሬክቶሬት የምጣኔ ሀብት ባለሙያ |


## ለመመሪያው ዝግጅት አስተዋፅኦ ያደረጉ

የአነስተኛ እና ጥቃቅን መስኖ ድጋፍ ሰጪ ፕሮጀክት እና የአራቱም ክልሎች የግብርና ቢሮ የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደ/ብ/ብ/ሕ እና ትግራይ)

## የመጀመሪያ ዕትም
## ነሐሴ 2011 ዓ.ም

በግብርና ሚኒስቴር የአነስተኛ መስኖ ልማት ዳይሬክቶሬት እና የኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት በጋራ ትብብር የተዘጋጀ ነው፡፡

## ስለዚህ ዕትም

ይህ መመሪያ የመጀመሪያ ዕትም ሲሆን የተዘጋጀው ለባለአነስተኛ ይዞታ የመስኖ ልማት ተጠቃሚዎች የሚሰጠውን የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለማረጋገጥ እና መሠረት ለመጣል እንዲሁም በመስኖ ልማት ሥራ ላይ ተሰማርተው ለሚገኙ የመስኖ ባለሙያዎችና የመስኖ ልማት ሠራተኞች ሙያዊ ድጋፍና መመሪያ ለመስጠት ያገለግላል፡፡

# መልዕክት

የባለአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት አርሶ አደሩንና ከፊል አርብቶ አደሩን ወደ ገበያ ተኮር የኢኮኖሚ ሥርዓት እና ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ሰብሎች ወደ ማምረት ማሸጋገር እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም ዘላቂ የአረንጓዴ ግብርና ልማት አቅጣጫ ነው፡ ፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት መንግስት ለእያንዳንዱ አርሶ/አርብቶ አደር ቤተሰብ ለሙሉ ወይም ለደጋፊ መስኖ የሚውል ቢያንስ አንድ የመስኖ ውሃ አማራጭ እንዲኖረው ለማስቻል ግልጽ የሆነ የአጭርና የረጅም ጊዜ ግብ አስቀምጧል፡፡ በሀገር ደረጃ የአነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደር ይዞታ የመስኖ ስትራቴጂ መረጃ ምንጭ መሰረት ኢትዮጵያ 11 ሚሊዮን ሄ/ር በመስኖ የማልማት አቅም ያላት ሲሆን አማካይ የአርሶ/አርብቶ አደር መስኖ ገብ ይዞታ 0.3 ሄ/ር ቢሆን ወደ 30 ሚሊዮን የሚደርሱ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ ስለሆነም የግብርና ሚኒስቴር በበኩሉ የባለአነስተኛ መሰኖ ይዞታ አርሶ/አርብቶ አደሮች የመስኖ ልማት ስትራትጂና ፕሮግራሞችን ለማስፈፀም ዝርዝር መመሪያዎችና ደንቦችን ለሁሉም የዘርፉ ፈጻሚ አካላት ማድረስ ወሳኝ ሚና እንዳለው በመገንዘብ የግብርና ሚኒስቴር የኤክሰቴንሽን አገልግሎቱን በማጠናከር ዘላቂና አስተማማኝ የመስኖ ልማት አግልግሎትን ለማረጋገጥ ከመስኖ ልማት ፍላጎት ልየታ የዳሰሳ ጥናት፣ ጥናትና ዲዛይን፣ ግንባታና ክትትል፣ ውሃ አጠቃቀም፣ የተለያዩ የተሻሻሉ መስኖ አሰራሮችንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በማስተዋወቅና በማላማድ፤ ብሎም ተጠቃሚ ለማድረግ ሀገራዊ የሆነ የመስኖ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አተገባበር መመሪያ በማዘጋጀት ከፍተኛ የሆነ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ከላይ ተመለከተውን ሰፊ የሆነ የግብርና ልማት ዘርፍ ዘላቂና አስተማማኝ ለማድረግ የመስኖ ልማት  ኤክስቴንሽን በዋናነት አነስተኛና ሰፋፊ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን በማቋቋምና በማደራጀት ሁለንተናዊ የመስኖ ውሃ ልማትና አስተዳደር ለአነስተኛና ሰፋፊ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች የምክርና የስልጠና ድጋፍ አገልግሎት በመስጠት የመስኖ ሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የመስኖ ምርት ገበያ ትስስርን ለማዘመን፣ የተሻሻሉና አዳዲሰ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም ተግባራዊ ለማድረግ፣ የመስኖ ግብዓት አቅርቦትን ለማሳለጥ፣ አነስተኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎትን በማጠናከር ዕውቀትና ክህሎትን በማዳበር ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር የማስፋት ስራ በመስራት ተጠቃሚዎችንና አጋር አካላትን በጋራ የሚያሰተባብር መመሪያ ያስፈልጋል፡፡

የዚህ መመሪያ ዝግጅት የፌደራል፣ የክልል ተቋማትና የልማት አጋሮችን ተሳትፎና ቅንጅት የጠየቀ ነበር፡፡ በመሆኑም በዚህ አጋጣሚ ለተቀመጡ የመሰኖ ልማት ኤክስቴንሽን መተግበሪያ መመሪያ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ወሳኝ ጉዳዮች ውስጥ በአዲሱ ኤክስቴንሽን ስትራቴጂ መሰረት ተግባራዊ በማድረግ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ገበያ ተኮር መርህን ተከትሎ የመስኖ ሰብሎችን ማምረት፣ ተፋሰስን መሰረት ያደረገና አረንጓዴ ልማትን በማረጋገጥ፣ ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፣ የሴቶችንና ወጣቶችን የልማት ተሳትፎና ተጠቃሚነት

በማረጋገጥ፣ ኩታ ገጠም የመስኖ አመራረት ዘዴን በመከተል፣ ገበያ ተኮር ተሳትፎአዊ የኤክስቴንሽን አግልግሎትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ውጤታማና ቀልጣፋ የኤክስቴንሽን አገለልግሎት እንዲሰርጽ የሚያስፈልገውን ሰፊ አምራች የሰው ኃይልና ሌሎች መሰረታዊ ሃብቶችን (መሬት፣ጉልበትና ውሃ) በማሰባሰብም ከፍተኛ ርብርብና ድጋፍ እንዲያደርጉ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

ወ/ሮ የኔነሽ ኤጉ የግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

በግብርና ሚኒስቴር

# ምስጋና

ውጤታማ የመስኖ ስልጠናና ምክር ስልቶችን ለማስፈፀም ብሔራዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው:: በመሆኑም የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን፣ የግብዓት አቅርቦትን እና የገበያ ትስስር አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማጎልበቻዎችን ለማሻሻል የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎችንና የመስኖ የኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን አግልግሎት ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቷል:: ይህ መመሪያ በሁሉም የመስኖ ወቅቶች በግብርና ሚኒስቴር የአነስተኛ መስኖ ልማት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬትና የኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት የመስኖ ልማት ተጠቃሚዎችን እና አስፈፃሚዎችን የመስኖ ልማት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ዘላቂ አገልግሎት ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ ብዙሃኑ በገጠሩ አካባቢ በሕዝብ ተሳትፎ የሚሰሩና የሚተዳደሩ የባለ አነስተኛ ይዞታ የመስኖ ተቋማት የልማት ውጤት ደካማ የሚሆንበት ዋናው ቁልፍ ችግር በደካማ የገበያ ትስስር ችግር ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ምክንያቶቹ ቀላልና ወይም በቀላሉ ሊተገበሩ የሚችሉ ናቸው፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ የመመሪያና የአሰራር ጉድለቶች ምክንያት የኤክስቴንሽን ዕቅድ አውጪዎች የመስኖውን ዘርፍ ለተቋማዊ ዕድገት ወይም ለተከታታይ ትግበራዎች አፈጻጸም ማደግ በቂ ትኩረት ስላልሰጡ ወይም በክልል መንግሥታቶች በቂ ያልሆነ ሴክተር መስሪያ ቤቶችን የማስተሳሰር ስራ ስላልተሰራ ለተጠቃሚው የተጠቆመና ከልማት አጋሮች ጋርም ያለተቀናጀ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አግባብነት ባለው ዕቅድ ባለመመራቱ ምክኒያት ዘርፈ ብዙ ችግሮችን፣ ማህበራዊ እና ኢካባቢያዊ ተጽእኖዎች፣ የገበያ ትስስር ችግር እና ዝቅተኛ ምርታማነት የታወቁ መገለጫዎች ሆነው በመስኖ ልማትታችን ላይ እንቅፋት ሲሆኑ ቆይተዋል፡፡ እነዚህ መመሪያዎች በአነስተኛ የመስኖ ልማት አሰራሮች አተገባበር ላይ የተራቀቁ የመስኖ ልማት አሰራሮችን እና የመስኖ ልማትን በተመለከተ ወደፊት ለሚከሰቱ የመስኖ ተከታይ ዘመናዊ አቀራረቦችን እና የአፈፃፀም ዘዴዎችን በማሳየት ወሳኝ ሚና ይኖራቸዋል፡፡

የዚህ መመሪያ ዝግጅት ዕውን ሊሆን የቻለው በግብርና ሚኒስቴር አነስተኛ መስኖ ልማት ማሳፋፊያ ዳይሬክቶሬት እና የኤክሰቴንሽን ዳይሬክቶሬት እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ከፍተኛ አስተዋፅዖና ድጋፍ ነው፡፡ ለዝግጅቱም መረጃ በመስጠትና በቴክኒክ ኮሚቴ አባልነት ተሳትፎ በፌደራል ግብርና ሚኒስቴር የአነስተኛ መስኖ ልማት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት፣ የኤክሰቴንሽን ዳይሬክቶሬትና በክልል መንግሥታት ቢሮዎች ከፍተኛ ባለሙያዎች የጋራ ቅንጅት ዕውን መሆን ስለቻለ ከፍተኛ ምሰጋና ላቀርብ እወዳለሁ ፡፡

በመጨረሻም ለዚህ መመሪያ ዝግጅት የፋይናንስና ቴክኒክ ድጋፍ አስተዋፅዖ ላደረጉት የኔዘርላንድና የካናዳ መንግስታት የአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ ድጋፍ ፕሮጀክት በአነስተኛ መስኖ ልማት እና በኤክሰቴንሽን ዳይሬክቶሬት ስም ከፍተኛ ምስጋና ላቀርብ እወዳለሁ፡፡



አቶ ኤሊያስ አወል የአነስተኛ መስኖ ልማት ማስፋፊያ ዳይሬክተር

በግብርና ሚኒስቴር

# መቅድም

ይህ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መተግበሪያ መመሪያ በአሥር ምዕራፎች ቀርቧል፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ የመስኖ ልማት በኢትዮጲያ ያለው ሁኔታ አጠር ባለ መልኩ ቀርቧል፡፡ እንዲሁም ስለ መስኖ ኤክስቴንሽን አሰጣጥ አስፈላጊነት ፣የመስኖ የኤክስቴንሽን መርሆዎችን እና አስፈላጊነትን ትርጉም በትክክል ያስረዳል፡፡ ሁለተኛው ምዕራፍ የመስኖ ቴክኖሎጂ አመራረጥ፣ ኤክስቴንሽን አገልግሎት እና መሠረታዊ ባህሪያት የሚያመለክት ሲሆን ሶስተኛው ምዕራፍ አሳታፊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልትና ዘዴ ምን እንደሚመስል የተነተነ ነው፡፡ አራተኛ ምዕራፍ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴዎችን መምረጥ፣ ዕውቀትን የመቀመርና እና የአዳዲስ ውጤቶች ግኝት እንዴት እንደሚመዘገብ ይገልፃል፡፡ አምስተኛው ምዕራፍ የመስኖ ሰብሎች የገበያ ምርት/ኮሞዲቲ/ እሴት ሰንሰለት አቀራረብ፣ የገበያ ዕድሎችን ለመፍጠር እና የምርቶች በስርዓት መያዝ የገበያ ተፈላጊነትን እንዴት እንደሚጨምር ያሳውቃል፡፡ ምዕራፍ ስድስት የመስኖ ልማት ስልጠና ዳሰሳ ጥናት ስልጠና ላይ ያለውን የግንዛቤ አሰጣጥና አሰራር ሂደትን የሚተነትን ሲሆን በሰባተኛው ምዕራፍ የመስኖ ልማት ሰራተኞች(IDAs) ተግባርና ሚና እንዲሁም በምዕራፍ ስምንት የተቋማት ትስስር/ ግንኙነትና ትብብር ምን መመስሰል እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዘጠነኛው ምዕራፍ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የዕቅድ አዘገጃጀት ሂደቶች የሚያሳይ ሲሆን በመጨረሻም በአስረኛው ምዕራፍ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አተገባበር የክትትል፣ግምገማና መማማር፣ ምክንያታዊ የኤክስቴንሽን ስልጠና የመስኖ ተፋሰስ ተጠቃሚዎችን ተገቢ የመማር ዘዴ እንዴት የመሰና ኤክሰቴንሽን ባለሙያው ወይም ወኪል እንደሚከታተልና ድጋፍ እንደሚያደርግ መመሪያ ይሰጣል፡፡

# የቁልፍ ቃላቶች መፍቻ

## በዚህ ሀገራዊ የመስኖ ኤክሰቴንሽን መመሪያ ዋና ዋና ቁልፍ ቃላት ትርጓሜ፤

መስኖ ልማት ማለት በቂ ዝናብ በሌለበት ወቅት ወይም ዝናብ በማይዘንብበት ቦታና ወቅት ያለውን የውሃ አማራጭ፤ የዝናብ፣ የገፀ-ምድርና የከርሰ-ምድር ውሃን ተጠቅሞ ለሰብል፣ ለእንስሳት መኖ ልማት፣ ለጥምር ደንና ሌሎች የግብርና ልማቶችን ለማካሄድ በእድገታቸው ወቅት ከዝናብ የማያገኙትንና የሚያስፈልጋቸውን የውሃ መጠን በሙሉ ወይም በደጋፊ ለሰብሉ ወይም ለመኖ ውሃ በመስጠትና የውሃ እጥረትን በመከላከል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እና የጥራት ደረጃውን ለመጠበቅ የሚያስችል ሰው ሠራሽ ቴክኖሎጂ ነው ፡፡

ዘመናዊ መስኖ ማለት ቀጣይነት ያለው ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ የመስኖ ተቋማትን የመሠረተ-ልማት፣ የመስኖ ውሃ አሰባሰብ፣ የውሃ ስርጭት፣ የውሃ አጠቃቀምንና ክፍፍልን በማዘመን ምጣኔ ሃብት አያያዝን (ጉልበትን፣ ውሃን፣ ኢኮኖሚንና አካባቢን) መርህ ያደረገ የመስኖ ተቋማዊ ለውጥና የአሰራር ሂደት ማለት ነው፡፡

የመስኖ ልማት ወኪል (IDA)፡- ማለት የመስኖ ልማት ባለሙያ ሲሆን በሰብል ልማትና በእንስሳት መኖ ልማት ላይ ያተኮረ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን በማሳተፍ፣ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን በማጠናከር፣ የግብዓት አቅርቦትን በማሳደግ፣ የምርምር-ኤክስቴንሽን-አርሶ/አርብቶ አደር ግንኙነትን በማጠናከር ከተቋማት የድጋፍ አገልግሎት ጋር በማስተሳሰር የመስኖ አውታርን ውጤታማ ለማድረግ ሁለንተናዊ የሙያ ድጋፍ ማድረግ የሚችልና ሙያው ያለው/ላት ለምሳሌ ተፋሰስን መሰረት ያደረገ በመስኖ ሙያ ዘርፍ የሰለጠነ/ች ወይንም በጊዜያዊነት በውክልና በቀበሌ ላይ ተመድቦ/ባ የሚሰራ/የምትሰራ ባለሙያ ማለት ነው፡፡

የባለ አነስተኛ አርሶ አደሮች የመስኖ ልማት ፡- ማለት ይህ ቃል የተሰጠው ትርጉም በግልም ሆነ በጋራ በማንኛውም የውሃ ማግኛ ዘዴ በአርሶ አደር ወይም በከፊል አርብቶ አደር ማሳ ላይ የሚለማ የመስኖ መሬት ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር የሚጠቀማቸውን ማንኛውንም የመስኖ ተቋማት ከቤተሰብ ደረጃ እስከ አርሶ አደር ስብስብ (ማህበረሰብ) በጋራ የሚለማ የአነስተኛ፣ መካከለኛ እንዲሁም ከፍተኛ የመስኖ ተቋም/ይዞታ የያዘ የመስኖ ልማትን የሚያቅፍ ማለት ነው፡፡

የመስኖ ማሳ ኩታ ገጠም ቡድን፡- ማለት በአንድ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች ማሳቸው ኩታ ገጠም ሆኖ የአንድ 2ኛ፣3ኛ ወይም 4ኛ ደረጃ የመስኖ ውሃ ቦይን በጋራ የሚጠቀሙ እና ብዛታቸው እስከ አምስት የሚደርሱ አርሶ/አርብቶ አደሮች ሲሆኑ ከውስጣቸው አንዱ የእነሱ ቡድን መሪ ነው፡፡

በመስኖ ልማት ቡድን፡-ማለት በውስጡ እስከ አምስት የመስኖ ማሳ ኩታ ገጠም ቡድኖችን ያካተተ ሲሆን ለመስኖ ውሃ አጠቃቀም፣ ለኩታገጠም ሰብል አመራረት ፣ ለግብዓት አቅርቦት፣ ለምርት ግብይት እና አጠቃላይ በመስኖ ልማት በኩል ለሚፈጠሩ ችግሮች በጋራ የመፍትሄ አቅጣጫ በማስቀመጥ እና በመፍታት የሚንቀሳቀስ የልማት ቡድን ነው፡፡

# የአሕጽኖተ ቃላት መፍቻ

| | |
|---|---|
| ADPLAC:- | የግብርና ልማት አጋር አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስል |
| AIOMP:- | የግብርና ግብዓት እና የምርት ገበያ ትስስር |
| ATA:- | የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ |
| AWP:- | ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ |
| BoA:- | ግብርና ቢሮ |
| BoWRD:- | የውሃ ሀብት ልማት ቢሮ |
| CPA:- | የህብረት ሥራ ልማት ኤጀንሲ |
| CPP:- | የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ሂደት |
| DA:- | የልማት ሠራተኛ |
| EABC:- | የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን |
| ESE:- | የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት |
| FAO:- | የምግብና እርሻ ድርጅት |
| FFG:- | የአርሶ አደር ጥናት ቡድን |
| FINA:- | የአርሶ አደር መረጃ ፍላጎት ዳሰሳ |
| FTC:- | የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል |
| HHMI | የቤተሰብ አነስተኛ መስኖ |
| ICT:- | የመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ |
| IDA:- | የመስኖ የልማት ሠራተኛ |
| IEP:- | የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሂደት |
| IMC:- | የመስኖ አስተዳደር ኮሚቴ/በወረዳ/ |
| ISC:- | የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ |
| IVR:- | በይነተገናኝ የድምጽ ምላሽ |
| IWUA:- | የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር |
| IWUG:- | የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ቡድን |
| JES:- | የመስክ መስኖ ሥራ ድጋፍ |
| KAP:- | ዕውቀት፣ ተነሳሽነት፣ ልምምድ |
| MI:- | ጥቃቅን መስኖ |
| MoA | ግብርና ሚኒስቴር |
| NGO:- | መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች |
| NRMP:- | የተፈጥሮ ሀብት አስተዳደር ሂደት |
| O&M:- | አሠራርና እና ጥገና |
| PIDM:- | አሳታፊ የመስኖ ልማት አስተዳደር |
| PITD:- | አሳታፊ የመስኖ የቴክኖሎጂ ልማት |
| PRA:- | አሳታፊ የገጠር ዳሰሳ ጥናት |
| REFG:- | የምርምር - ኤክስቴንሽን - አርሶ አደር ቡድን |
| SMIS:- | የአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ ድጋፍ ሰጪ ፕሮጀክት |
| SMS:- | የባለሙያዎች ቡድን |
| SSI:- | አነስተኛ መስኖ |
| TNA:- | የስልጠና ዳሰሳ ጥናት |
| WoADo:- | ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት |
| WUINA:- | የውሃ ተጠቃሚዎች መረጃ ዳሰሳ ጥናት |

# ማውጫ

ምስጋና ....................................................................................................i

መቅድም ....................................................................................................ii

የቁልፍ ቃላቶች መፍቻ ....................................................................................................iii

የአሕጽሮተ ቃላት መፍቻ....................................................................................................iv

ምዕራፍ-1 የመስኖ ልማት በኢትዮጲያ....................................................................................................1

1.1 መግቢያ ....................................................................................................1

1.2 የኢትዮጲያ መስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የነባራዊ ሁኔታ ትንተና ....................................................................................................2

1.3 በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ያሉ ተሞክሮዎች እና ክፍተቶች ....................................................................................................3

1.4 በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አሰጣጥ ላይ ያሉ ዕድሎች እና ተግዳሮቶች ....................................................................................................4

1.4.1 በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አሰጣጥ ያሉ ዕድሎች....................................................................................................4

1.4.2 በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አሰጣጥ ያሉ ተግዳሮቶች....................................................................................................4

1.5 ዓላማ....................................................................................................5

1.6 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት መተግበሪያ መመሪያ ጥቅም....................................................................................................5

1.7 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መተግበሪያ መመሪያ አስፈላጊነት ....................................................................................................5

1.8 የመመሪያው ወሰን (Scope)....................................................................................................6

1.9 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የትግበራ መርሆዎች....................................................................................................6

ምዕራፍ-2 የመስኖ ቴክኖሎጂ አመራረጥ፣ ኤክስቴንሽን አገልግሎት
እና መሠረታዊ ባህሪያት....................................................................................................10

2.1 የመስኖ ቴክኖሎጂ መረጣ....................................................................................................10

2.1.1. የተሻሻሉ አነስተኛ መስኖ ቴክኖሎጂዎች....................................................................................................10

2.1.2 የአነስተኛ መስኖ ቴክኖሎጂዎች ዕውቀት፣አጠቃቀምና አሠራር ....................................................................................................12

ፎቶ-3፡-በእግር ንቅናቄ/ፔዳል/ የሚሠራ የውሃ መሳቢያ ....................................................................................................14

ፎቶ-4፡- በሞተር ሀይል የሚሠራ የውሃ መሳቢያ ....................................................................................................14

ፎቶ-5፡- በሞተር ሀይል የሚሠራ የውሃ መሳቢያ ....................................................................................................14

ፎቶ-6፡-በባህላዊ ከጉድጓድ ማውጫ ዘዴ....................................................................................................14

2.2 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት....................................................................................................14

2.3. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መሠረታዊ ባህሪያት....................................................................................................15

2.3.1 መሰረታዊ የሆኑ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ባህሪያት....................................................................................................15

ምዕራፍ -3 አሳታፊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልትና ዘዴ....................................................................................................24

3.1. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ለመተግበር አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች....................................................................................................25

3.2. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መለየት ....................................................................................................26

3.3. አርሶ/አርብቶ አደሩን፤ እንዲሁም የግል ባለሀብቱን ማነሳሳት ....................................................................................................27

3.4. ገበያ ተኮር ተሳትፎአዊ የአክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ....................................................................................................27

3.5. ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዘዴ ....................................................................................................27

3.6. የተሰባጠረ መስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዘዴን መጠቀም ....... 28
3.7. ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት መዘርጋት ....... 28
3.7.1. ግብርና ምርምር ....... 28
3.7.2. ግብዓት አቅራቢዎች ....... 28
3.7.3. ብድር ሰጪ ተቋማት ....... 29
3.7.4. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ....... 29
3.8. የመስኖ ውሃን ማዕከል ያደረገ ሁሉን አቀፍ አቀራረብ ዘዴን መጠቀም ....... 30
3.9. የሥርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጪነት (Gender-Responsiveness) ....... 30
3.10. አሳታፊ የመስኖ ቴክኖሎጂ ልማት (PITD) ....... 31
3.11. የመስኖ ተጠቃሚዎችን ማደራጀት ....... 31
3.11.1 የመስኖ ልማት ቡድን ማደራጀት ....... 31
3.11.2. እሴት የሚጨምሩ የመስኖ ልማት ሥራዎች ላይ ማደራጀት ....... 34
3.11.3. ሴቶችን በቡድን ማደራጀት ....... 36
3.11.4. ወጣቶችን በቡድን ማደራጀት ....... 36
3.12. የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ....... 37
3.12.1. በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ንዑስ ቡድን ....... 38
3.12.2. የመስኖ ልማት ንዑስ ቡድን/ብሎክ/ መሪ ሚና ....... 38
3.13. የኤክስቴንሽን ልማት ቡድን ....... 39
3.14. የመስኖ ልማት ውጤታማነት ላበረከቱ የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት ....... 39
3.15. የመስኖ ልማት ምርጥ ተሞክሮ መቀመርና ማስፋት ....... 40
3.16. የመ/ ልማት ኤክስቴንሽን የክትትል፣ድጋፍ እና ግምገማ ሥርዓትን መዘርጋት ....... 41
ምዕራፍ-4 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴዎች ....... 45
4.1. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግንኙነት፣ ዕውቀት እና አዳዲስ ሀሳቦችን የመምረጥ ዘዴ ....... 45
4.1.1. ግላዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴ ....... 46
4.1.2. ቡድናዊ የአክስቴንሽን የተግባቦት ዘዴ ....... 47
4.1.3. የመስኖ ልማት መስክ ጉብኝት ማካሄድ ....... 58
4.1.4. የመስኖ ልማት ልምድ ልውውጥ ማድረግ ....... 59
4.1.5. የብዙሀን የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴ ....... 65
4.2. ተስማሚ ዘዴዎችን ለመምረጥ ጠቃሚ ሀሳቦች ....... 68
4.2.1. የግንዛቤ ደረጃ ....... 68
4.2.2. የፍላጎት ደረጃ ....... 69
4.2.3. የማመዛዘን ደረጃ ....... 69
4.2.4. የሙከራ ደረጃ ....... 69
4.2.5. ሥራ ላይ የመዋል ደረጃ ....... 69

4.3 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ውጤት ........ 70
4.4. የአዲስ ሀሳብና አሠራር ግኝት/ፈጠራ /ኢኖቬሽን/ ሥርዓት ........ 72
4.4.1. የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ /ኢኖቬሽን/ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሚና ..... 73
4.4.2. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕውቀት አስተዳደርን ማጠናከር ........ 75
4.4.3. አሳታፊ የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ልማት ........ 78
ምዕራፍ-5 የመስኖ ሰብሎች የገበያ ምርት/ኮሞዲቲ/ እሴት ሰንሰለት አቀራረብ........ 83
5.1 የእሴት ሰንሰለት ጽንሰ-ሀሳብ ........ 84
5.2 የእሴት ሰንሰለት ጽንሰ-ሀሳብና ጉዳዮች ........ 84
5.3. የእሴት ሰንስለት እና የገበያ መር የኤክስቴንሽን አቀራረብ አቅጣጫዎች........ 85
5.4 በመስኖ ልማት የእሴት ሰንስልት እና የገበያ መር የኤክስቴንሽን........ 87
5.4.1. የእሴት ሰንሰለት ትንተና........ 87
5.4.2. የእሴት ሰንሰለት ትንተና አስፈላጊነት ........ 87
5.4.3. በመስኖ ሰብል የገበያ ምርት/አቅርቦት እሴት ሰንሰለት ትንተና........ 88
5.4.4. እሴት ሰንሰለትን የተከተለ የመስኖ ልማት ዕቅድ ........ 90
5.4.5. የኢንዱስትሪ ሂደት/Proccessing/ ........ 92
5.4.6 የመስኖ ምርት ስርጭትና ግብይት........ 94
5.6 የእሴት ሰንሰለት ስትራቴጂ በመስኖ ልማት ........ 95
5.6.1 በመስኖ ሰብል እሴት ሰንሰለት የድጋፍና ተሳትፏዊነት ........ 96
5.6.2. አገልግሎትን ማመቻቸት/ማሳለጥ ........ 99
5.7. የኮንትራት ግብርና አስፈላጊነት........ 100
5.7.1. የኮንትራት ግብርና ዓይነቶች ........ 101
5.7.2. የአውት-ግሮወርስ አሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት ሊደረግ የሚገባው ቅድመ ዝግጅት........ 102
ምዕራፍ 6. የመስኖ ልማት ስልጠና ........ 108
6.1. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና አስፈላጊነት ........ 108
6.1.1 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና ግብ........ 119
6.1.2 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና ሳይክል/ዑደት........ 110
6.1.3 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የስልጠና ሂደት ........ 110
6.2. የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት (TNA) ........ 111
6.2.1 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አስፈላጊነት ........ 113
6.2.2. የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አተገባበር........ 113
6.2.3 የፍላጎት መጠንን መረዳት (Need Level) ........ 115
6.3. የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ደረጃዎች ........ 116
ደረጃ 2 ፦ ጠቃሚና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የስልጠና ርዕሶችን መለየት........ 116
6.4. የአርሶ አደሮችን የስልጠና ፍላጎት መለየት ........ 117

6.4.1 የስራ ትንተና ማካሄድ ........ 118
6.4.2. የክፍተት ትንተና ማካሄድ ........ 128
6.5 ውጤታማ የኤክስቴንሽን ስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ........ 131
6.5.1 ፍላጎትን መረዳት ........ 131
6.5.2 የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የአቀራረብ/ ዘዴ (Need Assessment Approaches) . 132
6.5.3 የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ቴክኒክ ........ 132
6.5.4 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠናዎችን ቅደም ተከተል መለየት ........ 132
ምዕራፍ-7 የመስኖ ልማት ሰራተኞች ተግባርና ሚና ........ 136
7.1. የመስኖ ልማት ሰራተኞች ተግባርና ኃላፊነት ........ 136
7.1.1 መረጃ መያዝና የስራ አከባቢን ማወቅ ........ 137
7.1.2 የመስኖ ልማት ሰራተኞች የሥራ መርሀ ግብር ይዘትና ቅርፅ ........ 137
7.2. የመስክ ጉብኝቶችና ስብሰባዎችን ማዘጋጀት ........ 138
7.2.1. የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች የቤት ለቤት ጉብኝት ........ 139
7.2.2. የመስክ ቀን ማካሄድ ........ 139
7.2.3. የልምድ ልውውጥ/ በተነሳሽነት የቡድን ጉብኝት ጉዞ ማድረግ ........ 140
7.2.4. በወረዳ የሚደረግ ወርሀዊ የመስኖ ሰራ የትኩረት አቅጣጫና ስልጠና ........ 140
7.2.5. የመስኖ ኤክሰቴንሽን የትኩረት አቅጫ ነጥቦች መረጣና ማብራሪያ ........ 141
7.3. የመስኖ ተጠቃሚዎች ሥልጠና ማዘጋጀት ........ 142
7.4. መረጃ መመዝገብና እና የውስጥ ሪፖርት ማዘጋጀት ........ 143
ምዕራፍ-8 የተቋማት ትስስር/ ግንኙነትና ትብብር ........ 145
8.1 የተቋማት ድጋፍና ትስስር ዓላማዎች ........ 150
8.2 የግንኙነት አሠራር ዘዴ ........ 151
8.2.1 በክልል ደረጃ ........ 151
8.2.2 በዞን ደረጃ ........ 153
8.2.3. በወረዳ ደረጃ ........ 154
8.3. ተግባራዊ የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ንዑስ መድረክ አወቃቀር ........ 155
8.4. በየደረጃው ያሉ የመስኖ ልማት አጋር አካላት የሥራ ድርሻ ........ 157
8.4.1 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የሥራ ሂደት (ዳይሬክቶሬት) ........ 157
8.4.2 የመስኖ ልማት  ግብዓት አቅርቦት እና ግብይት ........ 158
8.4.3. የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ የሥራ ክፍል ........ 159
8.4.4 የመስኖ ህብረት ሥራ ማህበራት ........ 159
8.4.5 የግብርና ምርምር ተቋም/ማዕከላት ........ 160
8.4.6. የአጋር አካላት ሚና ........ 160
ምዕራፍ-9 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ ሂደቶች ........ 162
9.1. ለዕቅድ መረጃ ማሰባሰብ ........ 166

9.2. የወረዳ አስተቃቀድ አውደ ጥናት ...... 167
9.3. የወረዳ መስኖ ልማት ሥራ ዝርዝር የአስተቃቀድ ቅጽ ...... 167
9.5. የክልል መስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ (ISC) ...... 168
9.6. የተጠቃለሉ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅዶችንና በጀትን ማስተካከል...... 168
9.7. የአሰልጣኞች ሙያዊ (ቴክኒክ) ስልጠናን ማካሄድ ...... 169
9.8. ወረዳ ላይ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና ማካሄድ...... 169
9.9. የአተገባበር ስትራቴጂ እና ክትትል ...... 170
9.10. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን መገምገም ...... 170
9.11. ዓመታዊ የበጀት ግምት ሪፖርት ማዘጋጀት ...... 170
ምዕራፍ-10 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የክትትል፣ግምገማና መማማር...... 172
10.1 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል አስፈላጊነት...... 172
10.2. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግምገማ አስፈላጊነት...... 174
10.3. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግምገማ ተግዳሮቶች...... 175
10.4. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለውጥን መለካት ...... 176
10.4.1 የኤክስቴንሽን አፈጻጸም አመላካቾች...... 176
10.4.2 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፋይዳ ግምገማና አመላካቾች ...... 177
10.4.3 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሂደት ዳሰሳ ...... 179
10.4.4 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ውጤት/Out come/ ዳሰሳ...... 183
10.4.5. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግምገማ ማዕቀፍ (ቅርጽ/ይዘት)...... 184
10.4.6 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፋይዳ ግምገማ (Impact Evaluation) ...... 185
10.4.7 የኤክስቴንሽን ክትትልና ግምገማን ማካሄድ...... 188
10.5. ተስማሚ የግምገማ መስፈርት እና አመላካቾችን መምረጥ ...... 190
10.6. እያደገ የመጣ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽንና ፋይዳ አመላካቾች አመራረጥ ...... 191
10.7 ትክክለኛ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ትግበራ ክትትልና ግምገማ አለካክ ...... 194
10.7.1 ተገቢ መረጃ ምንጭ መረጣ ...... 194
10.7.2 መረጃ ሰብሳቢን በጥንቃቄ መምረጥ፣ ማሰልጠን እና መከታተል...... 194
10.7.3 የወካይ ናሙና መረጣ ...... 195
10.7.4 የአጋጣሚ (የመሆን እድል) ናሙና መረጣ ...... 195
10.7.5 መረጃን መተንተን ...... 196
10.7.6 አሃዛዊ ትንተና ...... 196
10.7.7 ገላጫዊ ትንተና ...... 197
10.7.8 የመስኖ ልማት ኤክቴንሽን የግምገማ ውጤት አተገባበር...... 197

የዕዝል ዝርዝር ...... 198

# ሠንጠረዥ

ሠንጠረዥ- 1 የስልጠና ፍላጎት መጠንና ደረጃ......198
ሠንጠረዥ- 2 የተሟላ የስልጠና ልየታ ሂደት መመዝገቢያ......199
ሠንጠረዥ- 3 የዋና/አብይ ተግባር ትንተና ናሙና ሠንጠረዥ/ቅጽ......201
ሠንጠረዥ- 4 ናሙና የዝርዝር ተግባር መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ......203
ሠንጠረዥ- 5 ናሙና የድረጊትና ደረጃዎችን /Action& steps/......203
መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ......204
ሠንጠረዥ- 6 ናሙና የድርጊትና ደረጃዎችን /Action& steps/......205
መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ......206
ሠንጠረዥ- 7 የተግባር ክፍተት ትንተና መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ......208
ሠንጠረዥ- 8 የድርጊት ክፍተት ትንተና መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ/......214
ሠንጠረዥ- 9 ግንኙነትን ለማጠናከር የሚደረግ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ዝርዝር......219
ሠንጠረዥ-10 የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ መለስተኛ መድረክ......220
ሠንጠረዥ-11 አጠቃላይ ዓመታዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አስተቃቀድ ደረጃዎች......220
ሠንጠረዥ-12 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል......221
ሠንጠረዥ-13 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ክትትል አመላካቾች......221
ሠንጠረዥ-14 የመስኖ ኤክሰቴንሽን ተጽዕኖ አመላካቾች......222
ሠንጠረዥ-15 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዳሰሳ ጥናት አፈፃፀም/ግምገማ
ሂደት አመላካቾች......222
ሠንጠረዥ-16 ወቅታዊ የመስኖ ኤክስቴነሽን ክትትል ቅፅ......222
ሠንጠረዥ-17 የአፈጻጸም አመላካቾችና የማረጋገጫ......223
ሠንጠረዥ-18 በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ትግበራ በ3 ደረጃዎች......224
ለግምገማ የሚጠቅሙ የተለያዩ ቴክኒኮችና ሣሪያዎች
ሠንጠረዥ-19 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትልና ግምገማ
ንድፍ/ዲዛይን ደረጃዎች......225

# የምስል ዝርዝር

ምስል- 1 የግንዛቤ ደረጃ ማሳያ ቻርት......68
ምስል- 2 የአዲስ ሀሳብ /ኢኖቬሽን/የኤክስቴንሽን አሰራር (Swanson 2009)......72
ምስል- 3 የዕውቀት አስተዳደር ሂደት (Cong et.al 2007)......74
ምስል- 4 አሳታፊ የሃሳብ ልማት ንድፍ......78
ምስል- 5 የእሴት ሰንሰለት ትስስር ሥዕላዊ መግለጫ......87
ምስል- 6 የአርሶ/አርብቶ አደሮችና የካምፓኒዎች/የግል ባለሃብቶች/ፋብሪካዎች
የገበያ ትስስር......104
ምስል- 7 የመስኖ ንዑስ አጋር አካላት ግንኙነት......146
ምስል- 8 የዳሰሳ ጥናት ክለሳ፣ ክትትልና ግምገማ......172
ምስል- 9 የውጤት ሠንሰለት......189

## ፎቶ

ፎቶ- 1 የውሃ ማከማቻ ታንከር....................................................................12
ፎቶ- 2 የመሬት ውስጥ ታንከር....................................................................13
ፎቶ- 3 በእግር ንቅናቄ/ፔዳል/ የሚሠራ የውሃ መሳቢያ ........................................14
ፎቶ- 4 በሞተር ሀይል የሚሠራ .......................................................................14
የውሃ መሳቢያ ..........................................................................................14
ፎቶ- 5 በሞተር ሀይል የሚሠራ የውሃ መሳቢያ ፎቶ- 6፡- በባህላዊ
ከጉድጓድ ማውጫ ዘዴ...................................................................................14
ፎቶ- 7 በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋም ውስጥ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሥራ
መከናወን ይገባዋል (ጅማ ዞን ማና ወረዳ ኢላሳ ጉዳ ........................................20
ፎቶ- 8 ሴት አርሶ አደርን ማዕከል ያደረገ የመስኖ አጠቃቀም (ሰሜን ሸዋ ዞን
ምንጃር ሸንኮራ ወረዳ፤- ፎቶ በዶ/ር አካሉ ተሾመ) .........................................23
ፎቶ- 9 በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/ ከንባታ ጠምባሮ ዞን ደንቦያ ወረዳ የገረንባ
የአ/ማ/ተቋም መስኖን ......................................................................................
በመጠቀም እየለማ የሚገኝ የጓሮ አትክልት ልማት በከፊል ..................................56

## ሥዕል

ስዕል- 1 አርሶ/አርብቶ አደሩ በአካባቢያቸው የተፈጠረውን የመስኖ ውሃ
ችግር ለመፍታት ሲወያዩ፤ ..............................................................................7
ስዕል- 2 አርሶ/አርብቶ አደሩን ሙሉ ቤተሰብ በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን
ውስጥ እንዲሳተፉ እና እንዲወያይ ማድረግ ተገቢ ነው፤ ....................................8
ስዕል- 3 የመስኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያው ለአርሶ/አርብቶ አደሩ
በቬንዲያግራም በቀላሉ ሲያስረዳ.........................................................................9
ስዕል- 4 የዝናብ ውሃን ከጣራ ላይ የማሰባሰብ ዘዴ...............................................12
ስዕል- 5 በቀላል ወጪ የተሰራ የጠብታ መስኖ አጠቃቀም ዘዴ.................................13
ስዕል- 6 የመስኖ አውታር ተፋሰሶችን ከአፈር ክለት ለመከላከል
የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ .................................................................................16
ስዕል- 7 የመስኖ ልማት የሚከናወንባቸው ማሳዎች የአፈር ክልት
እንዳፈጠር በተገቢው መንገድ የውሃ ቦይ............................................................17
ስዕል- 8 ሴት አርሶአደሮችን በመስኖ ልማት ሥራ ውስጥ ማሳተፍ
ሌሎች አርሶአደሮችን ያበረታታል፡.......................................................................30
ስዕል- 9 ሴት አርሶአደሮችን በመስኖ ልማት ሥራ ውስጥ ማሳተፍ
ኤኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታ አለው .........................................................44
ስዕል-10 የመስኖ ልማት ሥራን በቤተ ለቤት ጉብኝት በማካሄድ
አርሶ አደሩን ማበረታታት እና ማሳደግ ይቻላል፡፡.................................................47
ስዕል-11 የመስኖ ልማት ውጤቶችን በገበያ ማስተሳሰር ዘለቄታዊ
ልማትን ያጎለብታል፡፡.......................................................................................86
ስዕል-12 በመስኖ ልማት ሥራ የመስክ ቀን ላይ አርሶአደሮችን
ማሳተፍ አርሶአደሮችን ያበረታታል፡ ...............................................................104

# ምዕራፍ-1 የመስኖ ልማት በኢትዮጲያ

## 1.1 መግቢያ

በሀገራችን የመስኖ ልማት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በግብርናው ዘርፍ ለአምራች የሰው ሀይል የስራ ዕድል ፈጥሮ ገቢን በማሳደግ ረገድ የጀርባ አጥንት ሲሆን እያደገ ለመጣው የምርት ቅነሳ ስጋት አስተማማኝ መፍትሄ ይሰጣል፡፡ በሀገሪቱ መስኖ ዋነኛ ዘርፍ የሆነና በዘላቂነት የረጅም ጊዜ የምግብ እህል ምርት ዕቅድ ይኖረው ዘንድ ግንዛቤ የተወሰደበት ሲሆን ውጤታማና ቁጥጥር ያለበት የውሃ ሀብት አጠቃቀምን እውን ያደረጋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ አዲሱ አስተሳሰብም በውሃ ሀብት ማኔጅመንት ማዕቀፍ የመስኖ ውሃ አስተዳደር ተግባራዊ እንዲሆን መሠረት ተጥሏል፡፡ በዚህም መሰረት አንድ አርሶ አደር/አርብቶ አደር ቢያንስ አንድ የውሃ አማራጭ እንዲኖረው ታሳቢ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ለመስኖ መስፋፋቱ በተለይ የአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ ግንባታዎች በባለአነስተኛ ይዞታ ደረጃ በፍጥነት እያደጉና እየተሻሻሉ ሲመጡ ቁልፍ የሆኑ ግብዓቶች አቅርቦት በይበልጥም በመስኖ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ውስጥ ማለትም በብድርና በገበያ ድጋፍን በማካተት ይወሰናል፡፡ በተጨማሪም የቴክኖሎጂ ፓኬጅ አቅርቦት ከአፈሩ ዓይነትና ከውሃው አቅርቦት የድርጊት መርሀ ግብር ጋር የተገናዘበ ሲሆን ለአነስተኛ አርሶ አደሮች የሚሰጠው ተቋማዊ የሆነ የገበያ ድጋፍ ለመስኖ ሰብል ልማቱ መጨመር ወሳኝ ነው፡፡

የምግብ ዋስትና ችግር በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ እየተከሰተ ያለው የግብርና ምርት በዝናብ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው፡፡ ሌላው ችግር የመስኖ እና የዝናብ ግብርና እርስ በርስ የሚጣጣሙ እና የሚጣመሩ አልነበሩም፡፡ የውሃ እጥረት ባለበት ጊዜ እና ቦታ ሁሉ መስኖ ከግብርና መስፋፋት ጋር አብሮ ሊኖር የሚያስችል ሲሆን በምግብ ራስን የሚያስችል፣ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ገቢ የሚያሳድግ፣ የውጭ ምንዛሬን የሚያጎለብትና የመስኖ ልማት  ልማት እሴት ሰንሰለቶችን በመተግበር በርካታ የሥራ እድል አማራጮችን የሚያስገኝ ዘርፍ ነው፡፡ ዘላቂ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ መስኖ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ በመስኖ ልማት የምግብ ዋስትናችንን የማረጋገጥ ተግባራችን አጠናክረን መቀጠል ይኖርብናል፡፡

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ትግበራ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሲሆን የውሃ ተጠቃሚዎችን በማሳተፍ፣ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን በማጠናከር፣ የግብዓት አቅርቦትን በማሳደግ፣ የምርምር-ኤክስቴንሽን-አርሶ አደር ግንኙነትን ባካተተ መልኩ ከተቋማት የድጋፍ አገልግሎት ጋር ያለውን ግንኙነት በማስተሳሰር የመስኖ አውታርን ውጤታማ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም የሚያመላክተው አሳታፊ በሆነ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ የባለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችን በማሳመን የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ተቀብለው በሥራ ላይ እንዲያውሉ ማድረግ ነው፡፡

ለዘላቂ የመስኖ ልማት ትግበራ የአነስተኛ አርሶ አደሮችን አቅም ለማሳደግ እየተደረገ ባለው ጥረት ውስጥ መንግስት በያዘው የልማት አጀንዳ ዘላቂ ልማትን እውን ለማድረግ የአነስተኛ መስኖ አቅም ግንባታ ስትራቴጂ አዘጋጅቷል፡፡ በስትራቴጂው አቅጣጫ 2 ላይ በተቀመጠው መሰረት የኤክስቴንሽን አገልግሎትን በማጠናከር ዘመናዊ የመስኖ ግብርናን ለመተግበር በእርሻ ማሳ የመስኖ ውሃ እና የሰብል ማኔጅመንትን ማጠናከር እንደሆነ ያሰቀምጣል፡፡ ይህም በማሳ ውስጥ

የሚደረገውን የውሃ እና ሰብል ማኔጅመንት ልምምድ በአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ አውታር ግንባታና ጥገና ላይ ያለውን የአርሶ/አርብቶ አደሩን ዕውቀትና ክህሎት ማሻሻልን ያካትታል፡፡

በሌላ በኩል የጥቃቅን መስኖ ልማት ስትራቴጂ የአርሶ/አርብቶ አደሩን የመስኖ ልማት እምቅ ሀብትና ችሎታ ሥራ ላይ በማዋል በጥቃቅን መስኖ ልማት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችን በመደገፍ የምግብ ዋስትናን እውን ለማድረግ በግብርና ሚኒስቴር በኩል እ.ኤ.አ በ2018 ተዘጋጅቷል፡፡

የመስኖ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መመሪያ ዝግጅት ከመስኖ ባለሙያዎችና ከልማት ጣቢያ ሠራተኞች ስልጠናና አቅም ግንባታ ጋር የተያያዙ ቁልፍ ተግባራትን መነሻ ሀሳቦች አቅርቧል፡፡

ይህ መመሪያ የተዘጋጀው በብሔራዊ የግብርና ኤክስቴንሽን ስትራቴጂ ላይ የተቀመጡትን ዘጠኝ የኤክስቴንሽን አምዶችን መሰረት አድርጎ ሲሆን ዋና ዓላማውም የአነስተኛና ጥቃቅን፣ የማህበረሰብ ኩሬ፣ የመስኖ አውታሮች ትግበራ ሀላፊነት ያለባቸው የክልል፣ የዞን እና የወረዳ የመስኖ ባለሙያዎችና የመስኖ ልማት ሰራተኞች በመስኖ ኤክስቴንሽን አተገባበር ላይ በቂ ዕውቀትና ክህሎት አግኝተው በመስኖ ልማት ስራ ላይ የተሰማሩትን ህብረተሰብ ክፍሎች ማስተማር፣መምከር ማሰልጠንና ሙያዊ ድጋፍ መስጠት እንዲችሉ ነው፡፡

በዋናነት የኤክስቴንሽን ስትራቴጂው የተዘጋጀው ልማታዊና አዳዲስ ሀሳቦች፣ በደንብ በሚሰራ (ሲስተማቲክ) እና ተለዋዋጭነት ወይም አዳጊነት ባለው የመስኖ ግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አማካኝነት የአነስተኛ አርሶና/አርብቶ አደሮች ምክርና ስልጠና፤እንዲሁም ሙያዊ ድጋፍ እያገኙ ምርትና ምርታማነታቸውን በማሳደግ ገቢያቸውን ጨምረው የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ ለማስቻል ነው ፡፡

መመሪያው የመስኖ ኤክስቴንሽንን መልክ፣ ተሳትፎአዊ አቀራረብ ዘዴን እና የኤክስቴንሽን ኮሙኒኬሽን ዘዴዎችን እንዲሁም በይበልጥ የመስኖ ልማት ሰራተኞች የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ለአርሶ አደሮች ለማስተላለፍ የሚኖራቸውን ሚና በአካተተ መልኩ ግልጽ አድርጓል፡፡ እንደዚሁም በወረዳ መስኖ ባለሙያዎች በኩል ለአርሶ አደሮች ስልጠና እንደሚሰጥና የክትትል ተግባራትን እንደሚያከናውኑ በሰነዱ ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

በአጠቃላይ የመስኖ ልማት ባለሙያዎች እና የመስኖ ልማት ሰራተኞች የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ተሳትፎአዊ የመስኖ ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴዎችን ተጠቅመው ውጤታማ በሆነ መልኩ የመስኖ ተጠቃሚዎችን በማስተዋወቅ በሰነዱ ላይ የተቀመጡትን የመስኖ ልማት አተገባበሮች በሚገባ መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ በመስክ በሚገኙ ተሞክሮዎችና ልምዶች እንዲሁም በመስኖ ግብርና በሚገኙ አዳዲስ የምርምር ግኝቶች አማካኝነት መመሪያው በቀጣይ ወቅታዊ ክለሳ ይደረግበታል፡፡

## 1.2 የኢትዮጲያ መስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የነባራዊ ሁኔታ ትንተና

በኢትዮጲያ ያለው በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት ስፋት አቅም 11.1 ሚሊዮን ሄ/ር እንደሆነ ቢገመትም እስካሁን በተለያዩ ደረጃዎች የለማው የመሬት መጠን ግን ከ2 ሚሊየን ሄ/ር አይበልጥም ይሁን እንጂ በመስኖ የሚሸፈነው መሬት በየዓመቱ ያለው ዕድገት ከ1,090-

1,150ሄ/ር በዓመት እንደሆነ ያለፉት 12 ዓመታት ተከታታይ የሆኑ መረጃዎች ያሳያል:: :: በመስኖ ልማት ላይ የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ልማት ሰራተኞች ብዛት ካሉት መደበኛ የልማት ሰራተኞች ውስጥከ 1% የማይበልጡ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ:: በአገሪቱ አሁን በመልማት ላይ የሚገኘው የመስኖ እርሻ በአነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደር ደረጃ በእያንዳንዳቸው ከ 0.2 እስከ 0.5 ሄ/ር የሚሸፍን ነው:: ይህን በባህላዊም ሆነ በዘመናዊ መልክ በመልማት ላይ የሚገኘውን የመስኖ እርሻ በቀበሌ ደረጃ ካሉት የልማት ሠራተኞች እና የመስኖ ልማት ሰራተኞች ጋር በመሆን ከሞላ ጎደል በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር እየተመራ ይገኛል:: ይሁን እንጂ እየለማ የሚገኘውን እና የለማውን መሬት በዘመናዊ መልክ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ትክክለኛ የመስኖ መሬት ምዝገባ አልተደረገም:: የመስኖ ልማት እንቅስቃሴውን በዋናነት እንዳያድግ እንቅፋት የሆነው ልማዳዊ የመስኖ አመራረት ዘዴን መከተል፣ የመስኖ ልማት የሚያገለግሉ ግብዓቶች እጥረት እና ዋጋ መናር፣ ውስን የተሻሻሉ ለመስኖ የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎች መኖር፣ ውስን በመስኩ የሰለጠኑ ባለሞያዎች እና አርሶ/አርብቶ አደሩን በቅርበት የሚረዱ የመስኖ ልማት ሰራተኞች መኖር ፣ በቂ ያልሆነ አቅም እና ክህሎት በዘርፉ መኖር፣ እና በቂ ያልሆነ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አሰጣጥ ዘዴ መኖር ዘርፉን ባለበት ወይም ከሚጠበቀው እድገት በታች እንዲሄድ አድርጎታል::

በመሆኑም የመስኖ ልማት እውቀት እና ክህሎት በሀገራችን ለመተግበር ማነቆ ሆነው የቆዩትን የሰው ኃይል ልማት፣ የመስኖ ስርዓት ቴክኖልጂ ዓይነትና ደረጃ፣ የመስኖ መሰረተ ልማት፣ የመስኖ ስራ አደረጃጀት እና ትስስር ስርዓት፣ የመስኖ ምርምር ስርዓት ፣የመስኖ መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ ማምረት ችግሮችን መፍታት እና የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መተግበር በእጅጉ ወሳኝ ነው:: እነዚህ ተግባራትን በበቂ እና አስተማማኝ በሆነ መልኩ በሀገራችን ለመተግበር የሚያስችል የመስኖ ልማት የትግበራ መመሪያ ማዘጋጀት ተገቢ ነው::

## 1.3 በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ያሉ ተሞክሮዎች እና ክፍተቶች

በአገሪቱ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሰፋ አለመሆኑና ያሉትም ተሞክሮዎች ዝናብን በመጠቀም ከሚለሙ ሰብሎች እምብዛም የተለየ አይደለም:: በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አሰጣጥ የተሻለ አፈጻጸም የሚታይባቸው ለገበያ ቅርበት ያላቸው፣ የመንገድ ችግር የሌለባቸው እና የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነታቸው የተሻለ እና የሰፋ አካባቢዎች ሲሆን በነዚህ አካባቢዎች ከልማት ሰራተኛ እና ባለሙያ ድጋፍ ውጭ ገበያው በሚመራው መሠረት የመስኖ ልማቱ እየተከናወነ ይገኛል:: በተወሰኑ የዘመናዊ መስኖ አውታሮች የተገነቡበት አካባቢ እንዲሁም የአርሶአደሩ አኗኗር መስኖን መሰረት ባደረገበት የባህላዊ መስኖ ተጠቃሚዎች አካባቢ በቂ ነው ባይባልም የሚያበረታታ የመስኖ ስራ እንቅስቃሴ ይታያል::

በሌላ ጎኑ ያሉትም የልማት ሠራተኞች በአብዛኛው የመኸር እና የበልግ ዝናብን መሰረት ያደረገ የኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጡ እንጂ መስኖን መሰረት ያደረገ ድጋፍ በትክክል ለአርሶ/ አርብቶ አደሩ እየሰጡ አይደለም:: ይህም ሊሆን የቻለው የመጀመሪያው እና ዋነኛው የአደረጃጀት ችግር ማለትም የመስኖ ልማት ባለስልጣን የተቋቋመባቸው ክልሎች እስከ ወረዳ ድረስ ብቻ የሚዘልቅ አደረጃጀት ያለና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ ባለሙያዎች ከሌሎች የግብርና ባለሙዎች በደምወዝ የተሻለ ክፍያ ያላቸው በመሆኑ የልማት ሰራተኞች አርሶአደሩን ለመደገፍ እንዲሁም ወረዳ ላይ የሚገኙ የግብርና እና የመስኖ ልማት ባለሙያዎች በቅንጅት መስራት ላይ ደካማ አፈጻጸም እንዲያስመዘግቡ አድርገዋል:: ከዚህ በተጨማሪ በቀበሌ የሚገኘው ልማት ሠራተኛ

1 (MoA,2011)::

2 (Nata et al.,2008; Bekele et al., 2012)

የመስኖ አማራጮች ባሉበት የአርሶአደር ማሰልጠኛ ተቋማት እንኳን አርሶአደሩን በግንዛቤ፣ በእውቀትና በክህሎት ለመደገፍ የተነሳሽነት ማጣት፣ የግብዓት አቅርቦት ችግር፣ የክትትል እና ድጋፍ አሰጣጥ እና ከገበያ ጋር የማስተሳሰር ችግር የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕድገቱ እንዲወሰን አስገድዶታል።

## 1.4 በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አሰጣጥ ላይ ያሉ ዕድሎች እና ተግዳሮቶች

በኢትዮጲያ የውሃ እና ኢነርጂ እና የግብርና ሚ/ር ባወጡት ሪፖርት በመስኖ ልማት ሥራ ላይ ያሉ ማነቆዎች እና ልማቱን ለማቀላጠፍ ያሉ ዕድሎች ተብራርተዋል። በመሆኑም በአነስተኛ መስኖ ልማት ላይ ያሉ ተግዳሮቶች እና ዕድሎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 1.4.1 በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አሰጣጥ ያሉ ዕድሎች

በኢትዮጲያ ያለው የመስኖ ልማት እንቅስቃሴ መንግስት በዕ.ት.ዕ. ከያዘው ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በተጨማሪ የአርሶ/አርብቶ አደሩ አካባቢያዊ እውቀት፣ የዝናብ ውሃ አሰባሰብ ዘዴን መተዋወቁ እና ጅምር የአነስተኛ መስኖ አጠቃቀም ሁኔታ መኖሩ፣ የመንግስት ፖለቲካዊ ውሳኔ እና ቁርጠኝነት መኖሩ፣ የግል ባለሀብትን የሚያበረታታ እና የሚጋብዝ ስርዓት መፈጠሩ፣ በቂ የውሃ አማራጭ፣ አመቺ የአየር ንብረት መኖሩ፤ በቂ የሰው ጉልበት መኖሩ፤ እና አመቺ ለመስኖ አገልግሎት የሚሆን መሬት መኖሩ በተለይ በአገሪቱ በሚገኙ ቆላማ አካባቢ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አሰጣጡን ውጤታማ ያደርጉታል።

### 1.4.2 በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አሰጣጥ ያሉ ተግዳሮቶች

በአገራችን እየተደረገ ያለው የአነስተኛ መስኖ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የቴክኒክ እና የዕውቀት ክፍተት ሚዛን የደፋ ተግዳሮት እንደሆነ በተለያዩ ጊዜ በተደረጉ ጥናቶች ለማወቅ ተችሏል። እነዚህም 1). በመስኖ ውሃ ማኔጅመንት ላይ ያለው የግንዛቤ እጥረት ማለትም፡- ለሰብሉ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ፕሮግራም፣ ውሃን የመቆጠብ ቴክኖሎጂ፣ ውሃን የመለካት ቴክኖሎጂ፣ የመስኖ ውሃ አውታሮች አጠቃቀምና እና ጥገና፤ 2) በመስኖ አግሮኖሚ ላይ በቂ የሆነ የተሻሻለ፣ የተስፋፋና ያደገ ዕውቀት አለመኖር፤3). በመስኖ ፓምፖች፣ጠብታ መስኖ፣ የርጭት መስኖ፣ የገጸ-ምድር እና የጎርፍ ውሃን ለመስኖ ልማት ማዋል ላይ በቂ የሆነ ሙያዊ ዕውቀት እና ቴክኒካዊ ክህሎት አለመኖር፤ 4). የአነስተኛ መስኖ ልማት ማስፋፋት ተፋሰስን/የአካቢ ስፋትን መሰረት ከማድረግ ይልቅ አውታርን መሰረት ያደረገ መሆኑ፤ 5). የአነስተኛ መስኖ ልማት ሥራ ውስጥ በቂ መሰረታዊ መረጃ አለመያዝ እና የመረጃ ልውውጥ አለመኖር፤ 6). ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀ አነስተኛ መስኖ ልማት ለመስራት በጥናት፣በዲዛይን፣ በግንባታ እና በክትትል በቂ የሆነ ልምድ አለመኖር፤ 7). በስራ ላይ የሚገኙት አነስተኛ መስኖዎች ምርታማነት ማነስ፤ 8). በአነስተኛ መስኖ ዕቅድ ዝግጅት፣ ግንባታና እና አያያዝ እና አጠቃቀም ትግበራ ላይ የህብረተሰቡ ተሳትፎ አነስተኛ መሆን፤ 9). ተጠቃሚው በቂ መነሻ ሀብት ያለማግኘት፤(ለመሰረተ ልማት ግንባታ፣ ለቴክኖሎጂ፣ ለግብዓት መግዣ፣ እና በግብዓቶች ላይ በየወቅቱ የሚጨምረውን ዋጋ ለመክፈል) እና 10). ለሚመረቱ ሰብሎች ቀዝቃዛ መጋዘን፣ የገበያ ሰንሰለት እና ኢንፎርሜሽን እጥረት መኖር የመሳሰሉት ናቸው።

3 (MoA,2011)።

## 1.5 ዓላማ

ይህ የመተግበሪያ መመሪያ/ ዓላማው የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎትን በዘላቂነት ለማሳደግ ተግባራዊ የሚሆኑ መልዕክቶችንና ምክሮችን በመስኖ ልማት ላይ ለተሰማሩ ባለሙያዎች እና ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች በመስጠት፣ አሳታፊ በሆነ መልኩ በመስኖ ውሃ የማልማት ተጠቃሚነታቸውን ከፍ በማድረግ ምርታማነታቸውን ለማሳደግ እና የተጠቀሚ ማህበረሰቡን ገቢ እንዲጨምር ለማድረግ እንዲረዳ ነው።

## 1.6 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት መተግበሪያ መመሪያ ጥቅም

አሳታፊ በሆነ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ የባለ አነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችን በማሳመን በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ዘላቂ የመስኖ ልማት ትግበራትን ለማከናወን፤ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን በማጠናከር፣ የግብዓት አቅርቦትን በማሳደግ እና አጠቃቀምን ለማሳደግ፣ የምርምር-ኤክስቴንሽን-አርሶ አደር ግንኙነትን በአካተተ መልኩ ከተቋማት የድጋፍ አገልግሎት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማስተሳሰር፣ የመስኖ አውታርን ውጤታማ በማድረግ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ተቀብለው ዘመናዊ የመስኖ ግብርናን ለመተግበር፤ የአካባቢ ጥበቃን መሰረት ያደረግ የሰብል ልማት አያያዝ በማጠናከር እና በሥራ ላይ እንዲያውሉ በማድረግ ለፍጆታ፣ ለኢንዱስትሪ እና ለውጭ ገበያ የሚውሉ ምርቶችን ለማምረት እንዲያስችል የሚረዳ ነው። በመሆኑም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ጥቅሙ፡-

- የምርት እድገትን ይጨምራል፤
- አካባቢ ጥበቃን መሰረት ያደረገ የመስኖ አጠቃቀም ማለትም ብክለትን እና የአፈር መሸርሸርን ይቀንሳል፣
- የግብዓት ተጠቃሚነት ቅልጥፍናን፣ የውሃ ፣የጉልበት እና ሀብት አጠቃቀምን ያሳድጋል፤
- በመስኖ አገልግሎት የሚመጡ ስጋቶችን እና ቢዝነስ ኪሳራን ይቀንሳል፡
- ተሳትፎአዊ እና ዘለቄታዊ የመስኖ ልማት ግልጋሎትን ያጎለብታል።

## 1.7 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መተግበሪያ መመሪያ አስፈላጊነት

ይህ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መተግበሪያ መመሪያ አገልግሎቱ ቴክኒካዊ የሆኑ መልዕክቶችን/ እውቀቶችን ለባለሙያው እና ለአርሶ/አርብቶ አደሩ በመስጠት በዕቅድ፣ በትግበራ እና በክትትል በማሳተፍ እንደ አገር ወጥ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት ሲሆን አሰጣጡን ዘለቄታዊ በሆነ መልኩ ተጠቃሚነታቸውን በማሳደግ ያለውን የመስኖ ውሃ ሀብት በአግባቡ በመጠቀም የአርሶ/አርብቶ አደሩን አኗኗር ሁኔታ እንዲሻሻል ለማድረግ ታስቦ ነው። በመሆኑም ይህ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መተግበሪያ መመሪያ ያካተተው የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ገጽታ፣መርሆዎችና ቴክኖሎጂ አመራረጥ፤ ተቋማዊ ድጋፍ፣ ማስተባበር እና ትስስር፤ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴዎች፤ የመስኖ ልማት ሰራተኞች ሚናና ተግባር፤ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባራት ዕቅድ፤ የመስኖ ሰብሎች የገበያ ምርት/ኮሞዲቲ/ እሴት ሰንሰለት አቀራረብ፤ የመስኖ ስልጠና ፍላጎት ልየታና የስልጠና ዕቅድ ዝግጅት፤ እና የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን

የክትትል፣ግምገማና ፋይዳ/በጎ ተፅኖን መቀመር የሚሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የመተግበሪያ መመሪያው የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽንን ገጽታ፣ ተሳትፎአዊ አቀራረብ ዘዴን እና የኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴዎችን እንዲሁም በይበልጥ የመስኖ ልማት ሰራተኞች የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ለአርሶ አደሮች ለማስተላለፍ የሚኖራቸውን ሚና በአካተተ መልኩ ግልጽ አድርጓል፡፡ በመሆኑም ይህ የመተግበሪያ መመሪያ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም እና አስተዳደር ስርዓትን የያዘ ነው፡፡ አጠቃቀሙንም ወደ ተጠቃሚው ለማድረስ በወረዳ መስኖ ልማት ባለሙያዎች በኩል ለአርሶ አደሮች ስልጠና እንደሚሰጥና የክትትል ተግባራትን እንደሚያከናውኑ በሰነዱ ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

## 1.8 የመመሪያው ወሰን (Scope)

ይህ የመተግበሪያ መመሪያ በመስኖ ልማት ላይ ለተሰማሩ አርሶ/አርብቶ አደር፣ ባለሙያ እና መንግስታዊ እና መንግስታዊ ላልሆኑ ባለድርሻ አካላት ሁሉ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን በውስጡ የተጠቀሱት ሙያዊ የሆኑ መመሪያዎች የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎትን፣ ክትትል እና የግምገማ ዘዴዎችን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡

## 1.9 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የትግበራ መርሆዎች

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መሰረታዊ ግብ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት በዘላቂነት ማረጋገጥ ሲሆን የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን በዋናነት የሚከተሉትን ቁልፍ ዓላማዎች ለማሳካት የራሱ የሆነ መርሆዎች አሉት፡፡ ከመሰረታዊ ግቦች ውስጥ ፡-

- አዳዲስና የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን እንዲሁም ጠቃሚ እና ተግባራዊ መረጃዎችን ማደራጀት እና ማሰራጨት
- የአርሶ/አርብቶ አደሩን የመስኖ ልማት እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ለማሳደግ ስልጠናዎችን መስጠት
- የገበያ ትስስርን ማመቻቸ፣ የእሴት ሰንሰለትን ማሻሻልና ማጠናከር
- የሥርዓተ-ፆታ, የወጣት እና የአመጋገብ ስርዓትን በመስኖ ስራዎች ውስጥ ማካተት
- አካባቢያዊ አያያዝ እና ዘላቂነትን ማጎልበት
- ተቋማዊ አደረጃጀቶችን፣ቅንጅቶችን እና ትስስርን ማጎልበት
- የልማት አጋሮችን፣የሰው ኃይል ልማት እና ውጤታማ የሆነ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥን ማጠናከር
- ጠንካራ ውጤትን መሰረት ያደረገ ክትትልና, ግምገማ
- ምርጥ የመስኖ ልማት ተሞክሮዎችን መቀመር እና መሳሰሉትን ግብ አንግቦ የሚሰራ ነው፡፡ የመስኖ ልማት  ኤክስቴንሽን መሠረታዊ መርሆዎች ከግብርና ኤክስቴንሽን ጋር የሚመሳሰል ሲሆን በዋናነት የሚከተሉት መርሆዎች አሉት፡፡

1. ተፋሰስን መሰረት ያደረገ የመስኖ ልማት ፍላጎት መለየትና የፍላጎት መርሃ ግብር ማዘጋጀት /Principle of interest and need/- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የአርሶ/አርብቶ አደሩን የመስኖ ልማት ስራ ፍላጎት መለየትና የመሰኖ ግብርና ፍላጎት መርሃ ግብር ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ይህም ተፋሰስን በማልማትና ሃብትን በመለየት የመስኖ ውሃ አቅርቦትን ከምንጭ፣ከዝናብ፣ ከከርሰምድርና ገጸ-ምድር በመለየትና የተፋሰስ ዕቅድ በማውጣት የውሃ ቅርቦት አቅም፣የመስኖ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች ብዛት፣በመስኖ ሊለማ የሚችል የመሬት ስፋትና ሰብል ወዘተ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተሳትፏዊ የመስኖ ልማትና አስተዳደር መርህን የተከተለ ስራ ይሰራል፡፡ ይህም የሚያስፈልገው የአርሶ/ አርብቶ አደር ፍላጎቶች ከግለሰብ ወደ ግለሰብ, ከመንደር ወደ መንደር፣ ከመስኖ ብሎክ ወደ ሌላ ብሎክ ፍትሀዊ የውሃ ሀብት ክፍፍል እንዲኖርና የሀብት ብክነትን ለማስውገድ ነው፡፡

2. የመስኖ ልማት ስራ ባህልና ልምድ ከአከባቢ ወደ አካባቢ ልዩነቶች እንዳሉት መረዳት / Principles of Cultural Difference/ - የኤክስቴንሽን ሥራ በባህላዊ እና ልማዳዊ ዳራ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡የመስኖ ልማት በሚሰራበት አከባቢ የሚኖሩ አርሶ/አርብቶ አደሮች የመስኖ ግንዘቤ ማሻሻል የሚጀምረው እንደ አከባቢው ተጨባጭ ሁኔት ደረጃ በደረጃ ብቻ ነው፡፡ ይህም ማለት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሰራተኛው/ ባለሙያው በአከባቢው የሚኖሩ አረሶ/ አረብቶ አደሮችን የመስኖ ልማት ግንዘቤ፣ ዕውቀት፣ ባህል፣የሚጠቀሙበትን የመስኖ ልማት ማሳሪያዎቸ፣ የሚጠቀሙትን ግብዓት፣ ልምድና ችሎታ፣ወጎች, እምነቶች, እሴቶች, ወዘተ መገንዘብ የኖርበታል፡፡

3. ተሳትፎዓዊነት /Principle of participation/ - ተሳትፎዓዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዋና መርሆ የወንድ/ሴት አረሶ/አረብቶ አደሮችን የመስኖ ግንዘቤ፣እውቀት፣ክህሎት እና አማለካካት ከመስኖ አውታር/የህብረተሰብ የውሀ ኩሬ ግናባታ ዳሰሳ ጥናት ጀምሮ በማሻሻል የራሳቸውን ችግር ራሳቸው በዘላቂነት እንዲፈቱ/እንዲቀርፉ የሚስችል አቅም መፍጠር ነው፡፡



ስዕል- 1፡-አርሶ/አርብቶ አደሩ በአካባቢያቸው የተፈጠረውን የመስኖ ውሃ ችግር ለመፍታት ሲወያዩ፤

ይህም የተዘጋጀ መፍትሔ ከመስጠት ይልቅ ወንድ/ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች የራሳቸውን ችግር ለመቅረፍ ጥረት እዲያደርጉና በራሳቸው ላይ መተማመንንና መማር እንዲቻሉ ያደርጋል፡፡

4. ከሁኔታዎች ጋር የመላመድ ብቃት /Principle of Adoptability/- የመስኖ ልማት እንደ አረሶ/አረብቶ አደሩ ግንዘቤ፣እውቀት፣ክህሎት፣አማለካካት፣አተገባበር ወዘተ ደረጃ ወይም አንዱ የውሀ ቡድን ከሌላኛው የውሃ ቡድን ይለያያል፡፡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሁኔታዎችም እንደዚሁ ከቦታ ቦታ ይለያያሉ፡፡ ስለዚህ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መርሃግብርም ይህንን ልዩነት/ተለዋዋጭንት በመረዳት ሊለዋወጥ የሚችል በመሆኑ እንደ አስፈላጊነቱ/በሚያስፈልግበት ጊዜ የተለያዩ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት አስፈላጊ ለውጦችን ማድረግና የመላመድ ብቃት ያስፈልጋል፡፡

5. የሙሉ-ቤተሰብ አቀራረብ ዘዴ / Principle of whole family/- የመስኖ ልማት ሰፊ የጉልበትና የካፒታል አቅም የሚጠይቅ ስራ ከመሆኑም በተጨማሪ ሳይንሳዊ እውቀትና ክህሎት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም የአርሶ/አርብቶ አደሩን ሙሉ ቤተሰብ በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና ማሳተፍ የአርሶ/አርብቶ አደሩን የጉልበት/ካፒታል ክፍተት ለመሙላት ስለሚያግዝ የመስኖ ሰራተኞች/ባለሙያዎች ይህንን በመገንዘብ በአጠቃላይ የቤተሰብ የአቀራረብ ዘዴ/ አሠራር መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ መርህ መሰረትም የተለየ እና የተቀናጀ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አቀራረብ ለቤተሰቡ አባላት በሙሉ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡



ስዕል- 2፡-አርሶ/አርብቶ አደሩን ሙሉ ቤተሰብ በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ውስጥ እንዲሳተፉ እና እንዲወያይ ማድረግ ተገቢ ነው፤

6. የትብብር መርህ /Principle of co-operation/- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የተለያዩ ተቋማዊ አደረጃጀቶችን፣ቅንጅቶችን እና ትስስርን በማጎልበት የመስኖ ልማት ግበዓትና የገበያ አካላትን ከመስኖ ውሀ ተጠቃሚ ቡድኖች ጋር የማቀናጀት ስራ መስራ ይኖርበታል፡፡ ይህም አዳዲስና የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን መረጃዎችን ለማደራጀት እና ለማሰራጨት፣ የገበያ ትስስርን ለማመቻቸ፣ የእሴት ሰንሰለትን ለማሻሻልና ማጠናከር፣ የሥርዓተ-ፆታ፣ የወጣት እና የአመጋገብ ስርዓትን ለማካተት፣ አካባቢያዊ አያያዝ እና ዘላቂነትን ለማጎልበት፣ ጠንካራና ውጤትን መሰረት ያደረገ ክትትልና ግምገማ ላማድረግና ምርጥ የመስኖ ግበርና ተሞክሮዎችን ለመቀመር ይረዳል፡

7. የእርካታ መርህ / Principle of satisfaction/- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የመጨረሻ ግብ የመስኖ ምርትና ምረታማነትን በማሳደግ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ማህበራዊና ኢኮኖሚዊ ችግር በዘላቂነት በመፍታት የሃገርን እድገት ማፋጠን ሲሆን የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የማስተማር/ ማሰልጠን ጥረት የመጨረሻ ውጤት በመስኖ ግብርና በሂደት ለሚታዩ ችግሮች መፍትሄ በመፍጠር የአርሶ/አርብቶ አደሩን ችግር በራሱ እንዲፈታና አዲስ ችሎታ ወይም ሌሎች የባህሪ ለውጦችን እንዲፈጥር በማስቻስል ነው፡፡

8. የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች አጠቃቀም መርህ/ The principle of the use of variety of teaching methods/- ይህ የሚያመለክተው አንድ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽ ጉዳይ የሚቀርብበት/ሚተላለፍበት መንገድ አረሶ/አረብቶ አደሩ በፍጥነት የጉዳዩን ግንዘቤ፣ እውቀት፣ ክህሎት፣ አማለካካትና አተገባበሩን በመረዳትና በማዳበር ወደ ተግባር እንዲቀይር ለማስቻል ነው፡፡ ስለዚህም ለተለያዩ ጉዳዮች ወይም ለአንድ አይነት ጉዳይ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ የማስተማሪያ/ማሰልጠኛ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈገልጋል፡፡



ስዕል- 3፡-የመስኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያው ለአርሶ/አርብቶ አደሩ በቬንዲያግራም በቀላሉ ሲያስረዳ

9. ውጤትን መሰረት ያደረገ የክትትልና ግምገማ መርህ/ Principle of Monitoring and Evaluation/- በሳይንሳዊ ዘዴ በመታገዝ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ያመጣውን የአመለካከት፣የክህሎት፣የአተገባበርና የባህሪ ለውጥ ያለማቋረጥ መከታተልና መገምገም ያስፈልጋል፡፡ ይህም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሥራና የለውጥ ሁኔታን በማጤን ውሳኔዎችን ማድረግ እንደሚስፈልግ ያስገነዝባል፡፡

10. የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበርን መሰረት ማድረግ (Irrigation Water Use Association/ IWUA/)፡-የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ተግባራዊ የሚደረገው አብዛኛውን ጊዜ በቡድን በመሆኑና ለዚህም ከግንባታው ጀምሮ እስከ በየዓመቱ የሚደረጉ ጥገናዎች እና እንክብካቤዎች በተጠቃሚው ማህበረሰብ ነው፡፡ የመስኖ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ለሚጠቀምበት ውሃ በየዓመቱ የገልግሎት ክፍያ መፈጸም እንዳለበት በመመሪያ የተደገፈ ነው፡፡ በመሆኑም የመስኖ ልማት የሚከናወንባቸው ማሳዎች የኩታ ገጠም ምርት ለማምረት፣ማሳዎችን ለመንከባከብ፣የመስኖ አውታሮች ሲበላሹ በጋራ ጥገና ለማድረግ፣ ወጪ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ በጋራ በመሆን ለማሳተፍ እንዲሁም ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ቢከሰቱ ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ ተጠቃሚው ማህበሰብ መደራጀት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አሰጣጥ መሰረት ማድረግ የሚገባውና እስካሁንም የተሻለ ውጤት እያስመዘገበ የሚገኘው በመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን መሰረት በማድረግ ስለሆነ የኤክስቴንሽን አሰጣጡም እዚህ ላይ ተንተርሶ መሆን ይገባዋል፡፡

# ምዕራፍ-2 የመስኖ ቴክኖሎጂ አመራረጥ፣ ኤክስቴንሽን አገልግሎት እና መሠረታዊ ባህሪያት

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አሰራር ዘዴ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ማህበርና አነስተኛ የመስኖ ተጠቃሚ አባውራ/እማወራ፤እንዲሁም ሰፋፊ የመስኖ እርሻዎችና አርሶ/አርብቶ አደሮች የተሻሻሉ የመስኖ መረጃዎችን በመጠቀም፣ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመለማመድ ተግባር ላይ በማዋል ምርትና ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ መደገፍ የሚያስችል ውጤታማ የሆነ አሰራር ወይም ዘዴ ነው፡፡ ይህንንም በዋናነት በዘላቂነት ሊያስተባብሩና ሊመሩ የሚችሉት የመስኖ ባለሞያዎችና የልማት ሰራተኞች ናቸው፡፡ ይህም ማለት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ በዋናነት በአዳዲስ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች፣ በመስኖ ልማት ባለሞያዎችና ልማት ሰራተኞ ዕውቀትና ብቃት ላይ ይወሰናል ማለት ነው፡፡ ሌሎች በመስኖ ስራ ላይ ቁልፍ ሚና የሚኖራቸው አካላትና ሂደቶችም ለምሳሌ የመስኖ ባለሞያዎችና የልማት ሰራተኞች፣ የአነስተኛና ሰፋፊ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች፤ የተለያዩ የተሻሻሉ የመስኖ ፓኬጆች፣ የመስኖ ሰርቶ ማሳያዎች፣ ስልጠናናድጋፎች፣ ምርምር፣ የግብዓት፣ የገበያ፣ የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂ ሜካናይዜሽንና የመስኖ ልማት ድጋፍ ሰጪ ተቋማት አገልግሎት ግንኙነት/ ቁርኝቶችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 2.1 የመስኖ ቴክኖሎጂ መረጣ

የመስኖ ቴክኖሎጂ መረጣ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ነባራዊ ሁኔታዎች እና አካባቢውን ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም የተወሰኑ የመስኖ ቴክኖሎጂ ዓይነቶች በሚመረጡበት ጊዜ የአርሶ/ አርብቶ አደሩን የመተግበር አቅምና ጥንካሬ ባገናዘበ መልኩ ሆኖ ሁለንተናዊ የአያያዝና የጥገና መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርበታል፡፡ ይህን እውን በማድረግ ረገድ ግድፈቶች ከመፈጠራቸው በፊት ቀድሞ አርሶ/አርብቶ አደሮቹን ቀርቦ ማማከር ተገቢ ነው፡፡ የቴክኖሎጂ ምርጫ ለአርሶ/ አርብቶ አደሮች እና አካባቢውን በማይጎዳ መልኩ ተስማሚ እንዲሆን የሚከተሉትን መስፈርቶች ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡

- ☞ የአርሶ/አርብቶ አደሩን የመስኖ ቴክኖሎጂ መግዣ ፋይናንስ አቅም ያገናዘበ መሆኑን፣
- ☞ አርሶ/አርብቶ አደሩ ያወጣውን የኢንቨስትመንት ወጭ የመስኖ ቴክኖሎጂው ሊመልስለት የሚችል መሆኑን፣
- ☞ አርሶ/አርብቶ አደሩ የሚያለማበት በቂ ማሳ መኖሩ፣
- ☞ አርሶ/አርብቶ አደሩ የሚያለማቸው የሰብል ዓይነቶች መለየታቸው፣
- ☞ ቴክኖሎጂው የሚፈለገውን ያህል የሰው ኃይል/ጉልበት አቅም መኖሩ፣
- ☞ የጥገና አገልግሎትና መለዋወጫ ዕቃዎች መገኘት፣
- ☞ የቴክኖሎጂዎቹ ዘላቂነት/ለረጅም ጊዜ የሚያገለግል መሆን፣
- ☞ ቴክኖሎጂው ሥራ ላይ በሚውልበት ወቅት ያለው አከባቢያዊና ማህበራዊ ገጽታ፣

## 2.1.1. የተሻሻሉ አነስተኛ መስኖ ቴክኖሎጂዎች

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በርካታ ጠቃሚ የሆኑ አዳዲስ የመስኖ ቴክኖሎጂ ግኝቶች/ፈጠራዎች ጎልብተው ወደ ገበያ ቀርበዋል፡፡ እነዚህም አድካሚ ያልሆኑ ቀላልና አነስተኛ የውሃ መውረጃ ቦዮች/ቱቦዎች/መስመሮች፣ በሞተር ፓምፕ የሚሰሩ የውሃ መሳቢያዎች፣ የመስኖ መሬት መደልደያ ማሽኖች፣ የርጭት መስኖ እና የጠብታ መስኖ በዘመናዊ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች የሚመሩ ቴክኖሎጂዎች ናቸው፡፡ የውሃ እጥረት ባለባቸውም ያደጉ ሀገሮች ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉት የጥቃቅን መስኖ ቴክኖሎጂዎች ውሃን በበለጠ ውጤታማ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ አይነቶች በርካታ ናቸው፡፡ በሀገራችን ለአነስተኛና ሰፋፊ መስኖ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች ተስማሚና የተሻሻሉ የአነስተኛ መስኖ ቴክኖሎጂዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የጠብታ፣ የቧንቧ ማሰራጫ ሲስተም -- (ለገፀ-ምድርና ከርሰ-ምድር መስኖ)፣
- የፔዳል/ትሪድል/ ሮፕና ወሸር እና የሞተር ፓምፕ -- (ውሃ ከመሬት ውስጥ ለማውጣት)፣
- ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸው የፕላስቲክ የውሃ ታንከሮች -- (በዝናብ ወቅት ውሃ ለማሰባሰብ)፣
- በመኖሪያ ቤት አካባቢ ውሃ ማከማቻዎች -- (የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብ)፣
- ባልዲና በርሚል የመሳሰሉ ቁሳቁሶች፣
- ቦሮቦሮችን በመገደብ SSD (Soil storage dum constructed on Gully)
- የውሃ እጥረትን የሚቋቋሙና አካባቢን ፈጥነው የሚላመዱ የተዳቀሉ ዘሮችን / የተሻሻሉ ዝርያዎችን/ መጠቀምና የተመጣጠነ ማዳበሪያ፣
- ታይድ ሪጅር በማሳ ውስጥ በመስራት
- የተራራ እና ኮረብታ ላይ መስኖ ልማት ቴክኖሎጂ
- ቲዩብ ዌል(Tubwell)
- በፀሃይ ኃይል የሚሠራ የውሃ መሳቢያ(Solar Pump)
- የውሃ መሄጃ ቆርቆሮን፣ የርጭትና የግፊት ቱቦን መጠቀም፣
- በእጅ የሚነቀነቅ ውሃ መሳቢያ፣
- የተቀናጀ የዕጽዋት ተባይና በሽታን መከላከል፣
- ባህላዊ እና ዘመናዊ የወንዝ ጠለፋ
- ምንጭ በማጎልበት እና ነባር ምንጭ ጠለፋ
- የውሃ ቦዮችን ከስርገት በመከላከል(Lined) በማድረግ ውሃን በአግባቡ በመጠቀም የሚለማ መሬት በማስፋት
- የቤተሰብ ኩሬ እና የህብረተሰብ ኩሬ በመገንባት የዝናብ ውሃን ማሰባሰብ፤(Family & community pond)

## 2.1.2 የአነስተኛ መስኖ ቴክኖሎጂዎች ዕውቀት፣አጠቃቀምና አሠራር

**የጣሪያ ውሃ ማሰባሰብ ዘዴ:-** በብዛት የተለመደና ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን የዝናብ ውሃ ማሰባሰቢያ ተፋሰስ ሦስት ዓይነት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት። እነሱም አንደኛው ክፍል ወይም አካል ጣሪያ ሲሆን እንደ ተፋሰስ ቦታ ሆኖ የሚያገለግል የውሃ መውረጃ ቱቦ /ጎረንዳዮ/ አሸንዳ እና የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር ናቸው። ሌሎችም ወደ ማጠራቀሚያ ታንከሩ የሚገቡ የአቧራና ፍርስራሽ መጠንን ለመቀነስ የሚያገለግሉ መቆጣጠሪያ ወይም የውሃ መልቀቂያ /መቀልበሻ/ እና ማፅጃ ክፍሎች ይኖራሉ። ጎረንዳዮ ወይም አሸንዳ ዋነኛው የውሃ ማሰባሰቢያና ማስተላለፊያ ክፍል ሲሆን የዝናብ ውሃን ከጣራው ላይ ተቀብሎ ወደ ታንከሩ የሚያስተላልፍ መስመር ነው። ይህም ቀላል ክብደት ያለው፣ ውሃ የማያሰርግና ለማያያዝ የተመቸ ነው።

የመገጣጠሚያዎችን መጠን በመቀነስ የውሃ ስርገት እንዳይኖር ለማድረግ ረጅምና ቀጥ ያለ ቁሳ ቁስ ያስፈልጋል። ለምሳሌ:-ለአሸንዳ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ቀርከሀ፣የድጋፍ እንጨት፣ፒቪሲ ወይም ላስቲክ እና የማይዝግ ብረት ናቸው። ለዚህም የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብ የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የጣሪያ ቅርጽ አመቺ ነው።



ስዕል- 4:-የዝናብ ውሃን ከጣሪያ ላይ የማሰባሰብ ዘዴ



ፎቶ- 1:- የውሃ ማከማቻ ታንከር

**የውሃ ማከማቻ ቅርጽ ዓይነቶች:-** ከጣሪያ ላይ የተሰባሰበ የዝናብ ውሃ አንድም በከርሰ ምድር ውስጥ አሊያም በገጸ ምድር ላይ ይጠራቀማል። እነዚህ ማጠራቀሚያዎች የሚገነቡት ከተለያዩ ቁሶች ማለትም ከብረት፣ ከእንጨት፣ ከፕላስቲክ፣ ከብሎኬት፣ ከድንጋይ እና ከስሚንቶ፣ ወዘተ ከመሳሰሉት ነው። የገፀ ምድር ውሃ ማጠራቀሚያን በሚመለከት የቤት ጣራ የውሃ ማሰባሰቢያ ዘዴ እንደሆነ የሚታወቅ

ሲሆን በዋናነት ከመሬት ከፍ ብሎ የሚቀመጥ ነው፡፡ የዚህ የገፀ ምድር ማጠራቀሚያ ታንከር ዋነኛ ጥቅም ውሃን ከታንከሩ በቧንቧ አማካኝነት ወደ ሌላ ቦታ ለመውሰድ ነው፡፡ይሁን እንጂ ከመሬት በታች ከሆነ ማጠራቀሚያ ታንከር ጋር ሲነጻጸር ዋጋው ውድ ነው፡፡



ፎቶ- 2፡- የመሬት ውስጥ ታንከር

**የመሬት ውስጥ ታንከር፡-** ምድር ውሃ ታንከር ጋር ሲነፃፀር ዋጋው ዝቅ ያለ እና ትንሽ ቦታ በመያዝ ውሃው በፓምፕ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ ታንከሩ/ቱቦው ክብ ቅርጽ ያለው ነው፡፡

ለግንባታው ስራም ቀላል ቁሳቁስ /ማቴሪያል/ የሚበቃው ሲሆን የግድግዳውንም ጥንካሬ ይጨምርለታል፡፡ በመሆኑን በትነት ምክንያት የሚባክነውን ውሃ በመቆጣጠርና በቂ ውሃ ለማከማቸት ውጤታማ ነው፡፡ ለዚህም የሚተነውን ውሃ ለመከላከል ጣሪያው በአካባቢው በሚገኙ ቁሳቁሶች/ማቴሪያሎች/ ይሸፈናል፡፡ የውሃ ማከማቻ ጉድጓዱ የውሃ መግቢያ፣ ማከማቻ ቦታ፣ ማፍሰሻ እና የጣራ ሽፋን ይኖረዋል፡

**የጠብታ መስኖ፡-** የጠብታ መስኖ ዘዴ ውሃን በማጠጣት ረገድ 90% የሆነ ብቃት ያለውና ከሁሉም የተሻለ ዘዴ ነው፡፡ ይህ ዘዴ መስመር ለመዘርጋት፣ ዲዛይን ለማውጣት እና ከከፍተኛ እርጥበት ጋር ተያይዞ ለሚከሰት በሽታ መቀነስ ቀላል ዘዴ ነው፡፡ ይህ ዘዴ በቤተሰብ ደረጃ በግል ማሳ ላይ በተናጠል ለማልማት የሚረዳ ነው፡፡ በመሆኑንም ለምግብነት የሚውሉ አትክልቶችን፣ የፍራፍሬ ዛፎችንና ሌሎች ሰብሎችን በአርሶ አደሩ ማሳ ላይ ማልማት የሚችል ሲሆን ክፍት በሆነ ነጻ መሬትም ላይ ሊዘረጋ የሚችል ነው፡፡ ይህ ዘዴ በስበት ሀይል የሚሰራ በመሆኑ ምንም ዓይነት የኤሌክትሪክ ሀይል አይፈልግም፡፡ ስለሆነም የመስኖ ዋጋ ክፍያውም ሆነ ጥገና ወጪው ዝቅተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም በየትኛውም ተራራማ አካባቢ እና የውሃ እጥረት ባለባቸው ቦታዎች ጠቃሚ ነው፡፡



wስዕል-5፡-በቀላል ወጪ የተሰራ የጠብታ መስኖ አጠቃቀም ዘዴ

የጠብታ መስኖ ዘዴ በቤተሰብ ደረጃ የሚጠቅም ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ዲዛይኑ የበለጠ ምክንያታዊ የሆነና ቴክኖሎጂው ለቤተሰብ ማሳ ጠቃሚ ሲሆን በጣም ውጤታማም ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር አጠቃቀሙን ከጥቃቅን መስኖ ቴክኖሎጂዎች ማኑዋል ላይ መረዳት ይቻላል፡፡

**ውሃ የማውጣት ዘዴ፡-** ውሃ ከተከማቸበት ቦታ ለማውጣት በጣም አስፈላጊ ከሆኑ የውሃ መሳቢያ ማሽኖች መካከል አንዱና ዋነኛው የእጅ ፓምፕ ወይም ፔዳል ፓምፕ ነው፡፡ በነፋስና በፀሐይ ኃይል የሚሰሩ የውሃ መሳቢያዎችን መጠቀም ለአካባቢ ተስማሚና ተጽዕኖን የማይፈጥሩ አማራጭ ቴክኖሎጂዎች ናቸው፡፡ በብዙ ያላደጉ ሀገሮች ገጠራማ አካባቢዎች ገመድ በባልዲ አስሮ ውሃ ከጉድጓድ ማውጣት አሁንም የተለመደ አሰራር ነው፡፡ሌላው የላስቲክ ቱቦ ወይም ጎማ በመጠቀም በስበት ኃይል ዘዴ ውሃን ማውጣት ይቻላል፡፡



ፎቶ-3፡-በእግር ንቅናቄ/ፔዳል/ የሚሠራ የውሃ መሳቢያ




ፎቶ-4፡- በሞተር ሀይል የሚሠራ የውሃ መሳቢያ



ፎቶ-5፡- በሞተር ሀይል የሚሠራ የውሃ መሳቢያ



ፎቶ-6፡-በባህላዊ ከጉድጓድ ማውጫ ዘዴ

## 2.2 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አካል ሲሆን በዋናነት አነስተኛና ሰፋፊ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን በማቋቋምና በማደራጀት ሁለንተናዊ የመስኖ ውሃ ልማትና አስተዳደር ለአነስተኛና ሰፋፊ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች የምክር፣የስልጠና የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የመስኖ ሰብል ምርትና ምርታማነትን በተሻለ መልኩ ለመፈፀም እንዲቻል የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ ለማድረግ አነስተኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መረጃ፣ዕውቀትና ክህሎት ማግኘት እንዲችሉ ተጠቃሚዎችንና አጋር አካላትን በጋራ ያስተባብራል፡፡

## 2.3. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መሠረታዊ ባህሪያት

በመስኖ ግብርና ኤክስቴንሽን ባደጉ በተለይም በመስኖ አስተዳደር ውጤታማ በሆኑና ለመስኖ ተጠቃሚ ማህበረሰቦች ተጨባጭ ጥቅምና የተለያዩ ልምዶች ባገኙ ሌሎች አገሮች የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሦስት ልዩ ገጽታዎች አሉት፡፡ እነዚህም ፓኬጅ፣ ዕቅድ፣ እና ትክክለኛነት (Precision) ሲሆኑ እነዚህንም አቀናጅቶ በመተግበር የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ሥራ ላይ ለማዋል ተችሏል፡፡ የተሻሻለ የመስኖ ፓኬጅ ሲባል የመስኖ ግብዓቶችን ማሟላት ሲሆን በውስጡ የግብዓት ተደራሽነትና በወቅቱ የማግኘት፣ የመስኖ ውሃ ተደራሽነት/በቂ የመስኖ ውሃ ለአነስተኛና ሰፋፊ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማድረስ፣ ተስማሚና የተሻሻሉ የሰብል/የአትክልት ዘር ማቅረብ፣ ሚዛናዊ የማዳበሪያ አጠቃቀምና ተመጣጣኝ የሰብል ጥበቃ እንዲኖር ማድረግ፣ ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችና ለመስኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ስልጠና መኖር የሚሉ ናቸው፡፡

ዕቅድ ሲባል የመስኖ ተጠቃሚዎችን በዕቅድና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ በአሳተፌ  መልኩ የመስኖ ሰብል ወቅትን መሠረት አድርጎ ዝርዝር የመስኖ ተግባራትን መለየትና እና የመስኖ እምቅ ሀብትን ጥቅም ላይ ለማዋልና ለማጎልበት የክትትል ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡ ይህም በመስኖ አውታር ደረጃ የመስኖ ልማት  ልማት ዕቅድ ዝግጅት ማለት ነው፡፡

በመጨረሻ ትክክለኛነት ሲባል የመስኖ ተግባራትንና ፓኬጆችን እውን ለማድረግ የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን የኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴዎችን ተጠቅሞ በትክክለኛው ቦታ፣ ወቅት፣ መጠንና አይነት ሥራ ላይ ማዋል ማለት ነው፡፡ ይህም ሊረጋገጥ የሚችለው በመተግበሪያ የኤክሰቴንሽን መመሪያ ነው፡፡

### 2.3.1 መሰረታዊ የሆኑ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ባህሪያት

የውሃ መገኛ አካላትን መንከባከብ፡- የዝናብ ውሃ ዋነኛ የመስኖ ውሃ ማግኛ ምንጭ ነው፡፡ የዝናብን/የጎርፍ ውሃ ከተፋሰስ ቦታዎች በማሰባሰብና በውሃ ማጠራቀሚያዎች በማከማቸት ወይም መሬት ውስጥ በማስረግ የተከማቸውን ውሃ ከመሬት ውስጥ በቀላሉ በማውጣት አትክልቶችን፣ ፍራፍሬዎችንና የምግብ ሰብሎችን በጓሮ /በቤት ዙሪያ/ ለማልማት ይቻላል፡፡ ደለልንና አላስፈላጊ ጎርፍን በመከላከል የተፋሰሱን የማስረግ አቅም መጨመር የምንጮችን የውሃ ማፍለቅ አቅም ከማጎልበቱም በላይ የመስኖ አውታሮች በደለል እንዳይዘጉ/እንዳይፈርሱ በማደረግ ዘላቂ የሆነ የመስኖ ልማት  ልማት እንዲኖር ያስችላል፡፡ በዋናነት እነዚህን ተግባራት ለማስፈፀም የመስኖ ልማት ባለሞያዎችና የመስኖ ልማት ሰራተኞች ይህንን የማስተማር፣የምክር አገልግሎት የመስጠትና የመደገፍ ሚና አላቸው፡፡

የመስኖ አውታር መጋቢ ተፋሰስ ማልማት፣መጠበቅና ማስተባበር፡- የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን/ ማህበረሰቡን በማነሳሳትና በማደራጀት የመስኖ አውታር ተፋሰሶችን የማልማትና የመጠበቅ እንቅስቃሴ ዋናና አስፈላጊ የመስኖ ልማት ስራ ሲሆን የአፈርና ውሃ ጥበቃ ቴክኒካል ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት የመስኖ ግድቦችን ከደለልና ከጎርፍ ለመከላከል ያግዛል፡፡ በደን ልማትና እንክብካቤ ተግባራትም በኩል ማህበረሰቡን በማሰልጠንና የተሻሻሉ የዛፍ ችግኞችን በመትከል የመስኖ አውታር አከባቢን በመጠበቅ በመስኖ አውታሮች አካባቢ ተፋሰሱ በተሻለ ሁኔታ ውሃ

ይዞ እንዲይቆይ ይረዳል።ይህንንም ተግባር የቀበሌ አስተዳደር፣የመስኖ ልማት ሰራተኛ፣የወረዳ መስኖ ባለሙያና ሌሎችም አጋር አካላት የማስተባበርና በአከባቢው ከሚገኙ ችግኝ ጣቢያዎች ጋር ማስተሳሰር ያስፈልጋል።



ስዕል-6፡- የመስኖ አውታር ተፋሰሶችን ከአፈር ክለት ለመከላከል የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ

ፍትሀዊ የመስኖ ውሃ ስርጭትን ማረጋገጥ፡- የመስኖ ልማት ሰራተኞችና የወረዳ መስኖ ባለሙያዎች ለአነስተኛና ሰፋፊ የመስኖ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በነፍስወከፍ የመስኖ መሬት እንዲገኙ ያደርጋሉ፤ ፍትሀዊ የመስኖ ውሃ ስርጭት እንዲኖር ያደርጋሉ፤ ምክር፣ ስልጠናና ድጋፍ ይሰጣሉ። ይህም ሊሆን የሚችለው ከመስኖ ውሃ ማህበራትና የማህበረሰብ ኩሬ ኃላፊዎች ጋር በመሆን የመስኖ ውሃ አቅምና ክምችትን መሰረት ያደረገ የመስኖ ውሃ ስርጭት ዕቅድ አዘጋጅቶ አገልግሎቶችን በመስጠት ነው። እቅዱም የሴት አርሶ አደሮችንና አቅመ ደካማ አርሶ አደሮችን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውሰጥ የሚስገባና በመስኖ ውሃ ፍታዊ ተደራሽነት ላይ ተጽዕኖ የማያስከትል መሆን ይኖርበታል።

የመስኖ ውሃ መሳቢያና ማሰራጫ እቃዎች ጥገና አገልግሎቶችን ማረጋገጥ፡- በዚህ ተግባር ላይ የመስኖ ልማት  ልማት ባለሞያዎችና የልማት ሠራተኞች ለአነስተኛና ሰፋፊ የመስኖ ተጠቃሚዎች የመስኖ እቃዎችን/ማሽኖችንና ሌሎች መጠቀሚያዎችን ማለትም እንደ ትሪድል እና ሞተር ፓምፕ፣ ጠብታ፣ የቧንቧ መስመሮች፣ የፕላስቲክ ውሃ ማጠራቀሚያዎችንና በርሚሎችን፣ ወ.ዘ.ተ ትክክለኛ የመስኖ ውሃ ስርጭት አገልግሎት እንዲሰጡ መከታተልን፣ ሲበላሹም ወቅታዊ ጥገና እንዲያገኙ ማድርግና ማስተባበር አስፈላጊ ነው።ይህም የመስኖ ውሃ እጥረት ከመጠን በላይ የሆነ የመስኖ ውሃ ወደ ማሳ ገብቶ በሰብል ላይ ጉዳት እንዳያስከትልና በመስኖ ውሃ እጥረት ምክኒያት ግጭት እንዳይፈጠር ይረዳል።

የአፈር ክለትን መቀነስ የሚችል የመስኖ ውሃ አጠቃቀም መተግበር፡- የመስኖ መሬት ውስጥ ከመሬቱ አቀማመጥ እና ከውሃ አጠቃቀም የተነሳ የመስኖ መሬቱ በአፈር ክለት እንዲጎዳ እና ከአገልግሎት ውጭ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ተዳፋትነት ባላቸው የመስኖ መሬት ላይ ተገቢው የአፈር ክለት ማገጃ ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲሁም በአፈሩ ላይ አደጋ ሊያደርስ የሚችል የውሃ አጠቃቀም እንዳይኖር የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያው ምክር ያስፈልጋል፤ ተገልጋዩም ህብረተሰብ መተባበር ይገባዋል።




ስዕል-7፡- የመስኖ ልማት የሚከናወንባቸው ማሳዎች የአፈር ክልት እንዳፈጠር በተገቢው መንገድ የውሃ ቦይ

**በመስኖ መሬቶች ላይ ከመጠን በላይ የመስኖ ውሃ እንዲተኛ አለማድረግ፡-** የመስኖ ውሃ ተገኘ ተብሎ በተለይ ደግሞ ምንም የተዳፋትነት መጠን በሌለባቸው አካባቢዎች እና አፈሩ ባህሪ ውሃን ወደታች የማስረግ አቅም በሌላቸው አካባቢ በማጥለቅለቅ እና ከመጠን በላይ የመስኖ ውሃን በማሳ ውስጥ መጠቀም ውሃው እንዲተኛ ወይም ረግረግ እንዲሆን ያደርጋል፣ እንዲሁም በማሳ ላይ የበቀሉ ሰብሎች ላይ የተለያዩ በሽታዎች እንዲፈጠሩ መነሻ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ተጠቃሚው ህብረተሰብ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያው በሚሰጠው የመስኖ ውሃ አጠቃቀም መመሪያና ተረፈ-መስኖ ውሃ የሚወገድበት የተለያዩ ማስወገጃ ስራዎች በመገንባት አላስፈላጊ ውሃ ማስወገድ እንዲሁም ከመጠን በላይ ውሃ ማሳ ውስጥ እንዳይተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባዋል፡፡

**የጨዋማ አካባቢ የመስኖ አጠቃቀምን መወሰን፡-** በሀገራችን ቀደም ሲል በተደረጉ ጥናቶች ከ11 ሚሊየን ሄ/ር በላይ ጨዋማ አፈር እንደሆነ ይገመታል፡፡ በጨዋማነት የተጠቃ መስኖ መሬት ሊስፋፋ የሚችለው የጨዋማ ንጥረ ነገርን ልቅ እና ተገቢ ያልሆነ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ሲኖር ነው፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለው ከገፀ-ምድር በታች ያለውን ጨዋማ አፈር (saline sedment) በመበጥበጥ ጨውን ወደ ላይኛውና ሰብሎች ሊበቅሉበት የሚችል ክፍል ላይ በማምጣት፤ የመስኖ ውሃው በራሱ ጨዋማ ሆኖ አርሶ/አርብቶ አደሩ በማሳው ላይ ሲጠቀምበት፤ ወይም ከመጠን በላይ እና ከባለሙያ ምክር ውጭ የኬሚካል ማዳበሪያ ብቻ (የተፈጥሮ ማዳበሪያ ባለመጠቀም) በአፈር ውስጥ ካለው የአፈር ኬሚካላዊ ይዘት ጋር በመዋሃድ የሚከሰት የተተከለውን/የተዘራውን ሰብል እንዳይበቅል ሊያደርግ ስለሚችል የመስኖ ውሃ አጠቃቀም በባለሙያ እና በመስኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ምክር አጠቃቀሙን መወሰን ይኖርበታል፡፡

**በተፈጥሮ ኩሬ እና ሀይቆች የሚገኘውን የመስኖ ውሃ በአግባቡ መጠቀም ፡-** እንደሚታወቀው በአገራችን የሚገኙት የተፈጥሮ ኩሬዎች እና ሀይቆች ውስን ናቸው፡፡ እነዚህ የውሃ አካላት ደግሞ በአካባቢው የሚገኘውን ብዛህ ህይወት የሚጠብቁ እና የአካባቢውን ተፈጥሮአዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚጠብቁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- በምስ/ሐረርጌ ዞን የላንጌ እና የሐሮማያ ሃይቆች በእንደዚህ አይነት አጠቃቀም ሁኔታ አሁን በሚገኙበት ደራጃ ይገኛሉ፤ በመሆኑም ከነዚህ የውሃ አካላት ያለአግባብ የመስኖ ውሃን መጠቀም ውሃው ሊያልቅ እና በአካባው የሚገኘውን ብዝሃ- ህይወት፣ የተፈጥሮ፣ የህብረተሰቡን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

ሊያዛባ ስለሚችል ለመስኖ አገልግሎት ከነዚህ የውሃ አካላት መጠቀም የሚቻለው በተፋሰሱ ወደ እነዚህ የውሃ አካላት ከሚገባው ውሃ መጠን በታች መሆን ስለሚገባው የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያው ለመስኖ አገልግሎት የሚጠቀሙትን የውሃ ፓምፖች ቁጥር እና መጠን መወሰን ይገባል፡፡

ተሳትፏዊ እና ፍላጎት ተኮር የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽንን ማሳደግ፤-የመስኖ ልማት ሥራ የጉልበት ፣የሀብት እና የጊዜን መስዋትንት የሚጠይቅ ነው፡፡ የመስኖ ውሃውንም ይሁን የሚጠቀሙበትን የመስኖ መሬት በዘላቂነት ለመጠበቅና ለመጠቀም የውሃውን የፍሰት አቅም እና የመስኖ መሬቱን ሊጎዱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ተጠቃሚው ህብረተሰብ እና የመስኖ ልማት ሥራውን ከሚያስተባብሩ መንግስታዊ ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲኖር የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያው መስራት ይገባዋል፡፡

በታችኛው እና በላይኛው ተፋሰስ የውሃ ተጠቃሚዎች ፍትሃዊ አጠቃቀምን ማጎልበት፤- በተፈጥሮ የሚፈስ የወንዝ እና የምንጭ ውሃ በተፋሰሱ ዙሪያ ለብዛ-ህይወት ከፍተኛ አገልግሎት እንደሚሰጥ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ሰው ለመስኖ አገልግሎት ሲባል የሚፈሰውን ወንዝ ወይም ምንጭ ሙሉ በሙሉ መጠቀም በታችኛው ተፋሰስ የሚገኙ ብዛህ-ህይወት ላይ ተጽዕኖ ስለሚኖረው እንዲሁም ከህብረተሰቡ ጋር ግጭት ሊፈጥር ስለሚችል የሚገደበውን ውሃ መጠን የመስኖ ልማት የኤክስቴንሽን ባለሙያው በሚሰጠው ምክር መሆን ይገባዋል፡፡

የመስኖ ውሃ ቦይ ጽዳትና እድሳት ማድረግ፡- የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች የመስኖ ቦዮችን በተለይም በየማሳቸው አቅራቢያ ያሉትን 3ኛ ደረጃ ቦዮች (tertiary canals) በማጽዳትና መለስተኛ እድሳት እንዲካሄድላቸው በማድረግ ያለምንም መንጠባጠብ አስተማማኝ የውሃ ፍሰት እንዲኖር ማድረግ አለባቸው፡፡

የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበር እንዲቋቋም መደገፍ/ Irrigation Water Use Association/ :- ለስኬታማ የመስኖ አውታር ግንባታ ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚመራውና የሚያስተዳድረው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ከውሃ ተጠቃሚዎች ጋር በመተባበር እንዲቋቋም ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም ዲሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ሂደትን ተከትሎ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ለማቋቋምና ልማቱን ለማሳለጥ የመስኖ ልማት ባለሙያዎችና የልማት ሰራተኞች ቁልፍ ተግባር መሆን ይኖርበታል፡፡

የመስኖ ውሃና መሬትን መሰረት ያደረገ ንዑስ ቡድን ማቋቋም፡- የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ንዑስ ቡድን እንዲመሠረት መደረጉ የራሱን ስራ በጋራ እያጠና የቡድኑ አባላት የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያበረታታል፡፡ በተጨማሪም ሁሉም የውሃ ተጠቃሚ አባላት ያላቸውን አቅም አሚጠው የመስኖ ልማት ዓላማን ለማሳካትና ችግሮችን በጋራ ለመቅረፍ፣ እንዲሁም በሥራቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ንዑስ ቡድኑ ጉልበት ይሆናቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ዕለት ተዕለት ወሳኝ በሆኑ የመስኖ ልማትና ሌሎች ጉዳዩች ዙሪያ የንዑስ ቡድኑ አባላት አብሮ በመስራት፣ በእቅዳቸው ላይ ተወያይቶ ክለሳ በማድረግ፤ አዳዲስና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች ሥራ ላይ መዋልቸውን ማረጋገጥና በማሳለጥ ረገድ የመስኖ ልማት ንዑስ ቡድኖች እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡

**የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ምክንያት የሚነሱ ግጭቶችን እና አለመግባባቶችን መፍታት፡-** በመስኖ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ በሚፈጠሩ አለመግባባቶች የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት ለችግሮቻቸው መፍትሄ ይሰጡ ዘንድ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት የቀበሌ አስተዳደር በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር እና ንዑስ ቡድን መሪዎች ጋር በመሆን የመስኖ ባለሙያዎችና የልማት ሰራተኞች በውሃ ተጠቃሚዎች መካከል በመስኖ ውሃ ስርጭት ምክንያት የሚፈጠረውን አለመግባባት ለመዳኘት ጉልህ ሚና ይጫዎታሉ፡፡

**የመስኖ ግብዓት፡-** የመስኖ ልማት ባለሞያዎችና የልማት ሰራተኞች ከመስኖ ንዑስ ቡድን እና ከአነስተኛና ሰፋፊ መስኖ ውሃ ተጠቃሚ መሪዎች ጋር በመሆን የመስኖ ግብዓት ፍላጎት መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የመስኖ ልማት ሰራተኞች የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን ከግብዓት አቅራቢዎች ጋር በማገናኘት ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የተባይና በሽታ መከላከያ መድሀኒቶች፣ የመስኖ ልማት መገልገያ መሳሪያዎችን እጅ በእጅ ግዥ ወይም በብድር መልኩ እንዲያገኙ ያመቻቻሉ፡፡

**የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ከገበያ አማራጮች ጋር ማስተሳሰር፡-** የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዋናው ዓላማ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ከንግድና ገበያ አማራጮች ጋር በማስተሳሰር የገበያ ፍላጎትን መሠረት አድርገው ገበያ ተኮር የሆኑ ሰብሎችን እንዲያመርቱ ማድረግና መደገፍ ነው፡፡ በመሆኑም የመስኖ ልማት ባለሞያዎችና የመስኖ ልማት ሰራተኞች ሚና ቀጣይነት ካለው የገበያ መሸጫ ቦታ፣ ከሁለገብ ሕ/ሥ/ማህበራት፣ በወረዳ ደረጃ ካሉ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲና ሌሎች የገበያ አማራጮች ጋር ትስስር እንዲኖር ማገዝ እና ትክክለኛ የገበያ መረጃ አሰባስቦ ለተጠቃሚዎች በወቅቱ በማሳወቅ ምርታቸውን በተሻለ ዋጋ እንዲሸጡ ማድረግ ነው ፡፡

**በመስኖ ኤክስቴንሽን ሥራ ላይ ሙሉ ጊዜን ማሳለፍና አስፈላጊ ተግባራትን ማያያዝ፡-** የመስኖ ልማት ከዝናብ ተኮር ግብርና ልማት የሚለይበት ዋና ጠባይ አንዱ ተከታታይ የሆነ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም፣ የተባይ ክትትል፣ የገበያ መረጃ ማሰባሰብና መተንተን፤ እንዲሁም የምርት ዓይነትንና ብዛትን የመወሰን ድጋፍ በትክክል ለውሃ ተጠቃሚዎች እንዲደርስ መስራት ማስፈለጉ ነው፡፡ በሌላ በኩል የመስኖ ባለሙያዎችንና የልማት ሰራተኞችን በታቀደና በተጠና የኤክስቴንሽን ዘዴ አዳዲስና የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋዎቅና የማላመድ ስራን፤ እንዲሁም ከውሃ ተጠቃሚዎች ጋር የጋራ መተማመን ላይ መድረስን ይጠይቃል፡፡

**የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን በዕቅድና በውሳኔ ሰጪነት ሂደት ላይ ተሳታፊ ማድረግ፡-** የመስኖ ውሃ ፍላጎት፣ አቅርቦትና ስርጭት፤ እንደዚሁም የማስራጫያና የማጠራቀሚያ ዓይነቶች፣ በአነስተኛና ሰፋፊ መስኖ ተጠቃሚዎች፣ በሴትና ወንድ አርሶ/አርብቶ አደሮች እንደ አከባቢው ሁኔታ በዓላማና በምርት ዕቅድ ይለያያል፡፡ የጠብታ መስኖ፣ የምንጭ ማጎልበት፣ የፔዳል ፓምፕ፣ የእጅ ፓምፕ፣ የአነስተኛ ሞተር ፓምፕ፤ የማህበረሰብ ኩሬ ወዘተ… የመሳሰሉት በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በፍላጎት ልየታ፤ ዕቅድና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የውሃ ተጠቃሚ አርሶ አደሮችን ተሳታፊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አነስተኛ/ ሰፋፊ የመስኖ ተጠቃሚዎችን ተሳታፊ በማድረግ በውሃ ተጠቃሚዎች ዘንድ የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠርና እንዲጎለብት በማድረግ የመስኖ አውታሮች ዘላቂታዊ አገልግሎት እና ጥቅም እንዲኖራቸው ይረዳል፡፡

**የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎች ሰርቶ ማሳያዎችን ማካሄድ፡-** የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ውጤታማ የሚሆነው አርሶ አደሩን በማሳተፍ፣ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን በማገናዘብና የመስኖ ግብዓቶች ተደራሽነት መሠረት አድርጎ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን በሠርቶ ማሳያዎች ደረጃ የማስተዋወቅና የማላመድ ሥራ ሲተገበር ነው፡፡ በመሆኑም የመስኖ ልማት ሠራተኞችና የመስኖ ባለሙያዎች በሰርቶ ማሳያዎች ላይ የተለያዩ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዘዴዎችን በመጠቀም እና የአርሶ አደር በዓል ቀን በማካሄድ የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ማጎልበት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም የመስኖ ባለሙያዎችና የልማት ሰራተኞች የአርሶ/አርብቶ አደር የመስክ በዓል ቀን ከማዘጋጀታቸው በፊትም በወሳኝ የሰብል እድገት ደረጃዎችና በሌሎች ተግባራት ወቅት ሌሎች አነስተኛ የመስክ ቀን ማዘጋጀትና ቁልፍ ተግባራትን ማሳየትና ማስተማር ይኖርባቸዋል፡ ፡ ለምሳሌ በስልጠና ዳሰሳ ጥናት ወቅት አርሶ አደሩ ባመላከታቸው የመስኖ መሬት ዝግጅት፣ የቦይ ጠረጋ፣ የመስኖ ችግኝ ዝግጅት፣ የመስኖ ውሃ ማጠጫ ዘዴዎች፣ መስኖ ሰብል ዘር መረጣ ቴክኒክ፤ የመስኖ ማደበሪያ አጠቃቀም፣ የመስኖ ሰብል አሰባሰብና ድህረ ምርት አያያዝ፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡



ፎቶ-7፡- በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋም ውስጥ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሥራ መከናወን ይገባዋል (ጅማ ዞን ማና ወረዳ ኢላሳ ጉዳ የአ/ማ/ተቋም)

**የመስኖ አውታሮችን ችግር መለየት፡-** ከመስኖ ልማት ሰራተኞች ዋና ዋና ሚናዎች መካከል የመስኖ አውታር ተሳትፏዊ ግንባታ፣ ክትትል፣ ጥገናና የወሃ አጠቃቀምና የመስኖ ተቋም አስተዳደርና አያያዝ ጋር የተያያዙ ቁልፍ ችግሮችን መለየት ነው፡፡ በተጨማሪም የልማት ሰራተኞች በመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ቡድኖች ደረጃ ለሚከሰቱ ችግሮች የጋራ ግንዛቤ በመፍጠር ለችግሮቹ መፍትሄ እንዲሰጡ ማድረግ ይኖርባቸዋል፤ ሆኖም ግን ከአርሶ አደሮች አቅም በላይ ከሆኑ ቸግሮቹን ከመፍትሄ ሀሳቡ ጋር ለሚመለከተው የበላይ አካል እንዲቀርብ ያደርጋሉ፡፡

**መደበኛ የመስኖ አውታሮች ጉብኝት፡-** የመደበኛ የመስኖ አውታሮች ጉብኝት አዳዲስ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን ለውሃ ተጠቃሚዎች የሚዳረሱበት፣ የአርሶ/አርብቶ አደሮች ችግርም ሆኑ የአካባቢ ተሞክሮ/ልምድ/ ለኤክስቴንሽንና ለምርምር ሴክተሮች የሚቀርቡበት የሁለትዮሽ የኤክስቴንሽን ተግባቦት አሠራር ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም የመስኖ ልማት ሰራተኞች ዘወትር የመስኖ አውታሮችን መጎብኘት ይኖርባቸዋል፡፡

**የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴ፡-** የመስኖ ልማት ሰራተኞች የውሃ ተጠቃሚዎች በሚፈልጉትና በሚጠብቋቸው ተገቢና ወቅታዊ በሆኑ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን

ርዕሶች ላይ መደበኛ እና ተስማሚ የሆነ ስልጠና መሠጠት አለባቸው፡፡ የውሃ ተጠቃሚዎች ቴክኖሎጂን ተቀብሎ ሥራ ላይ ለማዋል፣ ለውሃ ተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ ለማድረግ እና በመስኖ ተሞክሮዎች መሻሻሎችን ያለማቋረጥ ለመከታተል የኤክስቴንሽን መልዕክቶች ጠቃሚ ናቸው፡፡ የመስኖ ልማት ሰራተኞች በየሁለት ሳምንቱ ለውሃ ተጠቃሚዎች የተመረጡና ወቅታዊ የሆኑ የመስኖ ልማት  ልማት መልዕክቶችን ተደራሽ ለማድርግ እንደ ፖስተር፣ ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ወዘተ... የመሳሰሉትን የኤክስቴንሽን ማስተለፊያ ዘዴዎች መጠቀም አለባቸው፡፡

**የምርምር-ኤክስቴንሽን-አርሶ አደር ግንኙነትን ማስቀጠል፡-** የምርምር ተቋማት ከኤክስቴንሽን ባለሞያዎችና አርሶ አደሮች ጋር በመሆን የመስኖ ልማት  ልማት ችግሮችን በመለየት ጥናት ማካሄዳቸው ለስኬታማ የቴክኖሎጂ ልማት በጣም ወሳኝ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችንና ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን ሥራ ላይ ለማዋል አሳታፊ ቴክኖሎጂ ልማት አቀራረብ/ Participatory Technology Development/ ዘዴን ተጠቅሞ በአርሶ አደር ማሳ ላይ ወይም በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል ደረጃ በጋራ ሰርቶ ማሳያዎችንና የሙከራ ጣቢያዎችን ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ስለሆነም የመስኖ አርሶ/አርብቶ አደሩ ቴክኖሎጂን ተቀብሎ ሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል የአርሶ አደር - ምርምር - ኤክስቴንሽን ግንኙነትን ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡

በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ የመስኖ ልማት ሰራተኞች የውሃ ተጠቃሚ ቡድኖችን የሚጎበኙበት መደበኛ ቋሚ ፕሮግራም መኖር አስፈላጊ ሲሆን የመስኖ አርሶ/አርብቶ አደሩም የሚጎበኝበትን ጊዜ ማወቅና የሚደረግለትን የድጋፍ ዓይነት መግለፅ ይጠበቅበታል፡፡ በእያንዳንዱ ጉብኝት ወቅትም የመስኖ ልማት ሰራተኞች የውሃ ተጠቃሚ ንዑስ ቡድን ተወካዮችን በየብሎካቸው ማግኘትና ማነጋገር ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የልማት ሰራተኞች ሌሎችን አርሶ አደሮችን ለማግኘት ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

የልማት ሰራተኞች በተቻለ መጠን በርካታ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ለማግኘት የሚያስችሉ የኤክስቴንሽን ዘዴዎችንና አቀራረቦችን በመጠቀም ወቅታዊና ተገቢ ድጋፎችን ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም የአርሶ/አርብቶ አደር እና የመስኖ ውሃ ንዑስ ቡድን ተወካዮችን በማግኘት ቀደም ብሎ ማማከርና የተመቻቸ ቀጠሮ ማስያዝ ጠቃሚ ነው፡፡ ስለሆነም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መልካም ውጤት/መቃናት/ በዋናነት በሚከተሉት ጉዳዮች ይወሰናል፡፡

- የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበር/ የማህበረሰብ ኩሬ ተጠቃሚ ተወካይ/ኮሚቴ አርሶ/ አርብቶ አደሮች በተገቢው መንገድ መምረጥ፣
- የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደር ተወካዮችንም ሆነ ሌሎች የውሃ ተጠቃሚዎች በወቅቱና በመደበኛ ሰዓት መጎብኘት፣
- ከአርሶ/አርብቶ አደሮች ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ ወሳኝ መልዕክቶችን መለየትና በተወካዮች አማካኝነት ወደ ሌሎች አርሶ አደሮች እንዲሰራጩ ማድረግ፣
- የኤክስቴንሽን መልዕክቶችን ተቀብሎ ሥራ ላይ ለማዋል በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ግብረ መልስ መስጠት፣
- ለመስኖ ልማት ሰራተኞችና ለመስኖ ቴክኒሽያኖች በሚገባ የተደራጀ ወርሀዊ የስልጠና ፕሮግራም እንዲኖር ማድረግ፣
- ለመስኖ ልማት ሰራተኞችና አርሶ/አርብቶ አደሮች በመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ኮሚቴዎች

ዋና ተግባር ላይ ድጋፍ መስጠት፣

- ሱፐርቫይዘሮች በመስኖ ኤክስቴንሽን ተግባራት ወቅታዊነትና ትክክለኝነት ላይ የቅርብ ክትትል ማድረግ፣
- ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ተመራማሪዎችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በአካባቢው ቴክኒካል በሆኑ ጉዳዮች ላይ ምክረ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ማመቻቸት፣

ክፍል-1

ለፆታዊ እኩልነት ማነስ መነሻ የሆኑ ጉዳዮች ምንድን ናቸው;

የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ሴቶችን ተደራሽ ያላደረገ መሆን

- ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች ከወንዶች ይልቅ ከመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ጋር ያላቸው ግንኙነት አነስተኛ እና በቂ ባለሙሆኑ ምክንያት እና ተገቢውን የመስኖ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ባለማግኘታቸው የተነሳ በመስኖ ልማት ተሳታፊና በዘላቂነት የኢኮኖሚ ተጠቃሚ መሆን አልቻሉም፡፡ በተጨማሪም በልማዳዊና በባህላዊ ኋላ ቀር አስተሳሰቦች ምክንያት የወንዶች እና ሴቶች አርሶ/አርብቶ አደሮች የእርስ በእርስ እና ከመስኖ ልማት ሠራተኛ ጋር ያላቸው ግንኙነቶች ውስንነት ባለበት አካባቢ አልፎ አልፎ የመስኖ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሲቀርብ በተለይ ሴቶች አርሶ/አርብቶ አደሮችን ያላሳተፈና ያላመከለ በመሆኑ ተገቢውን የመስኖ ልማት እውቀት፣ ክህሎት እና ትምህርታዊ ስልጠናዎችን ሳያገኙ ይቀራሉ፡፡
- የሚቀርብላቸው የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሴት አርሶ/አርብቶ አደሮችን ፍላጎት፣ ችግር እና ጊዜን ያላማከለ በመሆኑ በቂ ዕውቀት ስለማያገኙ በመስኖ ልማት ረገድ ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች በብቃት ሲሳተፉ አይስተዋሉም ፡፡ ስለሆነም ቀጣይነት ያለውን የመስኖ ልማት ለማስመዝገብ የሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ሊረጋገጥ ስለሚገባ የመስኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና መስኖ ልማት ሠራተኞች ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፡፡



ፎቶ- 8፡- ሴት አርሶ አደርን ማዕከል ያደረገ የመስኖ አጠቃቀም (ሰሜን ሸዋ ዞን ምንጃር ሸንኮራ ወረዳ፤- ፎቶ በዶ/ር አካሉ ተሾመ)

- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት የሴት አርሶ/አርብቶ አደሮችን የስራ ጊዜን ያላገናዘበና ምቹ አገልግሎት የሚያገኙበትን ጊዜ ግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች በመስኖ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሰጪ እና ተጠቃሚ አያደርጋቸውም፡፡ በተጨማሪም የሚተላለፉ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መልዕክቶች የሴቶችን የተለየ የስራ ጫና ኃላፊነትና የሚገጥማቸውን ተግዳሮቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ረገድ ያነሰ ነው፡፡

የሚመረጡ የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎች የሴት አርሶ/አርብቶ አደሮችን ፍላጎት ያላማከለ መሆን

- ሴቶች አርሶ/አርብቶ አደሮች የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎችና የተሻሻሉ አሰራሮች ሲመረጡም ሆነ ሲተገበሩ የእነርሱን ፍላጎት ያላማከለ እና ያላሳተፈ በመሆኑ በአጠቃቀም እና በአተገባበር ላይ ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮችን ያላማከለ የቴክኖሎጂ አተገባበርና አጠቃቀም አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚፈጥር ሥራ ላይ የሚውሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች በዝቅተኛ ደረጃ እና በአነስተኛ ሁኔታ እንዲጠቀሙ ያደርጋቸዋል፡፡
- በአርሶ/አርብቶ አደሮች ማሳ እና ማሰልጠኛ ማዕከላት የሚሰሩ የመስኖ ልማት የቴክኖሎጂ ሰርቶ ማሳያዎችና የቴክኖሎጂ ምርምር ሙከራዎች በበቂ ሁኔታ ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮችን ተሳትፎ ያላማከለ እና ተጠቃሚነትን ያረጋገጠ አለመሆን፡፡

በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አሰራር የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን እንዴት ተደራሽ ማድረግ ይቻላል?

- ሥርዓተ-ፆታን ያማከለ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰራርን ጊዜ ቆጣቢና በቀላሉ ሊተገበሩ ሚችሉ የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ ተግባራዊ ማድረግ፡፡
- ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮችን በመስኖ ልማት ረገድ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ እነሱም በተለየ መልኩ ለማበረታታት የሴቶች ልማት ቡድኖችን አደራጅቶ የመስኖ ስልጠና እና ማልሚያ ቦታ፣ የልምድ ልውውጥ፣ትምህርታዊ ጉብኝት፣ እና የግንባር ቀደም የሴቶች ቡድን እና የሴቶች የመስኖ ማህበራትን እንዲመሠረት በማድረግ ሴቶችን በመስኖ ልማት ተደራሽና ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል፡፡
- በአርሶ/አርብቶ አደሮች ማሳ እና ማሰልጠኛ ማዕከላት የሚሰሩ የመስኖ ልማት የቴክኖሎጂ ሰርቶ ማሳያዎችና የቴክኖሎጂ ምርምር ሙከራዎች በበቂ ሁኔታ ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮችን ተሳትፎ ተደራሽነት እንዲያረጋግጥ ማስቻል፡፡

# ምዕራፍ -3 አሳታፊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልትና ዘዴ

በዋናነት በኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ ያለንን ውስን ሀብት፣ የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅም በተገቢው መንገድ ተጠቅመን የሚፈለገውን ሁለንተናዊ የሀገር ዕድገትና ለውጥ ማምጣት እንዲቻል ውጤታማ የኤክስቴንሽን አቀራረብና አተገባበር አቅጣጫዎችን መከተል ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥን ውጤታማ ለማድረግ ከዚህ በታች የሚከተሉትን አቀራረብና አተገባበር አቅጣጫዎች መከተል ያስፈልጋል፡፡

አሳታፊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ የባለአነስተኛ የመስኖ ይዞታ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን በመስኖ ውሃ ልማት ተነሳሽነት እንዲኖራቸውና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ በጎ ተጽዕኖ ፈጣሪ እንዲሆኑ የሚያደርግ የአሠራር ዘዴ ይዘረጋል፡፡ ይህ አቀራረብ ለሁለቱም የውሃ ተጠቃሚዎች እና ለመስኖ ልማት ሰራተኞች እንደ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት፣የመስኖ ህብረት ስራ ማህበራት እና የውሃ ተጠቃሚ ቡድኖች ማቋቋም እና የገጠር ማህበረሰብን ማካተት ከሚችሉ ከባለድርሻ አካላት ጋር ትስስር እንዲፈጠር ማድረግ ነው፡፡

ይህ ዘዴ ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችምና የመስኖ ልማት ሰራተኞች የመስኖ ልማት ልማት ቁልፍ ችግሮችን መለየት፤ በቅድም ተከተል ማስቀመጥ፤ ማቀድ፤ መተግበር፤ መከታተል እንዲሁም በመገምገም አሠራርን ከማጎልበት አልፎ የመስኖ ማህበራትና የውሃ ተጠቃሚ ቡድኖችን ለማቋቋምና ለማደራጀት አይነተኛ አካሄድ ከመሆኑም ባሻገር፣ አነስተኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማት ልማት ተጠቃሚዎችን በባለአነስተኛ ይዞታ የአርሶ አደሮችና አርብቶ አደር ማሳ ላይ መደገፍ ከሚችሉ አጋር አካላት ጋር ትስስር በመፍጠር ረገድ መማማርን ከፍ የሚያደርግ ነው፡፡

አሳታፊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ በዋናነት አርሶ/አርብቶ አደሩ በመስኖ ግብርና ጉዳይ ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲያዳብርና ይሄንኑ ሚና እንዲጫወት ማሳየትና ማገዝ ነው፡ ፡ ሌሎች አካላት አጋዥ/ድጋፍ ሰጪ መሆናቸውን ማሳወቅና ማስገንዘብም የዚሁ አቀራረብ ዘዴ አካል ነው፡፡ በመጨረሻም የማህበረሰቡን የግንዛቤ ፤አመለካከትና ክህሎት አቅም ከፍ በማድረግ የውሃ ተጠቃሚዎችንና የራሳቸውን የመስኖ አውታር/የማህበረሰብ ኩሬ በራሳቸው አቅም እንዲመሩት ያስችላቸዋል፡፡ ራስን መቻልና በራስ መተማመን ያዳብራል፡፡ በተጨማሪም አሳታፊ የሆነ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ የኤክስቴንሽን ባለሞያዎችና የመስኖ ልማት ሰራተኞችን ሚና ከአማካሪነት ወደ አመቻችነት እንዲቀየር ያደርጋል፡፡ በሂደትም ወደ መዋቅራዊ ለውጥና ወጪ መጋራት ያመራል፡፡

ፍላጎትን መሠረት በማድርግ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠናና የምክር አገልግሎትን ለመስጠት የመስኖ ውሃ ማኔጅመንት አገልግሎትን ተሳትፏዊ የኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴን ቢጠቀም ውጤታማ ይሆናል፡፡ የመስኖ ልማት ዕቅድ ትግበራን በተያዘለት ጊዜና ሀብት ለመተግበር የሚከተሉትን መስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴዎች ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ነው፡፡

## 3.1. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ለመተግበር አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች

ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች (SSI, HHMI & Community water pond) ምክር እና ድጋፍ ለመስጠት ሲፈለግ የመስኖ ባለሙያዎች፣የልማት ሰራተኞች ወይም ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሚከተሉትን ቅድመሁኔታዎችን ማወቅ ይኖርባቸዋል ::

የመስኖ ውሃ መገኛውን ማወቅ (irrigation water source):- ይህ ቅደመሁኔታ ምን አይነት የኤክስቴንሽን ትምህርቶችን መስጠት እንደሚያስፈልግና ለማን እንደሚሰጥ ያመላክታል። ይህንንም መሰረት በማድረግ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ዓይነትን፣የመስኖ ውሃ ፍላጎትን፣ የውሃ ክምችትን፣ ወዘተ ግምት ውስጥ በማስገባት ትክክለኛ የሰብል አመራረት ዘዴን ተከትሎ የመስኖ አውታርን ዕቅድና የግበዓት አቅርቦትን ለመወሰንና ለማዘጋጀት ይረዳል።

የአካባቢውን ስነ-ምዳር ማወቅ:- የአካባቢ ስነምህዳር ስንል በአካባቢው ሚገኘውን የአፈር አይነትና ቴክስቸር፣ የተዳፋትነት መጠን፣ ከባህር ጠለል በላይ ያለው ከፍታ፣ የዓየር ንብረት(የሙቀት ሁኔታ፣ዓመታዊ የዝናብ (መጠን፣ወቅት እና ስርጭት)፣ በአካባቢ የሚበቅሉ ዕጽዋቶች እና የዱር አራዊቶችንና አኗኗር ሁኔታ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ይህ አሰራር ዘዴ የልማት ሰራተኞችና የመስኖ ባለሙያዎች በመስኖ የሚለማውን ማሳና የአፈር አይነት ማወቅ፣ የመስኖ ውሃ አጠቃቀምን፣ የመስኖ ውሃ ማጠጫ ተራን፣ የማጠጫ ሰዓት ርዝመትን፣ የአፈሩ ውሃ የመሸከም ችሎታን፣ ወዘተ በማወቅና በማስተማር ፍትሀዊ የመስኖ ውሃ ክፍፍል እንዲኖር ከማደርግ  በተጨማሪ ተፈጥሮአዊ የሆኑ ነገሮችን በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የመፍትሄ አቅጣጫ ለመጠቆም፣እርምጃ ለመውሰድ እና የመስኖ  ልማት ተጠቃሚው ህብረተሰብ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ እንዲችልና የሚለሙ የሰብል ዓነቶችን ለመለይት ያስቸላቸዋል።

የመስኖ ተጠቃሚ ማህበረሰቡን ማወቅ:- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያው  የሚገናኘው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ጋር በመሆኑ የማህበረሰቡን ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ታሪካዊ አኗኗር ሁኔታዎችን በተገቢው ሁኔታ ማወቅ ያስፈልገዋል። ይህም ሁኔታ የመስኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያው ህብረተሰቡን የግንዛቤ ማስጨበጫ እና ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት ለአካባቢው እንግዳ የሆኑ ነገሮችን በመቀላቀል የመስኖ ኤክስቴንሽን ስር የታቀፉ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ከማደናገር እንዲቆጠብ እና በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዳያጣ ይረዳዋል።

- አዋጭነት ያላቸውን ቴክኖሎጂዎችን ተስማሚነት ማወቅ:
- የመስኖ ሰብሎችን የውሃ ፍላጎት ማወቅ፣
- ተስማሚ የሆነ የመስኖ ውሃ አጠጣጥ ዘዴን መምረጥ፣
- የመስኖ ውሃ ማጠጫ ፈረቃን መተግበር፣
- የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ማማከር ዋና ዓላማ መሰረት በማድረግ የአሁንና የወደፊት የውሃ ተጠቃሚዎችን ፍላጎትን ማርካት፣
- በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የእያንዳንዱን የውሃ ተጠቃሚ ንዑስ ቡድን ተወካዮች ማስመረጥ፣

- ለመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ማስፋፋት ተግባር ልምድ ያላቸው የመስኖ ተጠቃሚዎችን መምረጥ፣
- በመስኖ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ ጥናት ማካሄድና አስፈላጊ ምክረ ሀሳቦችን ማቅረብ፤ እንዲሁም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማፈላለግ የተሻለውን በመምረጥ የማላመድ ስራ ለመስራት ሰርቶ ማሳያ ማካሄደ፣
- ከምርምር ተቋማት ጋር መገናኘትና በውሃ ተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ ጥናቶች እንዲካሄዱ ማድረግ፣
- የራስን የግል የመፍትሄ ሀሳብ ሳያንፀባርቁ አስፈላጊ በራሪ ጽሁፎችን፣ የምክር አገልግሎቶችን፣ ምክረ ሀሳቦችንና መረጃዎችን ለውሃ ተጠቃሚዎች ማቅረብ፣
- ውስን የሆኑ ሀብቶችን ለመቆጠብ ሲባል በጥንቃቄ የተመረጡ ዋና ዋና ቅድሚያ በተሰጣቸው ግቦች ላይ ትኩረት መስጠት፣
- የአካባቢ ተጽዕኖን ለመቀነስ በውሃ አጠቃቀምና አስተዳደር ላይ አማራጭ መንገዶችን መፈለግ፣
- በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች መካከል ፍትሀዊ የውሃ ክፍፍል እንዲኖር የሚያስችል መርህን ተከትሎ የውሃ አጠቃቀም ዕቅድ ማዘጋጀት፣
- በየደረጃው ያለው የመስኖ ሥርዓት በውሃ ቁጠባ መርህ እንዲመራ ማድረግ፣
- በተግባር የተደገፈ ቴክኖሎጂን በሠርቶማሳያ ቅድመ-ማስተዋወቅ
- አካባቢ ተኮር ምክረሃሰብን መስጠት

## 3.2. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መለየት

በግብርና ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሕብረተሰብ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡን በማጠናከር በመስኖ ልማት ስራ ላይ የተሰማራው አርሶ/አርብቶ አደር ሙያዊ ድጋፍ እንዲያገኝ፣ የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የዝናብ ተጠቃሚ ከሆኑት አርሶ/አርብቶ አደሮች መካከል ተለይቶ መታወቅ አለበት፡፡ በዚህም መሰረት ከዘህ በታች የተዘረዘሩት የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ቡድኖችና ማህበራት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡

- አርሶ/አርብቶ አደረሮች፣
- ሴቶች፣
- ወጣቶች፣
- ሞዴል አርሶ/አርብቶ/አርብቶ አደሮች እና
- በግብርና መስክ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች፣
- የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት፣
- ዕሴት በሚጨምሩ የስፔሻላይዜሽን ስራዎች የተደራጁ ቡድኖች ይሆናሉ፡፡

## 3.3. አርሶ/አርብቶ አደሩን፤ እንዲሁም የግል ባለሀብቱን ማነሳሳት

አርሶ/አርብቶ አደሩ እና የግል ባለሀብቱ በቀጣይ ስለሚያከናውኑት ተግባራት፣ ሊጠቀሟቸው ስለሚገቡ የተሻሻሉ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትና አጠቃቀም በቂ ግንዛቤ አግኝተው ለስራ እንዲነሳሱ፤ በተጨማሪም በአካባቢው ያሉትን የግብርና አሰራርና አመራረት ችግሮች ለይተው በማወቅ አስፈላጊ የመፍትሄ እርምጃዎችን መውሰድ እንዲችሉ የቅስቀሳ ሥራዎችን መስራት ተቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች የተለያዩ የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅመው በወቅቱ ማከናወን የሚገባቸውን የመስኖ ልማት ተግባራት በማከናወን ምርትና ምርታማነታቸውን አሳድገው ገቢያቸውን በመጨመር የተሻለ ኑሮ መኖር እንዲችሉ ለማድረግ የማነሳሳት ሥራዎች በቅድሚያ ይሰራሉ፡፡

## 3.4. ገበያ ተኮር ተሳትፎአዊ የአክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት

አርሶ/አርብቶአደሩ፤ እንዲሁም የግል ባለሀብቱ ገበያ ተኮር አሰራርን ተከትሎ የተጠናከረ የኤክስቴንሽን አገልግሎትና የገበያ መረጃ በማግኘት የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅመው ምርትና ምርታማነታቸውን በማሳደግ የሀገር ውስጥ ፍጆታን ማሟላት፣ ለፋብሪካና ኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን፤ እንዲሁም ለውጭ ምንዛሬ ግኝት አስፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ዕሴት በመጨመር ገበያ ላይ በማቅረብ ገቢያቸውን ጨምረው የተሻለ ኑሮ መኖር እንዲችሉ ተሳትፎአዊ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ወሳኝ ነው፡፡ በተጨማሪም በየደረጃው ባሉ እሴት ሰንሰለቶች ላይ የስራ እድል ፈጠሮ የዜጎችን ስራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ ያለው ፋይዳ የሚናቅ አይደለም፡፡ በመሆኑም ይህን የአክስቴንሽን አቀራረብና አተገባበር ዘዴ ተከትሎ የመስኖ ልማት ማካሄድ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የመስኖ ልማቱን ውጤታማ ለማድረግ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ በአብዛኛዎቹ የመስኖ ልማት ምርታማነት እሴት ሰንሰለቶች ላይ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው መሆን ስላለበት የግብርና ምርታማነት እሴት ሰንሰለት በጂኦግራፊ-ተኮር የገበያ እድል መፍጠሪያ ስትራቴጂያዊ አቀራረብን እና በርካታ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት ለመተግበር የሚያስችሉ መድረክን በመፍጠር ገበያ ተኮር የኤክስተንሽን አሰራር ዘዴን መከተል ነው፡፡ ለምሳሌ፤- የሙዝ መንደር፣ የማንጎ መንደር እና የመሳሰሉትን አደረጃጀት በመከተል ከግብዓት አቅርቦት፣ ከመመሚሪያ ሁኔታ፣ ከቴክኒክ ድጋፍ ከማድረግ አኳያ፣ ከገበያ ጋር ለማስተሳሰርና ለማስተዋወቅ ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ዘዴ ነው፡፡ ይህም አርሶ/አርብቶ አደሩ የገበያ ፍላጎትንና የገበያ መረጃን መሰረት ያደረገ ገበያ ተኮር ምርትን ማምረት መቻል፣ ማለት ነው፡፡ የመስኖ ልማት ባለሞያዎችና የልማት ሰራተኞች በዚህ ረገድ የገበያ ፍላጎትን በማረጋገጥ፤ የገበያ መረጃን በማቅረብ፤ ጥራት ያለውና በቂ ምርት እንዲኖር በማድረግ፤ ጅምላና ችርቻሮ ገዥዎችን በማስተሳሰር፣ ወዘተ ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## 3.5. ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዘዴ

ይህ የመስኖ ኤክሰቴንሽን ዘዴ ወይም አሰራር የአርሶ/አርብቶ አደሩን ገቢ በመጨመር ዘላቂ መተዳደሪያ እንዲኖረው ይረዳል፡፡ የአርሶ/አርብቶ አደር የመስኖ ልማት ልማት ፍላጎት ልየታ ዳሰሳ ጥናት፣ ተሳተፎአዊ የገጠር ዳስሳ ጥናት (PRA) ፤ የልማት ሰራተኛ የውሎ ስራ መመዝገቢያ ማስታወሻ (DA extension diaries) ወዘተ የመስኖ ኤክስቴንሽን ዘዴ ወይም አሰራርን ለማከናወን የምንጠቀምባቸው ቴክኒኮች ናቸው፡፡

## 3.6. የተሰባጠረ መስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዘዴን መጠቀም

የመስኖ ልማት  ልማት ባለሙያዎቸና የመስኖ ልማት ሰራተኞች በመስኖ ተጠቃሚዎች የተዘጋጀውን ዕቅድ ለማስተግበርና የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ የተለያዩ/ የተሰባጠረ የኤክስቴንሽን ዘዴዎችን መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ሲባል የተናጥል፤የቡድን፤ የወል የኤክስቴንሽ ተግባቦቶችንና ተሳትፎዓዊ ቴክኖሎጂ የማላመድ ወይም ሌሎች የመስና ኤክሰቴንሽን ዘዴዎችን እያፈራረቁ ወይም በአንድ ላይ እንደ አስፈላጊነቱ ወይም እንደ ዓላማው መጠቀም ማለት ነው፡፡

## 3.7. ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት መዘርጋት

በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ለግብርና ልማት ሥራ ተግባራዊነት አጋር ከሆኑ መንግስታዊና መንግስታ ካልሆ የልማት ድርጅቶች ጋር ተቀናጅቶ መስራት የላቀ ጥቅም አለው፡፡ ስለሆነም በየደረጃው ከፌደራል እስከ ወረዳ ድረስ ከተቋቋሙት የልማት አካላት አማካሪዎች ጋር ያለውን የግንኙነት ጊዜ አጠናክሮ በማስቀጠል ለውጥ ሊያመጡ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ስምምነት ላይ በተደረሱ ውሳኔዎች እና መግባባቶች መሰረት ተጠያቂነት ባለው መንገድ የመስኖ ልማት ስራዎችን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሰረት በግብርና ልማትና በምርምር ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚንቀሳቀሱ አካላት ማለትም የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂ አቅራቢ ድርጅት፣ በግብርና የተሰማሩ ባለሀብቶች፣ የብድርና የምርት ማቀነባበሪያ ተቋማት፤ እንዲሁም በግብይት ተግባር ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች፣ የህብረት ስራ ዩኒየኖች፣ አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ ወዘተ… ተቀናጅተው እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ የመስኖ ልማት ሥራዎችን በመደገፍ ማፋጠን ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የግብርና ልማት አካላት ግንኙነት ምክር ቤት/ካውንስል ስር የሚገኙ ባድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 3.7.1. ግብርና ምርምር

የአርሶ/አርብቶ አደሩን የቴክሎጂ ፍላጎት ማርካት የሚቻለው የግብርና ምርምር ከኤክስቴንሽንና አርሶ/አርብቶ አደሩ ጋር ጥብቅ ትስስር ሲኖረው ነው፡፡ በዚህም መሰረት ምርምሩ ከሁለቱ አካላት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በማጠናከር በአርሶ አደር እጅ ገብተው ጥቅም ላይ የዋሉትን የመስኖ ቴክኖሎጂዎች እየፈተሸ ጉድለታቸውን በማስተካከል በተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች የመተካት ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም የአርሶ/አርብቶ አደሮችን የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችንና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክፍተቶችን መሰረት በማድረግ የምርት ዕድገት የሚያመጡ ቴክኖሎጂዎችን ከውጭም ሆነ ከሀገር ውስጥ በማፈላለግና በማመንጨት ማስተዋወቅና ማላመድ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪ በሚያቀርቧቸው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ላይ ተግባር ተኮር ስልጠና በመስጠት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን አቅም ማጎልበት ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 3.7.2. ግብዓት አቅራቢዎች

የግብርናን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብ በኩል የግብርና ግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች ሚናቸው በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም አርሶ/አርብቶአደሩ የሚጠይቃቸው ዝርዝር የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎች በወቅቱ ለሚመለከተው የግብዓት አቅራቢ ድርጅት በዓይነትና በመጠን ተለይተው ከቀረቡ በኋላ

ባሉት አደረጃጀቶች በኩል በወቅቱ እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

- የመስኖ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶአደር የሚፈልጋቸውን የመስኖ ልማት ቴክሎጂዎች ፍላጎት በወቅት ለይቶ ማወቅ፣
- ዝርዝር የቴክኖሎጂ ፍላጎቶች ተለይተው ከታወቁ በኂላ በወቅቱ ለሚመለከተው የግብዓት አቅራቢ ድርጅት በዓይነትና በመጠተን አደራጅቶ ማቅርብ፣
- የተጠየቁት የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎች ባሉት አደርጃጀቶች በኩል በወቅቱ ለአርሶ/ አርብቶአደሩ እንዲቀርቡ ማድረግ፣
- ከራሚ የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎች ካሉ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ በዓይነትና በብዛት ማሳወቅ፣

## 3.7.3. ብድር ሰጪ ተቋማት

የግብርናን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለማቅረብ መዋዕለ ንዋይ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የምርት ማሳደጊያ ቴክኖሎጂዎችን እጅ በእጅ ገዝቶ ለመጠቀም አቅም በሚያንስበት ወቅት የብድር አገልግሎት ማግኘት ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ አርሶ/አርብቶአደር የሚፈልገውን የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂ ገዝቶ ለመጠቀም አቅም በሚያንሰው ወቅት ለብድር አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጥያቄውን በማቅረብ ብድር ማግኘት ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር የብድር ሰጪ ተቋማት ለአርሶ/አርብቶ አደሩ የሚያደርጉት ድጋፍ ከፍተኛ ነው፡፡

ስለዚህ የመስኖ ግብርናን ምርት ለማሳደግ፣ ብክነትን ለመቀነስና ጥራትን ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ለአርሶ/አርብቶአደሩ በብድር እንዲቀርቡለት ሁኔታዎች ሊመቻቹለት ይገባል፡፡

## 3.7.4. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

በየደረጃው ለግብርና ምርትና ምርታማነት ዕድገት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋጽኦ ካላቸው መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶ ጋር ተቀናጅቶ መስራት ብዙ ጥቅም አለው፡፡ በመሆኑም መንግስታዊ ያልሆኑ ድረጅቶች የመስኖ ልማትን ለመደገፍና የምርት ብክነትንና ጥራት መጓደልን ለመቀነስ የቴክኖሎጂ ምርምር ሥራዎችንና አቅርቦቶችን፤ እንዲሁም በባለሙያዎች አቅም ግንባታ ሥልጠናዎች ላይ የሚያደርጉት የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ከፍተኛ ነው፡፡

የውሃ ተጠቃሚዎችን ልዩ ልዩ የመማር ፍላጎቶች ለማድረስ አስተባባሪ ኮሚቴዎችን በተለያዩ ደረጃዎች ካሉ ተቋማት፤ የድጋፍና አገልግሎት ሰጪዎችና አጋር አካላት ጋር ማስተሳሰር አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም በሀገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ በተዋረድ ያለው የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ኮሚቴ አማካኝነት የሚዋቀረውና የሚመራ መሆን አለበት፡ ፡ ይህም በሁሉም ደረጃዎች የመስኖ አገልግሎትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማቀናጀት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ መርሃ ግብሩ የተፋሰስ፣ የመስኖ አውታር የላይኛው ክፍል (headwork)፣ የመስኖ ውሃ ስርጭትና ክፍፍል ስርዓት፣በአውታሩ የሚለማ መሬት፣የአካባቢ ነባራዊ ሁኔታ ወይም ማለትም የላኛውና የታችኛው ተፋሰስ ተጠቃሚዎችን ፍላጎትና የውሃ ተጠቃሚ ሁኔታን ከአስተማማኝ የአረንጓዴ የአየርን ንብረት ልማት ጋር መስተሳሰርን ያጠቃልላል፡፡

## 3.8. የመስኖ ውሃን ማዕከል ያደረገ ሁሉን አቀፍ አቀራረብ ዘዴን መጠቀም

በቀበሌ ወይም በወረዳ ውስጥ የሚገኙ የመስኖ ማንኛውም መገኛ አካሎችንና አውታሮች በብቃት ለማሻሻል፣ ምርታማነትን እና የውሃ ተጠቃሚዎችን ገቢ ለማሳደግ የተቀናጀና የመስኖ አካልን ወይም አውታርን ማዕከል ያደረገ ሁሉን አቀፍ የኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ መተግበር በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤታማ ያደርጋል፡፡

## 3.9. የሥርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጪነት (Gender-Responsiveness)

ሴቶ አርሶ/አርብቶ አደር የመስኖ ተጠቃሚዎች በሁሉም የመስኖ ተግባራት ላይ በማሳተፍ እና ከመስኖ ልማት በሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ መሆናቸውንና በተለያየ ደረጃ በውሃ ኮሚቴ ውስጥ የውሳኔ ሰጪነት ድርሻ እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ልዩ ድጋፍ በማድረግ ፍትሃዊ ሥርዓተ ጾታ ስለመኖሩ በመስኖ ኤክስቴንሽን ትኩረት የሚሰጠው ቁልፍ ተግባር ነው፡፡ የመስኖ ልማት ሰራተኞቸና መስኖ ባለሞያዎች ሴቶች በመስኖ ግብርና ውስጥ በሁሉም የአመራረት ደረጃዎች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ፤ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ምክርና ሥልጠና እንዲያገኙ፤የብድር፤ የመስኖ ግብዓቶችንና ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን እንዲጠቀሙ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡



ስዕል- 8፡- ሴት አርሶአደሮችን በመስኖ ልማት ሥራ ውስጥ ማሳተፍ ሌሎች አርሶአደሮችን ያበረታታል፡

በመስኖ ስራ ውስጥ ለሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች ትኩረት ማደረግ ያስፈለገበት ምክንያት ፍትሀዊ የሆነ ሥራ እድል ለመፍጠርና በቤተሰብ ውስጥም የተመጣጠነ ስርዓተ ምግብ እንዲኖር ስለሚያስችል ጭምር ነው፡፡ የመስኖ ቴክኖሎጂ አመራረጥና ሰርቶ ማሳያዎችም, በኤክስቴንሽን ስልጠናዎች ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን እና ሌሎች የሴቶችን ፍላጎት መሰረት አቆራኝቶ ያያዘ መሆን አለባቸው፡፡

## 3.10. አሳታፊ የመስኖ ቴክኖሎጂ ልማት(Participatory Irrigate Technology Dev't) (PITD)

ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች ለማውጣትና ለመፈተሽ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችንና ሌሎች አርሶ አደሮች በአሳታፊ የቴክኖሎጂ ልማት ላይ ማካተት በዘላቂ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ስርጭት ላይ አዎንታዊ ተፅኖ አለው፡፡ ስለዚህ ከምርምርና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች ጋር በመሆን የራሳቸውን ዕውቀት እና ተግባራዊ ልምዳቸውን በማበርከት የአሳታፊ ቴክኖሎጂ ልማቱን ሂደት መምራት ይኖርባቸዋል፡፡ የአሳታፊ ቴክኖሎጂ ልማት ዓላማዎችም፡-

- ☞ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን የቴክኖሎጂ ሀሳቦች መፈተሽ፣
- ☞ ከመስኖ ውሃ ማኔጅመንት ጋር በተያያዘ በአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ውጤታማ የሆነ ቴክኖሎጂን ማፍለቅ፣
- ☞ በመስኖ ስራ ላይ ምክረ ሀሳብ በተሰጠባቸው ቴክኖሎጂዎች የበለጠ ውጤታማ ሊሆኑ በሚችሉበት አግባብ የማሻሻያ ሙከራ ማካሄድ፣
- ☞ በመስኖ አውታሮች ሙከራ እያካሄዱ ያሉ የመሰኖ ውሃ ተጠቃሚዎች የራሳቸውን ችግር መፍታት የሚችሉበትን አቅም ማጎልበት፡፡

## 3.11. የመስኖ ተጠቃሚዎችን ማደራጀት

ቀልጣፋና ዘላቂነት ያለው የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስኖ ተጠቃሚዎች ለመስጠት ያመች ዘንድ አርሶ/አርብቶ አደሩን በልማት ቡድን፣ በማህበራትና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ የምርት እሴት በሚጨምሩ ስራዎች ላይ በማደራጀት ተገቢ የሆነ የኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በዚህም መሰረት አርሶ/አርብቶ አደሩን፤ እንዲሁም ወጣቱንና ሴቶችን በቡድንና በማህበራት በማደራጀት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ጥቅሞቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ☞ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለበርካታ መስኖ ተጠቃሚ ቤተሰብ እና የህብረተሰብ ክፍሎች ለማዳረስ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣
- ☞ አርሶ/አርብቶአደሮች በመስኖ ልማት ሥራዎች ከዕቅድ ዝግጅት እስከ ክትትል እና ግምገማ ድረስ ባለው ሂደት ውስጥ በመሳተፍ አቅማቸው ይጎለብታል፣
- ☞ እርስ በእርስ ለመማማርና ምርጥ ተሞክሮዎችን ለማስፋት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣
- ☞ በተናጠል መውሰድ የማይችሉትን ቴክኖሎጂዎች/የግብርና ምርት እሴት የሚጨምሩ፣ የድህረ ምርት ቴክኖሎጂ..ወ.ዘ.ተ/ በጋራ በመውሰድ ለመጠቀም ያመቻል፣
- ☞ በጋራ የሚሰሩ የመስኖ ልማት ሥራዎችን ለማከናወን ይረዳል፡፡

### 3.11.1 የመስኖ ልማት ቡድን ማደራጀት

የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡን ለተጠቀሚዎች ምቹና ተደራሽ ለማድረግ አርሶ/አርብቶአደሩን የኩታ ገጠም እርሻ ቡድን ወይም በማሳ የመስኖ ቦይ ተጠቃሚዎች አደረጃጀትና በልማት ቡድን ማደራጀት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በመሆኑም በአመካኝ ከ20-30 ወይም ከ15-20 የሚደርሱ አርሶ/አርብቶአደሮች (አባዎራዎችንና እማዎራዎችን ባቀፈ መልኩ) በፍልጎትና በፈቃደኝነት

በልማት ቡድን ይደራጃሉ፡፡ አደረጃጀቱም የመኖሪያ አካባቢ ቅርበትን/የማሳ ድንበርን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡ የልማት ቡድኑ በ5 ሞዴል አርሶ/አርብቶአደሮች /በስራቸው A ደረጃ ያገኙ/ የሚመራ ሲሆን እያንዳንዱ የልማት ቡድን በስሩ እስከ 5 ንዑስ የልማት ቡድኖች /የኩታ ገጠም እርሻ ቡድን ወይም በማሳ የመስኖ ቦይ ተጠቃሚዎች ይኖሩታል፡፡ እነዚህ የንዑስ ልማት ቡድን የኩታ ገጠም እርሻ ቡድን ወይም በማሳ የመስኖ ቦይ ተጠቃሚዎች የራሳቸው መሪዎች ይኖራቸዋል፡፡

## ሀ. የልማት ቡድን መሪዎች አመራረጥ

- በግብርና ስራቸውና ቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸው ግንባር ቀደም የሆኑ እና ሙሉ ፓኬጅ በመጠቀም ለውጤት የበቁ፣
- በመልካም ስነምግባራቸው በህብረተሰቡ ዘንድ የታወቁ፣
- ያገኙትን ዕውቀትና ክህሎት ለሌሎች አርሶ/አርብቶአደሮች ለማስተላለፍ ፈቃደኛ የሆኑ፣
- አባላት ያሉባቸውን ችግሮች አሰባስበው ለመስኖ ልማት ሠራተኛው በማቅረብ መፍትሄ ማፈላለግ የሚችሉ፣
- ቢያንስ በጸሐፊነት የሚመረጠው ሰው ማንበብና መጻፍ የሚችል ቢሆን ጥሩ ነው፣
- አዳዲስ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ለመቀበል ፈጣን የሆኑ፣
- ሃሳባቸውን የመግለጽ እና የሌሎችን ሃሳብ የመቀበል ችሎታ ያላቸው፣
- ህብረተሰቡን በፍትሃዊነት ለማገልገል ቃል የሚገቡ፤
- በመስኖ አውታሩ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ችግሮች ቀድሞ በመረዳት ተጠቃሚውን ማህበረሰብ በማስተባበርእና ከሌሎች ከሚመለከታቸውን ጋር በመሆን በቅንጅት መፍታት የሚችል፤

  የቡድን መሪዎች የአባላትን ፍላጎት እና ተሳትፎ እንዳይገድቡ ጥንቃቄ የተሞላበት ክትትል ማድረግ አለባቸው፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የልማት ቡድን አባላቱ መሪዎቹን በሌላ እንዲተኩ የማድረግ መብት አላቸው፡፡

## ለ. የልማት ቡድን መሪዎች ተግባርና ኃላፊነት

- አበላትን ያሳተፈ እና የአካባቢውን የመስኖ ልማት አቅም ያገናዘበ የልማት ቡድን ዕቅድ እና የመርሃ ገብር/የስራ ጊዜ/ ሰሌዳ በመስኖ ልማት ሰራተኞች በመታገዝ ያዘጋጃሉ፣ ተግባራዊ እንዲሆን ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡
- በሚሰጣቸው ድጋፍ መሰረት የቢዝነስ ፕላን ያዘጋጃሉ፤ ሌሎች አርሶ አደሮች እንዲያዘጋጁ ይደግፋሉ፣
- በመስኖ ልማት ሰራተኞች አማካይነት የሚቀርቡ የድህረ ምርት ቴክኖሎጂ አያያዝና አጠቃቀም መልዕክቶችን ለአባላት ማድረስ፣ ማወያየት እና ከአባላት የሚነሱ ጉዳዮችን ለልማት ጣቢያ ሰራተኞች ያቀርባሉ፣
- ስለ አባላቶቻቸውና አካባቢያቸው መሠረታዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ ይጠቀማሉ፣
- የአባላቱን የመስኖ ልማት እንቅስቃሴ ሪፖርት ለመስኖ ልማት ሠራተኞች ያደርሳሉ፣
- በመርሃ ግብሩ/ስራ ሰሌዳው/ መሰረት ከመስኖ ልማት ሠራተኛው ጋር አጠቃላይ

በመስኖ ልማት ተግባራት አፈፃፀም ላይ ግምገማ በማካሄድ የቀጣይ ተግባራትን አቅጣጫ እያስቀመጡ ይተገብራሉ፣

- ፍላጎታቸውን እና የክህሎት ክፍተታቸውን መሰረት ባደረገ መልኩ አርሶ/ አርብቶአደሮች እንዲሰለጥኑ የማነሳሳት እና የማበረታታት ስራ ይሰራሉ፣
- የቡድኑ አባላት በመስኖ ቴክኖሎጂ ማስፋት ስራ ላይ በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው ምርጥ የመስኖ ልማት ተሞክሮዎችን የማስፋት ሥራ እንዲሰሩ ዕገዛ ያደርጋሉ፣
- የልማት ቡድን አባላት በመስኖ ልማት ስራ ላይ በስፋት እንዲሳተፉ ከሞዴል አርሶ አደሮች ጋር የእርስ በእርስ የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ያደርጋሉ፣
- ከአባላት መካከል በተለያዩ የመስኖ ልማት ምርጥ ተሞክሮ ሥራዎች ላይ ለመሳተፍ ፍላጐት ያላቸውን መምረጥና ለመስኖ ልማት ሠራተኛው ማድረስ፣
- በመስኖ አውታሩ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ችግሮች ቀድሞ በመረዳት ተጠቃሚውን ማህበረሰብ በማስተባበርእና ከሌሎች ከሚመለከታቸውን ጋር በመሆን በቅንጅት መፍታት የሚችል፤

### የሰብሳቢው ተግባር

- የልማት ቡድኑን ስብሰባ ይመራል፣
- የልማት ቡድኑን ወክሎ ስብሰባዎች ላይ ይሳተፋል፣
- የልማት ቡድን አመራሮች ተግባራቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል፣
- የልማት ቡድኑን የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለመስኖ ልማት ሰራተኛው ይልካል፣

### የፀሐፊው ተግባር

- ዋናው አስተባባሪ በማይኖርበት ሰዓት ተክቶ የማስተባበር ሥራውን ይሠራል።
- በመስኖ ልማት ሰራተኞች አማካይነት የሚመጡ መልዕክቶችን ለአባላቱ በንባብ ያሰማል።
- ከልማት ቡድኑ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ያስቀምጣል፣ ሲፈለግም ለተጠቃሚ ይሰጣል።

### ሐ. የልማት ቡድን አባላት ተግባር እና ኃላፊነት

- የቡድኑ አባላት በሌሎች እና በአካባቢያቸው ተሞክረው ውጤታማ የሆኑ ምርጥ የመስኖ ልማት ተሞክሮዎችን እንደ ፍላጐታቸው በራሳቸው ማሳ/ቤት አካባቢ መተግበር፤ ለሌሎች አባላት ማሳወቅ እና የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- የገፀ እና የከርሰ ምድር ውሃን እንደ አንድ የማይታለፍ ግብዓት መጠቀም፣
- በተናጠል መጠቀም የማይችሏቸውን የመስኖ ልማት ተክኖሎጂዎች በጋራ መጠቀም፣
- በጋራ የሚሠሩ የመስኖ ልማት ሥራዎችን በጋራ ማከናወን፣
- ቋሚ ፕሮግራም በማውጣት የሥራ አፈፃፀማቸውን በጋራ መገምገም፣
- ዓመታዊ ዕቅዳቸውን በግል እና በጋራ በማዘጋጀት፤ እንደ አስፈላጊነቱም በመከለስ በትክክለኛ የጊዜ ሰሌዳ መተግበር፣

- ☞ በጋራ የተላለፈ ውሳኔን፣ የቡድኑን መመሪዎችንና ደንብ ማክበር፣
- ☞ በቡድን ሰብሳቢው የሚሰጣቸውን ተግባራት መፈፀም፣
- ☞ በመስኖ ልማት ሠራተኛው ወይም በቡድን መሪው የሚጠየቁ መረጃዎችን መስጠት፣

### መ. የኩታ ገጠም እርሻ ቡድን ወይም በማሳ የመስኖ ቦይ ተጠቃሚዎች ቡድን መሪ ተግባር እና ኃላፊነት

በልማት ቡድን መሪነቱ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ጨምሮ በስሩ የሚገኙት አምስት አርሶ/አርብቶ አደሮች ያከናወኗቸውን ምርጥ የመስኖ ልማት ሥራዎችን በማስፋት የአርአያነት ሚና ይጫወታል፡፡ በማሳ ቦይ 4ኛ ወይም 3ኛ ወይም 2ኛ ደረጃ ሥር የሚጠቀሙ አርሶአደሮችን በኩታገጠም መሬታቸው መሰረት ይመራል፣ያስተባብራል ችግሮች ከተከሰቱ ችግሮችን ይፈታል፡ ፡ ለምሳሌ፡- በቤተሰብ ወይም በግልሰብ ደረጃ ሚለሙ አነስተኛ የመስኖ ልማት ስራዎችን ያከናውናል፣ የአረምና ጸረ-አርም ርጭትን ያከነውናል፣ የችግኝ ዝውውር፣ ምርት ስብሰባ ወ.ዘ.ተ የመስኖ ልማት ትግባራትን ለማከናውን ያገለግላል፡፡

## 3.11.2. እሴት የሚጨምሩ የመስኖ ልማት ሥራዎች ላይ ማደራጀት

ከግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ አቅጣጫዎች አንዱ አካባቢን መሰረት በማድረግ በተመረጡ የመስኖ ሰብሎች ላይ የስፔሻላይዜሽን ሥራ መስራት የሚፈልጉ አርሶ/አርብቶአደሮችን በቡድን አደራጅቶ በምርት እሴት መጨመር ተግባር ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ ሲሆን በግላቸው መግዛት የማይችላቸውን ግብዓቶች በቡድን ተደራጅተው ማግኘት እንዲችሉ አስፈላጊው የሙያ ዕገዛ ይደረግላቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር አርሶ/አርብቶአደሩ በቡድን ተደራጅቶ የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የኤክስቴንሽን አተገባበሮች መከተል ያስፈልጋል፡፡

- ☞ ፈቃደኛ የሆኑ አርሶ/አርብቶአደሮች፣ የገጠር ወጣቶች እና ሴቶች እሴት በሚጨምሩ የስፔሻላይዜሽን ስራዎች (ለምሳሌ፡- በምርት ማቆያ፣ ማሳቸውን ኩታ ገጠም በማድረግ በምርጥ ዘር ብዜት ስራ፣ በትራንስፖርት፣ በውኃ ፓምፕ ጥገና፣ በድህረ ምርት ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ፣ በአግሮ ፕሮሰሲንግ ስራዎች፣ በባልትና ስራዎች፣ወዘተ) ላይ እንዲሰማሩ በማነሳሳት ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች በፍላጎታቸው መሰረት በቡድንና በማህበራት በማደራጀት የስራ ዕድል እንዲፈጥሩ ማስቻል፣
- ☞ በተሰማሩበት የስራ መስክ ላይ የክህሎት ስልጠና መስጠት፣
- ☞ የመስኖ ግብዓት አቅርቦትንና የብድር አገልግሎትን ማመቻቸትና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣
- ☞ እንደ አስፈላጊነቱ የስራ ቦታ ማመቻቸት፣

በቡድን ተደራጅተው የድህረ ምርት አያያዝ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሊሰጥባቸው በሚችሉ የድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎች ውስጥ፡-

ሀ. መውቂያዎች

ለ. መፈልፈያዎች

አግሮ ፕሮሰሲንግ ወይም እሴት በመጨመር ሊሰሩ ከሚችሉ የምርት ዓይነቶች ውስጥ፡-

ሀ. የዘይት መጭመቂያዎች፣

ለ. የቲማቲም ድልህ ስራ፣ ወ.ዘ.ተ

የባልትና ስራዎች፡

ሀ. የምስር ክክ ማዘጋጀት፣

ለ. በርበሬ ማዘጋጀትና ማሸግ፣

ሐ. ቡላ ማዘጋጀት እና ማሸግ፣

መ. ቆሎ፣ ወ.ዘ.ተ

በአጠቃላይ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አካሄዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት ተግባራት መከናወን አለባቸው፡፡የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጡ የቀበሌ የልማት ባለሙያዎች በቀበሌያቸው ውስጥ እሴት የመጨመር ስራ ሊሰራባቸውና የተሻለ ገበያ ሊያስገኙ የሚችሉ የምርት ዓይነቶችን የመለየት ስራ ይሰራሉ፣

- በአካባቢው አርሶ/አርብቶአደሩ በተናጠል ሊያገኛቸው የማይችሉ ግን ደግሞ አቅራቢ ቢገኝ በኪራይ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉትን ቴክኖሎጂዎችን መለየት፣
- ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 በተጠቀሱት የስራ ዘርፎች ሊሰማሩ የሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች /አርሶ/አርብቶአደሮች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ መሬት አልባዎች/መለየት
- የተለዩትን ተጠቃሚዎች ወደዚህ ስራ እንዲሰማሩ መቀስቀስ፣ ማወያየት እና ስራውን እንዲጀምሩ ማማከር፣
- ፈቃደኛ የሆኑትን የህብረተሰብ ክፍሎች ለይቶ በቡድን ማደራጀት / አብዛኛዎቹ የህብረተሰብ ክፍሎች ቴክኖሎጂዎችን በግል ይዘው አገልግሎት ለመስጠት ሊከብድ ስለሚችል ነው/፣
- ለተደራጁ የቡድን አባላት የስራ መስኩን ለይቶ የክህሎት ስልጠና መስጠት፣
- የቡድኑ አባላት ለመስኖ ልማት የሚውል ግብአትና ብድር ሊያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት፣
- የቡድን አባላቱን በቢዝነስ ፕላን አሰራር ላይ ማሰልጠን እና አዋጭነቱን እንዲያምኑበት ማድረግ፣
- በቡድን ሲደራጁ ስልጠናና የምክር አገልግሎት ለማግኘት እንዳያስቸግር የአንድ ቡድን

አባላት ብዛት ከ20 ባይበልጥ ጥሩ ነው፣

- ለቡድኑ አባላት በሙሉ የክህሎት ስልጠና መስጠት፣
- በቡድን የተደራጁት አባላት የራሳቸውን የመተዳደሪያ ደንብ እንዲያወጡ ማድረግ፣
- እሴት በመጨመር ስራ ለሚሰማሩም ሆነ አንድን ቴክኖሎጂ በማከራየት ለሚሰማሩ ቡድኖች የገበያ መረጃ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- የሚደራጁት ቡድኖች በሂደት ወደ ሕጋዊ ማህበር መሸጋገር እንዲችሉ መደገፍ።

## 3.11.3. ሴቶችን በቡድን ማደራጀት

ሴቶች በመስኖ ግብርና ሥራ ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ ቢኖራቸውም ቀደም ሲል በነበሩት የኤክስቴንሽን ስርዓቶች በመስኖ ልማት ስራ ላይ ሳይሳተፉና በባህላዊ ተፅዕኖ፣ በግንዛቤ እና በመረጃ እጥረት፤ እንዲሁም በቤት ውስጥ ሥራ ጫና ምክንያት ተገቢውን አገልግሎት ሳያገኙ ቆይተዋል። በመሆኑም ይህንን ክፍተት ለመሙላት ሴቶች በመስኖ ልማት ስራ ላይ የሚያበረክቱትን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ግምት ውስጥ በማስገባት የመስኖ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ፍላጎት ያላቸውን ሴቶች በቡድን አደራጅቶ አስፈላጊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት (ትምህርትና ምክር) በመስኖ ልማት ሠራተኞች ሊሰጣቸው ይገባል።

በዚህም መሰረት፡-

- ለገጠር ሴቶች የገቢ ማስገኛ በሚሆኑ የመስኖ ልማት ሥራዎች ላይ ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸውን ሴቶች በቡድን በማደራት የመስኖ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- እማዎራዎች ምርጥ የመስኖ ልማት አሰራሮችንና ተሞክሮዎችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- የገጠር ሴቶችን ጎጂና ኋላቀር ከሆኑ ስራዎች ተላቀው ዘመናዊ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ ሆነው የግብርናውን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የተሻለ ገቢ ፈጥረው የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ ማድረግ፣
- ሴቶች ጉልበታቸውንና ዕውቀታቸውን አስተባብረው የጋራ ችግሮቻቸውን በጋራ መፍታት እንዲችሉ ድጋፍ ማድረግ፣
- የገጠር ሴቶችን ዘመናዊ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ ሆነው የግብርናውን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ በሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ማስቻል፣

## 3.11.4. ወጣቶችን በቡድን ማደራጀት

የገጠር ወጣቶች የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆን በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁኔታዎች ሊመቻችላቸው ይገባል። በዚህም መሰረት ወጣቱ በቡድን ተደራጅቶ የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ተዋውቆ ተጠቃሚ በመሆን የመስኖ ልማት ስራዎችን ሰርቶ የግብርናውን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ተጠቃሚ መሆን ይኖርበታል። ከዚህ አንፃር ለሚከተሉት ተግባራት ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ይገባል።

- የገጠር ወጣቶችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ወጣቱ በቡድን ተደራጅቶ የሚሳተፍበትን የገቢ ማስገኛ የመስኖ ልማት አማራጮችን በመለየት ሥልጠናና የብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት፣

- ወጣቶች ስለሚኖሩበት አካባቢ የጋራ ግንዛቤ ኖሯቸው በመስኖ ልማት ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ፣

- ወጣቶች ዕውቀታቸውን፣ ችሎታቸውንና ጉልበታቸውን በማስተባበር በመስኖ ልማት ስራ ላይ መሰማራት እንዲችሉ ያሉትን ችግሮች በጋራ ለይተው መፍትሄ መስጠት እንዲችሉ የተሳትፎ አቅማቸውን ማጠናከር፣

- ወጣቶች በቡድን ተደራጅተው በራሳቸው ፍላጎትና ተሳትፎ መሰረት የተለያዩ የገቢ ማስገኛ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን አዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ዕገዛ ማድረግ፣ ለምሳሌ፡- የምርት ብክነት በሚቀንሱና ጥራት በሚጠብቁ ፕሮጀክት ስራዎች፣ በምርት ላይ እሴት መጨመርና የገበያ ትስስር ፈጥሮ ዕውቀታቸውን፣ ችሎታቸውንና ጉልበታቸውን በመጠቀም የመስኖ ልማቱን ስራ ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ፣

- ታታሪ ወጣቶች የሰሯቸውን ምርጥ የመስኖ ልማት ስራዎችን ሌሎች ወጣቶች እንዲጎበኙና የልምድ ልውውጥ በማድረግ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲካሄድ ማገዝ፣

- ወጣቶች በመስኖ ልማት ዙሪያ አስፈላጊ የኤክስቴንሽንና የመረጃ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ የሚሉት ናቸው፡፡

## 3.12. የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር

ይህ ማህበር በባለአነስተኛ ይዞታ የአርሶና አርብቶ አደሮች መስኖ ልማት ላይ እና አነስተኛና ጥቃቅን የማህበረሰብ ኩሬን በጋራ በሚጠቀሙ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ፍላጎት የሚመሰረት ህጋዊ ተቋም ነው፡፡ አገልግሎቱም በመስኖ አውታሮች ውስጥ ፍትሀዊ የውሃ ክፍፍል እንዲኖር፤ ተፋሰስ ልማት፤የመስኖ ውሃ መስመር ጥገና፤ የመስኖ አውታሮችን ለማስተዳደርና ለመንከባከብ ነው፡፡ ማህበሩ የተለያዩ ተግባራትን የሚሰተባብሩ ኮሚቴዎች ያሉት ሲሆን ለአባላት አዳዲስ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን፤የግበዓት ፍላጎቶችንና ውጤታማ የሆነ ማኔጅመንት እንዲሰፍን በማድረግ አስተዋፅዖ አለው፡፡ የመስኖ ልማት ሰራተኞችም በሁሉም የመስኖ ልማት ጥረቶች ማለትም በአሳታፊ ዕቅድ ዝግጅት፣ በስልጠና፣ በክትትል፣ በተሻሻሉ የመስኖ ትግበራዎች፣ በገበያ/ግብይት ትስስር፣ በውሃ አጠቃቀም ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በመፍታት ረገድ ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ የአነስተኛ መስኖ አውታርና የማህበረሰብ ኩሬ እንደ ማሳው ስፋት በብዙ ብሎኮች ይከፋፈላል፡፡ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የአነስተኛ መስኖ አውታር/ የማህበረሰብ ኩሬ በአማካይ ከ 5-7 የማሳ ብሎክ ክፍሎች ያሉት ሲሆን በተለያየ ደረጃ የተለያየ ስራ ክፍፍል ያላቸው ከ7-9 አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትም የኖሩታል፡፡ የውሃ ተጠቃሚዎችም አስፈጻሚ የኮሚቴ አባላትን ይመርጣሉ፡፡ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ከእያንዳንዱ የማሳ ብሎክ ክፍል /ንዑስ ቡድን ይወክላሉ፡፡

### 3.12.1. በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ንዑስ ቡድን

በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ንዑስ ቡድን በአማካኝ ከ15-20 የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አባላትን ይይዛል፡፡ ይህም የመስኖ ባለሞያዎችና የልማት ሰራተኞች የንዑስ ቡድኑን አባላት በኩታ ገጠም አመራረት ዘዴ በማደራጀት፣ በቂ የመስኖ ውሃ ወደ ማሳ መድረስ አለመደርሱን፣ የተከሰተ ችግርና የሚስፈልገውን ድጋፍ፣ የሚመረቱ ምርቶችንና መካከለኛና መጋቢ ውሃ መሄጃ መስመሮችን ፅዳትና ጥገና እንዲቆጣጠሩና እንዲደግፉ ይረዳል፡፡ በዚህ የመስኖ ዘዴ አገልግሎቶች በዋናነት ፍላጎትን መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ንዑስ ቡድን የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት፡-

- በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች የፍላጎት ዳሰሳ ጥናትና ክትትል ከመስኖ ልማት ሰራተኞች ጋር መተባበር፣
- ከቡድን መሪዎችና የመስኖ ልማት ሰራተኞች ጋር በመሆን የአሳታፊ መስኖ ዕቅድ ማዘጋጀት፣
- የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበር የንዑስ ቡድን/የብሎክ/ መስኖ ዕቅድ እንዲከለስ በወቅቱ መስራትና መስጠት
- የግብዓት መጠቀምና አዳዲስ የእርሻ ቴክኖሎጂዎች ፍላጎትን መፍጠር፣
- ለመስኖ ሙከራዎችና ሠርቶ ማሳያዎች ተስማሚ ማሳ መምረጥ፣
- ከመስኖ ልማት ሰራተኞች በሚሰጥ ምክር መሠረት የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ለውሃ ተጠቃሚዎች ግንዛቤ መፍጠር፣
- በግብዓት ግዥ የንዑስ ቡድኑን አባላት ማነሳሳት እና የመስኖ ውሃ አለመግባባት ችግሮችን ለማቃለል የመስኖ ብሎክ ቡድን መሪዎችን ማገዝ፣
- በተፋሰስ ልማትና ጥበቃ፣ የውሃ ሀብትን በማዳረስ እና በሚሰጡ ስልጠናዎች ላይ መሳተፍ

### 3.12.2. የመስኖ ልማት ንዑስ ቡድን/ብሎክ/ መሪ ሚና

- በንዑስ ቡድኑ /ቡሎክ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ውስጥና በሌሎች ንዑስ ቡድኖች መካከል ጤናማ ግንኙነት እንዲፈጠር አስተዋጾ ማበርከት፣
- ከመስኖ ልማት ሰራተኞች ጋር ግንኙነት መፍጠር በመስኖ ተግባራት እድገት/ለውጥ ላይ መረጃ እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- በመስኖ ልማት የምርት እድገት ለማስመዝገብ ውጤታማ የመስኖ ውሃ ማኔጅመንት መስፈን ይችል ዘንድ የእያንዳንዱን የውሃ ተጠቃሚ ተነሳሽነት እና ሚና በመረዳት አመራር መስጠት፣
- በአነስተኛ መስኖ አውታር /የማህበረሰብ ኩሬ ዕቅድ መሠረት የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን እና ሰርቶ ማሳያዎችን በመጠቀም የተሻሻሉ የመስኖ አሠራሮችን ለመተግበር አመራር መስጠት
- በቡድኖች መካከል ችግር ሲፈጠር በተለይ በውሃ አለመግባባትን ለመቀልበስ የመሪነት ሚናን መውሰድ
- በግብዓት፣ በቴክኖሎጂ ፣ በብድር ተደራሽነት፣ እና በገበያ ጉዳዮች ላይ የቡድን አባላትን ማመቻቸት/ማዘጋጀት፣

- በኤክስቴንሽን እንቅስቃሴ፣ በመስክ ጉብኝትና በውይይት ወቅት ከመስኖ ልማት ሰራተኞች ጋር መተባበር፣

## 3.13. የኤክስቴንሽን ልማት ቡድን

ይህ የልማት ቡድን የክልል የመስኖና የዝናብ ተኮር ግብርና ኤክስቴንሽንን ለማቀድ፣ ለማቀናጀትና ለማስተግበር የሚያገለግል ዋነኛው የመንግስት ተቋም ነው። እንደ ክልላዊ የኤክስቴንሽን ስትራቴጂ መደበኛው የቀበሌ ልማት ሠራተኞች በሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ሀላፊነት አለባቸው፡፡ እነኝህም ቡድኖችን በማቋቋም ለሁሉም አርሶ አደሮች በብዛት በዝናብ ወቅት በሚካሄደው ግብርና ልማት በመደበኛ የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት እና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የተመረጡ አርሶ አደሮችን ማሰልጠን ነው። ሆኖም ግን በመስኖ ወቅት በጋራ የሚሰሩ ስራዎች እንደ የመስኖና የመኸር ግብርና ጋር የጋራ ዕቅድ ለማውጣት፣ተፋሰስ ልማት፣ መንገድ ልማትና ሌሎች ስራዎች ላይ ተባብሮና ተቀናጅቶ ለመስራት የሚያስችል ስርዓት ነው።

የልማት ቡድን ስትራቴጂን በሚመለከት እንደየክልሎቹ ነባራዊ ሁኔታ በሁሉም ቀበሌዎች አርሶ አደሮች በቡድን የተደራጁ ሲሆን ከ 30-40 የሚሆኑ አባውራዎች የአንድ ቡድን አባላት ናቸው፡፡ የአርሶ አደሮች የልማት ቡድን ለመመስረትም የመኖሪያ መንደር ቅርበት ዋነኛው መስፈርት ነው። እንደ ግብርና ሚኒስቴር መመሪያ የልማት ቡድኑ ሀላፊነት እና ሚናም በቀበሌ የፀደቀውን የግብርና/የገጠር ልማት ዕቅድ ተግባራዊ ማድረግ፤ በአርሶ አደር ቡድኖች መካከል የመረጃና የልምድ ልውውጥ እንዲካሄድ ማድረግ፤ በማህበረሰብ ደረጃ ለሚሰሩ ተግባራት ማለትም የአፈርና ውሃ እቀባ፣የገጠር መንገድ ግንባታዎች፣ የደን ተከላ ወ.ዘ.ተ.ሥራዎች ላይ አርሶ/አርብቶ አደሩን ማነቃነቅ፤የአባላቱን የግብዓት እና ብድር ፍላጎት መለየትና ማስተባበር፤ ከቀበሌ አስተዳደሩ ጋር በመሆን በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ያሉ ችግሮችን መፍታት ወዘተ ይገኙበታል።

የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና ገበያ ተኮር የመስኖ ሰብሎችን ለማምረት  የልማት ቡድኑ ወሳኝ ሚና ያለው ሲሆን የወረዳና የመስኖ ልማት ሰራተኞችም የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ እነኝህን ቡድኖች መጠቀም ይችላሉ። የልማት ቡድን አደረጃጀትም በተግባር ሲታይ ለመስኖ ስራው ችግር የሌለው መሆኑ ታይቷል። ለምሳሌ የኩታ ገጠም እርሻን ለመተግበር በጣም ጥሩ የኤክስቴንሽን ዘዴ ነው።

## 3.14. የመስኖ ልማት ውጤታማነት ላበረከቱ የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት

በየደረጃው የሚገኙ የመስኖ ልማት ፈጻሚ አካላት የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡን ውጤታማ ለማድረግ በመስኖ ልማት ሰራተኞች እና በባለሙያዎች ዘንድ የስራ ተነሳሽነትና የውድድር መንፈስ በመፍጠር የሥራ ቅልጥፍና እንዲመጣ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ሊሆን የሚችለው ውጤታማ ስራ የሰራ የሚበረታታበትና ያልሰራ ደግሞ መንፈሳዊ ቅናት አድሮበት ለስራ የሚነሳሳበትና የተሻለ ውጤት የሚያስመዘግብበት ስርዓት ሲዘረጋ ነው። በዚህም መሰረት በየደረጃው የሚገኙ የግብርና መዋቅሮች ለመስኖ ባለሙያዎች እና ለልማት ሰራተኞች ተገቢውን የገንዘብ እና የማቴሪያል፣ የምስክር ወረቀት፣ የደረጃ ዕድገት፣ የትምህርት ዕድል እና የቦታ ዝውውር ወ.ዘ.ተ ማበረታቻ ስርዓት በመዘርጋት የላቀ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ማበረታቻ

ሊኖር ይገባል፡፡ ይህም መሆን የሚገባው የዘመኑ የመስኖ ወቅት ጊዜ አልቆ ውጤቱ በመስክ እና በተገኘው ምርት ጋር በማገናዘብ ቅልጥፍናውን /Effecincy/ ማለትም ከጊዜ ጋር የተሰማራው አርሶ/አርብቶ አደር የተሳፊነት መጠን በጾታ፣ የውሃ አጠቃቀም፣ የመስኖ ግብዓት አጠቃቀም፣ በመስኖ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ የሚነሱ ግጭቶችን ከመፍታት፣ አካባቢን በመጠበቅ፣ ገበያ ትስስር (ሽጦ ማምረት) እና ዘለቄታነቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆን ይኖርበታል፡፡

## 3.15. የመስኖ ልማት ምርጥ ተሞክሮ መቀመርና ማስፋት

የመስኖ ልማት ምርጥ ተሞክሮ ማለት በአርሶ/አርብቶአደር ደረጃ ተተግብረው ከተለመደው ምርታማነት የተሻለ ውጤት ያስገኙ ቴክኖሎጂዎች ወይም አሰራሮች ናቸው፡፡ ምርጥ ተሞክሮ መቀመር ማለት ደግሞ ከላይ የተገለጹት ተሞክሮዎች እና ውጤታማ አሰራሮች ያለፉበትን ሂደት ለማስፋት ጠቃሚ በሆነ መልኩ ማዘጋጀት ማለት ነው፡፡ በዚህም መሰረት አርሶ/አርብቶአደሩን ከተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች ጋር በማስተዋወቅና በማላመድ፤ እንደሁም የነዚህ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ ሆኖ ምርትና ምርታማነቱን በማሳደግና ገቢውን በመጨመር ኑሮውን ማሻሻል እንዲችል በማሰልጠኛ ማዕከላትና በአርሶ/አርብቶአደሩ ማሳ ላይ ሠርቶ ማሳያዎችን በማካሄድ ወደ ሌሎች አርሶ/አርብቶአደሮችና አካባቢዎች የቴክኖሎጂ ማስፋት ሥራዎችን መስራት ይጠበቃል፡፡

ስለዚህ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማሰባሰብ እና በመቀመር ተመሳሳይ ስነ-ምህዳር ባላቸው አካባቢዎች እንዲሰፉ ማድረግ ዋናው የግብርና ኤክስቴንሽን አቀራረብ ነው፡፡

### ውጤታማ ቴክኖሎጂ አመራረጥ፡-

- ☞ በአካባቢው ከተለመደው ውጪ ምርታማ፣ የተሻለና አዋጭ መሆኑ፣
- ☞ በአካባቢው ሕብረተሰብ ተቀባይነት ያገኘ መሆኑ፣
- ☞ ቴክኖሎጂው ቀጣይነት ያለው መሆኑ፣
- ☞ ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር ተቀባይነት ያለው መሆኑ፣ ወዘተ.....

### የመስኖ ልማት ምርጥ ተሞክሮ ቅመራ አሰራር ስልት፡-

- ☞ በመስኖ ልማት ውስጥ ምርጥ ተሞክሮዎቹን በመቀመር ሂደት ሊሳተፉ የሚችሉ ባለሙያዎችን ከተለያዩ ክፍሎች፣ ኘሮጀክቶችና ሴክተሮች በመለየት ጥሪ ማድረግ፣
- ☞ ከተለዩት የቡድን አባላት ጋር በጋራ በመሆን በክልሎች ተገኝቶ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎችና ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር በክልሎቹ የሚገኙትን ውጤታማ የሆኑ የመስኖ ልማት ተግባራትን ተመሳሳይ ወደ ሆኑ አካባቢዎች ለማሸጋገር ልምዶችን ማሰባሰብ፣
- ☞ በየደረጃው በተሰባሰቡት የመስኖ ልማት ምርጥ ተሞክሮዎች ላይ ቡድኑ ውይይት በማድረግ ሰነድ ሊዘጋጅላቸው የሚችለውን ስራዎች መለየት፣
- ☞ የተለዩትን የመስኖ ልማት ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመቀመር የሚያስችል ቼክ ሊስት በጋራ ማዘጋጀት፣
- ☞ የተዘጋጀውን ቼክሊስት ለበላይ ኃላፊዎች በማቅረብ የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት ማዳበር፣
- ☞ ወደ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች በመውረድ ልምዶቹን ለመቀመር

የሚያስችል ፕሮፖዛል አዘጋጅቶ ወደ ተለዩት አካባቢዎች መንቀሳቀስ፣

- ☞ ከተለዩት አካባቢዎች የሚመለከታቸው የመስኖ ባለሙያዎች ቡድኑን እንዲቀላቀሉ በመጠየቅ በምርጥ ተሞክሮ ቅመራ ትግበራ ላይ የጋራ ግንዛቤ በመፍጠር ወደ ሥራው መግባት፣
- ☞ በክትትልና ድጋፍ ወቅት ልምድ ያላቸውን አርሶ/አርብቶአደሮች በማነጋገር ጥሩ ውጤት ያገኙበትን ዝርዝር ሂደት መረጃ በማሰባሰብ የተገኙ ዉጤቶችን በአካል ተገኝቶ መመልከት፣
- ☞ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በየእለቱ በማደራጀት የውሎ አካሄዶችን መገምገምና ለቀጣዩ ቀን ሥራ በግብዓትነት መጠቀም፣
- ☞ በተለዩት ምርጥ የመስኖ ልማት ተሞክሮዎች ላይ የተሰቡሰቡ መረጃዎችን በተመለከተ በየደረጃው ከሚመለከታቸው የመስኖ ባሙያዎችና ኃላፊዎች ጋር ውይይት በማድረግ መረጃዎቹን የጋራ ማድረግ፣
- ☞ የምርጥ ተሞክሮ ቅመራ ሥራውን መስክ ላይ በመጀመር የማጠቃለልና የእርማት ሥራዎችን በቢሮ ደረጃ ማከናወን፡፡

ለምርጥ ተሞክሮ ማስፋት የምንከተላቸው አቅጣጫዎች፡-

- ☞ በአርሶ/አርብቶአደር ደረጃ ተሞክረው ውጤታማ የሆኑ የተሻሻሉ የመስኖ ልማት አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች መረጃዎችን በተሟላ ሁኔታ ይሰበሰባሉ፣ ይቀመራሉ፣/ ቅመራው ሲዘጋጅ ቀደም ሲል የጎደሉትን መረጃዎች በማሟላት እና ተሞክሮው ወደ ሌሎች አካባቢዎች ሲሰራጭ ሊሟሉ የሚገቧቸውን ነገሮች እንዲሟላ በማድረግ ነው/፣
- ☞ በተቀመሩ ምርጥ የመስኖ ልማት ተሞክሮዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማመቻቸት/ማዘጋጀት፣
- ☞ ምርጥ ተሞክሮውን ተግባራዊ የሚያደርጉ አርሶ/አርብቶአደሮች እና ተስማሚ አካባቢዎች ይለያሉ፣
- ☞ የተለዩ አርሶ/አርብቶአደሮች ቢዝነስ ፕላን ያዘጋጃሉ፣
- ☞ በተቀመሩ ምርጥ የመስኖ ልማት ተሞክሮዎች ላይ በየደረጃው በተግባር የተደገፉ ስልጠናዎች ይሰጣሉ፣ የልምድ ልውውጥ ይደረጋል፣
- ☞ ለተቀመሩ ምርጥ ተሞክሮዎች አስፈላጊው ግብዓት ይቀርባል፣
- ☞ የተቀመሩ ምርጥ ተሞክሮዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ☞ አስፈላጊውን ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ለውጤት ማብቃት፣
- ☞ ለሚያመርቱት የመስኖ ምርት የገበያ ትስስር መፍጠር፣
- ☞ በቀጥታ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን መግዛት ለማይችሉ አርሶ/አርብቶአደሮች የብድር አገልግሎት ይመቻቻል፣

## 3.16. የመ/ ልማት ኤክስቴንሽን የክትትል፣ድጋፍ እና ግምገማ ሥርዓትን መዘርጋት

የኤክስቴንሽን ተግባራትን ለማጠናከር ከሚያስፈልጉ የአሰራር ዘዴዎች መካከል አንዱና ዋናው የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ሥርዓት ዘርግቶ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡ አሰራሩንም

ውጤታማ ለማድረግ የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ሥርዓቱ ተሳትፎአዊ ሆኖ በአፈጻጸም ሂደቱም ላይ የተለያዩ ተዋናይ አካላትን ያካተተ መሆን አለበት። የኤክስቴንሽን ክትትል፣ድጋፍና ግምገማ ሥርዓቱ በየጊዜው እያደገ የሚመጣውን አጠቃላይ የተጠቃሚዎች ፍላጎትና ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ክትትል በማድረግ መሻሻል የሚገባው ሲሆን በሚደረገው ግምገማ ውጤት መሰረትም መለወጥ ያለበት ሁኔታ ካለ ይለወጣል።

የግምገማው ሁኔታ በሁለት መንገድ ሊታይ ይችላል። አንደኛው መንገድ በአፈጻጸም ወቅት የሚደረግ ሲሆን ሁለተኛው መንገድ ደግሞ በአጠቃላይ ሥርዓቱ የሚገመገምበት ነው። ክትትልና ድጋፍ ማለት በመስኖ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያሉትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች፣ ክፍተቶችና ችግሮች በመለየት መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል ተከታታይ የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ሲሆን አስፈላጊነቱም በተመረጡ ውስን የውጤቶችና አፈፃፀም አመልካቾች ዙሪያ ትምህርታዊ ምክርና ሥልጠና፣ የሠርቶ ማሳያ፣ የአርሶ/አርብቶ አደር የመስክ በዓላት ቀን፣ የልምድ ልውውጥ፣ በማሳ ላይ የሚካሄድ የሙያ ድጋፍ እና በሌሎችም ተግባራት ላይ የመጡትን የዕውቀት፣ የክህሎትና የአመለካከት ለውጦች፤ እንዲሁም በተፈጠሩ የቴክኖሎጂ ፍላጎቶችና አጠቃቀም ላይ ሥልታዊ በሆነ ዘዴ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለመማማሪያነት ለማዋል፣ የበላይ አመራሩና ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የደረሱበትን የአፈፃፀም ደረጃ እና የተገኙ ውጤቶችን አስመልክቶ የተሟላ መረጃ በተገቢው ጊዜና ቦታ እንዲደርስ ያደርጋል።

**የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ አስፈላጊነት፡-የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ክትትልና ድጋፍ ማካሄድ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ለማከናወን አስፈላጊ ነው።**

- ለመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ዕቅድ ዝግጅት የሚረዱ ዋና ዋና መረጃዎችን ለማቅረብ፣
- በዕቅዱ መሠረት የመስኖ ልማት ስራዎች እየተተገበሩ መሆኑን እና አለመሆኑን ለመከታተል፣
- ዕቅድን ለመከለስና በድጋሚ ለማቀድ፣
- በየደረጃው ከሚገኙ መልካም የመስኖ ልማት ተሞክሮዎችና ክፍተቶች ላይ ትምህርት ለማግኘት፤ እንዲሁም በተገኙ ውጤቶችም ላይ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ፣
- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ ተከታታይነት ያለው ተግባር በመሆኑ ሳይቆራረጥ በሚመለከታቸው አካላት አማካኝነት በዕቅድና በጀት፣ በባለሙያና በተለያዩ ቁሳቁሶች ታግዞ እንዲካሄድ ማድረግ፣
- በመስኖ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድርጊት መርሃ ግብር ላይ በተቀመጠው መሰረት በመስኖ ልማት ስራዎች ዙሪያ በግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም፣ በትግበራና በግብ ስኬቶች(outputs) ላይ በመስኖ ባለሙያዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የክትትልና ድጋፍ ስራ ለማካሄድ፣
- በፌደራል ደረጃ በየሩብ ዓመቱ፣ በክልል ደረጃ በየሁለት ወሩ፣ በዞን ደረጃ በወር አንድ ጊዜ፣ በወረዳ ደረጃ በወር ሁለት ጊዜና በቀበሌ ደረጃ ዕለት በዕለት የሚደረገውን ክትትልና ድጋፍ ተከታትሎ ለማወቅ፣
- በየደረጃው ለሚገኙ ፈጻሚ አካላት ሁለንተናዊ አቅም የሚገነባ የስራ ላይ ስልጠና ለመስጠት፣
- ግልፅና የተደራጀ ቼክሊስት በማዘጋጀት ተከታታይ የሆነ ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ ቀጣይ ተልዕኮዎችን ለማስቀመጥ ነው።

ክፍል 2፦ ተሣትፎአዊ የመስኖ ኤክስቴንሽን ስርአት አተገባበር ስልት

## የስርአተ ፆታ ጉዳዮች

ሴት፦ አርሶአደሮች በግብርና ሥራ ውስጥ ተሳታፊ ቢሆኑም በመስኖ ግብርናው ምርትና ምርታማነት ላይ ያላቸው አዎንታዊ አስተዋጽኦ በጉልህ አለመታወቁና ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ ነው። ሴቶች በአሳታፊ መስኖ ኤክስቴንሽን ዕቅድ አስተቃቀድ ውስጥ ያላቸው ሚና ሴቶችን ያማከለ ዕቅድ በማዘጋጀት ውስጥ ተሳታፊ እንደማይደረጉ የሚያሳዩ በርካታ መረጃዎች አሉ።

- ☞ በርካታ የመስኖ ግብርና ልማት ዕቅዶች አዘገጃጀት በተወሰነ የሴት አርሶ አደሮች ተሳታፊነት የሚታቀድና አንዳንድ ጊዜም ያለሴት አርሶ/አርበቶ አደሮች ተሣታፊነት መሆኑ (ሴት አርሶ አደሮችን ያላሣተፈ/ያላማከለ ዕቅድ አዘገጃጀት)
- ☞ ሴት አርሶ አደሮች በአዳዲስ የመስኖ ግብርና ቴክኖሎጂዎች/በራሳቸው የሚመጥንና ሊተገብሩት የሚችሉትን ቴክኖሎጂ የመምረጥና ውሳኔ የመስጠት አቅም ዝቅተኛ መሆን ወይም ሙሉ በሙሉ አለመኖር በአብዛኛው የሚያቀርቡት ሀሳቦች ተቀባይነት ያጣሉ
- ☞ ሴት አርሶ አደሮች በአነስተኛ መስኖ አውታሮችና ማህበረሰብ ኩሬ የአተገባበርና ጥገና የዕቅድ አዘጋጃጀት፤ በተደራጁ የውሃ ተጠቃሚ ማህበራት አስተዳደር ውስጥ በጉልህ አለመኖር እነዚህ የስርዓተ ፆታ ክፍተቶች
- ☞ ሴቶች በማናቸውም የመስኖ ግብርና ውስጥ በሚደረጉ/በሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ በማሣተፍ የሚኖራቸውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማጎልበትና ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ በጉልህ አለመታየት
- ☞ የቀበሌ የመስኖ ልማት ባለሙያ በግብርና ልማት ዕቅድ ዝግጅት፣ የቴክኖሎጂ ምርጫና ግብይት ስርዓት ሂደት ውስጥ የሴቶች ተወካዮችን ማካተት፣
- ☞ ሁሉም ሴቶችና ወንዶች ፍትሃዊ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ድልድል በሚካሄድበት ሂደት ውስጥ ተሣታፊ መሆን አለባቸው፣ ማማከርና ግልጽ ሊሆንላቸው ይገባል። ይህም ለሴት እማወራዎች በምሽት የውሃ አጠቃቀም ድልድል ውስጥ ከመግባት ያድናቸዋል።
- ☞ በቴክኖሎጂ መረጣና ስርዓት ውስጥ የሴቶችንና የወንዶችን በውሳኔ መስጠት ሂደት ውስጥ

### የሚኖራቸውን ሚና እኩልነት ማረጋገጥ

- ☞ ሴትና ወንድ አርሶ/አረብቶ አደሮች በአነስተኛ የመስኖ አውታር አጠቃቀምን በተደራጁት የሴቶች የውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ውስጥ የሚኖራቸውን የአስተዳደር ሚና በኃላፊነት መምራታቸውን ማረጋገጥ

### የስርዓተ ፆታ ጉዳዮች እንዴት ተደራሽ ይሆናሉ;

- ☞ የኤክስቴንሽን አገልግሎት እማወራዎችንም ሆነ በአባወራ ውስጥ ያሉ ሴቶችን ተደራሽነት ማረጋገጥ አለበት።

- ☞ አመቺ ቦታ እና ጊዜ በማመቻቸት ሴት አርሶ አደሮችን ማበረታታት፣ ሴቶች እርስ በርስ ተገናኝተው ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ማድረግ፣ በጥንድ ላይ የተመሰረተ የኤክስቴንሽን ስልት ማሳደግ፣ ስርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ እንደ ሴት ማህበር ለሴቶች የተናጠል ስልጠናዎች ማዘጋጀት

- ☞ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ የሆኑ ስርዓተ ፆታ ተኮር ቴክኖሎጂዎችን ማዳበር፣

- ☞ የሴቶችንም ሆነ የወንዶችን አገር በቀል እውቀቶች ላይ የሚያተኩሩ ምርምሮች ማካሄድ እና ሴቶችን በግብርና ምርምሮች እና ግኝቶች ውስጥ ተሳታፊ ማድረግ፡፡

## የስርዓተ ፆታ ተደራሽነት ጥቅሞች

☞ ሴት እና ወንድ አርሶ አደሮች የኤክስቴንሽን እኩል ተጠቃሚ መሆን የመስኖ ቴክኖሎጂ አቀባበልን ያፋጥናል ይህም የሴት አርሶ አደሮችን ምርታማነት ያሳድጋል፡፡ እንደ ዓለም የምግብና እርሻ ድርጅት (2014) ሴት አርሶ አደሮች በአግባቡ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ካገኙ ምርት በ23% ያድጋል ይህም ለተመጣጠነ አመጋገብ እና የምግብ ዋስትና ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡



ስዕል- 9፡- ሴት አርሶአደሮችን በመስኖ ልማት ሥራ ውስጥ ማሳተፍ ኤኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታ አለው

# ምዕራፍ-4 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴዎች

## 4.1. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግንኙነት፣ ዕውቀት እና አዳዲስ ሀሳቦችን የመምረጥ ዘዴ

የኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴዎች ለአርሶ/አርብቶ አደሩ ስለተሻሻሉ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ምንነትና አጠቃቀም ትምህርት፣ የምክርና ስልጠና አገልግሎት የምንሰጥበት መሳሪያ ሲሆን በዋናነት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚተላለፈውን መልዕክት የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታና የተጠቃሚው ህብረተሰብ የመቀባበል ችሎታ ይወሰናል፡፡ ከዚህ አንፃር የኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴዎች ሦስት ናቸው፡፡ እነሱም ግላዊ፣ ቡድናዊና የብዙሀን መገናኛ ዘዴዎች ናቸው፡፡

በዋናነት መሰረታዊ የመስኖ-ኤክስቴንሽን አገልግሎት ስርዓት አስፈላጊነት የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ተጠቃሚው አርሶ/አርብቶ አደር በማስተላለፍ የመረጃ ግንኙነት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚደረግበት መንገድ ነው፡፡ የግንኙነት ሂደቱ የሚወሰነው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች በሚኖራቸው የትምህርት የዕውቀትና ክህሎት ደረጃ፤ እንዲሁም ለግንኙነት በሚኖራቸው የተደራሽነት አማራጭ መንገዶች ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም የአቀራረብና የማስተማር ዘዴው፤ እንዲሁም የግንኙነት ሂደት አመሠራረቱ ለሚተላለፈው የመረጃ ዓይነትና ውስብስብነት ምክንያት/ ወሳኝ ጉዳይ/ ይሆናል፡፡ እነዚህም ዘዴዎች የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ሀሳብ በመሳብና ፍላጎታቸውን በመቀስቀስ አዳዲስ ዕውቀትና ክህሎትን አግኝተው በአዳዲስ አሰራሮች ላይ ስኬታማ የሆነ ልምድ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚረዱ ናቸው፡፡

የኤክስቴንሽን መልዕክቶችን ለማስተላለፍ የኤክስቴንሽን ግንኙነት ዘዴዎች በሦስት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም፡- ግላዊ፣ የቡድን እና የብዙሀን ተግባቦት ዘዴዎች ናቸው፡፡ በአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ አውታሮች ላይ ሦስቱም መሠረታዊ ዘዴዎች በተናጠል ወይም በቡድን ወይም ሁሉንም በማቀናጀት የበለጠ ተስማሚ ናቸው፡፡ በመሆኑም የመስኖ ልማት ባለሙያዎችና የመስኖ ልማት ስራተኞች ሦስቱን የኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴዎች መሰረት በማድረግ የኤክስቴንሽን አገልግሎቱን ለመስኖ ተጠቃሚዎች ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሶስት የመልዕክት ማስተላለፊያ መንገዶች ተጠቅመው እንደአከባቢው ተጨባጭ ሁኔታና ፍላጎት ተደራሽ ያደርጋሉ፡፡

- ☞ ፅሁፍ- ይህ ዘዴ የገፅ ለገፅ ቅርርብ ባይኖረውም እንደ ደብዳቤ፣ ሪፖርት፣ ጋዜጣ፣ በራሪ ፅሁፍ፣ መፃህፍት፣ መጽሄቶች፣ ወዘተ… የመሳሰሉትን መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች ያጠቃልላል፡፡
- ☞ ንግግር - ይህ ዘዴ በስልክ፣ በስብሰባ፣ በፕላዝማ፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቢዥን፣ ወዘተ… በመሳሰሉት የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች አማካኝነት የገፅ ለገፅ ግንኙነት ለመጠቀም የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡
- ☞ ማሳየት- ይህ ዘዴ በሰርቶ ማሳያ፣ በኤግዝቢሽን፣ ወዘተ… ላይ የተሻሻሉ የመስኖ ልማት አሰራሮችንና የቴክኖሎጂ አጠቃቀሞችን፤ እንዲሁም ውጤቶቻቸውን ለማሳየት የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡

### 4.1.1. ግላዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴ

ይህ የመሰኖ ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴ /individual Irrigation Extension Communication method/ ከኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን የቀበሌ የልማት ባለሙያ በአርሶ/አርብቶ አደሩ ማሳና ቤት አካባቢ በመገኘት የማሳና የቤት ለቤት ጉብኝት የሚያካሂዱበት፣ የስልክ ግንኙነት፣ የጽሑፍ ግንኙነት፣ ወዘተ… የመሳሰሉትን ዘዴዎች ተጠቅሞ ስለተሻሻሉ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ምንነትና አጠቃቀም በግል ደረጃ ፊት ለፊት ለኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቀሚዎች በቂ ዕውቀትና ክህሎት ለማስጨበጥ ትምህርቶችን፣ ምክሮችንና ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጥበት የኤክስቴንሽን ዘዴ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ መመሪያ ላይ የመስኖ ልማት አተገባበርን ለማስረጽ የተቀመጠው ግላዊ የኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴ የማሳና የቤት ለቤት ጉብኝት ዘዴ ነው፡፡

ይህ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴ የቀበሌ መስኖ ልማት ባለሙያው ከአርሶ/አርብቶ አደሩ ጋር የገፅ-ለገፅ ወይም የማሳና የቤት ለቤት ግንኙነት፣ የስልክ ግንኙነት፣ ወዘተ… የሚያደርግበት ዘዴ ነው፡፡ይህ የኤክስቴንሽን ግንኙነት ዘዴ ውጤታማ የሆኑና አዳዲስ ዕውቀትና ክህሎቶችን ለማስተማርና በአርሶ/አርብቶ አደሩና በመስኖ ልማት ሠራተኛው መካከል መልካም የሆነ ግንኙነት በመፍጠር ረገድ በጣም ውጤታማ ነው፡፡ ሀገራዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስትራቴጂ በዋናነት ትኩረት የሚሰጠው ከቡድኖች ጋር አብሮ መስራትን ነው፡፡ ይሁንና በአስተኛ እና ጥቃቅን መስኖ አውታሮች አንድ አርሶ/አርብቶ አደርን ወይም አባውራን/እማወራን ለመጎብኘት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የተወሰኑ አመቺ ጊዜያቶች በመለየት የተናጥል ግንኙነት ማካሄድ ይቻላል፡፡

**የማሳና የቤት ለቤት ጉብኝት፡-** የማሳና የቤት ለቤት ጉብኝት ማለት የቀበሌ የልማት ሠራተኞችና የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በአርሶ/አርብቶ/ከፊል አርብቶ አደሩ ማሳና መንደር ውስጥ ተንቀሳቅሰው የማሳና የቤት ለቤት ጉብኝት ማካሄድ አርሶ/አርብቶ/ከፊል አርብቶ አደሩ የሚያካሄዳቸውን የልማት ተግባራት በመከታተል የሚገኙ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን፣ በአሰራር ላይ የሚታዩ ክፍተቶችንና ችግሮችን በመለየት አስፈላጊውን ትምህርትና ምክር፣ እንዲሁም የሙያ ድጋፍ በግል ደረጃ ፊት ለፊት የኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጡበት ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም የቀበሌ የልማት ሰራተኞች አርሶ/አርብቶ/ከፊል አርብቶ አደሩን፣ ወጣቶችንና ሴቶችን በማህበርና በቡድን የመስኖ ማሳ ኩታ ገጠም ቡድን አደረጃጀት እና በልማት ቡድን) ተደራጅተው ትምህርትና ምክር የሚያገኙበት ዘዴ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በመስኖ ልማት ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ የህብረተሰብ ክፍሎች (አርሶ/አርብቶ/ከፊል አርብቶ አደሮች፣ ወጣቶችና ሴቶች) ስለተሻሻሉ የመስኖ ልማት አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ትምህርትና ምክር፤ እንዲሁም ሙያዊ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ በአሰራር ላይ የተፈጠሩትን ፍላጎቶች ተግባር ላይ ለማዋል ያስችላል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

- በመስኖ ማሳ ኩታ ገጠም ቡድን እና በመስኖ ልማት ቡድን አደረጃጀት፣ በክላስተርና በማህበራት ደረጃ ተደራጅተው ለሚገኙ አርሶ/አርብቶ አደሮች ገበያ መር በሆኑ የመስኖ ሰብሎች አመራረት ላይ ትምህርትና ምክር፣ እንዲሁም ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጠበት ሲሆን በመስኖ ልማት አሰራርና አተገባበር፣ እንዲሁም በመስኖ

ቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም ላይ የተፈጠሩትን ፍላጎቶች ተግባር ላይ ለማዋልና በአሰራር ላይ ያጋጠሙ ማነቆዎችን ለመቅረፍ ያስችላል፡፡




ስዕል- 10፡- የመስኖ ልማት ሥራን በቤተ ለቤት ጉብኝት በማካሄድ አርሶ አደሩን ማበረታታት እና ማሳደግ ይቻላል፡፡

በጉብኝቶች ወቅት ገበያ ተኮር በሆኑ ሰብሎች ላይ በሚተገበሩ ትንንሽ የመስኖ ስራዎችና ቴክኖሎጂዎች (በድሪፕ/በመስኖ ጠብታ፤ በሮፕ ኤንደ ዎሸር፤ በሂፕ ፓምፕ፤ በትሪድል ፓምፕ፤ በዝናብ፤ በምንጭ እና በጉድጓድ ውሃ) አጠቃቀምና አሰራር ላይ ሙያዊ/ ቴክኒካል ዕገዛ ለማድረግ ያስችላል፡፡

## ግለሰብ አርሶ/አርብቶ አደርን መሠረት ያደረገ ምክር፡- የምክር አገልግሎት አሰጣጥ መሠረታዊ መርሆች፡-

- የመስኖ ውሃ ተጠቃሚውን ብቻ በመመለከት የእርሱን/ የእርሷን ችግር ራሱ/ ራሷ/ ሊያውቅ/ ልታውቅ/ ይችላል/ትችላለች ፡፡
- በራስ መተማመንን ያረጋግጣል (ለምሳሌ፡- በውይይት ወቅት ምንም ዓይነት ማስታዎሻ መያዝ አያስፈልግም)
- ቃል የገቡትን መጠበቅ/ተግባራዊ ማድረግ
- ብዙ ከመናገር ይልቅ መጠየቅ

በአነስተኛ መስኖ አውታር፣ በጥቃቅን መስኖ የውሃ አማራጮች እና በማህበረሰብ ኩሬ የሚለማ የግለሰብ አርሶ/አርብቶ አደር ማሳን በተናጠል/በግል መጎብኘት ዋናው ዓላማ የሚታዩ ዋና ዋና ችግሮችን ለመለየትና ለተለዩት ችግሮች ትክክለኛ ትንተና በመስጠት ውጤታማ የኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት እና ትክክለኛ የሆነ መፍትሄ ለመስጠት ይረዳል፡፡ በአብዛኛው በተናጠል/ ግለሰብ አርሶ/አርብቶ አደር የማግኘት ዘዴ ዓላማዎች፡-

- በመስኖ አውታር፣ በጥቃቅን መስኖ የውሃ አማራጮች እና በማህበረሰብ ኩሬ የሚያለሙ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ተጨባጭ/ትክክለና የሆነ የምክር አገልግሎት እንዲጠይቁ፤
- የመስኖ ባለሙያ እና የመስኖ ልማት ሠራተኛ በዋናነት በመስኖ አውታሩ፣ በጥቃቅን መስኖ የውሃ አማራጮች እና በማህበረሰብ ኩሬ የማምረት ሂደቶችን በመለየት እውቀታቸውን አሳድገው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን

በዋናነት የጋራ የሆኑ ችግሮችን እንዲለይ/እንድትለይ፣

- የመስኖ ልማት ሠራተኛው/ዋ በጎበኟቸው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች መካከል ግንዛቤ ፈጥሮ/ራ በመስኖ ኤክስቴንሽን ተግባራት ላይ እንዲካተቱ ለማነሳሳት፣
- የመስኖ ልማት ሠራተኛው/ዋ ከግብርና ውጭ በሆኑ ተግባራትም ጭምር በተወሰኑ ማሳዎችና ቤተሰቦች ዘንድ እውቅና ፈጥሮ/ፈጥራ በመተዳደሪያቸው ላይ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት/እንድታበረክት
- የመስኖ ልማት ሠራተኛው/ዋ አዳዲስ የመስኖ ልማት ተግባራቶች እና የተሸሻሉ አሰራሮች ሥራ ላይ በዋሉ የመስኖ ሀሳቦችና ትግበራዎች ወይም በተወሰኑ የውሃ ተጠቃሚዎች የተካሄዱ በአነስተሰኛ መስኖ አውታሮች፣ በጥቃቅን መስኖ እና በማህበረሰብ ኩሬ አጠቃቀምና አያያዝ ዙሪያ አዳዲስ አሰራሮችን እንዲማር/እንድትማር
- የመስኖ ባለሙያ እና የመስኖ ልማት ሠራተኛ ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ጋር በጋራ በሁለንተናዊ የመስኖ ዕቅድና ማኔጅመንት ላይ መወያየት እንዲችሉ ነው፡፡

ምንም እንኳን የባለ አነስተኛ ይዞታ አርሶ/አርብቶ አደሮች በመስኖ የሚለማ ማሳ ላይ የሚደረግ ጉብኝት በኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ እምነትና በራስ መተማመንን በማዳበር ረገድ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ለመደገፍ የሚመሠረት ጠቃሚ መንገድ ቢሆንም ብዙ ቁጥር ያላቸው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ውጤታማ በሆነ ዘዴ ለማስተማር በዕቅድና አተገባበር ላይ ጊዜ የሚወስድና ወጪ ቆጣቢ ያልሆነ የኤክስቴንሽን ዘዴ ሲሆን በጥንቃቄ ሊታሰብበትና ሊታቀድ የሚገባው ነው፡፡

በመስክ ጉብኝት ወቅት የመስኖ ባለሙያዎችና የመስኖ ልማት ሠራተኞች ሁልጊዜ አርሶ/አርብቶ አደሮች በቀላሉ የሚረዷቸውንና የለመዷቸውን ቃላቶች/ቋንቋዎች መጠቀም አለባቸው፡፡

በዚህ ረገድ የመስኖ ባለሙያዎች እና የመስኖ ልማት ሠራተኞች ጥሩ አድማጭ እንዲሁም ጥሩ መልዕክት አስተላላፊ እንዲሆኑ ይፈለጋል፡፡ አርሶ/አርብቶ አደሮችም በራሳቸው ቦታ እና በራሳቸው የአነጋገር ዘይቤ እንዲገልጹና በመስኖ ልማት ጉዳዮች ላይ በግልፅ እንዲወያዩ ይበረታታሉ፡፡ የመስኖ ልማት ባለሙያው/ዋ እና የመስኖ ልማት ሠራተኛው/ዋ ተገቢ የሆኑ ጥያቄዎችን በማንሳት የአርሶ/አርብቶ አደሩን አከባባዊ ትኩረት እና ፍላጎት ለይቶ/ታ እንዲያውቀው/እንድታውቀው ይረዳል፡፡ ባጠቃላይ የተናጠል/የግለሰብ አርሶ/አርብቶ አደር የኤክስቴንሽን ግንኙነት ዘዴ ውጤታማ የሆነ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት እና የባለ አነስተኛ ይዞታ የመስኖ አርሶ/አርብቶ አደር አዳዲስ መስኖ ልማት አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን በመተግበርና በማለመድ የእያንዳንዱን አርሶ/አርብቶ አደር ችግሮችን በመለየት ውጤታማ የሆነ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት ይረዳል፡፡ ይህንንም ተግባር ውጤታማ ለማድረግ ተለያዩ የማሳ ጉብኝቶችን፣ የስልክ አገልግሎት፣ የቤት ለቤት ጉብኝት እና ገፅ-ለገፅ ግንኙነት በማድረግ ውጤታማ የሆነ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ይቻላል፡፡

☞በስልክ የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ፡- ባደጉ ሀገራት የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡን ተደራሽነት ፈጣንና ቀልጣፋ ከሚያደርጉት የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ የስልክ አገልግሎት ሲሆን በሀገራችንም የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡን ለማሳለጥ የድምጽ መልዕክትና አጫጭር ጽሑፎችን ለማስተላለፍ ጠቃሚ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ የመስኖ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደር ስለሚፈልጋቸው የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ምንነትና አተገባበር ጥያቄ መጠየቅ ሲፈልግ የሚመለከተውን ባለሙያ/አካል በስልክ መጠየቅ ይችላል፡፡ የተጠየቀውም ባለሙያ/አካል ወዲያውኑ በስልክ ተገቢውን መልስ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎች አሰጣጡን በማጠናከር የመስኖ ልማቱን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ የስልክ አገልግሎቱን እንደ አንድ ፈጣንና ቀልጣፊ የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴ መጠቀም ይገባል፡፡ በተጨማሪም የማህበራዊ ሚዲያዎችን እንደ ፌስ ቡክ፣ ዩቲዩብ ትዊተር የመሳሰሉትን ፈጣንና ቀልጣፋ የመልእክት መላኪያና መቀበያ ዘዴዎችን በመጠቀም አርሶ/አርብቶ አደሩ ስለ ተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የምክርና የግብረ-መልስ አገልግሎት፣ እንዲሁም የተለያዩ ወቅታዊ የገበያ መረጃዎችን፣ የአየር ሁኔታዎችን ስለልዩ ልዩ ወረርሽኝ ተባዮች መከሰት፣ የመሳሰሉን ወቅታዊ መረጃዎች በነዚህ ፈጣን የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች ማድረስ ይቻላል፡፡

☞በቢሮ ደረጃ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፡- ይህ የኤክስቴንሽን መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴ በአብዛኛው የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመንግስት ሳይሆን በግል በሚሰጥበት ሁኔታ በይበልጥ ይተገበራል፡፡ በኛም አገር በስፋት ባይሆንም እየተተገበረ ነው፡፡አንዳንድ አርሶ/አርብቶ አደሮች በገበያ ቀን ወደ ገበያ ሲመጡ ወይም ለሆነ ጉዳይ ወደ ከተማ ሲመጡ ወደ ግብርና ቢሮ ጎራ በማለት ስለተሻሻሉ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም፣ በአሰራር ላይ ስላጋጠሟቸው ችግሮች መረጃ ይጠይቃሉ፡ ፡ ብዙውን ጊዜ ስለ ማዳበሪያ፣ ስለምርጥ ዘር፣ ስለተባይ ችግርና መከላከያ ዘዴና ስለመድሃኒት አጠቃቀም ባለሙያ በመጠየቅ ተገቢውን መልስ አግኝተው ይመለሳሉ ፡ ፡ በመሆኑም የመስኖ ልማቱን ውጤታማ ለማድረግ ይህን አሰራር ወይም የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴ መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ የግንኙነት ዘዴ አርሶ/አርብቶ አደር ወደ ቢሮ በሚመጣበት ወቅት ከበርካታ ባለሙያዎች ጋር የመገናኘት እድል ስለሚፈጥርለት ከያንዳንዱ ባለሙያ የሚፈልገውን ጥያቄ ጠይቆ ተገቢውን መልስ አግኝቶ የመመለስ እድል ይፈጥርለታል፡፡

### 4.1.2. ቡድናዊ የአክስቴንሽን የተግባቦት ዘዴ

ቡድናዊ የመሰኖ ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴ /Group Irrigation Extension Method/ ከኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴዎች አንዱ ሲሆን ከ15 እስከ 20 የሚደርሱ አርሶ/አርብቶ አደሮችን በቡድንና በማህበር በማደራጀት ስለተሻሻሉ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ምንነትና ጠቀሜታ፣ አስፈላጊነትና ዝርዝር አተገባበር የንድፈ ሀሳብ እና ተግባር ተኮር ትምህርት፣ ምክርና ስልጠና የሚሰጥበት ዘዴ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተሳታፊዎች ቁጥር እንደ ትምህረቱ ዓላማና አስፈላጊነት፣ የተሳታፊዎች ዕውቀትና ክህሎት፣ እንዲሁም የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አቅርቦት ሊጨምር ወይም ሊያንስ ይችላል፡፡ በዚህም መሰረት በመስኖ ልማት ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ አርሶ/አርብቶ አደሮችን በማደራጀት ስለተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ምንነትና ጠቀሜታ፣

አስፈላጊነትና ዝርዝር አተገባበር የንድፈ ሀሳብ እና ተግባር ተኮር ትምህርት፣ ምክርና ስልጠና መስጠት ይቻላል፡፡ ቡድኖቹ ብዙውን ጊዜ በመስኖ ውሃ አስተዳደር እና በመስኖ ብሎክ ባላቸው ቀረቤታ እንዲሁም የጋራ በሆነ ፍላጎት ላይ ተመስርተው ይደራጃሉ፡፡ ይህ ዘዴ እንደዚሁ ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ጋር ገፅ-ለገፅ ግንኙነትን የሚያካትት ሲሆን በተለያዩ አዳዲስ እና የተሸሻሉ የመስኖ ልማት አሰራሮች ዙሪያ ሀሳቦችን እርስ በእርስ እንዲለዋወጡ፣ በችግሮችና በሚሰጡ ሙያዊ/ቴክኒካዊ ምክረ ሀሳብ ላይ እንዲወያዩ እንዲሁም ወደፊት ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ይወስናሉ፡፡ ቡድኑ በመስኖ ልማት ሠራተኞችና በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች መካከል ውጤታማ ግንኙነት እንዲፈጠር በማድረግ መረጃ ለመለዋወጥና የተሸሻሉ የመስኖ ልማት አሰራሮችን/ ቴክኖሎጂ ለማስተላለፍ ምክንያት የሆኑ ችግሮችን ለመለየትና አዳዲስ ሀሳቦችንና ግኝቶችን ለማስተዋወቅም ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ አስቸጋሪ የሚሆነው ውስን በሆነ ባለሙያና ሀብት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የምክር አገልግሎት ለእያንዳንዱ አርሶ/አርብቶ አደር በተናጠል ለመስጠት ይከብዳል፡፡ ተለምዷዊ/ልማዳዊ የኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ ብዙን ጊዜ ከላይ ወደ ታች እና ውጤታማ ያልሆነ ነው፡፡ ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ጋር አብሮ መስራት የመስኖ ልማት ሠራተኞች በተመሳሳይ ሰዓት በውስን ሀብት ውጤታማ በሆነ መልኩ ብዛት ካላቸው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች አርሶ/አርብቶ አደሮች ጋር መገናኘትን ይፈቅዳል፡፡ በተጨማሪም ከግለሰቦች ይልቅ ቡድኖች በበለጠ ብዙ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ የቡድን አባላት ጉልበታቸውንና ሀብታቸውን ያቀናጃሉ፣ ግንባር ቀደም ወይም መሪ አርሶ/አርብቶ አደሮችን በመፍጠር ሥራዎችን ይከፋፈላሉ፣ አንዱ ከሌላው ይማራል፣ በጋራም ይወስናሉ፡፡ የቡድን መስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዘዴ ጥቅሞች:-

- ☞ የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በመቀናጀትና የተለያዩ ሀሳቦችን በማዋጣት የቡድን አባላት በተናጠል መፈፀም/መፍታት ያልቻሏቸውን ጉዳዮች በጋራ በመወያየት ችግሮቻቸውን ይፈታሉ፡፡ ብዙን ጊዜ ቀጣይነት ያለው የመስኖ ሙያዊ ሥራዎች ብዙ ጉልበት የሚፈልጉ በመሆናቸው የአነስተኛ መስኖ አውታርን፣ የጥቃቅን መስኖ የውሃ አማራጮች እና የማህበረሰብ ኩሬ በመጠቀም የተለያዩ የመስኖ ልማት ሥራዎችን ለማሻሻል አርሶ/አርብቶ አደሮቹ በጉልበት እንዲተጋገዙ ቡድኑ ይፈቅዳል፡፡

- ☞ በግለሰብ አርሶ/አርብቶ አደር ደረጃ በተናጠል ሊፈታው የማይችለውን ወይም ጫና የሆነበትን ብዙ የመስኖ ልማት ሥራዎችን በመከፋፈል አባላት ያቃልሉለታል፡፡

- ☞ አርሶ/አርብቶ አደሮቹ የመስኖ ልማት ትግበራን፣ አነስተኛ የእርሻ ማሽነሪዎችን፣ የመዝሪያ መሳሪያዎችንና ሌሎች የእርሻ መሳሪያዎችን ለመጠቀም የጋራ ያደርጋሉ/ ይስማማሉ፣

- ☞ እያንዳንዱ የቡድን አባል ተጨባጭ ጥቅምን ያገኛል (የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር፣ የኬሚካል መርጫ መሳሪያዎችን፣ የምርት ማሰባሰቢ መሳሪያዎችን እና የምርት ማከማቻ ቴክኖሎጂዎችን እና ወዘተ አገልግሎቶችን ያገኛሉ)

- ☞ የቡድን አባላት የተለያዩ ሀሳቦችን፣ እርቆ አስተዋይነትን፣ ልምድንና በመስኖ

ልማት የሚታዩ ችግሮችን ሃሳብ እንዲለዋወጡ በማድረግ፣ ቡድኑ አብሮነትንና በህብረት መሥራትን በማጠናከር ረገድ፣ መልካም አጋጣሚን ይፈጥራል፣

☞ የመስኖ ባለሙያዎችና የመስኖ ልማት ሠራተኞች የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ችግሮችንና ፍላጎቶችን በጋራ በመለየት አግባብነት ያለውን ምክረ-ሀሳቦችና ክህሎቶችን እንዲያስተዋውቁ በቡድኑ በኩል የቡድን አባላት ውይይት/የምክክር መድረክ ያካሄዳሉ፣

☞ ቡድኑ ብዙ ጊዜ በመስኖ የሚለሙ ሰብሎችን በማምረት እንደ ምርት ሽያጭ ያሉ የገንዘብ ማግኛ ተግባራት ላይ ብዙ ሥራዎችን ያከናውኑ ይሆናል፡፡ በዚህም ተግባራት ለአባላትም ሆነ ለቡድኑ ገቢ ያስገኛል፡፡ ይሁንና ቡድኑ በቀጥታ ገንዘብ የማያስገኙ ግን ጠቃሚ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ለምሳሌ ከሁለገብ ህ/ሥራ ማህበራት የመስኖ ግብዓቶች ግዥ፣ ብስባሽ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) ዝግጅት፣ የመስኖ ምርት ግብይት፣ እና ሌሎች ከመስኖ ጋር ተያያዥ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

☞ የባለ አነስተኛ ይዞታ አርሶ/አርብቶ አደሮች በመስኖ ልማት የሚደራጅ ቡድን የመስኖ ልማት ሥራዎችን ለመደገፍ መንግስታዊ ካልሆኑ ወይም ከድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች በጀት ሊያፈላለግ ይችላል፡፡ ይህ ዓይነቱ ድጋፍ ብዙውን ጊዜ በግለሰቦች ደረጃ አይገኝም፡፡ይህ በዚህ እንዳለ በዚህ ተግባቦት ዘዴ ውስጥ የተለያዩ ማስፈጸሚያ ዘዴዎች/ቴክኒኮች ይኖራሉ፡፡ እነሱም ከዚህ በታች የሚከተሉት ናቸው፡፡

## አነስተኛ ይዞታ ያላቸውን የመስኖ ልማት ቡድኖችን መምራት

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አብዛኛው ተግባራት የማይቋረጡና በተመሳሳይ ሰዓት የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ የመስኖ ባለሙዎችና የመስኖ ልማት ሠራተኞች አርሶ/አርብቶ አደሩን ከማስገደድና ወስኖ ከማሳወቅ ይልቅ አሳታፊ በሆነ አካሄድ የቡድን አባላትን ማገዝና መምራት አለባቸው፡፡ ስለዚህ የመስኖ ባለሙያዎችና የመስኖ ልማት ሠራተኞች ማከናወን ያለባቸው ጉዳዮች፡-

☞ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ተነሳሽነትና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ለመለየት እና የመስኖ ውሃ አስተዳደርና አካባቢውን ለመረዳት መነሻ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡

☞ በቀበሌው የሚገኝ የመስኖ ውሃ አማራጮች፣ በመስኖ የሚለማ መሬት፣ የአፈር ዓይነትና የቀበሌው ስነምህዳር እና የአየር ሁኔታ፣ በመስኖ የሚለሙ ሰብሎች ዓይነት፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ መረጃ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ይህ ጥናት የአሳታፊ የገጠር ጥናት/ግመታ (PRA) ቴክኒክን፣ መጠይቆችን እና አሁን የቀበሌ አስተዳደሩና በቁልፍ መረጃ ሰጪዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች ገምገሞ በማካተት መጠቀም ይቻላል፡፡ ዳሰሳ ጥናቱ በወረዳ የመስኖ ባለሙያዎች እየታገዙ በመስኖ ልማት ሠራተኞች ሊካሄድ ይችላል፡፡

☞አርሶ/አርብቶ አደሮች በመስኖ ልማት የሚታዩ ችግሮቻቸውን እንዲለዩና በቅደም

ተከተል እንዲያስቀምጡ፣ ለችግሮቹ መፍትሄ ያሏቸውንና መልካም አጋጣሚዎችን እንዲለዩ የመስኖ ባለሙያውና የመስኖ ልማት ሠራተኛውን ማገዝ ይጠበቅባቸዋል

☞ ስለቡድን የመስኖ ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ ከአርሶ/አርብቶ አደሮች ጋር በመወያየት የቡድን መሰኖ ልማት ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴን ጠቀሜታውን በውይይት እንዲረዱት/ እንዲያውቁት ማድረግ፡፡

☞ በመስኖ አውታሮች፣ በጥቃቅን መስኖ ውሃ አማራጮች እና በማህበረሰብ ኩሬ አርሶ/አርብቶ አደሮች በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ቡድን እንዲቋቋሙ ማገዝ

☞ ወደ መስኖ ልማት ቡድኑ ለመቀላቀል ፍላጎት ያላቸውን አርሶ/አርብቶ አደሮች መለየት፡፡ የሚቋቋሙ የቡድን አባላቶች የጋራ መለያ ፀባይ ሊኖራቸው ይገባል፡- ተመሳሳይ መሬት የሚያርሱ፣ በአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ አውታሮች ተመሳሳይ ሰብሎችን የሚያለሙ ወይም ተመሳሳይ መስኖ ቁሳቁሶችን የሚጠቀሙ፣ የቡድን ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ የሚችሉ፣ በሚቀርቡ ርዕሶች ላይ ፍላጎት ያላቸው፣ ለመማርም ሆነ የእነርሱን ዕውቀት ለሌላው ለማስተላለፍ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ተስማሚው የቡድን አባላት መጠን በዓላማውና በሚኖረው ትኩረት ይወሰናል፡፡ ይሁንና ከ15-20 የአርሶ/አርብቶ አደር አባላት ያሉት ቡድን የተሻለ እንደሚሆን ይታሰባል፡፡ በቡድኑ የሴቶች ተሳትፎ መኖር በመስኖ ልማት ረገድ ሴቶች ተምረው ዕውቀት እና ክህሎት እንዲኖራቸው፣ ገቢያቸውን እንዲያሳድጉ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ የህላፊነትና የአመራር ድርሻቸውን እንዲወስዱ ያደርጋል፡፡

☞ የተደራጀው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ቡድን ምን ለመሥራት እንደሚፈልግ፣ ዓላማውንና ተግባራትን፣ ዕቅዱንና ኃላፊነቱን ራሱ እንዲወስን ማገዝ፡፡ ይህ ያልተቋረጠ ሂደት መሆን አለበት፡-ሁኔታዎች በተቀያየሩ ጊዜ መደበኛ በሆነ መልኩ ቡድኑ ዕቅዱን መገምገም ይኖርበታል፡፡

☞ በተለዋዋጭ ሁኔታዎችና በቅደም ተከተል በሚሰሩ ድርጊቶች ቡድኑ ያለውን ችሎታ እንዲያውቅ ማገዝ፡-ስብሰባዎች እንዴት እንደሚካሄዱ?፣ የመስኖ ተግባር ሥራዎች እንዴት እንደሚደራጁ?፣ ተግባራት እንዴት እንደሚገመገሙ? እና እንደ አስፈላጊነቱ በቡድን አመራር፣ በአስተዳደር፣ በቡድን እንቅስቃሴ እና በመዝገብ አያያዝ ርዕሶች ላይ ስልጠና መስጠት፣

☞ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ የአርሶ/አርብቶ አደሮች ቡድን እንዴት እንደሚመራ መወሰን እንዲችል ማገዝ እንዲሁም ቡድኑ የውስጥ ድንቦችንና ህጎችን እንዴት ማዘጋጀት እንደሚችሉ በመስኖ ልማት ሠራተኞች አማካኝነት ድገፍ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ እነኝህ ህጎችና በቅደም ተከተል የሚሰሩ ድርጊቶች ያልተቋረጡ ሂደቶች መሆናቸውን የቡድኑ አባላት መወሰን እንዲችሉ ማገዝ፡፡ ቡድኑ ሁሉንም ጉዳዮች በአንዴ እንዲተገበር ማሰብ የለበትም፤ ሁኔታዎች በተቀያየሩ ጊዜ ውሳኔዎችን እንደገና መገምገም አለበት፡፡

☞ አሳታፊ እና ግልፅ በሆነ ሂደት ዖታን መሠረት ያደረገ የቡድኑ መሪ እንዲመረጥ

ማገዝ፡፡ የቡድኑ መሪ እንደ አገናኝ አርሶ/አርብቶ አደር ሆኖ ይሰራል፡፡ የቡድኑ መሪ ዋና ሚና፡- የመስኖ ልማት ሥራዎች በታቀደው መሠረት የቡድኑ አባላት እንዲተገብሩት ማመቻቸት፣ ችግሮችን መፍታት፣ ንቅናቄ መፍጠር፣ አመራር መስጠትና ማነሳሳት፣ ከዋነኛ አጋር አካላት ጋር ትስስርን ማሳደግ ነው፡፡

☞ ቡድኑ የገንዘብ መዋጮ የሚኖራቸው ከሆነ በገንዘብ አያያዝና በተቀማጭ ገንዘብ አስተዳደር ላይ እንዲወስኑ የመስኖ ባለሙያውና የመስኖ ልማት ሠራተኞች ማገዝ ይኖርባቸዋል፡፡

☞ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች ውጤታማና ተስፋ ሰጪ የሆኑ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን እንዲሞክሩና እንዲላመዱ በማድረግ ጠቃሚ የሆኑ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን እንዲለዩ የመስኖ ልማት ሠራተኞች መደገፍ ይኖርባቸዋል፡፡ የተመረጡ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ በመስክ ወይም በአርሶ/አርብቶ አደሩ ማሳ ላይ፣ በአርሶ/አርብቶ አደሩ ማሰልጠኛ ማዕከላት እና በግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ፣የምርምር ተቋማት፣ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ሌሎች በግሉ ዘርፍ ውስጥ የሚካሄዱ ሰርቶ ማሳያ ስራዎች እንዲፈተሹ የመተግበሪያ ንድፍ/ዲዛይን በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲያውሉት የቀበሌ የመስኖ ልማት ሠራተኞች የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ማገዝ ይጠበቅባቸዋል (ተሳትፏዊ ቴክኖሎጂ ልማት የአቀራረብ ዘዴ ክፍልን ይመልከቱ)፡፡

☞ በመጀመሪያ ደረጃ፣መለስተኛና ከፍተኛ ት/ቤቶች የተሻሻሉ መስኖ ልማት አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ለማላማድ፣ ለማስተዋወቅ እና ተግባር ተኮር ሰርቶ ማሳያዎችን ለመተግበር የቀበሌ መስኖ ልማት ሰራተኛው ሰርቶ ማሳያዎችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

☞ የመስኖ ባለሙያዎች እና የመስኖ ልማት ሠራተኞች ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/ አርብቶ አደሮች አዳዲስ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ ለቡድን አባላት ስልጠናና የመስክ ጉብኝቶችን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይም በምርምር ጣቢያዎች እንዲሁም በአነስተኛ፣ በጥቃቅን/በቤተሰብ እና በማህበርሰብ ኩሬ የመስኖ አውታሮች ለሰርቶ ማሳያነት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና ችግሮች እንዴት እንደሚፈቱ የሚያሳዩ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት ማካሄድ ጠቃሚ ነው፡፡

☞ የመስኖ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች ያቀዱት ዕቅድ በትክክል ስለመታቀዱ ማጣራት እና በአግባቡ እንዲተገብሩት ቡድኑን ማገዝ፤

☞ ቡድኑ አገልግሎት እና ሀብትን ማለትም ዘር፣ ማዳበሪያ፣ ብድር፣ የመስኖ እርሻ መሳሪያዎችና የግብይት ማሳለጫዎችን ማግኘት ይችሉ ዘንድ ከወረዳ ጽ/ቤቶች፣ ከምርምር፣ ከህ/ሥራ ማህበራት፣ ከግብዓት አቅራቢዎች፣ ከብድር ወኪሎች፣ ከአስመጪ ነጋዴዎች፣ ገበያ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ማስተሳሰር፤

☞ ከቡድኑ አባላት ጋር በመሆን የባለአነስተኛ ይዞታ አርሶ/አርብቶ አደር መስኖ ልማት ውጤትን መገምገም፡፡ ከሁሉም አባላት ጋር የግምገማ መድረኮችን

ማዘጋጀት እና መረጃን በሰፊው ለማሰራጨት ከሌሎች ቡድኖች አባላትን መጋበዝ፡፡ እነኝህ ስብሰባዎች/መድረኮች የውስጥ ስሜትን፣ ፍላጎትን እና የውሃ ተጠቃሚዎች ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ለመረዳት መልካም አጋጣሚዎች ናቸው፡፡

የሚከተሉት የቡድን ኤክስቴንሽን መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች ናቸው፡-

- ☞ ሠርቶ ማሳያ (የአሠራር ዘዴ እና የውጤት ማሳያ ሠርቶ ማሳያዎች/የቴክኖሎጂ ማስተዋወቂያ ሰርቶ ማሳያ)፣
- ☞ የመስክ በዓል ቀን (የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች የመስክ በዓሎች)፣
- ☞ የመስክ በዓል ቀን ማካሄድ፣
- ☞ የመስክ ጉብኝት ማካሄድ፣
- ☞ የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- ☞ ትምህርታዊ የጉዞ ጉብኝት/የመስክ ጉዞ ጉብኝት/ተነሳሽነትን የሚፈጥሩ ጉዞዎች፣
- ☞ ስልጠና መስጠት፣
- ☞ የቡድን ውይይት/ስብሰባ የመሳሰሉት የኤክስቴንሽን መልዕክት ማስተላለፊያ መንገዶች በኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴ ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡

**ሠርቶ ማሳያ፡-** ሠርቶ ማሳያ ማለት የተሻሻሉ አሰራሮችንና አመራረት ዘዴዎች እንዲሁም የአዳዲስ ቴክኖሎዎጂዎች አጠቃቀሞች ደረጃ በደረጃ ተግባር ተኮር ትምህርቶች፣ ምክሮችና ሥልጠናዎች ከሚሰጥባቸው የኤክስቴንሽን መልዕክት ማስተላለፊያዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ሲሆን በስሩም ሁለት ዓይነት ሠርቶ ማሳያዎች ይገኛሉ፡፡ እነሱም የአሰራር ዘዴ (Method Demonstration) እና የውጤት (Result Demonstration) ሰርቶ ማሳያዎች ናቸው፡፡

**የመስኖ ልማት አሠራር ሰርቶ ማሳያ ዘዴዎች፡-** የመስኖ ልማት አሠራር ሠርቶ ማሳያዎች /irrigation method demonstration/ አዳዲስ ክህሎቶችንና ተሞክሮዎችን ለማስተማር አንዳንድ ተግባራት በምን ዓይነት በዘዴ ሊፈፀሙ እንደቻሉ ለማሳየት የሚካሄዱ ናቸው፡፡ የአተገባበር ዕቅድ ቅድም ተከተል እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡-

- ☞ የሠርቶ ማሳያውን ዓላማ እና አስፈላጊነቱን መወሰን
- ☞ ደረጃ በደረጃ የአሠራር ቅደም ተከተልን ማዘጋጀት፣
- ☞ ቁልፍ ነጥቦችን መለየት፣

- ☞ አስፈላጊ ቁሳቁሶች/ ማቴሪያሎችን/ መለየትና መግዛት፣
- ☞ ደጋፊ የሆኑ ምስሎችን/ፎቶግራፎች/ቪዲዮዎችን ማዘጋጀት፣
- ☞ ለሙከራ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት፣
- ☞ ሠርቶ ማሳያውን ደጋግሞ መናገር/መግለፅ፣
- ☞ ተሰብሳቢ/ን/አድማጭን ለማግኘት ማስተዋወቅ፤

## የአሠራር ዘዴ ማሳያ ሠርቶ ማሳያዎችን በተግባር ለማካሄድ፡-

- ☞ የሥራ ቦታ ተስማሚ መሆኑንና አለመሆኑን ማረጋገጥ፣
- ☞ ተሰብሳቢው አርሶ/አርብቶ አደር እያየ እና በጥሞና እያዳመጠ ስለመሆኑ ማረጋገጥ፣
- ☞ በተግባር ልምምድ ወቅት ተሳታፊዎች አስቀድመው ምን እንደሚያውቁ መለየት/ ማወቅ፣
- ☞ በተግባር ልምምድ ሂደት ጊዜ የትምህርት ፍላጎት እንዲኖራቸው ማስቻል፣
- ☞ የሠርቶ ማሳያውን ዓላማ እና አስፈላጊነት መግለጽ፣
- ☞ ገለጻ ሲደረግ ደረጃ በደረጃ እያንዳንዱን አሠራር ማሳየት፣
- ☞ አስፈላጊ ሲሆን ደረጃውን/ቅደም ተከተሉን መደጋገም፣
- ☞ በቁልፍ ነጥቦች ላይ ማተኮርና ጠቃሚ መሆናቸውን ለተሰብሳቢው መናገር፣
- ☞ የሚቀርበውን ዝግጅት በጥንቃቄ፣ በዝግታና በትዕግስት ማቅረብ፣
- ☞ ወደ ሌላው ደረጃ ከመቀጠል በፊት በእያንዳንዱ ቅደም ተከተል/ደረጃ ጥያቄ እንዲነሳ ማድረግ፣
- ☞ ሌሎች ደጋፊ እይታዎችን በተገቢው መንገድ እና በሰዓቱ ማቅረብ፣
- ☞ በመጨረሻ ሁሉንም ደረጃዎች/ቅደም ተከተሎች/ማጠቃለል፣
- ☞ የስብሰባው ታዳሚዎች በራሳቸው እንዲሞክሩ እድል መስጠት፣
- ☞ ተጨማሪ ለሰርቶ ማሳያው ደጋፊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ማሰራጨት፣

ፎቶ-9፡- በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/ ከንባታ ጠምባሮ ዞን ደንቦያ ወረዳ የገረንባ የአ/ማ/ተቋም መስኖን





በመጠቀም እየለማ የሚገኝ የጓሮ አትክልት ልማት በከፊል

## በክትትል ሂደት ላይ፡-

- ☞ የተሳታፊዎችን ዝርዝር መያዝ
- ☞ ተጨማሪ መረጃ የሚፈልጉ ተሳታፊዎችን ማገዝ
- ☞ በተመረጡ ወካይ ተሳታፊዎች ላይ ክህሎታቸውንና እርካታቸውን ማረጋገጥ

**የውጤት ማሳያ/ውጤት ተኮር ሠርቶ ማሣያ፡-** ይህ የሰርቶ ማሳያ ዘዴ በተሰጠው ቴክኖሎጂና ተሞክሮ ላይ ምን ለውጥ እንደመጣ ወይም ምን ውጤት እንደተገኘ ለማሳየት ወይም ሠርቶ ማሳያ ለማካሄድ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አዲሱን ግኝት ወይም የተለየውን ተሞክሮ ከነባሩ /ከተለመደው/ ጋር በማነጻጸር ለምን ተቀባይነት አግኝቶ ሥራ ላይ እንደዋለ በተግባር ለማሳየት ነው፡፡ ለምሳሌ፤ የማዳበሪያ አጠቃቀምን ማሳየትና በምርትና በጥራት ላይ ያመጣውን ውጤት/ተጽዕኖ ለማመላከት ሠርቶ ማሳያ ማካሄድ፡ ፡ ይህ በመስኖ ባለሙያዎች እና በቀበሌ የመስኖ ልማት ሠራተኞች የቅርብ ክትትል በአርሶ/አርብቶ ዘንድ የሚካሄድ ሠርቶ ማሳያ ነው፡፡ በመስኖ አውታሮች (የአነስተኛ መስኖ ተቋም፣ ጥቃቅን/የቤተሰብ መስኖ እና የማህበረሰብ ኩሬ መስኖ) የውጤት ማሳያ ሠርቶ ማሳያ ለማካሄድ በሚታቀድበት ጊዜ፡-

- ☞ በሰርቶ ማሳያው የሚቀረፉ ችግሮችን መለየት፣
- ☞ ዓላማዎችንና ግቦችን መወሰን፣
- ☞ የተሟላ መረጃ ማሰባሰብ፣
- ☞ በዕቅድም ሆነ ሠርቶ ማሳያዎችን በማካሄድ የተገልጋዩን ድጋፍ መሻት፣
- ☞ የተሟላ የሥራ ዕቅድ/የድርጊት መርሀ-ግብር ማዘጋጀት፣
- ☞ አመቺ የሆነና ለአርሶ/አርብቶ አደሩ በቅርበት የሚገኝ የሠርቶ ማሳያ መሬት መምረጥ፣
- ☞ አሰራሩን ቀድሞ የተቀባለ አርሶ/አርብቶ አደርን መጎብኘትና ከእርሱ ጋር በተግባር አብሮ መስራት፣
- ☞ በሠርቶ ማሳያ ሂደት ላይ የአካባቢ መሪዎችን ትብብር መጠየቅ፣

- ☞ ሠርቶ ማሳያውን ዘወትር መጎብኘትና የመስኖ አውታሩን ስኬት ማረጋገጥ፣
- ☞ ሠርቶ ማሳያውን ለስብሰባና ለጉብኝት ጉዞ እንዲያገለግል/እንዲሆን ማድረግ፣
- ☞ የሁለቱንም ውጤት መያዝ/ ልማዳዊውንና አዲሱን)፣
- ☞ ሠርቶ ማሳያውን ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደር ማሳየት፤

**የመስኖ የመስክ በዓል ቀን ማካሄድ፡-** የመስክ በዓል ቀን ማለት የአንድ አከባቢ ማህበረሰብ (ባለሙያዎችና አመራሮች፤ እንዲሁም አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ ወጣቶችና ሴቶች) በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን፣ በክልል ደረጃ፤ እንዲሁም በሌላ አካባቢዎች በጋር በአርሶ/አርብቶ አደሩ ማሳ እና በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ደረጃ በተካሄዱ ሠርቶ ማሳያዎችና ሙከራ ጣቢያዎች ላይ ተገኝቶ የተሻሻሉ አሰራሮችንና የቴክኖሎጂ አጠቃቀሞች የሚተዋወቅበትና የነዚህም አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ትምህርትና ምክር የሚሰጥበት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሄድበትን ቡድናዊ የኤክስቴንሽን መልዕክት የሚተላለፍበት መንገድ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የመስኖ መስክ በዓል ቀን በተመረጡ የመስኖ ልማት ሰርቶ ማሳያዎችና ሙከራ ጣቢያዎች ላይ መካሄዱ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

የመስኖ ልማት መስክ በዓል ቀን ለማዘጋጀትና ለማካሄድ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዋና ዋና ተግባራት መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

- ☞ የሠርቶ ማሳያ በዓል ቀን ዕቅድ ማዘጋጀት፣
- ☞ የሚታየውን ሠርቶ ማሳያ በጥንቃቄ መምረጥ፣
- ☞ ሰርቶ ማሳያው የተካሄደበትን ማሳ፣ አካባቢና መተላለፊያ መንገዶችን ማፅዳት፣
- ☞ ስለሠርቶ ማሳያው አሰራርና ዓይነት፣ የቴክኖሎጂ ዓይነትና አጠቃቀም የሚገልጹ ፅሁፎችን ወይም ምልክቶችን ከሠርቶ ማሳያው ፊት ለፊት ማስቀመጥ/ማቆም፣
- ☞ የሠርቶ ማሳያ በዓሉ የሚካሄድበትን ቀን፣ ጊዜና ቦታ በግልጽ ማሳወቅ፣
- ☞ ለሚካሄዱ የሰርቶ ማሳያ በዓላት በራሪ ፀሁፎችን ማዘጋጀት፣
- ☞ ከሰርቶ ማሳያው ጉብኝት ቀን ቀደም ብሎ ለተሳታፊዎች ጥሪ ማስተላለፍ እና የተሳታፊዎችን ብዛት በተቻለ አቅም ለውይይት እንዲያመች ማድረግ፣
- ☞ በዓሉን በሰዓቱ መጀመር፣
- ☞ የበዓሉን ዋና ዓላማና አስፈላጊነት በበዓሉ ላይ መግለጽ፣
- ☞ የሚነሱ ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን መዝግቦ በመያዝ ለሚመለከተው አካል በሪፖርት ማሳወቅ፣

**በመስክ ቀን ዕቅድ ሂደት ላይ፡-**

- ☞ የሚደረስባቸውን ግቦች መለየት፣

- ☞ በመስኖ አውታሩ የሠርቶ ማሳያ ቦታን መምረጥ፣
- ☞ የመስክ ቀኑን ለአርሶ/አርብቶ አደሩ ይፋ ማድረግ፣
- ☞ በሚገበኘው ቦታ ላይ አርሶ/አርብቶ አደሩ በቀላሉ ሊረዳው በሚችል ሁኔታ የሚታይ ስዕላዊ መግለጫዎችን፣ የተገኙ ውጤቶችን እና መልዕክት አስተላላፊ ማስታዎቂያ በሰሌዳ መለጠፍ፣
- ☞ ተገቢነት ያላቸውን ቁሳቁሶች ለጉብኝት ማዘጋጀት፣
- ☞ ከተቻለ አመቺ የሆነ ትራንስፖርት ማመቻቸት
- ☞ በመስክ ቀኑ ዙሪያ ማጠቃለያ ሀሳቦችና አስተያየቶች የሚቀርቡበት አመቺ ቦታ ማዘጋጀት፤

### በመስክ ቀን፡-

- ☞ ስለ ሠርቶ ማሳያው አተገባበር ጽሁፎችን ማሰራጨት፣
- ☞ በማሳው ዙሪያ የሚገበኙ አርሶ አደሮችን መውሰድ፣
- ☞ ተቀባዩ አርሶ አደር በሠርቶ ማሳያው አተገባበርና ስለ አገኘው አዲስ ትምህርት ገለጻ እንዲያደርግ ማድረግ፣
- ☞ ተሳታፊዎች በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ እና ስለ መስክ ቀኑ ግብረ መልስ እንዲሰጡ ማድረግ፤

### በክትትል ወቅት

- ☞ የመስክ ቀኑን ውሎ መገምገም፣
- ☞ ፍላጎት ያደረባቸውን አርሶ አደሮች ማግኘት፣

## 4.1.3. የመስኖ ልማት መስክ ጉብኝት ማካሄድ

የመስክ ጉብኝት ማለት በየደርጃው ከፌደራል እስከ ቀበሌ መዋቅር ድርስ የሚገኙ አመራሮችና የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በራሳቸው አካባቢ ወይም በሌላ አካባቢ በአርሶ/አርብቶ አደር ማሳ ወይም በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ደረጃ በተካሄዱ ሠርቶ ማሳያዎችና ሙከራ ጣቢያዎች ላይ ተገኝተው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሩን በግልም ሆነ በቡድን ትምህርትና ምክር የሚሰጡበት፤ የመሰኖ ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያካሄዱበት፣ በመስኖ ልማቱ አሰራር ላይ ያሉ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን፣ የመስኖ ልማት ክፍተቶችንና ችግሮችን፣ እንዲሁም የመስኖ ተጠቃሚ አርሶ/ አርብቶ አደሩ ፍላጎት የሚታወቅበትና የሚለይበት ቡድናዊ የኤክስቴንሽን መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴ ነው፡፡ ውጤታማ የመስክ ጉብኝት ለማካሄድ ከዚህ በታች የተገለጹት ተግባራት መከናወን ይኖርባቸዋል፡-

- ☞ የጉብኝት ዕቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፣
- ☞ ስለጉብኝቱ አስፈላጊውን መረጃ ማሰባሰብ፣
- ☞ የመስክ ጉብኝቱ ጥቅምና ዓላማ ያለው መሆን ይኖርበታል፣
- ☞ የጉብኝቱን ዓላማና አስፈላጊነት በግልጽ ማስቀመጥ ተገቢ ነው፣
- ☞ የመስክ ጉብኝቱ ውጤታማ እንዲሆን የተወሰነ ጊዜ ኖሮት ችግር ፈቺ በሆነ መልኩ በተከታታይ ለባለሙያዎችና አመራሮች፣ እንዲሁም ለአርሶ/አርብቶ አደሮች ትምህርት የሚሰጥበትና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሄድበት መሆን አለበት።

## 4.1.4. የመስኖ ልማት ልምድ ልውውጥ ማድረግ

የልምድ ልውውጥ ማለት አርሶ/ አርብቶ አደሮች በሌሎች ቀበሌዎችና ወረዳዎች በመገኘት የተሻለና ትምህርት ሰጪ ሥራዎችን እንዲጎበኙ፣ ትምህርትና ልምድ እንዲቀስሙ የሚደረግበት ዘዴ ነው። የልምድ ልውውጡ የልማት ቡድን መሪዎችን እና ሞዴል አርሶ/ከፊል አርብቶ አደሮችን፣ ሴቶችና ወጣቶችን ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

እንደዚሁም በየደረጃው የሚገኙ የክልል፣ የዞን፣ የወርዳ እና የቀበሌ አመራሮች እና አግባብ ያላቸው የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በኩታ ገጠም የመስኖ ማሳ ቡድኖች፣ በክላስተርና በማህበራት የተደራጁ አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ በግብርና ምርምር ማዕከላት፣ በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት፣ በግብርና ቴክኒክና ሙያ፣ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች እና በግንባር ቀደም አርሶ/አርብቶ አደር ማሳ ላይ በሚካሄዱ ሠርቶ ማሳያዎች ላይ በተሻሻሉ የመስኖ ልማት አሰራሮችና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ የዕውቀትና ክህሎት፣ የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማካሄድ የምንጠቀምበት የኤክስቴንሽን ዘዴ ነው። ይሁን እንጂ የልምድ ልውውጥ ሊካሄድባቸው የሚችሉ አካባቢዎችን በቅድሚያ መለየት ያስፈልጋል። ውጤታማ የልምድ ልውውጥ ለማካሄድ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባራት መከናወን ይኖርባቸዋል፡-

- ☞ የልምድ ልውውጥ ዕቅድ ማቀድ፣
- ☞ የልምድ ልውውጥ ዓላማ ማስቀመጥ፣
- ☞ የልምድ ልውውጡን አስፈላጊነት መግለፅ፣
- ☞ የልምድ ልውውጡ በተወሰነ ወቅት በቀጣይነት መካሄድ ያለበት ሲሆን የዕውቀት፣ የክህሎት እና የአመለካከት ክፍተቶችን መሙላት የሚያስችል የኤክስቴንሽን መሳሪያ ነው፣
- ☞ የልምድ ልውውጡ በአርሶ/ከፊል አርብቶ አደር ማሳ፣ በአርሶ/ከፊል አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት፣ በቴክኒክና ሙያ፣ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች፣ በግንባር ቀደም አርሶ/ከፊል አርብቶ አደሮች ማሳ እና በግብርና ምርምር ማዕከላት ላይ የሚካሄድ ይሆናል፣

**ትምህርታዊ የጉብኝት/የመስክ ጉብኝት ጉዞ፡-** ትምህርታዊ የመስክ ጉብኝት ጉዞ በማዘጋጀት አግባብ ያላቸውን የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመውሰድ ከአከባቢያቸው የተሻለ የመስኖ ልማት የአሰራር ዘዴ በማየት እንዲማሩ ማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም ከእነርሱ አካባቢ ውጪ ያሉ ሠርቶ ማሳዎችንና የምርምር ውጤቶችን እንዲያዩ ይደረጋል፡፡ ይህ ዓይነት የመስክ ጉብኝት ጉዞ ተሳታፊዎች ከቤታቸው ርቀው ከሌሎች አርሶ/አርብቶ አደሮች አዳዲስ ሀሳቦችና አሠራሮችን እንዲያውቁና ልምድ እንዲያገኙ ለማድረግ የሚዘጋጅ ነው፡፡ የመስክ ጉብኝት በሚታቀድበት ጊዜ፡-

- ☞ የጉብኝት ጉዞውን ዓላማና ግብ መለየት፣
- ☞ የጉብኝት ጉዞውን ለማቀድ በቂ ጊዜ መመደብ፣
- ☞ የጉብኝት ፈቃድ ለማግኘት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ማድርግ፣
- ☞ መጓጓዣ አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ☞ ጊዜያዊ የዕለት የሥራ ዕቅድ ማዘጋጀት፣
- ☞ ዝርዝር የሥራ ዕቅዱን ማጠቃለል፣
- ☞ ከጣቢያ ተወካይ/ተቀባይ ጋር በመሆን ማስተባበር፤

**ትምህርታዊ ገለጻ፡-** ይህ ዘዴ በአብዛኛው አከባቢ የተለመደ ሲሆን በተለይ ብዙ ቁጥር ላለው ተሰብሳቢ በጣም ከተለመዱ መረጃን ማቅረቢያ ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡ የትምህርታዊ ገለጻ ሂደት በአብዛኛው የግንኙነት አንዱ መንገድ ነው፡፡ ትምህርታዊ ገለጻው ወደ ታዳሚው ሲቀርብ ማዳመጥና ማስታዎሻ መያዝ ያስፈልጋል፡፡ ውጤታማ የሆነ ትምህርታዊ ገለጻ የመስኖ ባለሙያዎች ወይም የመስኖ ልማት ሠራተኞች የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ለአርሶ/አርብቶ አደሩ በማስተዋወቅ እና በማስተላለፍ ሞራላቸውን/በራስ መተማመንን ያሳድጋል/ ይጨምራል፡፡

## የትምህርታዊ ገለጻ ጥቅም

- ☞ ብዙ/ሰፊ ቡድን ላላቸው ተሰብሳቢዎች ይጠቅማል፣
- ☞ ከሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር ሲነጻጸር ለማደራጀት ይቀላል፣
- ☞ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ የትምህርት ዓይነቶችን ማስተማር ይቻላል፣
- ☞ በአብዛኛው ቦታ ላይ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል

## የትምህርታዊ ገለጻ ጉዳት

- ☞ በመምህራንና በተሳታፊዎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ይቀንሳል፣ ተሳትፎም ሆነ ግብረ መልስ አይኖርም፣
- ☞ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ወደ አለው ግብ ለመድረስ ውጤታማ አይደለም፣ ለምሳሌ፡- ማዋሀድ፣ ትኩረት መስጠት፣ መተንተን፣
- ☞ ላልተማሩ አርሶ/አርብቶ አደሮች ያን ያህል ጠቃሚ/ውጤታማ አይደለም፤

**ስልጠና፡-**ሥልጠና ከቡድናዊ ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴዎች ውስጥ የኤክስቴንሽን መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴ ሲሆን በየደረጃው ለሚገኙ አርሶ/አርብቶ አደሮች በተለያዩ የተሻሻሉ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች ምንነትና ጠቀሜታ፣ እንዲሁም አስፈላጊነትና ዝርዝር አተገባበር ላይ ተከታታይ የንድፈ ሃሳብና ተግባር ተኮር ትምህርቶች፣ ምክሮችና ስልጠናዎች፣ እንዲሁም ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጥበት የኤክስቴንሽን ተግባቦት መሳሪያ ነው፡፡ ስልጠና በሁለት ዓይነት መልኩ የሚሰጥ ሲሆን አንደኛው ለአርሶ አደሮች፣ ለልማት ሰራተኞች እና በየደረጃው ላሉ ባለሙያዎች በስራ ቦታ ላይ ተገኝቶ የሚሰጥ ሲሆን ሁለተኛው ዓይነት ስልጠና ደግሞ የተለዩ ክፍተቶችን መሰረት በማድረግ በቂ ዝግጅት ተደርጎ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር በመስኖ ልማት ላይ ተሰማርተው ለሚገኙ አካላት ሥልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡

**ሀ) የመስኖ ባለሙያዎች ሥልጠና፡-**የባለሙያዎች ሥልጠና ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ ለሚገኙ ባለሙያዎች የሚሰጥ ሲሆን አተገባበሩም በየጊዜው በአፈጻጸም ላይ ያለውን የዕውቀት፣ የክህሎትና የአመለካከት ክፍተቶች ለይቶ ለመሙላት ጊዜ ተመድቦለት በተገቢው ወቅት ይሰጣል፡፡ በዚህም መሰረት የመስኖ ልማት ስራን ለማስፈፀም በየደረጃው የሚገኙ የመስኖ ባለሙያዎችን ዕውቀትና ክህሎትን በመፈተሽ ስለተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ግንዛቤ ጨብጠው አቅም ፈጥረው ጥሩ ውጤት ማምጣት እንዲችሉ የባለሙያዎች ሥልጠና በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በሌላ በኩልም በየደረጃው የሚቀጠሩ አዳዲስ ባለሙያዎች አስፈላጊውን ሥልጠና እንዲያገኙ የደረጋል፡፡ ይህ ሥልጠና የባለሙያዎችን የትምህርት ደረጃ ለማሻሻል የሚሰጠውን የረጅም ጊዜ ሥልጠና ማካተት አለበት፡፡ በተጨማሪም የሥራ ላይ የተለዩ ክፍተቶችን መሰረት አድርጎ ሥራዎቹ ከመከናወናቸው ከፌደራል እስከ የወረዳ ድረስ ለሚገኙ የመስኖ ባለሙያዎች ሥልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡

**ለ) የመስኖ ልማት ሠራተኞች ሥልጠና፡-** የልማት ሠራተኞች ምርጥ ተሞክሮዎችን ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ለማስፋት አቅም ሊፈጥሩ ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት በየጊዜው ተቀምረው የሚቀርቡ ምርጥ ተሞክሮዎችን ተመሳሳይ በሆኑ አካባቢዎች ማስፋት እንዲችሉ ወቅታዊ ሥልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም በአዳዲስ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች ላይ የሥራ ላይ ሥልጠና አግኝተው አቅማቸው እንዲጎለብት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የመስኖ ልማት ስራን ውጤታማ ለማድረግ የልማት ሠራተኞች ወቅታዊ ሥልጠናዎችን ማግኘት ይኖረባቸዋል፡፡

በሌላ በኩል በተመደቡበት ቀበሌ ለአርሶ/አርብቶ አደሩ ሁለገብ የሆነ የሙያ ድጋፍ ማድረግ እንዲችሉ ከተመደቡበት ሙያ ውጭ በሚሰሩ ተግባራት ላይ ያለባቸው የሙያ ክፍተቶች እየለዩ በየጊዜው ተከታታይ የሆኑ የአጫጭር ጊዜ ሥልጠናዎች በክልልና በወረዳ ባለሙያዎች ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

**ሐ) የአርሶ/አርብቶ አርሶ አደሮች ሥልጠና፡-**አርሶ/አርብቶ አደሩ ከተሻሻሉ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም፤እንዲሁም ከምርጥ ተሞክሮዎች ጋር ተዋውቆና የነዚህም ተጠቃሚ ሆኖ ምርትና ምርታማነቱን ማሳደግ እንዲችል በየጊዜው በማሳው ላይ፣ በግንባር ቀደም አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ በማሰልጠኛ ጣቢያዎች፣ በአርሶ አደር በአል ቀን፣ እና በልምድ ልውውጥ ወቅት ሥልጠናዎች ማግኘት ይኖርበታል፡፡ በዚህም መሰረት የተለያዩ የውሃ አማራጮችን ተጠቅሞ በመስኖ ልማት ስራ ላይ ተሰማርቶ የሚገኘው አርሶ/አርብቶ አደር ወቅታዊ ሥልጠናዎችን በተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ዙሪያ፤ እንዲሁም በምርጥ ተሞክሮዎች ላይ በመስኖ ልማት ሠራተኞች አማካኝነት ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ በሁሉም ደረጃ ሥልጠናዎችን ለመስጠት ከዚህ በታች የተመለከቱት ተግባራት መከናወን ይገባቸዋል፡፡

**የማሰልጠኛ ማዕከላትን መሰረት ያደረገ የመስኖ ሥልጠና፡-** ከመደበኛ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ውጭ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የሚከናወን ሲሆን በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በያንዳንዱ ቀበሌ አንድ የአርሶ/ አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከልን በማቋቋምና የልማት ሠራተኞችን በመመደብ የአርሶ/ አርብቶ አደሩን ዕውቀትና ክህሎት፤ እንዲሁም ግንዛቤ ለማሳደግ የተሻሻሉ አሰራሮችንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅና ለማላመድ፤ብሎም ተጠቃሚ ለማድረግ በክፍል ውስጥ እና በሠርቶ ማሳያ ላይ ለአርሶ/አርብቶ አደሩ የንድፈ ሃሳብና ተግባር ተኮር ሥልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ በያንዳንዱ አርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል አርሶ/አርብቶ አደሩን ከተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጋር በማስተዋወቅና በማላመድ ተጠቃሚ ለማድረግ በክፍል ውስጥ እና በሠርቶ ማሳያ ላይ የንድፈ ሃሳብና ተግባር ተኮር ሥልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡

**ዋና ዋና የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ተግባራት፡-**

- ☞ ለስልጠና በሚያመች መልኩ ለተለያዩ የመስኖ ልማት ሥራዎች ሠርቶ ማሳያዎችን ማደራጀት፣
- ☞ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ዕውቀትና ክህሎት ለማዳበር የሚያስች የሞዱላር እና የአጫጭር ጊዜ ሥልጠናዎችን መስጠት፣
- ☞ አርሶ/አርብቶ አደሩ፤ እንዲሁም በመስኖ ግብርና ስራ ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ወቅታዊ መረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የአየር ሁኔታ ዘገባና ትንበያ መረጃ፣ የገበያና መሰረታዊ መረጃዎችን፣ ወዘተ… በማሰባሰብና በማደራጀት ማቅረብ፣
- ☞ ምርጥ የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎች ትምህርት ሰጭ በሆነ አግባብ ተሰባስበው በቋሚነት የሚታዩበት ኤግዚቢሽን ማዕከል ማደራጀት፣

- ☞ በየአካባቢው የሥራ ዕድል ለመፍጠር ለሚንቀሳቀሱ አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ ወጣቶች፣ ሴቶችና ባለሀብቶች የቀበሌውን የመስኖ ልማት አማራጮች በመለየትና የአዋጭነት ስሌት በመስራት የምክር አገልግሎት መስጠት፣

**የስልጠና ፍላጎትንና ዓይነትን ለመለየት የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ (TNA) ፡-** ይህ የጥናት ዘዴ ስልጠናው ከመሰጠቱ በፊት የሚሰጠው ሥልጠና በምን ላይ ማተኮር እንዳለበት ለማወቅ ይረዳል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

- ☞ በመስኖ ልማት ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማወያየት በአካባቢው ለመስኖ ልማት ምቹ አጋጣሚዎችን መለየት፣
- ☞ በአካባቢው የሚገኙ ዋና ዋና የመስኖ ልማት ስራ ማነቆዎችን መለየትና እንደ ክብደታቸው በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣ እና
- ☞ በአካባቢው ለሚገኙ ችግሮች ወይም ማነቆዎች የመፍትሄ ሀሳቦችን ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

**የስልጠና ዕቅድ ማዘጋጀት-** የሥልጠና ዕቅድ የሚዘጋጀው በስልጠና ፍላጎትና ዓይነት ልየታ ወቅት የተለዩ ምቹ ሁኔታዎችንና ማነቆዎችን መሰረት በማድረግ ሲሆን ዕቅዱም የሚሰጠውን ሥልጠና በተገቢው መንገድ መስጠት እንዲቻል የስልጠና ቦታን፣ ጊዜን፣ የተሳታፊዎችንና አሰልጣኞችን ብዛት በየሙያ ዓይነቱ፣ ለሥልጠናው የሚስፈገልገውን ግብዓት ለማመላከትና ሙያዊ ዝግጅት ለማድረግ ይረዳል፡፡ በዚህም መሰረት የሚከተሉትን ተግባራት ማሟላት ይኖርበታል፡፡

- ☞ የስልጠናውን ዓይነት፣ ይዘት፣ ጊዜ፣ ሥልጠናው የሚሰጥበትን ቦታ፣ የሰልጣኞችንና የአሰልጠኞችን ብዛት በየሙያ ዓይነቱ መለየት፣
- ☞ ለሥልጠናው የሚያስፈልጉትን የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማመላከት፣
- ☞ በመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎች አተገባበርና አጠቃቀም ላይ ለሚሰጡ የንድፈ ሀሳብና ተግባር ተኮር ስልጠናዎች በቂ ጊዜ መመደብ፣
- ☞ ምቹና ማዕከላዊ የስልጠና ቦታ ማዘጋጀት፣
- ☞ ስልጠናው ከመቼ እስከ መቼ እንደሚሰጥ አስቀድሞ ዝግጅት በማድረግ ጥሪ ማስተላለፍ፣
- ☞ ስልጠናውን ቤተሰብ አቀፍ እና ተሳትፎአዊ በሆነ መልኩ በተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ምንነትና አጠቃቀም (ከምርት ስብሰባ ጀምሮ እስከ ምርት ገበያ ላይ እስከሚወጣ ድረስ፣ ስለፀረ-ተባይ መድሀኒቶች ምንነትና አጠቃቀም፣ ያለው ሰንሰለት ጠብቆ፣ ወዘተ...) ዙሪያ፣ በመሳሰሉት ላይ ወቅቱን

ጠብቆ በተከታታይ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**የሥልጠና ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ፡-** የስልጠና ክትትልና ድጋፍ ስራ የሚካሄደው ስልጠናው ከተሰጠ በኋላ ሲሆን የስልጠናውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች፤ እንዲሁም ክፍተቶች ለማወቅ ሰልጣኞች በተሰጡ ስልጠናዎች ላይ ያገኙትን ዕውቀትና ግንዛቤ በማወቅ ለተለዩት ለውጦች፣ ድክመቶች፣ ክፍተቶች መፍትሄ የሚሰጥበት አግባብ ነውበዚህም መሰረት የስልጠና ክትትልና ድጋፍ ሥራን ተግባራዊ ለማድረግ በቅድሚያ መከናወን የሚገባቸው ዝርዝር ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የክትትልና ድጋፍ ሥራ ለማካሄድ በመጀመሪያ ደረጃ ቼክሊስትና መጠይቅ ማዘጋጀት፣
- በተዘጋጀው ቼክሊስትና መጠይቅ መሰረት አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ በማድግ የሚታዩ ጠንካራ ጎኖችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን በማበረታታት በድክመትና በክፍተት ለሚለዩት ችግሮች ሙያዊ ድጋፍ/ግብ-መልስ መስጠት፣
- ስልጠናው ሲጠናቀቅ ሰልጣኞች በስልጠናው ላይ ያገኙትን ዕውቀትና ግንዛቤ ተጠቅመው የዕቅድ ዝግጅት እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- በመስኖ ልማት ስራ ላይ ውሳኔ ወይም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት በየደረጃው ለሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች ማቅረብና መፍትሄ ማሰጠት ያስፈልጋል፡፡

**መ) የቡድን ውይይት/ስብሰባ፡-** የቡድን ውይይት/ስብሰባ የተሻሻሉና አዳዲስ የመስኖ ልማት አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ለአርሶ/አርብቶ አደሩ ለማስተዋውቅና የነዚህም ተጠቃሚ ለማድረግ ግንዛቤ ከሚፈጠርባቸው የቡድን ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡

ስለዚህ ስኬታማ የቡድን ውይይት/ስብሰባ ለማካሄድ የሚከተሉት ተግባራት በወቅቱ መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

- የቡድን ውይይቶችን ወይም ሰበሰባዎችን በዕቅድ መመራት ይኖርባቸዋል፣
- ውይይቶችን ወይም ስብሰባዎችን ለማካሄድ ወጪ የሚጠይቅ ከሆነ በጀት (ለምሳሌ፡ -ለስብሰባ አዳራሽ ኪራይ፣ ለመጓጓዣ/ለነዳጅና ቅባት፣ ለውሎ አበል፣ ለሻይ/ቡና፣ ወዘተ…) እንዲያዝላቸው ማድረግ፣
- የሚካሄዱትን ውይይቶችና ስብሰባዎች ቀን፣ ቦታና ሰዓት፣ ዓላማና አስፈላጊነት በዓይነት (በመደበኛ-ወርዊ/የሩብ ዓመት፣ ወዘተ… /አስቸኳይ በማለት) ለይቶ ማስቀመጥና መግለጽ፣
- የውይይቱን ወይም የስብሰባውን ወቅታዊነት ማረጋገጥ፣

☞ ለሚካሄዱ ውይይቶች ወይም ስብሰባዎች ቃለ-ጉበኤዎችን መያዝና በመጨረሻም የተወሰኑ ውሳኔዎችን ለተሳታፊዎች ግልፅ ማደርግና ማፅደቅ፣

☞ የቀጣይ ውይይቶችን ወይም ስብሰባዎችን አቅጫ አስቀምጦ መለያየት፣

## 4.1.5. የብዙሀን የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴ

ይህ የተግባቦት ዘዴ በመስኖ ማሳ ኩታ ገጠም ቡድን፣ በመስኖ ልማት ቡድን፣ በክላስተርና በማህበራት ለተደራጁ አርሶ/አርብቶ አደሮች ትምህርት፣ሥልጠናና የምክር አገልግሎት የሚሰጥበት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴ ነው፡፡ ከብዙሀን መስኖ ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ህትመት እና ኤሌክትሮኒክስ ነው፡፡

☞ ህትመት እና ኤሌክትሮኒክስ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴ፡- በህትመት እና ኤሌክትሮኒክስ መገናኘኛ ዘዴዎች ውስጥ የኤፍኤም ሬድዮ ጣቢያ፣ ጋዜጣዎች፣ መፅሄቶች፣ ቴሌቪዥን፣ ዶክመንተሪ ፊልሞች፣ የሞባይል አጫጭር መልዕክቶችና ጽሁፎች፣ በይነተገናኝ የድምጽ ምላሽ (IVR)- 8028፣ ኢንተርኔትና ማህበራዊ ድረ-ገፆች፣ በራሪ ፅሁፎች፣ ኤግዚቢሽኖች፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴከኖሎጂዎች፣ ወዘተ...የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል፡፡ የህትመት እና ኤሌክትሮኒክስ ማስትማሪያ ዘዴዎችን ስንጠቀም የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል፡፡

☞ በብዙሀን መገናኛ ዘዴዎች የሚተላለፉት የመስኖ ሰብል ፓኬጅ አሰራሮችና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዘዴዎች በተግባር የተፈተሹና የተረጋገጡ መሆን ይኖረባቸዋል፣

☞ በብዙሀን መገናኛ ዘዴዎች የሚተላለፉት ትምህርቶች፣ምክሮችና መልዕክቶች በተቻለ መጠን ለአርሶ/አርብቶ አደሩ ቀላልና ግልጽ በሆነ አቀራረብና አገላለጽ መቅረብ ይኖርባቸዋል፣

☞ የሚተላለፉት ትምህርቶች፣ ምክሮችና መልዕክቶች የመስኖ ሰብል ፓኬጅ አሰራሮችን ወቅት የተከተለ መሆን ይኖርባቸዋል፣

☞ የሚተላለፉትን ትምህርቶች፣ ምክሮችና መልዕክቶች በፅሁፍና በስዕል ማስደገፍ ተመራጭ ነው፣

☞ በይበልጥ የንግግር፣ የመፃፍና የማሳየት መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎችን በጥምረት መጠቀም ተመራጭ ነው፣

ይህ የመስኖ ኤክስንሽን ተግባቦት ዘዴ በተሻሻሉ አሰራሮችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ላይ ለተጠቃሚዎች አዲስ መረጃዎችን በማስተላለፍ ሰምተውና አይተው እንዲጠቀሙበት መርዳት ሲሆን በመስኖ ልማት ሥራ ላይ ተሰማርተው ለሚገኙ በርካታ የውሃ ተጠቃሚዎች ጠቃሚ መረጃዎችን በማስተላለፍ በኩል ጠቀሜታው እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ የመገኛ ዘዴ የውሃ ተጠቃሚዎች አርሶ/አርብቶ አደሮች በፍጥነት አዳዲስ

የመስኖ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን እንዲገነዘቡ እና ግብዓቶች እየቀረቡላቸው አግባብ ያለው አገልግሎት እንዲያገኙ በበለጠ ይጠቅሟቸዋል፡፡ ይህ ዘዴ፣ በአንድ ጊዜ ብዙ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ማግኘት ያስችላል፡፡ ሆኖም ግን በግል እና በቡድን ግንኙነት ዘዴ መረጃን ለሚፈልጉና ጥቅም ላይ ማዋለል ለሚፈልጉ የውሃ ተጠቃሚዎች መድረስ አያስችልም፡፡ የብዙሀን ኤክስቴንሽን ተግባቦት ዘዴ ከዚህ በታች የተመለከቱት ጥቅሞች ይኖሩታል፡፡

- ☞ ወጪው አነስተኛ ይሆናል፣
- ☞ በግልና በቡድን የተማሩ አርሶ/አርብቶ አደሮችን በድጋሚ ለማስተማር ይረዳድ፣
- ☞ በአዳዲስ እና የተሻሻሉ የመስኖ ልማት ቴክኒዮሎጂዎች ላይ ፍላጎትን ይጨምራል፣
- ☞ በመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች በኩል ሊወሰዱ የሚገባቸውን አስቾካ ምክሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማድረስ ይረዳል፣

በዚህ ምክንያት ሬድዮን ጨምሮ የብዙሀን መገናኛ የትምህርት ግንዛቤና ፍላጎትን በማሳደግ ረገድ የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛል፡፡ የሬዲዮ ግንኙነት ፈጣን፣ የበለጠ ተደራሽነትና ተደማጭነት ያለው ሀይል ያለው ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ጋር ለመገናኘት ዋናው መንገድ ነው፡፡ በመስኖ ግብርና ስርጭት ፕሮግራም አማካኝነት በአርሶ/አርብቶ አደሩ መካከል ግንዛቤ ለመፍጠርና የቴክኖሎጂ ልውውጥ ለማምጣት ሬዲዮ ትርጉም ያለው ሚና ይጫወታል፡፡

ሌሎች ተገቢነት ያላቸው በወረቀት የሚታተሙ መገናኛዎች የተለጠፉ ማስታዎቂያዎች፣ በራሪ ጽሁፎች፣ የቅስቀሳ መፈክሮች ሲሆኑ ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች በቂ መረጃን የሚሰጡ ናቸው፡፡ እነዚህ ቴክኖሎጂን ተቀብሎ ሥራ ላይ ለማዋልና ለማሰራጨት በህብረተሰቡ መካከል ግንዛቤን የሚፈጥሩ ናቸው፡፡

የተለጠፉ ማስታዎቂያዎች ብዙውን ጊዜ ትልልቅ የወረቀት ቁራጮች ሲሆኑ ብዙ ቁጥር ላላቸው የውሃ ተጠቃሚዎችና ለሌሎች አርሶ/አርብቶ አደሮችም መልዕክት በቀላሉ ይተላለፍባቸዋል፡፡ መጪውን የኤክስቴንሽን ሁኔታ ለማስተዋዎቅ ወይም ቀላል ቴክኖሎጂዎችንና መረጃዎችን ለማስተላለፍ ሊረዱ ይችላሉ፡፡ ተጨማሪ መረጃ መጠየቅ ሳያስፈልግ ፍላጎትን የማነሳሳት አቅም አላቸው፡፡ የሚለጠፉ ማስታዎቂያዎች በቀለም የተዋቡና ሳቢ ሲሆኑ ሁሉም ሊያያቸው በሚችልባቸው ቦታዎች ለምሳሌ፡- በገበያ ቦታ ወይም ህብረተሰቡ በሚሰበሰብባቸው፣ በአርሶ/አርብቶ አደር ማሠልጠኛ ማዕከላት ወይም በቢሮዎች ላይ ይለጠፋሉ፡፡

በራሪ ጽሁፎች/የመልክት ጥርቅም ማህደሮች ታትመው የሚወጡ ገጾች ሲሆኑ በትምህርት ገለጻ/ የትምህርት ዓይነት ወይም በሠርቶ ማሳያ፣ ወይም በተለየ አስቸኳይ ጉዳይ ላይ ግልጽነትን የሚያላብሱ ናቸው፡፡ አስፈላጊ ጉዳዮችን ለማስቀጠል የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ጨምሮ ለህዝቡ ጠቃሚ ማጣቀሻ ማቴሪያሎች ናቸው፡፡ በኤክስቴንሽን ሂደት እነዚህን በመጠቀም ተሳታፊዎች ማስታዎሻ መጻፍ አያስፈልጋቸውም፡፡ በራሪ

ጽሁፎች በተለይ ጠቃሚ የሚሆኑት ተሳታፊዎች የተለዩ መረጃዎችን ማለትም የተሻሻሉ የሰብል ዝርያዎችን ስም፣ የግብርና ግብዓቶች የሚገኙበት ቦታ፣ የመስኖ እርሻ መሣሪያዎችን፣ የግብርና ኬሚካሎችን፣ ገበያን ወዘተ--- እንዲታውሱ በማድረግ ጥልቅ የኤክስቴንሽን መልዕክቶችን ወይም ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን ለማስተላለፍ ይጠቅማሉ፡፡

እንደ ሀገርም የመስኖ ቴክኖሎጂን በማሰራጨት ረገድ ፈጣንና ቀልጣፋ ወቅታዊ መረጃዎችን ለማስተላለፍ ዋነኛው ቁልፍ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስትራቴጂ የብዙሀን መገናኛ ዘዴ እንደሆነ ነው፡፡

**በመስኖ ኤክስቴንሽን የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ፡-** በብሔራዊ ግብርና ኤክስቴንሽን ስትራቴጂ አማካኝነት አጽንኦት የተሰጠው በዲጂታል እና የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረተ የኤክስቴንሽን ኮሚዩኒኬሽን ስርዓት ነው፡፡ ለአርሶ/አርብቶ አደሩ መረጃ ለማድረስ ወይም ለማስተማር በዋናነት ቀጥተኛ ባልሆነ (በሬዲዮና ቴሌቪዥን) በቀጥታ በምልከታ መማርን ተከትሎ በቃል ንግግር ግንኙነት ሲሆን ይህም ስልጠናን፣ ስብሰባን፣ ኮንፈረንስን እና ማህበራዊ መሰባሰብን ያካትታል፡ ፡ የዚህ መስመር/መንገድ ውጤታማነቱ ከፍ ሊል የሚችለው አርሶ/አርብቶ አደሩ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተደራሽነት ሲኖረው ነው፡፡ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ውጤታማና ተደራሽ በሆነ እና በሚማርክ መልኩ አርሶ/አርብቶ አደሩ መረጃን የሚያገኝበት መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- "ዲጂታል ግሪን ቪዲዮን መሠረት ያደረገ የአቀራረብ/ማስተማሪያ ዘዴ "የቴክኖሎጂ መድረክ ሲሆን አርሶ/አርብቶ አደሮች ራሳቸው የተሻሉ የግብርና ተሞክሮዎችን በሠርቶ ማሳያ ለተከታዮቻቸው በቪዲዮ አማካኝነት ያስተላልፋሉ፣ ከእያንዳንዳቸው የሚነሱ ጥያቄዎችንም ይመልሳሉ፡፡

ዘላቂ የአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ አውታሮች ላይ ትኩረት በማድረግ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና የመስኖ ልማት ሠራተኞች ውጤታማ በሆነ መልኩ በተለያዩ ማህበራዊ ክፍሎች (ሥርዓተ ጾታ፣ ሀብት፣እድሜ ወዘተ---)፣ሥነ-ምህዳሮች ላይ በተለያዩ የኤክስቴንሽን ግንኙነት መንገዶች ወደ አርሶ/አርብቶ አደሮቹ ለመድረስ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የሚከተሉት የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተግባራት ሥራ ላይ እንዲውሉ ሀሳብ ቀርቧል፡-

- የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ለአርሶ/አርብቶ አደሩ አልግሎት የሚሰጡ ትንንሽ ሱቆችን መመስረት
- ጥሬ መረጃ እና የአፈጻጸም ማኔጅመንት ሲስተም መመስረት
- ሞባይል ስልክን፣ በይነተገናኝ የድምጽ ምላሽ (IVR)-8028፣ ቪዲዮን መሠረት ያደረገ የአቀራረብ ዘዴ፣ የግብርና ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን ወዘተ---የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ ቴክኖሎጂን ማስተዋወቅ፣
- የዕውቀት ሀብት ማዕካላት፣
- ማህበራዊ የመገናኛ ዘዴዎችን መጠቀም፣

## 4.2. ተስማሚ ዘዴዎችን ለመምረጥ ጠቃሚ ሀሳቦች

የኤክስቴንሽን ኮሚዩኒኬሽን ዘዴዎች የሚባሉት መሣሪያዎችና ቴክኒኮች ሲሆኑ በዚህም በአርሶ/አርብቶ አደሮችና በመስኖ ልማት ሠራተኞች መካከል ግንኙነት ይኖር ዘንድ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ፡፡ እነዚህን ዘዴዎች በሚገባ መረዳትና ለተለዩ የመስኖ ድጋፎች መምረጥ አስፈላጊ ነው፡፡ የመስኖ ልማት ሠራተኞች በመስኖ አውታሮቹ ተጨባጭ ሁኔታ ወደ አርሶ/አርብቶ አደሮች እንዴት መድረስ እንደሚቻልና የትኛው የኤክስቴንሽን ኮሚዩኒኬሽን ዘዴ ተስማሚ እንደሆነ ይገመግማሉ፡፡ የትኛው ዘዴ በበለጠ ተስማሚ እንደሆነ የመስኖ ልማት ሠራተኞች እንዴት ይወስናሉ? አንደኛው ቁልፍ መንገድ የኤክስቴንሽን ዘዴዎችን ተቀብሎ ሥራ ላይ የማዋሉ ደረጃና ሂደት ነው፡፡ የኤክስቴንሽን ዘዴዎችን ተቀብሎ ሥራ ላይ ማዋል 5 ደረጃዎች አሉት፡፡ እነርሱም፡- ግንዛቤ፣ ፍላጎት፣ ማመዛዘን፣ ሙከራ እና የኤክስቴንሽን ዘዴዎችን ተቀብሎ ሥራ ላይ ማዋል ናቸው፡፡ በመስኖ ኤክስቴንሽን ሊተገበሩ የሚችሉ ተስማሚ/ተገቢ የሆኑትን ዘዴዎች ለመምረጥ ይህ ጠቃሚ መመሪያን የሚሰጥ ነው፡፡

### 4.2.1. የግንዛቤ ደረጃ

በዚህ ደረጃ የአዳዲስ ግኝትና ፈጠራ ዕውቀት ለግለሰብ አርሶ/አርብቶ አደር የውሃ ተጠቃሚ ወሳኝ ነው፡፡ ብዙሀን መገናኛና ተወኔት የተመረጡ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም በተመሳሳይ ሰዓት ብዙ የውሃ ተጠቃሚዎችን ማግኘት ይቻላል፡፡ ብዙሀን መገናኛን ለመጠቀም የመስኖ ልማት ሠራተኞች እና የመስኖ ባለሙያዎች ትኩረት ሊሰጡት የሚገባቸው ጉዳይ ለሚያቀርቡት ይዘት የተሰብሳቢውን ዓይነተኛ ፀባይ ማለትም የአካባቢ ቋንቋ፣ ባህል እና ማህበራዊ ልማድ ጠንቅቆ ማወቁ ላይ ነው፡፡

### 4.2.2. የፍላጎት ደረጃ




ምስል- 1፡-የግንዛቤ ደረጃ ማሳያ ቻርት

ይህ ደረጃ አጽንኦት የሚሰጠው አዲስ ሀሳብንና አሠራርን ተቀብሎ ሥራ ላይ የማዋል ሂደትን፣ ዕውቀት ያለማቋረጥ ጠቃሚ እንዲሆን ሲሆን ነገር ግን ለአዳዲስ ሀሳቦችና አሠራሮች አወንታዊ ተነሳሽነትን መገንባት ወሳኝ እየሆነ የመጣ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የሚፈለጉ ዘዴዎች እንደ ግብ መረጃን ማጠናከርና ተነሳሽነትን መገንባትን ማካተት አለባቸው፡፡ እነኝህ ዘዴዎች የመስማትንና የማየትን ስሜት በተናጠልም ሆነ በስብስባ መጠቀም ያለባቸው፡፡ የቡድን ስብሰባ፣ የቡድን ውይይት፣ የራዲዮ ፎረም ዕውቀትን ለማጠናከር ሀሳብ የቀረበባቸው ናቸው፡፡ ይሁንና የመስክ ቀን እና የማሳ ጉብኝት ግለሰቦች ሲሰሙት የነበረውን እንዲያዩ ይፈቅዳል፣ በዚህም ለአዳዲስ ሀሳቦችና አሠራሮች የታሰበውን ተነሳሽነት ለመገንባት መልካም አጋጣሚ ነው፡፡

## 4.2.3. የማመዛዘን ደረጃ

ይህ አዲስ ሀሳብንና አሠራርን ተቀብሎ ሥራ ላይ ለማዋል የበለጠ ወሳኝ ደረጃ ነው፡፡ ምክንያቱም ውጤቱ የግለሰብ እና የጋራ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደር ወደ ሙከራና አዲስ አሠራርን ተቀብሎ ሥራ ላይ ማዋል ደረጃ መሸጋገርን ይወስናል፡፡ በዚህ ደረጃ አርሶ/አርብቶ አደሮች እውቀታቸውን ከአውነታው ጋር ማመዛዘን ይፈልጋሉ፡፡ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች የሰሙትንና ያዩትን በእርግጥም ተግባራዊ ሊሆን ስለመቻሉ ማረጋገጥ ይፈልጋሉ፡፡ የምርት ውጤት ሠርቶ ማሳያ የአርሶ/አርብቶ አደር የልምድ ልውውጥ፣ የመስክ ቀን ተግባራዊ እንዲደረጉ የሚመከርበት ምክንያት አርሶ/አርብቶ አደሮች ባዩት ተጨባጭ ማስረጃ ፍላጎታቸውን እንዲያጎለብቱ ይፈቅዳሉ፡፡ በእነኝህ የቡድን ዘዴዎች ውስጥ የአርሶ/አርብቶ አደር የአዲስ አሰራሮች ልምድ ልውውጥ ጠቃሚ ዘዴ ነው፡፡

## 4.2.4. የሙከራ ደረጃ

የውሃ ተጠቃሚው የቴክኒክና የማኔጅመንት ክህሎት ዋነኛው ዒላማ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህ ደረጃ የተናጥል አርሶ/አርብቶ አደር ጉብኝት በይበልጥ እየተመረጠ የመጣ እና አርሶ/አርብቶ አደር የመስኖ ውሃ ተጠቃሚው ፍላጎት ሊታሰብበት የግድ ይላል፡፡ ይህ ማለት የመስኖ ልማት ሠራተኛ ለግለሰብም ሆነ ለቡድን የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች በተመሳሳይ ሁኔታዎች እቅዳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ የመስኖ ልማት ሠራተኞች ማስታወስ የሚገባቸው ምንም እንኳ ተመሳሳይ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ተመሳሳይ ቴክኒኮችን ሥራ ላይ እያዋሉ መሆኑን፣ ልምድ የተወሰደባቸው ችግሮች ሁልጊዜ ተመሳሳይ እንዳልሆኑ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ በአርሶ/አርብቶ አደር/የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ/ ልምድ ልውውጥ እና በክህሎት ስልጠና የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት የማጉላት ዘዴ አርሶ/አርብቶ አደሮች አዳዲስ አሠራርን ተቀብለው ሥራ ላይ ለማዋል ሊያግዝ ይችላል፡፡

## 4.2.5. ሥራ ላይ የመዋል ደረጃ

በዚህ ደረጃ አርሶ/አርብቶ አደሮች አዲስ ሀሳብንና አሠራርን ተቀብሎ ሥራ ላይ ማዋል ይጀምራሉ፣ የመስኖ ኤክስቴንሽኑም ባለሙያ እና የመስኖ ልማት ሠራተኛው ጥረታቸውን ያለማቋረጥ መደገፍ አለበት፡፡ እውቅና የመስጠት ፕሮግራም የመስኖ ውሃ

ተጠቃሚዎችን በማበረታታት የውሃ ተጠቃሚዎች አዳዲስ ሀሳብንና አሠራርን ተቀብሎ ሥራ ላይ ማዋልን እንዲቀጥሉበት ያበረታታል፡፡ የእነኝህ ዘዴዎች ግብ እና መስፈርት በደካማ ዕቅድና አፈጻጸም ምክንያት አሉታዊ የሆነ ጉዳት እንዳይኖር በጥንቃቄ ማዘጋጀት ነው፡፡

በተለያ ደረጃዎች ከተመረጡ ዘዴዎች ከፍተኛውን ውጤት ለማሳካት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያውና የመስኖ ልማት ሠራተኞች የተረዱትን የመማር ሂደት የግድ ሥራ ላይ ማዋል አለባቸው፡፡ ለምሳሌ፡- በቡድን ስብሰባ የመስኖ ልማት ሠራተኞች በቪዲዮ በመታገዝ እና የቡድን ውይይትን ተከትሎ የትምህርት ገለጻ አቀራረብን መጠቀም ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል በመስኖ ኤክስቴንሽን ከላይ የተጠቀሱ ተስማሚ ዘዴዎችን በመምረጥ ረገድ የመስኖ ልማት ሠራተኞች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማገናዘብ አለባቸው፡-

- ወጪ- የሚመረጡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዘዴዎች ወጪ ቆጣቢና በአነስተኛ በጀት የሚተገብር መሆን አለበት፣

- ሽፋን- የሚመረጡ የቡድን ኤክስቴንሽን ዘዴዎች በርካታ የውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮችን፣ እማወራና አባወራን ያሳተፈ እና ወጣቶችን ያሳተፈና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል መድረስ የሚችል መሆን አለበት

- ውስብስብነት /ክብደት - የሚመረጡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዘዴዎች ቀላል እና በአነስተኛ ቁሳቁስ ሊፈፀሙ የሚችሉ፣ ብዙ ጊዜ የማይወስዱ እና በቀላሉ ሊተገበሩ የሚችሉ መሆን አለባቸው፣

- ክህሎት - የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ማስተማሪያ ዘዴን ስንመርጥ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያውና የመስኖ ልማት ሠራተኛው መፈፀም ወይም መተግበር የሚችለውና ተጨማሪ ስልጠና የማይጠይቅ መሆን አለበት

- ኢላማ - የሚመረጡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ማስተማሪያ ዘዴዎች ለእያንዳንዱ የውሃ አውታሮች አይነት እና ለሁሉም የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች ያማከለ፣ ለወጣቶች አና ለሴቶች ተስማሚ የሚሆን እንዲሁም የሴቶችንና የወጣቶችን ተጠቃሚነት እና ተሳትፎን ማረጋገጥ የሚችል መሆን አለበት፡፡

## 4.3 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ውጤት

- ግንዛቤ መፍጠር - የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች እንዲሁም ሴትና ወጣት አርሶ/አርብቶ አደሮች ራሳቸውን የመለወጥ ደረጃ ላይ ለመድረስ የባህሪ ለውጥ ከማግኘታቸው በፊት ተገቢ እና ተመጣጣኝ የሆነ መረጃ በሰዓቱ ማግኘት ይፈልጋሉ፡፡ ለተጠቃሚዎች አስፈላጊ መረጃ ለመስጠት ግንዛቤ ፈጠራ መዘጋጀት አለበት፡፡ ስለሆነም በመካከላቸው የባህሪ እና የተነሳሽነት ለውጥ ይመጣል፡፡

- ዕውቀትን ማሻሻል - የኤክስቴንሽን መልዕክት ውስብስብ በሆነ ጊዜ እርሱን ለመረዳት

ቀላል ላይሆን ይችላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ተጠቃሚዎች በመልዕክቱ ስለተካተቱ የተወሰኑ ተሞክሮዎች ጥቂት መሠረታዊ መመሪያዎችን እንዲማሩ ይፈለጋል፡፡

☞ ክህሎትን ማሻሻል - ተጠቃሚዎች ስለ አንድ ነገር በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው ነገር ግን በበቂ ክህሎት እጥረት ምክንያት አስፈላጊውን ተግባር ባልፈፀሙ ጊዜ በሰርቶ ማሳያ፣ በማሳ ለማሳ ጉብኝት፣ ወይም በሞጁላር ስልጠና አስፈላጊ የሆነ ክህሎት ማስታጠቅ ያስፈልጋል

☞ የባህሪ ለውጥ - ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮችን ለመረዳትና በእነርሱም ስምምነት ላይ ለመድረስ ከተፈለገ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ማሳመን ያስፈልጋል፡፡ በአርሶ/አርብቶ አደሩ መካከል ጠንካራ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር በመፍቀድ አማራጩ የኤክስቴንሽን ዘዴ ከቡድን ዘዴ እና ከሠርቶ ማሳያ ጋር የተያያዙ ናቸው፡ ፡ ልምዶች እንደሚያሳዩት ለተጠቃሚዎች ስለ አዲስ ሀሳብ/ቴክኒክ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ማብራራትና ሠርቶ ማሳያ ማካሄድ በቀላሉ ያሳምናቸዋል፡፡

የመስኖ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር መጀመሪያ በአርሶ/አርብቶ አደሩ እና በሴት እና በወጣት አርሶ/አርብቶ አደር የኢንፎርሜሽን ስብሰባዎች ላይ አሁን ባሉ የዘመኑ ተስማሚ አመራረት ዘዴዎች ላይ  ግንዛቤ መፈጠር ይኖርበታል፡፡ ችግሮች በመስኖ ልማት ሠራተኞች በኩል ተለይተው እያለ ነገር ግን አርሶ/አርብቶ አደሩ እና ሴት እና ወጣት አርሶ/አርብቶ አደሩ ባልገባው ጊዜ ይህ አሠራር አስፈላጊ ነው፡፡ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች አስፈላጊውን ግንዛቤ ከጨበጡና ፍላጎት ካሳደሩ በኋላ ምናልባት ስልጠና ሲሰጥ፣ አውደ ጥናትም ሊካሄድ ይችላል፡፡ የሚቀጥለው ደረጃ ከደንበኞች ጋር ውይይት ከተካሄደ በኋላ ሠርቶ ማሳያ ሥራ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ ነው፡፡ በውይይት ጊዜም በሠርቶ ማሳያዎች ወይም በሚኀበኙ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችና ምርጥ ተሞክሮዎች ላይ የተጠቃሚዎችን ተሳትፎ ለማጎልበት የጥናት ቡድኑ መነሳሳት አለበት፡፡ አዳዲስ ተሞክሮዎችንና ሀሳቦችን/አሠራሮችን/ ተቀብሎ ሥራ ላይ ለማዋል የተነሳሳው የጥናት ቡድኑ አባላት በቡድኑ ውስጥ በአዳዲስ ሀሳቦች ሰርቶ ማሳያ ተግባራት ላይ መሳተፍ ይኖርበታል፡፡ በዚህም የሚከተሉት ደረጃዎችን መጠቀም ይቻላል፡-

☞ በአሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ላይ ግንዛቤ መፍጠር፣

☞ በስልጠናና ሠርቶ ማሳያ ሥራ ላይ እንዲሳተፉ መጋበዝ፣

☞ ተጠቃሚዎች ራሳቸውን ከተለመደው አሠራር ያላቀቁ መሆኑን መለየትና አዲሱን ተሞክሮ እንዲቀበሉ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ ማስቻል፣

☞ የታሰበውን የልማት ግብ በተጠቃሚዎች ዘንድ ለማሳካት የተወሰነ አስፈላጊ ክህሎትን መለየት፣

## 4.4. የአዲስ ሀሳብና አሠራር ግኝት/ፈጠራ /ኢኖቬሽን/ ሥርዓት

የአዲስ ሀሳብና አሠራር ግኝት/ፈጠራ/ኢኖቬሽን/ ስፋት ያለው ቃል ሲሆን ይህም ሙሉ በሙሉ በተለየ መንገድ አንድን ነገር መፈፀም ወይም የነበረውን ቴክኖሎጂ ማሻሻል ማለት ነው። የአርሶ/አርብቶ አደር አዲስ ሀሳብና አሠራር ፈጠራ /ኢኖቬሽን/ የሚጀምረው በአርሶ/አርብቶ አደርነት ህይወቱ ውስጥ እንጂ የተወረሰ ነገር አይደለም።




ምስል- 2፡-የአዲስ ሀሳብ /ኢኖቬሽን/የኤክስቴንሽን አሰራር (Swanson 2009)

የአርሶ/አርብቶ አደር አዲስ አሠራር ፈጠራ ምናልባት ከሀገር በቀል ዕውቀት ወይም ከዘመናዊ/ ሳይንሳዊ/ ዕውቀት የሚመነጭ ይሆናል። የአርሶ/አርብቶ አደር አዲስ ሀሳብ/ አሠራር ፈጠራ /ኢኖቬሽን/ የተለየ ፀባይ የሚሆነው አዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጣሪው ላለው አውቀት ዋጋ መስጠቱ ሲሆን መነሻው ምናልባት ዘመናዊ ሳይንሳዊ ዕውቀት ወይም የአርሶ/አርብቶ አደሩ የአካባቢ ጥበብ ሊሆን ይችላል። በዚህ ግንኙነት የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ/ኢኖቬሽን/፣ ሂደት ውጤት በአርሶ/አርብቶ አደሩ የሚፈፀም ሲሆን ቴክኖሎጂው ከነባራዊው ጋር እንዲስማማ ወይም ውጤታማነትን፣ ብቃትን፣ ምርታማነትን፣ ትርፋማነትን፣ ለብዙ ጊዜ ቆይታን፣ በገበያ ተፈላጊነትን፣ ተስማሚነትን/ ምቹነትን፣ ሊላመድ መቻልን፣ ዘላቂነትን ወዘተ---ለማሻሻል ነው። በግልጽ የአርሶ/ አርብቶ አደር አዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ /ኢኖቬሽን/ እንደ ሂደት ሁሉንም መደበኛ ያልሆነ የአርሶ/አርብቶ አደር ሙከራ እና ፈጠራ ሲሆን እንደ ምርት ደግሞ በመካከል ወይም በሂደቱ መጨረሻ ምናልባት ለለውጥ የተሰጠው ዋጋ ነው።

የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ /ኢኖቬሽን/ የመስኖ ልማት ተሞክሮዎች የመስኖ ውሃ ቅልጥፍናን ማሳደግ የሚችሉ፣ ለአርሶ/አርብቶ አደሩ ኢኮኖሚ ጥቅም የሚያስገኙ እንደዚሁም የአካባቢ ጫናን የሚቀንሱ ናቸው፡፡ የመስኖ ውሃ ቅልጥፍና ዘዴ እና የተሻለ የመስኖ ውሃ ቅደም ተከተል መኖር የውሃ እና አልሚ ምግብ ማኔጅመንትን ማቀናጀት የሚችል ሲሆን በዚህም የግብርና ኬሚካል በጎርፍ መወሰድና እጥበት ችግሮችን ይቀንሳል፡፡ በብዙ አርሶ/አርብቶ አደሮች የመስኖ ተሞክሮዎች ላይ ጥናት እንደተካሄደው በሰብሎች የውሃ ፍላጎት እና እንደ ወቅቱ ሁኔታ አመችነት የመስኖ አጠጣጥ ሁኔታ መካከል አለመጣጣም ነበር፡፡ ምንም እንኳ ሁሉም ወቅታዊ የመስኖ አጠጣጥ ጥልቀት ከሰብሉ የውሃ ፍላጎት ጋር ምናልባት የሚጣጣም ቢሆንም ብዙ ጊዜ አርሶ አደሮቹ በመጀመሪያው ሰብል እድገት ደረጃ የሚሰጠው ውሃ ዝቅተኛ ሲሆን በመጨረሻው የሰብል እድገት ደረጃ ደግሞ ብዙ ውሃ ይሰጣል፡፡ ብዙዎቹም ጥልቅ የሆነ የውሃ አጠጣጥን ይመርጣሉ፡፡

### 4.4.1. የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ /ኢኖቬሽን/ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሚና

የአርሶ/አርብቶ አደር የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ /ኢኖቬሽን/ አሁን ያለውን የመስኖ ልማት ስርዓት የሀይለኛ እርሻ /ኢንቴንሲቭ/ እና በልዩ ልዩ ዓይነት ምርት ለማስኬድ በሠርቶ ማሳያ አማካኝነት ለሚገኘው ፈጠራ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ እነኝህ አርሶ/አርብቶ አደሮች ምንጊዜም ስኬታማ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ጥቂቶቹ "የአርሶ/አርብቶ አደር ሚሊየነር" እየሆኑ መጥተዋል፡፡ እነኝህ የአርሶ/አርብቶ አደር የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ /ኢኖቬሽን/ አርሶ/አርብቶ አደሮች በፍላጎታቸው ላይ ተመስርተው የግብርና ውጤታቸውን ለማሳደግ ከፍተኛ ዋጋ  በአላቸው አዳዲስ ሰብሎች፣ እንስሳት እና ሌሎች ትርፋማ ሥራዎች ላይ ሳይታክቱ መስራታቸው በትርፋማነት ላይ ስትራቴጂካዊ ሚና ተጫውተዋል፡፡ በመጀመሪያ የሚያደርጉት የአካባቢያቸውን የተለየ መልክአ ምድራዊ ሁኔታ፣ መሬት፣ የጉልበት ሀይል  ተደራሽነት ጋር በማገናዘብ እነኝህ አዳዲስ ሰብሎች ወይም የግብርና ምርቶች በገበያ ተፈላጊነታቸውን መዳሰስ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በውስን ሙከራ ላይ ተመስርተው ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማምረትና በገበያ ተጠቃሚ ለመሆን መሞከር ነው፡፡ በዚህ ስኬታማ መሆናቸውን ሲያረጋግጡ ተሞክሯቸውን ያሰፋሉ፡፡ በመስኖ ኤክስቴንሽን ሲስተም እነዚህ የአርሶ/አርብቶ አደር የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ /ኢኖቬሽን/ ሰዎች እንደ "አርሶ/አርብቶ አደር ፕሮፌሰር" ሆነው ያገኙትን ትምህርት ለሌላውም በማስተላለፍ እና ውጤታማነታቸውን ወደ ሌላ በመስኖ ልማት ላይ የተሰማራ አርሶ/አርብቶ አደር በማስፋት ረገድ ሚና ያላቸው ናቸው፡፡

በእነዚህ አርሶ/አርብቶ አደር ውስጥ ያሉ በርካታ አነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደሮች እነኝህ የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ /ኢኖቬሽን/ አርሶ/አርብቶ አደሮች በአዳዲስ አሠራሮች ላይ ጥረት እንደሚያደርጉ ይረዳሉ፡፡ ጥቂቶች ግን ይህን የተረዱና የሚባለውን ለመፈፀም የሚችሉ ቢሆንም ምርታቸውን የሚረከባቸው ገበያ ከሌለ በሚል ስጋት የሚያድርባቸው ናቸው፡፡ ከዚህ በታች በተመለከተው ስዕል የአርሶ/አርብቶ አደሮችን መሬት፣ ጉልበት፣ ጾታ፣ ፍላጎት መሠረት በማድረግ የአዳዲስ ሀሳብና አሠራር ፈጠራ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አሰራር በመጀመሪያ እነዚህን አዳዲስ ሀሳብ ፈጣሪ አርሶ/አርብቶ አደሮችንና ሀብታቸውን መለየት መቻልና ወደ ተለያዩ የአርሶ/አርብቶ አደር ቡድኖች ተሞክሮውን ማስፋት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በአብዛኛው የገጠሩ ማህበረሰብ ዝቅተኛና ሴት እና ወጣት አርሶ/አርብቶ አደሮች በአጠቃላይ ይህን ብቅ ብቅ እያለ ያለ ገበያ ገና አልተረዱትም፡፡ ነገር ግን አንዴ ከተረዱት በተለይም በአርሶ/አርብቶ አደር ግመታ አማካኝነት ግንዛቤ ካለገኙ በአነስተኛ ግብርና ላይ ኪሳራን በቀነሰ መልኩ ገበያ መር ምርቶች ላይ ለመሰማራትና ፈጥነው ለመማር ዝግጁ ናቸው፡፡ እንደገናም በዚህ ሂደት ላይ እነኝህ የአርሶ/አርብቶ አደር የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጣሪዎች/ኢኖቬተርስ/ እና የአርሶ/አርብቶ አደር ፕሮፌሰሮች ኤክስቴንሽኑን በመደገፍ ፍላጎት ያላቸውን አርሶ/አርብቶ አደሮች በአምራች ቡድኖች በማደራጀት በጋራ ገበያ መር የግብርና ተግባራት ላይ እንዲሰማሩ ስትራቴጂካዊ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ እነኝህ ጀማሪ አምራች ቡድኖች በአብዛኛው የሚጀምሩት ወደ አካባቢ ገበያ ለማቅረብ ነው፡፡ ነገር ግን ምርታቸውን እያሰፉ ልምድ ሲያገኙ ወደሚቀጥለው ሰፊ የከተማ ገበያ ብሎም በተወሰነ ደረጃ ወደ ዓለም ገበያ ይዘው ይሄዳሉ (ማለትም የእሴት ሰንሰለትን ያሳድጋሉ)፡፡




ምስል- 3፡-የዕውቀት አስተዳደር ሂደት (Cong et.al 2007)

በመስክ ላይ ያሉ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ልማት ሠራተኞች ይህን ሂደት በሚያሳልጡበት ጊዜ ከምርምር እና ከግል ሴክተሩ ጠንካራ ግብረ መልስ ድጋፍ ይፈልጋሉ፡፡ ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ አዳዲስ አሠራር ፈጣሪ የሆኑ አርሶ/አርብቶ አደሮችም ቢሆን ከአዳዲስ ሰብሎችና ሌሎች የግብርና ምርቶች ጋር በተያያዘ ወቅታዊ መረጃ እና ቴክኖሎጂ አይኖራቸውም፡፡ በእነኝህ መረጃዎችና ቴክኖሎጂዎች የመስኖ ልማት ጣቢያ ሠራተኞች የሚታገዙበት ቁልፍ የግንኙነት አሠራር ዘዴ በወረዳ ደረጃ ላይ ባለው የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የባለሙያዎች ቡድን አማካኝነት ነው፡፡ ይሁንና መጀመሪያ ላይ ብቅ ብቅ እያለ ስላለው ገበያ እውቅና እንዲኖራቸው እና እነኝህን የግብርና ምርቶችንም እንዴት ወደ ገበያ ማቅረብ እንዳለባቸው ብዙ መማር ይፈልጋሉ፡፡ በተጨማሪም በእነኝህ ብቀ ብቅ ማለት የጀመሩ የግብርና ድርጅቶች ላይ እውቅና ሲኖራቸው የወረዳው የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ቡድን የመስኖ ልማት

ሠራተኞችን (በምርምር ወይም የግል ባለሀብቶች አማኝነት )ሊያሰለጥን ይችላል፣ የአካባቢ አምራቾች ቡድኖችንም በወረዳ ደረጃ ላይ ትልልቅ የገበያ አማራጭ ካላቸው አምራች ማህበራት ጋር ለማገናኘት ያግዛሉ። በዚህ የልማት ደረጃ ላይ ገንዘብ እንደዚሁ ትልቁን ሚና ይጫወታል። በርካታ አርሶ አደሮች በአዲሱ መልካም አጋጣሚ ፍላጎት በአሳደሩ ጊዜ ለአዳዲስ አርሶ/አርብቶ አደሮች በዚሁ ተግባር ላይ እንዲሳተፉ መነሻ ካፒታል ለመስጠት ገንዘብ አነቃቂ ሀይል በመሆን ጉዳዩን ያፋጥነዋል።

## 4.4.2. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕውቀት አስተዳደርን ማጠናከር

የዕውቀት አስተዳደር ሲባል ሂደት ሲሆን የዕውቀት ፈጠራን፣ ልየታን፣ አጠቃቀምን፣ ማጠራቀምን፣ ማከፋፈልን እና መማማርን ያካትታል። ዕውቀት በሙከራ፣ በማለማመድ፣ፊት ለፊት/ገፅ-ለገፅ በመነጋገር/በመወያየት/ እና በሌሎች መማማሪያ ድባቦች የሚያድግ ሲሆን ውጤቱም የዕውቀት ብልፅግና ይባላል። በዕውቀት አስተዳደር የዕውቀት ሂደትንና የመጨረሻ አፈጻጸም ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩት አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ ተመራማሪዎች፣ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና የመስኖ ልማት ባለሙያዎች፣ ፖሊሲ አውጪዎች እና ሌሎችም ቁልፍ ተዋንያን እንደሆኑ ይታሰባል፡ ፡ ለዕውቀት አስተዳደር ሁሉ አቀፍ/የዙሪያ ፍሰት ሁለቱ ማለትም ከነባሩ የተሻለ በቂ አውቀት እና መተላለፊያ ዘዴ/መንገድ መኖር አለባቸው። በዕውቀት አስተዳደር ሳይንሳዊ ዕውቀት እና ልማዳዊ/የአካባቢ በቀል ዕውቀት ጥምረት ሊሠራ የሚችልንና የተጣራ/ የተሻሻለ ዕውቀትን ለማጉላት ወሳኝ ነው። የግብርና ዕውቀት ውጤታማነትን ለማሻሻል የአሠራር ዘዴን ማሳደግ አስፈላጊ ሲሆን ውጤታማ በሆነ ሂደትና የተቋም አደረጃጀት እንዲሁም ውጤታማ በሆነ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አማካኝነት ዕውቀትንና መረጃን ማፍለቅ፣ መያዝ እና ማሰራጨት ያስፈልጋል።

ለዚሁም የሚከተሉት ቁልፍ የድጋፍ ተሳትፎዎች/ኢንተርቬንሽን/ ቀርበዋል። ይህ ስትራቴጂ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ልማዳዊ ዕውቀት ከዘመናዊው ዕውቀት (ከምርምር፣ ከዩኒቨርሲቲዎች እና ኤክስቴንሽን የፈለቀ) ጋር ለማቀናጀትና ወደፊት ወደ ባለአነስተኛ መስኖ ይዞታ አርሶ/አርብቶ አደሮች የዕውቀት ስርጭትን ከፍ ለማድረግ እንዲያስችል የታሰበ ነው።

- ☞ ለዕውቀት አስተዳደርና አውታር ግንባታ በቁልፍ የልማት ተዋንያን መካከል ጥብቅ/ ጠንካራ የሆነ ትብብርን መመስረትና ማጠናከር

- ☞ ፈጣን ቀልጣፋ እና ወጪ ቆጣቢ ዕውቀት አስተዳደርን ለማሳለጥ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን መጠቀም። የብዙዎቹ አገሮች ልምድ የሚያመለክተው ለጥሬ መረጃ እና ኢንፎርሜሽን ፍሰትን የሚያሳልጠው ፈጣን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት በግብርና እጅግ ብዙ የዕውቀት አስተዳደርን ተሞክሮ አሳድጓል (ለምሳሌ፡ በህንድ ቾፓል፣ እና ኤም ክሪሺ፣ በኬንያ ኤም ፋርም ሊሚትድ)

☞ የመስኖ ልማት ዕውቀት ምንጭ እንዲሆኑ እንዲሁም በተመራማሪዎች፣ በመስኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፣ የመስኖ ልማት ሠራተኞች እና በአርሶ/አርብቶ አደሮች መካከል የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ብሎም ለፖሊሲ አውጪዎች እንደ ግብዓትነት እንዲያገለግሉ የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን ማጠናከርና የተሻለ አውታር እንዲዘረጋላቸው ማድረግ

☞ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን በመጠቀም በቀላሉ ለመገናኘትና በተለያዩ የመስኖ ልማት ተዋንያን (የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፣ የመስኖ ልማት ሠራተኞች፣ አርሶ/አርብቶ አደሮች እና ተመራማሪዎችን ወዘተ-- በማካተት) በመካከል ያለውን ትብብር ለማሳለጥ መስመር ላይ ሆነው እና ሳይሆኑ እየሰሩ ያሉ መድረኮችን መመስረት

☞ አዳዲስ አሠራሮችን ተቀብሎ ሥራ የማዋል እድልን ለመጨመር በዕውቀት አስተዳደር ሂደት ላይ ወንዶችና ሴቶችን ማካተትና ተሳትፏዊ ሂደት ላይ ዕውቀትን ማፍለቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህ የአርሶ/አርብቶ አደሮች የአገር በቀል ዕውቀትንና የአሁኑን የምርምር ግኝቶች ማቀናጀት ያስችላል፣ በተጨማሪም ወደ አነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደሮች የተሰራጨውን ዕውቀት የመጠቀም እድልን ያሳድጋል፡፡

**ቀበሌያዊ /ከባቢያዊ/ የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ፡-** ቀበሌያዊ/አርሶ/አርብቶ አደር አዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ ሲባል የተሻለ ሆኖ የተገኘ አካባቢ በቀል ዕውቀት ሲሆን ይህ ዕውቀት በማህበራዊ ቡድን ውስጥ የሚያድግ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ከራስ ልምድ መማርን የሚያካትት፣ እንደዚሁም በአንድ ወቅት ከሌላ ምንጭ የተገኘ፣ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ በዚያው አካባቢ ባለ ሀሳብና ድርጊት ላይ ሀሳቡን ወስዶ የራስ የማድረግ ማለት ነው፡፡ አርሶ/አርብቶ አደር አዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ ሂደት ሲሆን በዚህም ግለሰቦች ወይም ቡድኖች አዲስና በተሻለ መንገድ ሀብትን ማስተዳደርን ወይም ማጎልበት፣ የአካባቢ በቀል ዕውቀታቸውን ወሰን ማሳደግና ማስፋፋት ነው፡፡ አዲስ ሀሳብና አሠራር ፈጠራ ምናልባት ቴክኒክ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ - ተቋም ርስት ጭምር ነው፡፡ መተዳደሪያ ዘዴዎች ለአየር ንብረት አደጋ ላይ በወደቀ በተለይ በድርቅ አካባቢ ስኬታማ የሆነ አዲስ ሀሳብና አሠራር ፈጠራ ብዙውን ጊዜ አዲስ መንገድን ተደራሽ ማድረግ፣ ወይም ተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምን ማስተካከል፣ በአዲስ መንገድ የህብረተሰብን ማደራጀት፣ ወይም በአዲስ መንገድ የአጋር አካላት የእርስ በርስ ትስስር መፍጠርን ያካትታል፡፡ በሁሉም የዓለም አካባቢ ቀበሌያዊ/ከባቢያዊ አዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ መደበኛ ባልሆነ ሙከራ ይካሄዳል፡፡ ነገር ግን የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ ሂደትና የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራውን የመለየትና በሰነድ የማስቀመጡ ትኩረት እየጨመረ የመጣው አሁን በቅርቡ ብቻ ነው፡፡

**ቀበሌያዊ/ከባቢያዊ አዲስ ሀሳብና አሠራርን ከፍ ማድረግ፡-** በአለፈው ጊዜ የውጭ ግብዓቶችን በመጠቀም የገጠር ልማትን በሥራ ዘርፎች የማካተት ጥረት በዋናነት ቁጥጥርን ዓላማ በማድረግ በቴክኒክ የድጋፍ ተሳትፎ ( ኢንተርቬንሽን) ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ነበር፡፡ በሀገራችንም ይህ ጥረት በአጠቃላይ ለአነስተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች ብዙ አስተማማኝ ተደራሽነት እንዲኖራቸው ለማድረግ እና

መተዳደሪያቸውን ለማሻሻል ያላስቻለ ነበር፡፡ ይሁንና ጥቂት ስኬቶች ነበሩ፡፡ እነዚህም የተወሰኑ የግብርና ፈጠራ ሥራዎች (ኢንተርፕራይዞች) ማለትም እርጥበት ባለባቸው አካባቢዎች ቡና፣ ሻይ እና የወተት ላሞች እርባታ ናቸው፡፡ በገጠር ልማት ለምርምር፣ ለኤክስቴንሽን እና ለትምህርት ዋነኛው የአቀራረብ ዘዴ እስካሁን "ቴክኖሎጂን ማስተላለፍ "የሚከተለውን መንገድ የተከተለ ነው፡፡ ይህ ተመራማሪዎች በፓኬጅ የተቀመጠ እና በኤክስቴንሽን አገልግሎት ለአርሶ/አርብቶ አደሮች የሚሰራጭ ዕውቀትን ይፈጥራሉ በሚል ግምት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ የአቀራረብ ዘዴ ውጤታማ በሆነ መልኩ የቀበሌ/ከባቢያዊ ፈጠራ እና አዲስ ሀሳብ/አሠራር የእርምጃ ድምጽ ያሰማል፡፡ እነርሱም የተሟላ ቴክኒኮችንና የቀበሌ/ከባቢያዊ አዲስ ሀሳብን/አሠራርን ለማሳደግ በሀብት ተጠቃሚዎችና በድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች አማካኝነት አሳታፊ የድርጊት ትምህርትን ከፍ ያደርጋሉ፡፡ በድክመታቸውና በችግራቸው ላይ ከመነጋገር ይልቅ በጥንካሬ ላይ ያተኮረ፣ የተለዩ መልካም አጋጣሚዎችን ፈልጎ የሚያገኝ፣ ከቀበሌ/ከባቢያዊ ሀሳብ/አሠራር የሚነሳ አወንታዊ የአቀራረብ ዘዴ ቁልፉ የሚያነቃቃ አዲስ ሀሳብ/አሠራር ነው፡፡

**አዲስ ሀሳብ/አሠራር አመንጪዎች እነማን ናቸው?፡-** የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና የመስኖ ልማት ሠራተኞች አስተዋውቀዋቸው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመውሰድ ፊት ለፊት የተሰለፉ አርሶ/አርብቶ አደሮች አዲስ ሀሳብ/አሠራር አመንጪዎች እንደሆኑ ይገመታል፡፡ ይሁንና በእውነቱ እነዚህ ተመሳሳይ ህዝቦች ናቸውን?፣ የአርሶ/አርብቶ አደር አዲስ ሀሳብ/አሠራር የአቀራረብ ዘዴ የሚጨነቀውስ ለማን ነው? አይደሉም፡፡ የአርሶ/አርብቶ አደር አዲስ ሀሳብ/አሠራር አመንጪዎች ባህላዊ/ልማዳዊ ቴክኖሎጂ ተቀባዮች አይደሉም፣ በመስኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያው እና በመስኖ ልማት ሠራተኞች ወደ አሰራሩ የገቡ ናቸው፡፡ አስፈላጊ ለውጦችን አምኖ በመቀበል በእውነትም አንዳንዴ አዳዲስ አሠራርን ይቀበላሉ፣ ግን ዘወትር ቴክኖሎጂን ለራሳቸው ለመቀበል ይሞክራሉ፡፡

ከሌሎች የተማሩትን እና ወደ ራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ወስደው ወደ እውነታ ለመቀየር እና ለመለወጥ ደፋሮችና ተነሳሽነት ያላቸው ናቸው፡፡ ይህ በእርግጥም ማን አዲስ አስተሳሰብ አመንጪ እንደሆነ እና የአመንጪው በጣም ጠቀሚ ባህሪ ምን እንደሆነ አንዱ ብቻ አመላካች ነው፡፡ በአጭሩ ከአያት ቅደመ አያት በተገኘ የሀገር በቀል ዕውቀትን እንጂ ሳይንሳዊ ዕውቀትን ብቸኛ አድርገው አይመኩበትም፡፡

የአርሶ/አርብቶ አደር አዲስ ሀሳብ/አሠራር ፈጠራ እንደ አቀራረብ ዘዴ "የቴክኖሎጂ አቀራረብ ዘዴን ማስተላለፍ "የስልጠና ተግባራትንና የኤክስቴንሽን አገልግሎትን አጠቃሎ ሥራ ላይ በማዋል ረገድ ለአርሶ/አርብቶ አደር አዲዲስ ተሞክሮዎች ሁሉንም በሚመለከት አይደለም፡፡ ይሁንና የአቀራረብ ዘዴው በሚገባ እውቅና የሚሰጠው ተከታታይ በሆኑ የትራንስፎርሜሽን ሂደቶች ከራሳቸው እውነታ ጋር ለማጣጣም ቴክኖሎጂዎችን ሥራ ላይ የሚያውሉ የአርሶ/አርብቶ አደሮችን ጠቢብነት ነው፡፡ ቴክኖሎጂን ሥራ ላይ ከማዋል እይታ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና የመስኖ ልማት ሠራተኞችንና ተመራማሪዎችን በማገዝ የቴክኖሎጂ መስፋፋት ሞዴል ላይ በተለያዩ እና በተወሳሰበ አካባቢ በይበልጥ እየተመካኙባቸው ያሉ ውስንነቶችን ለመቋቋም ይህ አቀራረብ ዘዴ አማራጭ ነው፡፡

ስለዚህ ምንም እንኳ ይህ ከመስኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና ከመስኖ ልማት ሠራተኞች ለመማር እና ቴክኖሎጂን ተቀብሎ ሥራ ላይ ለማዋል ንቁ ለሆኑ አርሶ/አርብቶ አደሮች እውቅና ቢሰጥም ዋነኛው እምነት የሚጣልበት የአቀራረብ ዘዴ የሚያተኩረው አዲስ ነገር ለማምጣት ወይም የሚመጡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በራሳቸው ጠቢብነት/ፈጠራ እና ልምድ ወደ ራሳቸው እውነታ ለማጣጣም የሚፈትሹን ግብርናን በአትኩረት የሚተገብሩ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ነው፡፡

የሚከተሉት ቀመሮች በማንኛውም አጠቃላይ መንገድ የአርሶ/አርብቶ አደር አዲስ ሀሳብ/አሠራርን ለመግለጽ ምናልባት የሚረዳ ይሆናል፡፡ ይሁንና ይህ እንደሞዴል የትኛው የአርሶ/አርብቶ አደር አዲስ ሀሳብ/አሠራር (FI) = የአርሶ አደር ጠቢብነት/ፈጠራ (FW) + [-] አገር በቀል ዕውቀት (IK) + [-] ሳይንሳዊ ዕውቀት (SK) + እሴት መጨመር (VA)

$$FI = FW + [-] IK + [-] SK + VA$$

ሂሳባዊ ቀመሩ የሚያመለክተው አርሶ/አርብቶ አደሮች በአገር በቀል ዕውቀት ወይም ሳይንሳዊ ዕውቀት ለውጥ እያመጡ ነው፡፡ ይህ ለውጥ ጥቂት ሀሳቦችን/ተሞክሮዎችን አስወግዶ አዲስ ባህሪይ በዕውቀት አካል ላይ ለማስቀመጥ የታሰበ ነው፡፡ እሴት መጨመር በእርግጥም የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ሂደት የወጣ ንብረት ነው፡፡ በዚህ ሂደት ሙሉ በሙሉ አዲስ እሴት ከነባሩ ላይ ሲጨመር ነው፡፡ ይህ ምናልባት በአዲስ ሀሳብ/አሠራር ዓይነትና ውስብስብነት ላይ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 4.4.3. አሳታፊ የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ልማት

አሳታፊ የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ልማት በብሄር/ሀገር እና ህዝብ የሚወሰን ሲሆን ለገጠር ልማት የመንደር መደበኛ ያልሆነ አገር በቀል ዕውቀት ከማንኛውም ሳይንሳዊ መደበኛ የሆነ ዕውቀት ጋር እኩል ጠቃሚ ነው፡፡ ይሁንና ሁለቱ የዕውቀት ዓይነቶች ይለያያሉ፡ ፡ በአሳታፊ የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ልማት ዘዴያዊው ብዙውን ጊዜ የሚያንፀባርቀው የሰፈር/ከባባዊ ዕውቀት ስለ እነርሱ ውስብስብ ሁኔታ ከውጫዊው ዕውቀት (ሳይንሳዊ ዕውቀት፣ እና የአርሶ/አርብቶ አደር ዕውቀትን ከሌላ አካባቢ፣ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን እና የመስኖ ልማት ሠራተኞችን ወዘተ---)ጋር የተጣመረ ነው፡፡




ምስል-4፡-አሳታፊ የሃሳብ ልማት ንድፍ

በአሳታፊ የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ልማት የሚገጥመው አስቸጋሪ ጉዳይ በከባባዊ ዕውቀት፣ ልምድ እና ክህሎት እና በሳይንሳዊ የሰለጠነ ተመራማሪና በመስኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና በመስኖ ልማት ጣቢያ ሠራተኞች መካከል የፈጠራ ጥምረትና ማዘጋጀቱ ነው፡፡ አጽንኦት የተሰጠውም ተግባራዊ ሙከራ በጋራ ማካሄድ ላይ ነው፡፡ ግቡ አዲስ ግኝት ለመፈለግና የሚሰራበትን መንገድ ለመፈለግ ነው፡፡ በእርግጥ በአብዛኛው እነኝህ ወደ ቦታው የመጡ የሚታወቁ ቴክኖሎጂዎችን ወይም የታወቁ መሠረታዊ ነገሮችን ከአዳዲሶቹ ጋር በብልሀት ማገናኘት ነው፡፡ አዳዲስ የመስኖ ልማት አሰራሮችና መንገዶች በሀገር በቀል ዕውቀት ሲስተም ውስጥ መጣጣምና መተከል/ መገንባት አለባቸው፡፡ አዳዲስ አሰራሮችና መንገዶች እውን የሚሆኑት ለተባለው አርሶ/ አርብቶ አደር ያለ ውጫዊ ድጋፍ ሲተገበር ነው፡፡ የምርት መገልገያ ሊገኝና በአቅም ሊገዛ የሚችል በገበያም የሚገኝ መሆን አለበት፡፡ ሂደቱና ማደራጀቱ በአካባቢ ባለ አቅም ሊመራ/ሊስተካከል/ የሚችል መሆን አለበት፡፡ ምንም እንኳ አሳታፊ የአዲስ ሀሳብ/ አሠራር ልማት ብዙውን ጊዜ የሚሰራው በግብርና ተሞክሮዎች “ሥራ ላይ የሚውሉ አዳዲስ ነገሮችና መንገዶች “የቴክኖሎጂ ሙከራ መሠረት ቢሆንም ብዙ ችግሮች፣ መልካም አጋጣሚዎች፣ አምራቾች የቴክኖሎጂ ጉዳይ አይደሉም፡፡

- ☞ ቀበሌያዊ/ከባቢያዊ አዲስ ሀሳብ/የአሠራር ሂደት፡- ይህ ሂደት ሲሆን በዚህም በቀበሌ /ልዩ ቦታ ላይ በአካባቢው የተገኙ ሀብቶችን በመጠቀም እና ያለምንም ግፊት ወይም ከመደበኛው የምርምር ወይም ከልማት ወኪሎች ቀጥተኛ ድጋፍ ሳያስፈልግ በራሳቸው ተነሳሽነት በተሻለ መንገድ አዳዲስ ነገሮችን ፈልጎ ማግኘት ወይም ማጎልበት ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ሂደትን ነው፡፡

- ☞ ቀበሌያዊ/ከባቢያዊ አዲስ ሀሳቦች/አሠራሮች፡- ይህ የሂደት ውጤት ሲሆን ለምሳሌ፡ - የመስኖ እርሻ ቴክኒኮችን ወይም ሥራዎችን ማደራጀት ለዚያ አካባቢ አዲስ ነው ይህ የሚያሳየው የሂደት ውጤትን ነው፡፡

- ☞ የአርሶ አደር አዲስ ሀሳብ/አሠራር፡- አዳዲስ ሀሳብ አመንጪዎች ኑሮአቸውን ለማሻሻል ድንቅና በጣም ጥሩ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ እነኝህ የቀበሌ/የአካባቢ አርሶ/አርብቶ አደሮች ሲሆኑ የራሳቸውን ፈጠራ በማካተት በአዲስ መንገድ የመስኖ እርሻ ሥራን ማካሄድ ወይም ተፈጥሮ ሀብትን መንከባከብ ዋነኛ ተግባራቸው ነው

- ☞ የአርሶ/አርብቶ አደሮችን አዲስ አሠራር መረጃ አያያዝ፡- በመረጃ ማረጋገጥ/ በሰነድ/ ሲባል ማስረጃ የመስጠት ሂደት (የአንድ ጉዳይን ሰነድ ለመያዝ) ነው፡፡ በመረጃ ማረጋገጥ/ሰነድ በቀበሌ/ከባቢያዊ አዲስ ሀሳብ/አሠራር ወይም በአሳታፊ መስኖ ልማት ሲባልም ስለ አካባቢው አዲስ የፈጠራ ሥራ፣ ሙከራዎች፣ እና አሳታፊ መስኖ ልማት መረጃን መያዝ ሂደት ማለት ነው፡፡ የቀበሌ/ከባቢያዊ አዲስ ሀሳብ/አሠራር በሰነድ መልክ መረጃን ማሰባሰብ አሳታፊ መስኖ ልማትን ከፍ ለማድረግ መልካም ጅምር ሥራ ነው፡፡ አዲስ ሀሳብ/አሠራርን ሰነድ በመያዝ (በመረጃ በማረጋገጥ) አንድ ባለሙያ ከአርሶ/አርብቶ አደሮች ጋር ይቀራርባል፣ ሀሳባቸውንም ይረዳል፡፡ አዲስ ሀሳብ/አሠራር በሰነድ ሊያዝ የሚቻለው በፎቶግራፍ፣ በቪዲዮ(ተንቀሳቃሽ ፊልም)፣ እና በኦዲዮ (እንደ ሬዲዮ ድምጽ መቅረጫ ዓይነት) ነው፡፡ ስለ አዲስ ሀሳብ/አሠራር የተለያዩ ዘዴዎችን ማለትም ምልከታ፣ መጠይቅ፣

የምርምር ጥናትን በመጠቀም መረጃ ማሰባሰብ ይቻላል፡፡ በሰነድ አያያዝ/መረጃ ማረጋገጥ/ ሂደት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መመለስ ያስፈልጋል፡፡

- ለማን? - የተጠቃሚን ማንነት መፈለግ
- ለምን? - ውስጣዊውና ውጫዊው ፍላጎት
- የት? - ቦታው፣ አዲስ ሀሳብ/አሠራር እየተከናወነበት ያለው
- ማን? - ምርቱ ፣ የታየውና በመጨረሻም ያስዋወቀው

## የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ሰነድ/ማስረጃ/ ይዘት ፡-

- የአዲስ ሀሳብ/አሠራር ዓይነት
- ለአዲስ ሀሳብ/አሠራር ምክንያቶች
- አዲስ ሀሳብ/አሠራር መቼ ተጀመረ?
- ሀሳቡ ከየት መጣ? አዲስ የውጪ (ባህላዊ የተስተካከለ/ ሀገር በቀል ዕውቀት/)
- አዲስ ሀሳቡን/አሠራሩን ለማሳደግ ምን ያህል ጊዜ ወሰደብህ?
- ለአዲስ ሀሳብ/አሠራር የፈጀው ጉልበት መጠን
- በአዲስ ሀሳብ/አሠራር ጥቅም ላይ የዋለ ምን አስፈላጊ ነገር ነበር?
- በአዲስ ሀሳብ/አሠራር ላይ የገጠመ ችግር
- ወደፊት ችግርን ለመፍታት ምን ሀሳብ አለ?
- አዲስ ሀሳብ/አሠራርን ምን ያህል ሌሎች አርሶ አደሮች ኮርጀዋል?
- ሌሎች አርሶ/አርብቶ አደሮች በአዲስ ሀሳብ/አሠራርን እንዴት እና መቼ እዩት?
- አዲስ ሀሳብ/አሠራር ሥራ ላይ ለማዋል አስቸጋሪ ሁኔታ ገጠሞ ነበር ወይ (ልምድ)?
- የትኞቹ አዲስ ሀሳቦች/አሠራሮች ህብረተሰቡን ወጪ አስወጡት?
- ሎሎች ማንኛውም አዲስ ሀሳቦች/አሠራሮች?

### ክፍል 3፡- የኤክስቴንሽን ተግባቦት እውቀት እና ፈጠራ

### የሥርዓተ ፆታ አካላት ጉዳዮች

- የኤክስቴንሽን አሰጣጥ ዘዴ መረጣ ወቅት ስርዓተ ጾታን የትምህርት ደረጃ እና እድሜን መሰረት ሳያደርግ ለልማት ግንኙነት ተጠቃሚዎች ሊያስፋፉት ይችላሉ በሚል ታሳቢ የተመረጠ ነው፡፡
- በአብዛኛው ጊዜ ባል ለቤተሰብ የተማረውን ያካፍላል የሚል አመለካከት በመያዝ የቤቱ መሪ አባወራ እና እማወራ ትኩረት ያደርጋል፡፡
- በሴቶች የሶስትዮሽ የሥራ ተግባር እና እቤት ውስጥ በስራ ውጥረት ስለሚያከናውኑ በቡድን ግንኙነት ወቅት እንዳይሳተፉ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ በሚደረግ ቡድን ውይይት ወቅት ሴቶች ተሳታፉነት አዝጋሚ ነው፡፡ ወንዶች የተሻለ እውቀት አላቸው ብለው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ወንድ አ/አደሮች እና የኤክስቴንሽን ሰራተኞች ሴቶች ስለግብርና እውቀት የላቸውም የሚል አስተሳሰብ አለ፡፡ በስብሰባዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያበረታታቸው አካል የለም፡፡
- ሥርዓተ ፆታን ለማስረጽ እና ሴቶች በኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲሳተፉ ለማስተባበር የኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን እና የግብርና ልማት ሠራተኞች የእውቀትና የክህሎት ችግር አለባቸው፡፡ የሴቶችን ተጨባጭ ፍላጎት እና ምርጫቸውን ለመለየት ይቸገራሉ፡፡ በተጨማሪም ሊሰራ እና ሊተገበር የሚችል መልኩ እንዴት በኤክስቴንሽን አገልግሎት መሳተፍ እንዳለባቸው በማድረግ ረገድ የክህሎት ውስንነቶች ይታያል፡፡
- ባለትዳር ሴቶች በቤተሰብ ውስጥ ውሳኔ በመስጠት ረገድ ዝቅተኛ ስለሆኑ በኤክስቴንሽን አገልግሎት ተሳትፎ የሴቶች ተሳትፎ አነስተኛ ነው፡፡
- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሰራተኛ ቴክኖሎጂ በመለየት ረገድ የሚሰጡት ውሳኔ መስጠት ከሚችሉት በአብዛኛው ከወንዶች ጋር ነው፡፡ ቴክኖሎጂ በማስፋት በማስወገድ ረገድ/ የሴቶች ተሳትፎ አስፈላጊነት ግምት ውስጥ አይገባም፡፡

### እንዴት ማድረስ ይቻላል?

- ሁሉም የኤክስቴንሽን የአተገባበር ዘዴ በእኩል ለወንድ ለሴትም አስፈላጊ አይደለም፡፡ ለወንዶች የተሻለ የሚሰራው ለሴቶች በእኩል ላይሰራ ይችላል፡፡ በአጠቃላይ ለሴቶች በተለይም ለባለትዳር ሴቶች በግልጽ የልማት ፍላጎታቸውን ለማሳካት የሚያስችል የአተገባር ስልት ያስፈልጋል፡፡ በቀላሉ ሊረዱት እና ሊተገበር የበሚችል መልኩ በአብዛኛው ቤት ለቤት/ በማሳ ደረጃ የሚደረግ ግንኙነት በሰርቶ ማሳያ በታገዙ መልኩ ይመረጣል፡፡ በተግባር የሚደረጉ የቴክኖሎጂ ስርዓት ሰርቶ ማሳያዎች እምነት ይጣልባቸዋል፡፡ በግል የሚያገኙ የግንኙነት ዘዴዎች በባለትዳር ሴቶች በጣም ይመርጡታል፡፡ ምክንያቱም ለእነርሱ በሚመቻቸው ጊዜ ማድረግ ስለሚቻል መደበኛ መግባቢያ አይነት ሊሆን ይችላል፡፡ ሴቶች ያላቸውን ፍላጎት በነፃነት መግለጽ ስለሚያስች የኤክስቴንሽን ዘዴ እና አቀራረብ ትልቅ ቦታ አለው፡፡
- ወንዶች እና ሴቶች በመስኖ ግብርና ላይ ማሳተፍ ከቻልን ቤተሰብን በጥቅል ወንድ እና ሴት በጋራ ለማግኘት ሁለቱም በጋራ ስልጠናዎችንና ሰርቶ ማሳያዎችን በማካሄድ በአተገባበር ላይ አንድ አይነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ የወንድ እና የሴቶች ለየብቻ ቡድን መፍጠር የወንዶች የበላይነት ለማስቀረትና ሴቶች በነፃነት እና በራስ ለመተግባር ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና የመስኖ የልማት ሰራተኞች ሴት አ/ አደሮች እንዲሳተፉ በማሰብ ማበርታት በእማወራ ቤተሰብ ውስጥ ኃላፊነትን ሊሸከሙ የሚችሉ ወጣቶች ላይ መስራት አለበት፡፡

- የልማት ሰራተኞች/ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እንዴት ለሴቶች ተስማሚ የሆነ ስልጠና አቀራረጽ እና ዘዴ ለተሻለ የሴቶች የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ በጣም ተስማሚ እና ምቹ ዘዴ አመራረጥ ላይ የሰለጠነ መሆን አለበት፡፡
- የልማት ሰራተኛው የቤተሰብ ኃላፊነትን በመከፋፈል የሴቶችን የሥራ ጫና ለመቀነስ ውሳኔ በመስጠትና በቤተሰብ ውስጥ ያላቸው የመወሰን አቅም መጨመር የሚያስችል እና የሚያበረታቱ የትግበራ ዘዴዎችን ማፈላለግ አለበት፡፡ ይህም ለሴቶች በመስኖ ልማት ግብር እና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተሳትፎ ቀጥተኛ የሆነ ፋይዳ አለው፡፡
- የኤክስቴንሽን አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ማን ማቀድ እንዳለበት፣ ማን አገልግሎቱን እና መረጃውን መቀበል እንዳለበት አገልግሎቱን ማን መስጠት እንዳለበት ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የመስኖ ልማት ባለሙያ ሴት ከሴት አ/አደሮች ጋር ለመገናኘት የባህል ተጽዕኖ ካለ ወይም ሴት አ/አደሮች ከወንድ የመስኖ ልማት ባለሙያ ለመወያየት ምቹ ካልሆኑ የኤክስቴንሽን የአገልግሎት አሰጣጥ ለአብነት ያህል ባልየውን ቀድሞ በማግኘት ስለ ጉብኝቱ አላማ በማሳወቅ ቤተሰቡን መጎብኘት አልያም ከባልየው ጋር በጋራ ሚስቱን ማግኘት፣ ሴቶችን በቡድን ማግኘት መንግስታዊ ድርጅቶችን እገዛ በመጠየቅ ወይም በሴቶች ላይ የሚሰሩ ተቋማት በመጠየቅ በሴቶች የመስኖ ውሃ ተጠቃሚነት ንዑስ ኮሚቴ ማነጋገር እና ከሌሉም በአከባቢው ካሉ በመጠቀም እገዛ በማድረግ ነው፡፡

ጠቀሜታ

- ሴቶችና ወንዶች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ማግኘት መቻል ዘላቂ በሆነ መልኩ ኑሮአቸው ይለወጣል፡፡
- ቴክኖሎጂዎች በእነርሱ አይን በቀላሉ ማየትና ማላመድ ይቻላል፡፡
- ሴቶች አቅማቸው ይጎለብታል፣ የቤተሰብ በምግብ እና በሥረዓተ-ምግብ ማረጋገጥ ይቻላል፡ :

# ምዕራፍ-5 የመስኖ ሰብሎች የገበያ ምርት/ኮሞዲቲ/ እሴትሰንሰለት አቀራረብ

ሀገራዊ የግብርና ኤክስቴንሽን ስትራቴጂ አርሶ/አርብቶ አደሩ ከኋላ ቀር አመራረት ተላቆ ወደ ገበያ ተኮር አመራረት ለማሸጋገር እና የግብርና ምርትን ለማሳደግና የአነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ኑሮ ለማሻሻል ገበያ መር የግብርና ልማት ስትራቴጂ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ አምራቾች፣ መንግስት፣ ምርምር እና የኤክስቴንሽን ተቋማት በዋናነት ያተኮሩት የተሻሻሉ ቴክኖሎችዎችንና መልካም ተሞክሮዎችን ማመንጨትና ማስተዋወቅ ላይ ይሁን እንጂ እሴት በሚጨምሩ እና በግብይት ስርዓት ላይ የተሰጠው ትኩረት አናሳ ነው፡፡ በሌላ በኩል አርሶ/አርብቶ አደሮቹ ለቤተሰባቸው ቀለብ ያህል በማምረት እያካሄዱ ያሉት ከእጅ ወደ አፍ የሆነ አመራረት ዘዴ የወደፊት እሳቤው ምርት መጨመር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ አርሶ/አርብቶ አደሮቹ ፍላጎት በእያንዳንዱ የአመራረት ዘዴ አሴት በሚጨምሩ በተለይም ከፍተኛ ገቢ በሚያስገኙት ኢኮኖሚያዊ የመስኖ ሰብል የገበያ ምርቶች/ኮሞዲቲ/ ላይ በርትቶ ከመስራት ዓመታዊ የቤተሰብ ፍጆታንና ገንዘብ ለሚያስፈልጋቸው አስገዳጅ ጉዳዮችን እንደ ግብርና አልባሳት የመሳሰሉ ወጪዎችን ማሟላት ላይ የተኮረ መሆኑ ነው፡፡

በመስኖ የማምረት ፍላጎት እያደገ የመጣው የተፈጥሮ አደጋንና እየጨመረ የመጣውን በተፈጥሮ ፈተናዎች የተሞላው ያልተለመደ የአየር ንብረት መዛባትን መቋቋም የሚያስችል ግብርናን ለማስፈን በመንግስትም ሆነ በአርሶ/አርብቶ አደሩ ዘንድ ትኩረት በማግኘቱ ነው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመስኖ ምርት እያደገ የመጣውን ያህል የእሴት ሰንሰለቱ በተገቢው ሁኔታ ያልተተገበረ እና አብዛኛው አርሶ/አርብቶ አደርም ሆነ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በእያንዳንዱ የአመራረት ተግባር ላይ ያላቸው አቅም ውስን ነው፡፡ በተጨማሪም ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የመስኖ ሰብሎች ምርት በዝናብ ከሚለማው ሰብል በበለጠ በገበያ ላይ ለቤተሰቡ ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኝ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የእሴት ሰንሰለትን ውጤታማነትንም የሚያጎለብት ሲሆን ተዋናዮችም ይበልጥ ትርፋማ ሆነው ምርታቸውን እንዲያሳድጉ እያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም ግልፅ፣ ተጨባጭ ለውጥ የሚያመጣ እና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው እና በገበያ ተፈላጊ የሆኑ በመስኖ የሚለሙ ሰብሎችን እንደሚከተለው ማዘጋጀት ይቻላል፡-

- ☞ በመስኖ ኤክስቴንሽን የአቀራረብ ዘዴ ከፍተኛ ዋጋ ላላቸው የመስኖ ሰብል ምርቶች/ ኮሞዲቲዎች/ ስኬታማ የአቀራረብ ዘዴዎችና ድጋፎችን በማስፋት የመስኖ አክሰቴንሽን ባለሙዎች እና የቀበሌ መስኖ ልማት ሠራተኞች በመስኖ ልማት በሚለሙ ሰብሎች ዙሪያ በቂ ዕውቀት እንዲኖራቸው የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማጠናከር፤

- ☞ በመስኖ በሚለሙ ስብሎች ጠንካራ የሆነ የገበያ ትስስር እንዲኖራቸው ተከታታይ እና ጠንካራ የገበያ ማስተዋወቅ ሥራዎችን በመስራት ከገበያ ተዋንያኖች ጋር

ትስስር እንዲፈጠር ማድረግ፤

☞ የተመረጡ መረጃ ማስተላለፊያ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም አርሶ/አርብቶ አደሩ፣ የቀበሌ መስኖ ልማት ሠራተኛው እና የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያው በቂ የገበያ መረጃ እንዲኖራቻው ማስቻል፤

☞ በግብርና ቴክኒክ ማሰልጠኛ ማዕከላት ሠልጥነው የሚወጡ ባለሙያዎችና የቀበሌ መስኖ ልማት ሠራተኞች በመስኖ በሚለሙ ሰብሎች አመራረት፣ በእሴት መጨመር እና በገበያ እሴት ሰንሰለት ዙሪ በቂ እውቀት ጨብጠው እንዲወጡ ማድረግ ስፈልጋል።

## 5.1 የእሴት ሰንሰለት ጽንሰ-ሀሳብ

የእሴት ሰንሰለት ሲባል ምርትን ከመነሻ ግብዓት አቅርቦት ደረጃ ጀምሮ የተለያዩ የማምረት ደረጃዎችን በማለፍ ገበያን መዳረሻ ለማድረግ ከግብዓት አቀራቢ እስከ ተጠቃሚ ድረስ  የሚደርሱ ተግባራት በቀላሉ ሊገለጹ የሚችሉበት ጽንሰ ሀሳብ ነው፡ ፡ የምርት ደረጃ የአካላዊ ለውጥ እና የተለያዩ አምራቾችና አገልግሎቶች ተሳትፎን የሚፈልግ ሲሆን ሰንሰለቱ ከምርት የሚወገዱትንም ያካትታል። በምርት ላይ ከባህላዊ የግል ትኩረት በተቃራኒ ጽንሰ ሀሳቡ የሚመነጨው በእያንዳንዱ ደረጃ እሴት መጨመር ላይ ሲሆን በዚህም ምርትን መንከባከብ የሰንሰለቱ አንዱ አካል ነው።

## 5.2 የእሴት ሰንሰለት ጽንሰ-ሀሳብና ጉዳዮች

ሀገራዊው ማክሮኢኮኖሚ፣ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ መተዳደሪያ ደንቦች፣ ስነ-ሥርዓቶች እና ተቋማዊ መሠረታዊ ነገሮች ማለትም ምርምር፣ አዳዲስ አሠራርና አስተሳሰብ፣ የሰው ሀብት ልማት እና ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶች አካባቢን የሚፈጥሩ ሲሆን በውስጡ ሁሉም ተግባራት ይከናወናሉ።

የእሴት ሰንሰለት በርካታ በውስጡ የተሳሰሩ ተግባራትንና ኢንዱስትሪዎችን ከብዙ ዓይነት የንግድ ድርጅቶች እንደ ሀገር የተለያዩ ክልሎችን ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ የተለያዩ አገሮችን በማካተት  የበለጠ ውስብስብ የመሆን አዝማሚያ አለው። ለአብነት በመስኖ ግብርና ነክ የምግብ እሴት ሰንሰለት የሚያጠቃልለው በማሳ ላይም ሆነ በገጠር መንደሮች እና በከተማ አካባቢ የሚከናወኑ ተግባራትን ነው። አነርሱም ግብዓት አቅራዎችን (ዘር፣ ማዳበሪያ፣ ኬሚካሎች፣የውሃ ማውጫ ቴክኖሎጂዎች፣ የመስኖ እርሻ መሳሪያዎች ወ.ዘ.ተ.)፣ የእርሻ ማሽነሪዎችን፣ እና ሌሎች እሴት ለመጨመር የሚያገለግሉ ቴክኖሎጅዎችን የሚፈልጉ ሲሆን በአያያዝ፣ በክምችት፣ በማምረት ሂደት፤ በማሸግ እና በማከፋፈል ተግባራት ይቀጥላል። ሌሎች መሠረታዊ ነገሮች ማለትም የሀይል አቅርቦት፣ መንገድ፣ አስፈላጊ አቅርቦቶች ወ.ዘ.ተ. የሰንሰለት አካባቢን የሚፈጥሩ ሲሆን የእሴት ሰንሰለት አፈጻጸም ላይ በጎ ተጽዕኖ ይፈጥራሉ።

## 5.3. የእሴት ሰንሰለት እና የገበያ መር የኤክስቴንሽን አቀራረብ አቅጣጫዎች

አሁን ያለውን የአመራረት ስርዓት ከኋላ ቀር አመራረት ዘዴ ወደ ገበያ መር ዘመናዊ ግብርና ምርት አመራረት ሂደት ለማሸጋገር በመስኖ ልማት የሚለሙ ሰብሎችን እሴት ሰንሰለት መተግበርና የገበያ መር ኤክስቴንሽን አሰራሮችንና አቅጣጫዎችን ተከትሎ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችንና የመስኖ ልማት ሠራተኞችን አቅም በማሳደግ አርሶ/አርብቶ አደሩ በገበያ ተፈላጊና ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን የመስኖ ሰብሎችን አምርቶ ምርትና ምርታማነቱ አድጎ ገቢው እንዲጨምር በማድረግ ቀጣይነት ያለውን የገበያ መር መስኖ ልማት መፍጠር ይቻላል፡፡ ስለሆነም በየደረጃው የሚገኙ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና የመስኖ ልማት ሠራተኞች የሚከተሉትን የገበያ መር መስኖ ኤክስቴንሽን አቀራረብ/አቅጣጫዎችን መከተል ይኖርባቸዋል፡-

- ☞ በየደረጃው የሚገኙ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በገበያ መር የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን እና በመስኖ ሰብሎች እሴት ሰንሰለት ዙሪያ በቂ የሆነ ግንዛቤ ጨብጠው አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማድረግ በተመረጡ ከፍተኛ ዋጋ ባለቸው የመስኖ ሰብሎች እሴት ሰንሰለት እና የገበያ መረጃ ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት፣ለቤተሰብ/ጥቃቅን መስኖ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች እና ለማህበረሰብ ኩሬ ተጠቃሚዎች እንዴት ተደራሽ ማድረግ እንደሚችሉ ስልጠና መስጠት፤

- ☞ የአከባቢ ስፔሻላዜሽንን እና ዳይቨርሲኬሽንን መሠረት ያደረገ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውንና በገበያ ተፈላጊ የሆኑ የመስኖ ሰብሎችን በጥራትና በብዛት በማምረት ለውጪ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ እንዲቀርቡ ማድረግ፤

- ☞ በመስኖ ሰብሎች እሴት ሰንሰለት የሚገኙ የገበያ ተዋንያኖችና የባለድርሻ አካላት ትብብርና ትስስር እንዲጠናከር ተከታታይነት ያለው የገበያ ማስተዋወቅ እና አቅማቸውን የማጠናከር ስራዎች መስራት እና በመስኖ እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚገኙ አካላት ትስስራቸውን ለማጠናከር የመስኖ ልማት መለሰተኛ መድረኮችን በመመስረት ማጠናከር ያስፈልጋል፤

- ☞ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም አርሶ/አርብቶ አደሩ፣ የቀበሌ መስኖ ልማት ሠራተኛው እና የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያው በቂ የገበያ መረጃ እንዲኖራቻው ማስቻል፤

- ☞ በግብርና ቴክኒክ ማሰልጠኛ ማዕከላት ሠልጥነው የሚወጡ ባለሙያዎችና የቀበሌ መስኖ ልማት ሠራተኞች በመስኖ በሚለሙ ሰብሎች አመራረት፣ በእሴት መጨመር እና በገበያ እሴት ሰንሰለት ዙሪያ በቂ እውቀት ጨብጠው እንዲወጡ ማድረግ፤

- ☞ ከትናንሽ የመንደር ገበያዎች ጀምሮ እስከ ትላልቅ ገበያዎች ያሉት የመስኖ እሴት ሰንሰለት የገበያ ተዋንያኖችን በመለየት ወቅቱና ገበያው የሚፈልገውን የመስኖ ሰብሎች ምረቶችን በጥራትና በብዛት አምርቶ ለማቅረብ ሁሉ አቀፍ ዕቅድ ማቀድ፤

☞ ከአርሶ/አርብቶ አደር ማሳ ጀምሮ እስከ ሸማቹ ህብረተሰብ ድረስ የገበያ ማዕከላትን በመፍጠር የመስኖ ሰብል ምርቶችን የገበያ ትስስር መፍጠር፤



ስዕል-11፡-የመስኖልማት ውጤቶችን በገበያ ማስተሳሰር ዘለቂታዊ ልማትን ያጎለብታል ፡፡

☞ የወጣቶችና የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በመስኖ ሰብሎች እሴት ሰንሰለት አሰራር ላይ የስራ እድል በመፍጠር ገቢያቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ፤

☞ በመስኖ ሰብሎች ምርት ላይ እሴት በመጨር ለአነስተኛ እና ለከፍተኛ አግሮፕሮሰሲግ ኢንዳስትሪዎች ጥሪ እቃዎችን ለማቅረብ እና የገበያ ሰብሎችን ምርትን ገበያ ላይ በማውጣት የውጪ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ፤

☞ ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ ለመስኖ ግብዓትና ቴክኖሎጂ አቅራቢ የግል ድረጅቶች እና ማህበራት የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያው ከብድር ተቋማት ጋር ማስተሳሰር አለበት፤

☞ የኮንትራት እርሻ አገልግሎት በመፍጠር የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደር ሽጦ ወደ ማምረት የአሰራር ሂደት እንዲገባ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያው እና የቀበሌ መስኖ ልማት ሠራተኛው አርሶ/አርበቶ አደሩን መደገፍ እና ማብቃት፤

☞ ገበያን መሠረት ያደረገ የመስኖ ሰብሎች እሴት ሰንሰለት መልካም ተሞክሮዎችን በመለየት እንዲሰፋ ማድረግ፣

☞ አርሶ/አርብቶ አደሩ በቀላሉ ሊጠቀምባቸዉ የሚችሉ የሜካናይዜሽን ማሽነሪዎችና ሌሎች ከሜካናይዜሽን ተግባራትጋር ተያያዥ ተግባራተን የማስተዋወቅና የማስፋፋት ስራ መስራት፣

## 5.4 በመስኖ ልማት የእሴት ሰንሰልት እና የገበያ መር የኤክስቴንሽን

### 5.4.1. የእሴት ሰንሰለት ትንተና

የእሴት ሰንሰለት ትንተና በአመራረት ላይ ከተለመደው ያነሰ አተያይ በተሻለ በመጓዝ በተዋንያን መካከል ያለውን ግንኙነትና ትብብር እንዲሁም የንግድ ሥራንና ፖሊሲውን አጥብቆ ይመረምራል፡፡ በዚህም እያደገ የመጣውን ትስስር የማይቀበሉ ባህላዊ የሴክተር ዳሰሳ ጥናቶች እና መደበኛ ያልሆኑ አሠራሮች ላይ ያሉ ውስንነቶችን ይቀርፋል፡፡

የእሴት ሰንሰለት ትንተና በተለያዩ መስሪያ ቤቶች እና አጋር አካላት ያሉ ተዋንያንን በማካተት ተለዋዋጭና እያደገ የመጣውን የኢኮኖሚ፣ ድርጅታዊና አስገዳጅ ተግባራትን ግልጽ ያደርጋል፡፡ መሰናክሎች እንዴት እንደሚፈጠሩና ችግሮች እንዴት እንደሚሰራጩ ለመረዳት የጠበቀ ግንኙነት አስፈላጊ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ እይታ ተወዳዳሪነትን ያገናዝባል፡፡ የእሴት ሰንሰለት ትንተና ጥንካሬንና ድክመትን በማሳየት የጋራ እይታን እንዲያሳድጉና ሰንሰለቱ እንዴት ተፈጻሚ ሊሆን እንደሚገባ እንዲሁም ያለውን በትብብር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት በመለየት ረገድ ተዋናዮች እንዲሳተፉ ያግዛል፡፡ ይህም በሚከተለው ስዕላዊ መግልጫ ተመልክቷል፡፡




ምስል- 5፡-የእሴት ሰንሰለት ትስስር ሥዕላዊ መግለጫ

### 5.4.2. የእሴት ሰንሰለት ትንተና አስፈላጊነት

የእሴት ሰንሰለት ትንተና ጠቃሚ የምዘና መሳሪያ ሲሆን ሁሉ አቀፍ ኢንዱስትሪ እንደገና የመደራጀትን አዝማሚያ ለመረዳትና የለውጥ ወኪሎችንና ለፖሊሲ የቴክኒክ ጣልቃ ገብነት አስገዳጅ ጉዳዮችን ለመለየት ያግዛል፡፡ ለተሻለ አላማ በተለያዩ ዘርፎች የእርዳታ ለጋሾችና የልማት አጋዥ ድርጅቶች ድጋፍ የእሴት ሰንሰለት ትንተናን መሠረት እያደረገ የመሆኑ ጉዳይ ማለትም በንግድ አቅም፣ በንግድ ድርጅቶች ተወዳዳሪነት፣ በገቢ ክፍፍልና በእሴት ሰንሰለት ተሳታፊዎች መካከል ባለ ፍትሀዊነት ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡

## 5.4.3. በመስኖ ሰብል የገበያ ምርት/አቅርቦት እሴት ሰንሰለት ትንተና

*ለመስኖ ሰብሎች እሴት ሰንሰለት ምቹ ሁኔታዎች:-* በሃገራችን ያለውን በቂ የሆነ መሬትና ጉልበትን በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል እንዲሁም ሀብትን/ካፒታልን/ በቁጠባ ሥራ ላይ በማዋል የግብርናውን ምጣኔ ሀብት/ኢኮኖሚ/ ለማሳደግ አመች የሆነ በገጠሩ ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚ ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በመቅረጽ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂው ዓላማ ነጻ የኢኮኖሚ ሥርዓትን እውን ማድረግ፣ በዚህም በምርት ሥርዓቱ ውስጥ የግብይት ሰንሰለት ተዋንያን በማምረት ሥራ አሰራሩ የማምረት፣ ሀብታቸውን የማንቀሳቀስና የማስተላለፍ፣ ምርታቸውን በፈለጉት ዋጋ እና በየትኛውም ቦታ የመሸጥ፣ መብታቸውን በማስከበር ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙትን ጥረት እውን ማድረግ ነው፡፡ በኢኮኖሚ ልማቱ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ደረጃ በመስኖ የግብርና ኢኮኖሚ ላይ ምናልባት ሊኖር የሚችለውን የግብዓትና የምርት ውጤት ላይ የገበያ ውድቀት እንዳይኖር የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም ከግለሰብ ፈጻሚ አካላት አቅም በላይ ከሆኑት የመስኖ መሠረተ ልማት ሥራዎች ላይ መንግስት መዋዕለ ንዋይ ይመድባል እንዲሁም ስትራቴጂያዊ የግብዓት አቅርቦት ማለትም ማዳበሪያና የምርምር አገልግሎት ላይ ይደገፋል፡፡ በአጠቃላይ ለዝቅተኞችም ሆነ የግብርና ምርትን ወደ ውጭ ላኪዎች የሚያመቻች የገንዘብ ፖሊሲ በሀገሪቱ ተስማሚ የመስኖ ሰብል የገበያ ምርት/ኮሞዲቲ/ የእሴት ሰንሰለት እንዲኖር በማድረግ ረገድ በክልሎች የግብርና መዋዕለ ንዋይ ፍሰት ላይ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ቁጥጥርን በሚመለከት የግብርና ሚኒስቴር፣ የጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን በተቋም ደረጃ ተቋቁመው የመስኖ ምርት በተገቢው እንዲመረት በማድረግ ለመስኖ የገበያ ምርት/ኮሞዲቲ/ የመዋእለ ንዋይ ፍሰት እና የግብዓት ቁጥጥርን ያካሂዳሉ፡፡ የደረጃዎች ቁጥጥር አገልግሎት እና የእጽዋት ጤና ክሊኒኮች የንጽህና ቁጥጥር (ፋይቶ ሳኒታሪ) አገልግሎት እንዲሰጡ የተቋቋሙ ተቋማት ሲሆኑ ውጤታማና ብቃት ያለው የእሴት ሰንሰለት እንዲሰፍን የሚያስችሉ ናቸው፡፡

*ተቋማትን ማመቻቸት:-* በክልል መንግስታት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ለመስጠት፣ ለመስኖ መሠረተ ልማት እና የተቋሚት አስተዳደር የመስኖ ሂደት/ ዳይሬክቶሬት/ አቋቁመዋል፡፡ በመስኖ ሰብል ምርት ሂደት ላይ ክልሎቹ በዕቅድ፣ በግብዓት ፍላጎት መረጃ አሰባሰብ፣ በአቅርቦትና በማከፋፈል ረገድ የመስኖ ልማትን እያሳለጡ ይገኛሉ፡፡ የክልል ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ተቋማዊ አደረጃጀት ከክልል እስከ ወረዳ የተዘረጋ ሲሆን የማስተባበር፣ በዩኒየኖችና የማከፋፈል አገልግሎት በሚሰጡ ማህበራት አማካኝነት የመምራትና የግብዓት ፍላጎትንና አቅርቦትን የመቆጣጠር ሀላፊነት አለበት፡፡

የክልል ግብርና ቢሮዎች እስከታች በቀበሌ ደረጃ የተረጋጋ የኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲሰፍንና የግብዓት አቅርቦትና ስርጭት ለማስተባበር አስቻይ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ተቋም ነው፡፡ የእጽዋት ክሊኒክ እና ተለያዩ የግብርና ላቦራቶሪ ማዕከላት እንደ ተቋም የተቋቋሙ ሲሆን በመስኖ ሰብል ምርት ውጤታማና ቀልጣፋ ሥራዎችን የመፈፀም ትልቅ ሚና አላቸው፡፡

ንግድና ገበያ ልማት ተቋም አገልግሎት በመስጠት ረገድ የሚሠራ፣ በመስኖ ሰብል ምርት ንግድ ላይ ተዋንያን በነጻ እንዲገቡና እንዲወጡ የሚያስችል ተቋም ነው፡፡ ይህ ነጻና ቀልጣፋ የሆነ የአመራረት ዘዴ ከፍተኛ ምርት በማስገኘት የመስኖ ሰብል የገበያ ምርትን/ኮሞዲቲ/ ከፍ ለማድረግ የእሴት ሰንሰለት ተዋንያንን አዲስ ሀሰብ እና አሠራር ያበረታታል፡፡ እንደ መሬት እና ሌሎችም የመስኖ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት የመሳሰሉ የመስኖ ሀብት የባለቤትነት መብቶች፣ የበለጠ ቀልጣፋ የሆነ ሰንሰለትን በማስፈን የመስኖ ልማትን እያበረታታ ነው፡፡

የአርሶ/አርብቶ አደር ቅንጅታዊ አሠራር ማለትም የልማት ቡድን እና አንድ ለአምስት አደረጃጀት ጠቃሚ ተቋማት ሲሆኑ የመስኖ ልማት ፍላጎትን ያሳድጋል፤ የአርሶ/አርብቶ አደር አሠራር ችሎታን ያጎለብታል፤ የእሴት ሰንሰለትን በበለጠ ቀልጣፋ በማድረግ በማምረት ሂደት ሞዴል አርሶ/አርብቶ አደሮች ለሌሎች አርሶ አደሮች ተሞክሯቸውን እንዲያስተላልፉ ያደርጋል፡፡

**የመስኖ ሰብል ምርት የእሴት ሰንሰለት ልማት፡-** የመጀመሪያው የመስኖ ሰብሎች የእሴት ሰንሰለት አርሶ/አርብቶ አደሮችን ለመስኖ ግብርና ልማት ማነሳሳት ላይ ይነሳል፡ ፡ በዚህ ደረጃ አርሶ/አርብቶ አደሮች ያላቸውን ሀብት በመስኖ ልማት ላይ እንዴት ሥራ ላይ እንደሚያውሉ ይነሳሳሉ፡፡ በመስኖ ግብርና ለማምረት ከተነሳሱም በኋላ ከፍተኛ ገቢ ማግኘት በሚያስችላቸው የሰብል አመራረት ላይ ያቅዳሉ፡፡ በተጨማሪም የመስኖ ሰብል ለማምረት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በእያንዳንዱ ደረጃ በቅድሚያ የሚታቀዱ ሲሆን እነርሱም፡-

**ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት፡-** በአርሶ/አርብቶ አደሩ ፍላጎትና የመሬት ስፋት ላይ ተመስርቶ የግብዓት ፍላጎት መረጃ ተሰብስቦ ይጠቃለልና በመስኖ ልማት ላይ ለተሰማሩ አርሶ/አርብቶ አደሮች በዝግጅት ምዕራፍ እንዲዘጋጁ ይቀርብላቸዋል፡፡

**የመስኖ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ማሰልጠን፡-** በአርሶ/አደሮች የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ላይ በመመስረት ከማምረት በፊት ወይም ከዝግጅት ምዕራፍ በፊት በማሳ ላይ እና በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ስልጠና ይሰጣል፡፡ በዚህ ደረጃ አርሶ/አርብቶ አደሮች የሚሰለጥኑት በሚከተሉት ቅደም ተከተሎች መሠረት የማልማት ማነቆ/ችግሮችን ለመቅረፍ ነው፡፡

- ውጤታማ እና ቀልጣፋ የእሴት ሰንሰለት አሠራርን የሚያደናቅፉ፣ የመስኖ ልማትን አፈፃፀምን ዝቅ የሚያደርጉ ወይም መሠረታዊ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን አርሶ/አርብቶ አደሮች ይለያሉ፤
- የመስኖ ልማት አሠራሮችን የሚያደናቅፉ የመሠረታዊ ማነቆዎች ምክንያት አርሶ/አርብቶ አደሮች ይለያሉ፤
- በስልጠና ወቅት በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ እና በአስተዳደር የሚንፀባረቅ፣ በእሴት ሰንሰለት መሠረታዊ ማነቆ የሆነውን ተጽዕኖ አርሶ/አርብቶ አደሮቹ ያስሳሉ/ይመረምራሉ፤

- በመጨረሻም በአርሶ/አርብቶ አደሮች ተግባራዊ እና ውጤታማ ሊያደረግ የሚችል ተገቢ መፍትሄ ላይ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ሊደረግ ይገባል፡፡

ከላይ የተለዩ ችግሮች ላይ በመመስረት በአመራረት ዘዴ ላይ የእሴት ሰንሰለቱ ውጤታማና ቀልጣፋ ይሆን ዘንድ ለሁሉም ማነቆዎች አርሶ/አርብቶ አደሮች መፍትሄ እንዲያስቀምጡ ይፈለጋል፡፡

### 5.4.4. እሴት ሰንሰለትን የተከተለ የመስኖ ልማት ዕቅድ

የመስኖ ልማት ዕቅድ አርሶ/አርብቶ አደሮች ከሰለጠኑ እና ለመስኖ ልማት ፍላጎት ከተፈጠረ በኋላ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በእያንዳንዱ አርሶ/አርብቶ አደር በፍላጎት ላይ የተመሠረተ እና ገበያን መሠረት ያደረገ የመስኖ ዕቅድ ተዘጋጅቶ አሳታፊ እንዲሆንና በአፈጻጸም ወቅት በቀላሉ ለመከታተልና ለመገምገም ለአንድ ለአምስት እና ለልማት ቡድን ይቀርባል፡፡

**የመስኖ እሴት ሰንሰለት ደካማ ግንኙነቶችና በቀጣይ መሰራት ያለባቸው ተግባራት፡**
- ይህ ሰንሰለት ለሌሎች የመስኖ ሰብል ምርቶች ቀሪ የእሴት ሰንሰለት ውጤታማና ቀልጣፋ አሠራር መሠረት ነው፡፡ እንደሚታወቀው በእያንዳንዱ ደረጃ የሚፈጠረውን እሴት የሚወስነው የመስኖ ምርት ጥራትና መጠን እንዲሁም የጉልበትና ሌሎች ሀብቶችን ማንቀሳቀስ፣ የማምረት ማነቆዎችን መቅረፍ የሚያስችል አቅም የሚፈጥር የአርሶ/አርብቶ አደሮች የስልጠና አሰጣጥ ደረጃ፣ ውጤታማ የሆነ የግብዓት አቅርቦትና ስርጭት አሰራር ደረጃ እና በፈጻሚው ባለቤትነት የመስኖ ልማት ዕቅድ አሠራር ነው፡ ፡ በሌላ እሴት በሚጨምር ሰንሰለት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር የዚህ ሰንሰለት ደካማ ግንኙነት እንደሚከተለው ተለይቷል፡-

- ☞ በመስኖ ልማት የአርሶ/አርብቶ አደሩን ተሳትፎ እስከ መጨረሻው ለማሳደግ ሀብትን በማንቀሳቀስ ረገድ በአስተዳደሩ በኩል የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን፤
- ☞ ለውጤታማ አቅርቦትና ስርጭት የመስኖ ግብዓት ፍላጎት ጥሬ መረጃ ከግለሰብ አርሶ/አርብቶ አደር ፍላጎት የፈለቀ አለመሆን፤
- ☞ የግብዓት አቅርቦት አሰራር ለአርሶ/አርብቶ አደሩ ከፍተኛ ፍላጎት በጊዜ፣ በቦታ እና በዋጋ አትጋቢ ምላሽ የሚሰጥ አለመሆን፡፡ ይህም አርሶ/አርብቶ አደሩ ህጋዊነቱ ካልተረጋገጠባቸው ገበያ እንደ አማራጭ እንዲመለከት ማድረጉና በመጨረሻም ከደረጃው በታች ወደ ሆነ እና ወደማይፈለግ ግብዓት ማምራትን ማስከተሉ በዚህም ደካማ የእሴት ሰንሰለት ምርት አሠራር መስፈን፤
- ☞ የአመራረት ችግርን ማለትም የተነሳሽነት፣ የክህሎት እና የአቅርቦት ችግርን መቅረፍ የሚያስችል የአርሶ/አርብቶ አደሮች ስልጠና ውጤታማ ባለመሆኑ የእሴት ሰንሰለት አንቀሳቃሽ ሞተር ክፍልን ደካማ ማድረጉ፤
- ☞ በአጠቃላይ የዕቅድ አካል የሆነው የግለሰብ አርሶ/አርብቶ አደር የመስኖ ልማት ዕቅድ

ከግለሰቡ የመስኖ ልማት ፍላጎት የመነጨ አለመሆን፡፡ ይህ አኳኋን የአፈጻጸም ክፍሉን ደካማ ማድረጉ እና በምርት ሰንሰለት የተፈጠረውን እሴት ዝቅ አድርጎ መታየቱ፤

**የድህረ-ምርት አያያዝ እሴት ሰንሰለት፡-** ይህ የሰብል ምርት አሰባሰብ የመነሻ ደረጃ ሲሆን በዚህ ላይ ሰብሉ ከተሰበሰበ በኋላ ሰንሰለት ይጀምራል፡፡ የሰብል ምርት አሰባሰብ ዘዴ እና ጊዜ በምርት እሴትና በመጠን ላይ ወሳኝ የሆነ ሀይል አለው፡ ፡ የማሰባሰብ ዘዴው በወሳኝነት ሰብሉ ከለማ በኋላ የመስኖ ምርት ብክነት ላይ ወሳኝነት አለው፡፡ በሰንሰለቱ ከሰብሉ ከለማ በኋላ ያሉ አሠራሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ☞ የሰብል ምርቶችን የማሰባሰቢያ ጊዜ መወሰን፤
- ☞ ተገቢውን የመሰብሰቢያ ዘዴ እና የመሰብሰቢያ መሣሪያዎችን መወሰ፤
- ☞ በተፈለገው መስፈርት መሠረት የምርት ደረጃ ማውጣት፤
- ☞ በደረጃ የተለየውን በመልክ በመልኩ ወደሚቀመጥበት ቦታ ማጓጓዝ፤
- ☞ ለምርቱ ደረጃ ማውጣት፤
- ☞ ምርቱን መለካት/መመዘን/፤
- ☞ በተገቢ ቦታ ላይ ማከማቼት፤
- ☞ ለንግድ በሚፈለገው መጠን ማሸግ፣ ማጓጓዝ እና ወደ ተጠቃሚ ማድረስ ናቸዉ

**የድህረ-ምርት አያያዝ እሴት ሰንሰለት ደካማ ግንኙነቶች፡-** ይህ የእሴት ሰንስለት ግንኙነት ከሰብል ልማቱ በኋላ በርካታ የምርት ብክነት የሚከሰትበት ሂደት/ቦታ ነው፡፡ ለምርት ብክነቱ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስድበት ምክንያት በዚህ የእሴት ሰንሰለት አምራቹም ሆነ አማካሪ ባለሙያዎቹ በአመራረት የአሠራር ሂደት ላይ ያላቸው ትኩረት ውስን መሆኑ ነው፡፡ ብዙ ተመራማሪዎች፣ ፖሊሲ አውጪዎች፣ አምራቾች እና ልማትን የሚደግፉ ተቋማት ትኩረት የሚያደርጉት ከምርት ማሰባሰብ በፊት ባለ ሂደት ላይ ሲሆን ብዙ ምርት እየባከነ ያለው ግን ከምርት ማሰባሰብ በኋላ ነው፡፡ ስለሆነም በተለይ በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ሂደት መከናወን ስላለባቸው የመስኖ እሴት ሰንሰለት ሥራዎች ላይ ልዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በአጋር አካላት ዘንድ ትኩረት የሚሹ ደካማ ግንኙነቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ☞ በተሻለ ጥራት ለማምረት የምርት ማሰባሰቢያ ዘዴ እና ጊዜ በመርሀ ግብር/በዕቅድ/ እየተመራ አለሆን፤
- ☞ በምርት ማሰባሰብ ሂደት ምርቱ እንዳይበላሽ የሚያግዙ የተሸሻሉ የምርት ማሰባሰቢ መሣሪዎች ማለትም ኬሻ፣ የአትክልት ማጓጓዣ ሳጥን የመሳሰሉት ተስማሚ ያለመሆናቸው፤

- ☞ በመስኖ ምርት ማሰባሰቢያ መዕከላት፣በጊዜያዊ ምርት ማከማቻ መገዝኖች እና በአርሶ/አርብቶ አደር ማሳ አካባቢ ምርቱ የሚሰበሰብበት ቦታ የንፅህና ጉድለት ያለው መሆኑ ለመስኖ ምርት እሴት ሰንሰለት ግንኙነት ደካማ ግንኙነት መነሻ በመሆኑ በመስኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያውና ቀበሌ መስኖ ልማት ሠራተኛው ለአምራች አርሶ/አርብቶ አደሩ ምርቱን በንፅህና እንዲያሰባስብና እንዲያከማች የምክር አገልግሎት ሊሰጠው አለመስጠት፤

- ☞ በማሳ ላይ ስምምነት በተረደረሰበት የጥራት ደረጃ መሠረት ዋጋ ለመደልደል ምርትን በዓይነት ለመለየትና ደረጃ ለማውጣት የጥራት ደረጃ መመዘኛ/መለኪያ/ አለመኖር፤

- ☞ በመጫንና በማውረድ ሂደት በምርት ላይ አደጋ የሚደርስ መሆኑ፤

- ☞ ማሳ ላይ በምርት ጥራት ደረጃ አምራቹን በተሻለ ለማበረታታት የሚያስችል የተለመደ አሠራር አለመዘጋት፤

- ☞ የመሠረተ ልማትና የገበያ ምቹ ሁኔታዎች በሚገባ አለመልማት፤

- ☞ ማሳ ላይ የምርት ሽያጭ በጥራት ደረጃ መሠረት በአግባቡ ያለመታገዝ እና የምርት ክምችት ሲኖር ገዥውን ብቻ በሚጠቅም አግባብ በግምት መገዛቱ፤

- ☞ በምርቱ ጥራት ደረጃ መሠረት ለምርት እሴት ዋጋ ለማስቀመጥ/ለማውጣት/ ደረጃ ማውጣትና ምርትን በእያይነቱ መመደብ በአምራቹ በኩል አለመለመዱ፤

- ☞ በገጠሩ አካባቢ የተለያዩ ማሳለጫ ምቹ ሁኔታዎች ባለመኖራቸው በምርት ላይ እሴት ለመጨመር በተቋምም ሆነ በግል ሴክተሩ የማሸግ እና ከፊል የምርት ሂደት/ፕሮሰሲንግ /አገልግሎቶች አለመኖራቸዉ፡፡

## 5.4.5. የኢንዱስትሪ ሂደት/Proccessing/

የመስኖ ሰብል ምርት እሴት የመጨመር ሂደት በዋናነት የሚከናወነው በዚህ ሰንሰለት ሲሆን አብዛኛው እሴት የመጨመር አሠራር የሚፈፀመው በዚህ ሂደት ይከናወናል፡፡ በኢንዱስትሪ ሂደት የሚከናወኑ ሥራዎች የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው፡-

- ☞ ከጀምላ ሻጮችም ሆነ ከቸርቻሪዎች ጥሬ እቃ በብዛት መግዛት፤

- ☞ ኢንዱስትሪው ወደ ሚገኝበት ቦታ ምርት ማጓጓዝ፤

- ☞ በፊት የገባውን ቀድሞ/በቅደም ተከተል በማስወጣት ዘዴ መሠረት አድርጎ ምርትን ማከማቼት፤

☞ ኢንዱስትሪው በአስቀመጠው የጥራት ደረጃ መሠረት ለምርቱ እንደገና ደረጃ ማውጣት፤

☞ ምርቱ በኢንዱስትሪ ሂደት እንዲያልፍ ማድረግ፤

☞ የኢንዱስትሪ ውጤቱን ደረጃ ማውጣትና በየዓይነታቸው መከፋፈል፤

☞ የምርት ውጤቱን ማሸግ፣ማከፋፈል እና ማስተዋወቅ፡፡

**በኢንዱስትሪ ፕሮሰሲንግ እሴት ሰንሰለት ደካማ ግንኙነቶች፡-** በሀገራችን የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ሂደት ገና በጅምር ደረጃ ላይ ነው፡፡ የግብርና ኢንዱስትሪ ሂደት በመስኖ ሰብል የገበያ ምርት/ኮሞዲቲ/ ላይ እሴት ለመጨመር ያለዉ አቅም ውስን ነው ለዚህ ምክንያቱ የኢትዮጵያ ግብርና ገና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ደረጃ ላይ መሆን እና ለቀጣይ ሂደት የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪን ለመሳብ ማለትም ለገበያ የሚሆን ትርፍ ምርት በቂ አለመሆኑ ነው፡፡ በመስኖ ሰብል ልማት ዘርፍ ወደ ገበያ ምርት ለማቅረብ የሚመረትባቸውና የማይመረትባቸው ወቅቶች አሉ፡፡ በዋና የመስኖ ምርት ወቅት ከፍላጎትም በላይ ብዛት ያለው አቅርቦት ስለሚኖር የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ዋጋ ይወርዳል፡፡ የአደገ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ባለመኖሩ ከፍላጎት በላይ በብዛት የቀረበው ምርት አንድም በዝቅተኛ ዋጋ ይሸጣል አሊያም በማሳ ውስጥ እንዳለ ይቀርና የአምራቹን ሞራል ከሚገባው በላይ ይጎዳል፡፡ ይሁንና በማይመረትበት ወቅት የመስኖ ሰብል ምርት ዝቅ ስለሚል በአንጻሩ አቅርቦቱ ከፍላጎት በታች ስለሚሆን ዋጋው ተመልሶ ጣራ ስለሚነካ የምርቱን ተጠቃሚ ሞራል ይነካል፡፡ ከተመረተ በኂላ በክምችት ላይ እንዳሉ ቶሎ የመበላሸት ባህሪ ያላቸው ምርቶች አርሶ/አርብቶ አደሩ ክስረቱን መቋቋም እንዳይችል ያደርጋሉ፤ ይህም ችግሩን አባብሶ ዘላቂ የሆነ የምርት አቅርቦት እንዳይኖር እና በገበያ ላይ የዋጋ መዋዠቅ እንዲከሰት ያደርጋል፡፡ ይህ ሁኔታ ዘላቂ የመስኖ ልማት እንዳይኖር የሚያደርግ ሲሆን መስኖ ልማት ላይ የተሰማራው አርሶ አደር ቀደም ሲል በአገኘው ዋጋ ማምረቱን ለመቀጠልም ሆነ ለማቆም ይወሰናል፡፡ ቀደም ሲል ያገኘው ዋጋ ዝቅተኛ ከሆነ የመስኖ ልማቱን ወደ ኂላ ይመልሰዋል፣ በአንጻሩ የተሻለ ዋጋ ከነበረ የመስኖ ልማቱን ያበረታታዋል፡፡ በመስኖ ልማት ይህ የችግር አዙሪት የሚከሰተው የመስኖ ምርት በሌለበት ወቅት በፋብሪካ የተዘጋጀውን ምርት የሚያቀርብ የመስኖ ሰብል ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ እጥረት በመኖሩ ነው፡፡

በዚህ ሰንሰለት ሌላው ውስንነት የትኛው መጀመሪያ መምጣት እንዳለበት አለመገንዘብ ነው፡፡ የመስኖ ሰብል ምርት መጀመሪያ ከመጣ በቅድሚያ አምራቹ ገበያ በማጣቱ ይጨነቃል፡፡ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪው መጀመሪያ ከመጣ በቅድሚያ በቂ ጥሬ እቃ ስለማያገኝ ይቸገራል፡፡ በመሆኑም የእሴት ሰንሰለት ተዋንያን ይህን ያለመጣጣም ችግር መፍታት ይኖርባቸዋል፡፡

## 5.4.6 የመስኖ ምርት ስርጭትና ግብይት

ስርጭት፡- የመስኖ ሰብሎች ምርት ፍላጎት በሀገሪቱ ሁሉም አካባቢዎች በተመሳሳይ መልኩ እኩል ስርጭት የለውም፡፡ ይህም የሆነበት በአገሪቱ አሁን እየተመረቱ የሚገኙት አብዛኛው የመስኖ ልማት ምርቶች ወዲያው ሊበላሹ የሚችሉ እና የትራንስፖርት እና ዘለቄታው የገበያ ትስስር የሌላቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም ምርቱ ወይም የመስኖ እርሻ ማሳው ከሆነ ከተማ ሩቅ ሆኖ እያለ ሳይሆን የአትክልትና ፍራፍሬ ፍላጎት በአካባቢው እንኳን በቤት ውስጥ ተጠቃሚዎች፣ በሆቴሎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ በማረሚያ ቤቶች ወ.ዘ.ተ. ከፍተኛ ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህ ሁኔታ ሲፈጠር በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት የእሴት ሰንሰለት አሠራርን ለመዘርጋት የስርጭት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ማቋቋም ጠቃሚነት አለው፡፡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ስርጭት የገበያ ፍላጎት መረጃን ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ምርት የት መሰራጨት እንዳለበት ከተመረተበት ወደ ተጠቃሚው ከመጓጓዙ በፊት መረጃው ያስፈልጋል፡፡በዚህ ላይ ደላላዎች ጅምላ ሸማቾችንና ጅምላ ሻጮችን በማገናኘት ረገድ ለስርጭት ማሳለጥ አገልግሎት ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ሰንሰለት ተያይዘው የሚፈፀሙ ስርጭት ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ☞ ሊኖሩ ስለሚችሉ ሸማቾች መረጃ ተዳስሶ ለሁሉም የመስኖ ምርት አምራቾች ይሰጣል፤
- ☞ የትኛው ምርት? በምን ያህል መጠን? በማን? የት? እና መቼ? ይፈለጋል? ለሚሉ ጥያቄዎች በአሰራጮች ዘንድ መታወቅ አለባቸው፤
- ☞ በምርት ማሰባሰቢያ ቦታ ላይ መጫኛና ማውረጃ መዘጋጀት አለበት፤
- ☞ በማሳ መግቢያ አካባቢ በየዓይነቱ ለመለየት፣ ደረጃ ለማውጣት፣ ለመመዘን፣ ለማሸግና ለመጫን ጊዜያዊ ማከማቻ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

ግብይት፡- በተለያዩ ደረጃዎች ማለትም ከሰብል ማምረት በፊት በእርሻ ማሳ፣ ከምርት በኋላ በማሳ መግቢያ አካባቢ፣ ከመለየትና ደረጃ ከማውጣት በኋላ በጊዜያዊ ማከማቻ ቦታ፣ በማዕከላዊ ገበያ አጠቃላይ ሽያጭ፣ የተሟላ ሽቀጣሸቀጥ መገበያያ ሱቅ፣ በችርቻሮ መልክ በመንገድ ዳር መገበያያ፣ የመስኖ ሰብል ምርት ግብይት ይካሄዳል፡፡ በግብይት የእሴት ሰንሰለት የተወሰኑ አሠራሮች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ☞ የሚጠበቁ ሸማቾች ወይም ጅምላ ሸማቾች ትክልትና ፍራፍሬ ከመመረቱ በፊት በአንድ ላይ ወደ ማሳ በመሄድ የዋጋ ድርድር ያደርጋሉ፤
- ☞ የምርቱን ገዢዎች ጥራቱን ለማስጠበቅ ሲሉ በማሳ ላይ ግብይት በመፈፀም ምርቱን ይሰበስባሉ፤
- ☞ በማሳ ላይ ምርቱ በደረጃ ይለያል፤
- ☞ ቸርቻሪዎች ከጅምላ ሻጩ/አከፋፋይ ወደሚገዙበት ወደ ማዕከላዊ ገበያ ምርቱ ይጓጓዛል፤

☞ የተወሰነ ምርት ተጠቃሚው በመጨረሻ ምርቱን በሚያገኝበት በሸቀጣሸቀጥ ሱቅ ይሸጣል፡፡

**በግብይት ሂደት የእሴት ሰንሰለት ደካማ ግንኙነት፡-** የዚህ ሰንሰለት ደካማ ግንኙነት በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ገበያ ላይ በመካከል ያሉ አገናኞችን ወይም ደላሎችን በማዛባት በበለጠ የከፋ ያደርገዋል፡፡ የተለመደው የገበያ አሠራር የሚሸፍነው የገበያ ፍላጎትና አቅርቦት ምርቱን በሚያበረታታና ተጠቃሚውንም ደህንነት በማገናዘብ በተመጣጣኝ ዋጋ በተገቢው ሲከናወን ነው፡፡ በመስኖ ሰብሎች ግብይት በአሁኑ ሰዓት ያሉ ትልቅ እንቅፋት የሆኑ የተወሰኑ ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፡-

☞ በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ግብይት አምራቹን የሚያበረታታና የተጠቃሚውን ደህንነት ያገናዘበ ተመጣጣኝ ዋጋ ለማስቀመጥ በሚገባ በስምምነት ላይ የተደረሰበት ደረጃውን የጠበቀ ምርት አለመኖር፤

☞ በገጠር የአትክልትና ፍራፍሬ ገበያ ላይ የተመሰከረለት/ተአማኒ ሚዛን አለመኖር፤

☞ የዋጋ መረጃ ፍሰት ችግር፤

☞ የደላሎች አገልግሎት በተሻለ አኳኋን/ሥርዓት/አለመኖር፤

☞ አቅራቢዎችና ተጠቃሚዎች የገበያ ውድድርን ለመፍጠር እርስ በእርስ በደንብ ያለመተዋወቅ፤

☞ አዲስ ነገር ማስተዋወቅና የማስታወቂያ አገልግሎት የተለመደ/የጋራ/ አለመሆን፤

☞ ለተመጣጠነ ዋጋ በየቀኑ ጨረታ የሚካሄድበት በሚገባ ደረጃውን የጠበቀ የህዝብ ገበያ ምቹ ሁኔታዎች አለመኖር፤

☞ የመስኖ ሰብል ምርቶች/ኮሞዲቲ/ ወደ ጎረቤትና ሌሎች ሀገራት ማለትም ወደ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ እና ደቡብ ሱዳን ለመላክ የውጭ ገበያን የማስተዳደር ሲስተም አለመኖር፤

☞ የማጓጓዣና የግብይት ምቹ ሁኔታዎች በሁሉም ቦታዎች አለመኖር፡፡

## 5.6 የእሴት ሰንሰለት ስትራቴጂ በመስኖ ልማት

በመስኖ ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ የታለሙ የመስኖ ሰብል የገበያ ምርቶችን/ኮሞዲቲዎችን/ ለማሳደግ ለእሴት ሰንሰለት አውታር ላይ አጽንኦት ይሰጣል፡፡ ይህ አውታር የእሴት ሰንሰለት ተዋንያን በተለያዩ የእሴት ሰንሰለት ደረጃዎች እሴት መጨመርን እና ግለሰቦችና ድርጅቶች ለእሴት ሰንሰለት ተዋንያን ግብዓት/አገልግሎት መስጠትን ያገናዝባል፡፡ የመስኖ ልማትን በሚመለከት ቁልፍ የእሴት ሰንሰለት ተዋንያን የሚባሉት በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ የግብርና ግብዓት እና የምርት ውጤት አምራቾች፣ ነጋዴዎች፣ አቀናባሪዎች ናቸው፡፡ አስፈላጊ አገልግሎት ሰጪዎች

የመንግስት ምርምር እና የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሴክተርን የሚያካትት ሲሆን የቴክኖሎጂ ልማት፣ አቅም ግንባታ፣ አውቀት ማፍለቅና የማሰራጨት ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

የግብርና ምኒስቴር በግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት በመስጠት ረገድ ይሳተፋል፡፡ ለምሳሌ፡- ዘር፣ የመስኖ ቁሳቁሶች፣ እና ሌሎችንም የግብርና ሰብል ግብዓቶችን ያቀርባል፡ ፡ ግብዓት በማምረት እና አገልግሎት በመስጠት የህብረተሰቡ፣ የህ/ሥራ ማህበራት፣ በመስኖ የሚያለሙ አርሶ/አርብቶ አደሮች እና የግሉ ሴክተር ተሳትፎ ብቅ ብቅ ማለት ጀምሯል፡፡ ሀገራዊ የግብርና የምርምር እና የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሲስተም ውጤታማነትን በማሻሻል ገበያ መር የመስኖ ሰብል የገበያ ምርትን/ኮሞዲቲ/ ለመደገፍ በሚኖር ፍላጎት ላይ ያተኩራል፡፡ እናም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና የመስኖ ልማት ሠራተኞች ሊፈጽሙት የሚችሉት፡-

- ☞ ለእሴት ሰንሰለት እድገት ተሳትፏዊ፣ በገበያ የሚመራ፣ ሥርዓተ ጾታ ያማከለ ስሜት ያለው እና ዘላቂ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴን ማበረታታት፤

- ☞ በልማት ሂደት የእሴት ሰንሰለት ተዋንያን፣ ግብዓት አቅራቢዎችንና አገልግሎት ሰጪዎችን ማበረታታት፤

- ☞ አውታሮችን፣ በቀበሌና በወረዳ ደረጃ የማህበረሰብ እድገትን፣ ህ/ሥራ ማህበራትን፣ አርሶ/አርብቶ አደር እና የግል ሴክተሩን ምርትን እና የግብዓት አቅርቦት አገልግሎት አሰጣጥን ይደግፋሉ፤

- ☞ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ ትስስርን/የንግድ አውታርን፣ የእሴት ሰንሰለት ተዋንያን እና አገልግሎት ሰጪዎችን ማበረታታት፤

- ☞ በእሴት ሰንሰለት በመስኖ ሰብል የገበያ ምርቶች/ኮሞዲቲዎች እና በአነስተኛ እና ጥቃቅን መስኖ ፕሮጀክት ቦታዎች ለመማማር፣ እና ከፕሮጀክት ቦታዎች ውጪ ለማስፋት ውጤትና ትምህርት የተወሰደባቸውን መዝግቦ በሰነድ መያዝ፣ የድጋፍ ጣልቃገብነት ምርመራ/ለይቶ ማወቅን፣ ድርጊትንና ተጽዕኖ ጥናትን ማበረታታት

## 5.6.1 በመስኖ ሰብል እሴት ሰንሰለት የድጋፍና ተሳትፏዊነት

በሀገር አቀፍ ተገቢነት ካላቸው አጋር አካላት እና የእሴት ሰንሰለት ተዋንያን ጋር በመሆን የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና የመስኖ ልማት ሠራተኞች አዳዲስ ሀሳብና አሠራር ዘዴን እና የእሴት ሰንሰለት አቀራረብ ዘዴን በመጠቀም እንዲሁም ትስስርን/ ግንኙነትን በማስጠበቅ በመስኖ ልማት የእሴት ሰንሰለትን ማስተዋወቅ ይፈልጋሉ፡፡ አዲስ አስተሳሰብ/አሠራር የሚያካትታቸው ድርጅታዊ፣ ተቋማዊ እና ጠንካራ ቴክኖሎጂ ድጋፍ ናቸው፡፡ ከዚህ በታች የተመለከቱት ለገበያ ምርት/የመስኖ ኮሞዲቲ/ የእሴት ሰንሰለት እድገት የመስኖ ሰብል እሴት ሰንሰለት መተግበር ያለባቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡-

**የተመረጡ እሴት ሰንሰለቶች፡-** አትክልት እና ስራስሮች - ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ጥቅል ጎመን፣ ቃሪያ፣ ካሮት፣ ድንች፣ ቀይ ስር ወ.ዘ.ተ.

- ☞ ፍራፍሬዎች - ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ፓፓያ፣ ሙዝ፣ አፕል፣ ፕለም፣ የብርቱካንና ሎሚ ዝርያዎች
- ☞ ጥራጥሬዎች ፤
- ☞ ቅመማቅመም፤
- ☞ የቅባት፤
- ☞ ብርዕ ሰብሎች፤
- ☞ መኖ - ሳሮች እና ሌሎችም፡፡

**አምራቾች/ገበያዎች ፡-**

- ☞ አምራቾች - በግል የመስኖ እርሻዎች (በግል የተመረጡ) - በአነስተኛ መስኖ፣ ጥቃቅን መስኖ እና የማህበረሰብ ኩሬ የመስኖ አውታሮች ያሉ አርሶ አደሮች (ቅድሚያ ያልተመረጡ) ናቸዉ፡፡
- ☞ ገበያዎች - የግል አባውራዎች - ነጋዴዎች - ትላልቅ ፍራፍሬና አትክልት አምራቾች - ሸቀጣሸቀጥ ሱቆች - የጭማቂ ፋብሪካዎች ወ.ዘ.ተ.
- ☞ አዳጊ የመስኖ ሰብል የድጋፍ ተሳትፏዊነት፡-
- ☞ የማሳ ላይ - ሰብል ልማት እና የውሃ አጠቃቀም፤
- ☞ የግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት መስጠት - ሰብሎች - ውሃ፤
- ☞ የግብይት/የማቀነባበር፡፡

**የምርት ድጋፍ ተሳትፏዊነት ፡-**የምርት መጨመር፣ የመስኖ ሰብል የገበያ ምርት/ኮሞዲቲ/ ምርታማነት እና ገቢ፣ በተለያዩ የማሳ ዓይነቶች ልዩነት/ አሰራርና የምርት ድጋፍ ተሳትፏዊነት፣ የተሻሻሉ/በገበያ የሚፈለጉ ዝርያዎች፣ የተሻሻለ ሰብልና የውሃ እርሻ ተሞክሮዎች፣ የተሻሻሉ ግብዓቶችን በማካተት የተከላ ቅደም ተከተል፣ ከምርት መሰብሰብ በኋላ ጥራት፣ እየጨመረ የመጣ የመስኖ ቦታ እና ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ሰብሎች በመቶኛን ያካትታል፡፡

**የሰብል ዝርያዎች ፡-**

- ☞ ፍራፍሬዎች - የላይኛው ቆዳቸው የሚበሉ/የዘር ማመጣጠን - ማንጎ፣ አቮካዶ -የሚቀመስ - ሁሉም ፍራፍሬዎች - ምርታማነት - ሁሉም ፍራፍሬዎች - በቶሎ የሚበስሉ - ሁሉም ፍራፍሬዎች፤
- ☞ አትክልቶች - ሽንኩርት ከሀበሻ ሽንኩርት ጋር - ምርታማነት - ሁሉም አትክልቶች

፤

- ☞ መኖ - ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው - በፕሮቲን የበለፀጉ - ምርታማነት፡፡
- ☞ የቅባት እህሎች እና ቅመማ ቅመም

## የተሻሻለ ሰብል ልማት/የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ተሞክሮዎች

- ☞ሰብል ማፈራረቅ - ዓመታዊ የመኖ ሰብሎችን ጨምሮ፤
- ☞ ተባይ/በሽታ መከላከል - አፈራርቆ መዝራት፤
- ☞ የመስኖ ቴክኖሎጅ አጠቃቀም፤
- ☞ የድህረ ምርት ተግባራት፤
- ☞ የውሃ ምንጭ/ክምችት፤
- ☞ የመስኖ ውሃ መሳቢያ መሣሪያ፤
- ☞ የመስኖ ውሃ ስርጭት ዘዴ፡፡

## የሰብል ምርት ግብዓት አገልግሎት የድጋፍ ተሳትፏዊነት በቡድንና በግል ፡-

- ☞ የአትክልት ዘር ማባዛት - የሸንኩርት፣ የድንች- የመኖ ወ.ዘ.ተ
- ☞ የፍራፍሬ ችግኝ ጣቢያ - የችግኝ ማባዛት፣ማዳቀል፣ የሙዝ ቅጥያ እና ሌሎችም፡፡
- ☞ የሰብል ግብዓት/አገልግሎት አቅርቦት የድጋፍ ተሳትፏዊነት፡-
- ☞ በፌዴራል/ክልል/ዞን/ወረዳ /ቀበሌ ደረጃ ያለ ግንኙነት - አግሪ ቢዝነስ (የመስኖ ቁሳቁስ፣ የግብርና ኬሚካሎች)፤
- ☞ በፌዴራልና በክልል ደረጃ የተሻሻሉ ዝርያዎች አቅራቢዎች (በወረዳ ደረጃ አባዥዎ የዘር ፣ ችግኝ አምራቾች) ሰርቲፊኬት፡፡

## የማቀነባበር እና የግብይት የድጋፍ ተሳትፏዊነት፡-

- ☞የተሻሻለ ግብይት እና የሰብል ምርት ማቀነባበር በወረዳ/ዞን ህ/ሥራ ማህበራት እና በግል ባለሀብቶች፤
- ☞ አነስተኛ መስኖ ማቀነባበር እና የክምችት ቁሳቁስ ማስተዋዎቅ፤
- ☞ ለገበያ ብዙ ማምረት፤
- ☞ ለአምራቹ የጋራ መዋቅር ግብይት ማቋቋም (መደበኛ የሆነና ያልሆነ)፤
- ☞ በትስስር የኮንትራት እርሻ (ሽጦ ማምረት)፡፡

### የማቀነባበርና የግብይት የድጋፍ ተሳትፎአዊነት፡-

- ☞ በፌዴራል/ በክልል እና በወረዳ ደረጃ አግሪ ቢዝነስ አቀናባሪዎችና ነጋዴዎች መካከል ያለ ትስስር - አትክልትና ፍራፍሬ ጀምላ ሽያጭና የተመረጡ ሸቀጣሸቀጥ ሱቆች፤
- ☞ በወረዳ/ቀበሌ ደረጃ አገልግሎት ሰጪዎች እና በፌዴራል ደረጃ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መካከል ያለ ትስስር፤
- ☞ የሰብል ዋጋ (ኢንተርኔት) መረጃ - ማህበራት (አትክልትና ፍራፍሬ) እና ፕሮጀክቶች፤
- ☞ ጥራት - የጥራትና ደረጃ መዳቢ ቢሮ/EIAR/
- ☞ ክምችት፣ብዙ ማምረት፣ድህረ ምርት ወ.ዘ.ተ.

## 5.6.2. አገልግሎትን ማመቻቸት/ማሳለጥ

አገልግሎት ለመስጠት ምቹ ሁኔታዎች የሚባሉት ከታች ላሉ መጨረሻ ተጠቃሚዎችን የመስኖ ሰብል ምርት ተደራሽ ለማድረግ ዋነኛ ጠቃሚ ነገሮች ናቸው፡፡ ከታች ላሉ የመጨረሻ ተጠቃሚዎች ተፈላጊው በሰብል ምርት የበለጠ ጠቃሚዎቹ አገልግሎቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

**የመጓጓዣ አገልግሎት፡-** መጓጓዣ አንዱ ዘዴ ሲሆን በእርሱ አማካኝነት ምርት ከተመረተበት ቦታ ወደ ገበያ ብሎም ወደ ተመጋቢው ጠረንጴዛ ይደርሳል፡፡ የመስኖ ምርትን ከማሳ ወደ አካባቢ ገበያ ለማድረስ ዋነኛዎቹ የተለመዱ ማጓጓዣዎች እንስሳት ማለትም በእንስሳትና በእንስሳት በሚጎተቱ ጋሪዎች አንዳንዴም በሰው ጉልበት የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ከአካባቢ ገበያ ወደ ማዕከላዊ ገበያ በጭነት መኪና ይጓጓዛል፡፡

**የማከማቻ/መጋዝን አገልግሎት፡-** ብዙዎቹ የመስኖ ሰብል ምርቶች በተፈጥሮ ቶሎ የሚበላሹ ናቸው፡፡ የብዙዎቹ የሰብል ምርቶች በእቃ መደርደሪያ በቆይታ ጊዜያቸው በኩል ምቹ አይደሉም፡፡ ይሁንና በምርት ማሰባሰብ እና ምርቱን በመጠቀም መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ምርቱ ሳይበላሽና ሳይባክን በተገቢው ሊከማች ይገባል፡፡ ማሳ ላይ ለአጭር ጊዜ በበለጠ የተለመደው የምርት ክምችት በማሳ መግቢያ አካባቢ እንደ ድንች ያሉት በጊዜያዊ መደርደሪያ ሲሆን ቀዳዳ እንዲኖረው በማድረግ በአፈር እንዲሸፈኑ በማድረግ የቆይታ ጊዜያቸው እንዲራዘም ይደረጋል፡፡ በማዕከላዊ ገበያ ምርቱ መጀመሪያ የገባ መጀመሪያ ይወጣል በሚባለው ዘዴ በመጋዝን በማከማቸት የምርቱ ቆይታ ጊዜ ይራዘማል፡፡ በአጠቃላይ ዋነኛ የምርት ጥራትን የሚያስተጓጉለው የመጋዝን አገልግሎት ጉዳይ ነው፡፡

**ማቀነባበር፡-** የመስኖ ሰብልን (አትክልትና ፍራፍሬ፣ የብዕር ሰብሎች እነዘ የእንስሳት መኖ) የማቀነባበር አገልግሎት ኢንዱስትሪዎች በሀገራችን ገና በጅምር ላይ ያለ እና አገልግሎቱም ዝቅተኛ ነው። ለመስኖ ሰብል የገበያ ምርቶች /ኮሞዲቲዎች/ እሴትን ለመጨመር እና ምርቱ በዘላቂነት እየቀረበ መሆኑን ለማረጋገጥ በኢትዮጵያ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች አናሳ በመሆኑ ምክንያት ከሁሉም የበለጠውን ጠቃሚ አሠራር አውን ማድረግ አልተቻለም።

**ማሸግ፡-** የተቀነባበሩ እቃዎችን/ምርቶችን ማሸግና ምልክት መለጠፍ ለመስኖ አትክልትና ፍራፍሬ እና የብዕር ሰብሎች ምርት የበለጠ ጠቃሚ አሠራር ነው። ያን ያህል ትርጉም ያለው የተቀነባበረ ምርት ባለመኖሩ በምርት ላይ እሴት በመጨመር ረገድ አገልግሎት በዚህ አገር በደንብ የተጠናከረ አይደለም።

**ወደ ውጭ ሀገር መላክ፡-** የኤክስፖርት አትክልትና ፍራፍሬ፣ የብዕር ሰብል ምርት ከዚህ ግባ የሚባል እንዳልሆነና እሴት ጨምሮ ለመላክ የሚፈለገው አሠራር ውስን ነው። ይሁን እንጂ በተወሰነ ደረጃ ከአሶሳ አካባቢ ሩዝ እየተመረተ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች መላክ መጀመሩ የሚበረታታ ነው።

**ነጋዴዎች፡-** ግብርና ነክ በሆኑ ምርቶች ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች ለሸማቾችና አቅራቢዎች የበለጠ ጠቃሚ የመረጃ አገልግሎት ሰጪዎች ናቸው። ምን ዓይነት ምርት፣ በምን ያህል መጠን እና የት እንደሚገኝ መረጃ ይሰጣሉ። ሸማቾችንና ሻጮችን አገናኝቶ የግብይት ሂደትን ለማፋጠን የማይተካ ሚና አላቸው።

**ግንኙነት፡-** ሸማቾችንና ሻጮችን በማገናኘት ረገድ ግንኙነት በጣም ጠቃሚ እና ተፈላጊ የሆነ አገልግሎት ነው። በገጠሩ አካባቢ በይበልጥ ደላላዎች እና በግብርና ምርት ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች ይህን ተግባር ያከናውናሉ። ገበያ መር የኤክስቴንሽን አካሄድ የሞባይል ስልክ፣ ቴሌቪዥን፣ እና ሬዲዮ በመጠቀም ከዋና ዋና ሸማቾች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ላይ ትኩረት ያደርጋል። በእሴት ሰንሰለት ላይ ያሉ ጠቃሚ አሠራሮችን የሚያሳይ ምሳሌ በዕዝል 10 ይመልከቱ።

## 5.7. የኮንትራት ግብርና አስፈላጊነት

ኮንትራት ግብርና/ contract farming/ ማለት ሥርዓት/system/ ሆኖ የማእከላዊ ማቀነባበሪያና /central processing/ ኤክስፖርቲንግ ዩኒት ከእያንዳንዱ አርሶ አደር የተሰበሰበውን የግብርና ምርት የሚገዛበት ሥርአትና የግብይት ሂደቱም በኮንትራት ስምምነት የሚካሄድበት ነው። የኮንትራት ውሉም የተለያየና አብዛኛውን ጊዜ የሚገልፀው ገዢዎች የተመረተውን ምርት ምን ያህል እንደሚገዙና በምን ያህል ዋጋ እንደሆነ ነው። ውል ሰጭው /contractor/ ብዙውን ጊዜ የብድር እና ሙያዊ ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጥበት የግብይት ስርዓት ነው።

በኮንትራት ግብርና አሰራር የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አምራች አርሶ/አርብቶ አደር (የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት፣ በተናጠል በመስኖ ልማት የሚሳተፉ አርሶ/አርብቶ አደሮቸ እና በማህበረሰብ ኩሬ መስኖን የሚያለሙ) እና የመስኖ ምርት ሰብሳቢዎች፣ ገዢዎች፣

አቀነባባሪዎች እና ላኪዎች የመስኖ ምርቶችን በጥራት፣ በብዛት እና በተቀመጠለት ጊዜ ውስጥ ለመረካከብ የሚያደርጉት የገበያ ውል ስምምነት ነው። የኮንትራት ግብርና ዉል ሰጭዉ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ምርት በምን ያህል ዋጋና ምን ያህል ምርት እንደሚፈልግ በመዋዋል የሚረከብበት ሲሆን አፈፃፀሙም ዉል ሰጭዉ ምርቱ እንዲመረትለት ቀድሞ በመዋዋል ለምርቱ የግብዓት ብድር እና የቴክኒክ ድጋፍ የሚሰጥበት ነው። ውሉን በሚፈራረሙበት ወቅትም የገበያውን ሙሉ ሃላፊነት ሲወስድ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሩ ምርቱን በጥራትና በመጠን ለማቅረብ ግዴታ ይገባል። የውል አፈፃፀሙም/ስምነቱን ለማሳለጥ፣ ተወዳዳሪ እና ውጤታማ ለማድረግ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ዋና ዋና የኮንትራት ግብርና መሠረታዊ መገለጫዎችን ማወቅና መተግበር ይጠበቅባቸዋል። እነዚህም፡-

ገበያን ማመቻቸት፡- ገዢና ምርት አምራች ወደፊት በሚገበያዩበት ሁኔታ ላይ መስማማት እንዲችሉ መደገፍ ይጠበቅባቸዋል፤

የማምረቻ ሁኔታን ማመቻቸት፡- ለገበያ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ገዢው ክፍል ተገቢ የሆነ ግብዓት ማቅረብና የቴክኒክ ዕገዛ እዲያደርግ ማመቻቸት ይገባዋል፤

የአሰራር ሁኔታን ምቹ ማድረግ፡- አምራቹ/ሻጩ ተገቢ የሆነ ምክረ-ሃሳቦችን መቀበልና በተገቢው መንገድና ጊዜ ለማቅረብ ስምምነት እንዲያደርግ ምቹ ሁኔታን ያመቻቻል፤

የአነስተኛ፣ የጥቃቅን/የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ኑሬ መስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች አቅማቸው እንዲጎለብት ድጋፍ ያድጋል፤

- ☞ የመንግስትና የግል ሴክተሩ በሚመረቱ የመስኖ ምርቶች ተገቢውን የጥራት ደረጃ እንዲኖረው በጋራ ተባብረው እንዲሰሩ ያበረታታል፤
- ☞ በአግሪ ቢዝነስ ካምፓኒዎች መካከል ጤናማ የሆነ የገበያ ውድድር እንዲጎለብት ያመቻቻል።

## 5.7.1. የኮንትራት ግብርና ዓይነቶች

የቃልና/Soft contracts/ gentleman's agreement /የጽሁፍ ኮንትራት፡- የመጀመሪያው የውል ዓይነት በሁለቱ ወገኖች መካከል በቃል የሚፈፀም ሲሆን በአንፃሩ የጽሁፍ ኮንትራት በሕግ ፊት ሊቀርብ የሚችልና አሳሪ የሆነ የውል ዓይነት ነው /በውሎቹም መካከል የመግባቢያ ሰነድ/MOU/ ይኖራል።

መሰረታዊ ሸቀጥና ምርት አቅርቦት ኮንትራት፡- ይህ አይነቱ ኮንትራት የሸቀጥ ምርትን ብቻ በማቅረብ ላይ ያተኩራል።

የሙሉ አገልግሎት ኮንትራት፡- ከመሬት ዝግጅት ጀምሮ ግብዓትና መገልገያ መሳሪያዎችን ትራንስፖርት' ቴክኒካል አገልግሎትና ሥልጠና በማቅረብ የሚገለፅ ሲሆን ለምሳሌም የዘር ምርት ኮንትራቶችና የአውት ግሮወር አሰራር ኮንትራቶች ሊገለፁ ይችላሉ።

**የሁለትና የብዙ ወገኖች /የገዢና ሻጭ/ ኮንትራት፡-** የመጀመሪያው ኮንትራት የሚመለከተው ሁለቱን ወገኖች ብቻ ሲሆን በአንፃሩ የብዙሃን ወገን ስምምነት ወይም ኮንትራት ደግሞ ብዙ አካላትን በአንድ ላይ የሚያስተሳስር ነው፡፡ ለምሳሌ አምራቾች፣ ግብዓት አቅራቢዎች፣ የአርሶ/አርብቶ አደር ድርጅቶች እና ባንኮች የሚተሳሰሩበት የኮንትራት ዓይነት ነው፡፡

**የአጭር እና የረዥም ጊዜ ኮንትራቶችም፡-** እነዚህ የኮንትራት ዓይነቶች ባለው መዋለ ንዋይ መጠን፣ ዓይነትና ቆይታ የሚወሰኑ ይሆናል፡፡

### 5.7.2. የአውት-ግሮወርስ አሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት ሊደረግ የሚገባው ቅድመ ዝግጅት

ማንኛውም የአውት-ግሮወር አሰራር ቅድመ ሁኔታዎች ካልተቀመጠለት ውጤታማ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ ለሁለቱም ወገን አትራፊ መሆን ይገባዋል፡፡ ለዚህም አትራፊ ለመሆን የሚከተሉትን መዳሰስ ያስፈልጋል፡፡

**አትራፊ ገበያ መለየት /profitable market/፡-** ገዢው ክፍል ገበያውን መፈለግና ለረዥም ጊዜ መቀጠል አለመቀጠሉንና ትርፋማ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡ አርሶ/ አርብቶ አደሮችም ገቢን ሊያስገኝና ገበያን ሊስብ የሚችል የአመራረት አሰራር በመከተል ሊያጋጥማቸው የሚችሉ ችግሮችን ሊቋቋሙ በሚችሉ አካሄዶች ትኩረት መስጠት ይገባቸዋል፡፡

**የአካባቢ ሁኔታን ማጥናት /physical and social environment/፡-**

☞ የገበያ ሁኔታ ቀጣይና የተጠናከረ እንዲሆን ምርቱ የሚለማበት የመሬት አቀማመጥ፣ የአየር ሁኔታ፣ የአፈር ለምነት፣ የውሃ ምንጭ፣ ምርቱ በገበያ ላይ ያለው ተፈላጊነት፣የአምራቹ አሰፋፈር አመችነት መረጋገጥ/መታወቅ/ ይገባዋል፡፡

☞ አትራፊ ገበያ መለየትና የአካባቢን ሁኔታ ማጥናት የምርቱን ጥራትና አትራፊነት የሚያረጋግጡ ሲሆኑ በተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የመስኖ ልማት አሰራር ኋላቀር በሆኑ የአመራረት ዘዴዎች ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ዘመናዊ የመስኖ ልማት ዘዴን ቶሎ ተቀብሎ ውጤት ለማምጣት ያላቸው ተነሳሽነት አዝጋሚ ነው፡፡ በመሆኑም ተረካቢው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት በአካባቢው ሕብረተሰብ የተለመዱትን የግብርና አሰራሮች መለየት ይገባዋል፡፡ እነዚህም:-

- ለሚመረተው ምርት የአካባቢው ሁኔታ ተስማሚ መሆኑን ማረጋገጥ፤
- በቂ የሆኑ የመገናኛ አውታሮች መኖራቸውን ማረጋገጥ /መንገድ የምርትን ዕሴት ለመጨመር የሚረዱ የኃይል ምንጮች ለምሳሌ መብራትና ውሃ/፤
- በቂ የሆነ የማምረቻ መሬትና የይዞታ ማረጋገጫ መኖሩን ማረጋገጥ፤
- ግብዓትና የሚገኝበት ምንጭ ማረጋገጥ እና
- የማሕበረሰቡን ሁኔታ ማገናዘብ ማለትም ባህላዊ አመለካከትና ልምዱን መገንዘብ ናቸው፡፡

**የመንግስት ድጋፍ /Government support/ ማረጋገጥ፡-** መንግስት አነስተኛ የመስኖ እርሻ መሬትና አቅም ያላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች የአውት ግሮወር አሰራር በሚዘረጋበት ጊዜ በተዋዋዮች መካከል ያለው ትስስር ውጤታማ እና ሕጋዊነት እንዲኖረው የሚጫወተው ሚና ወሳኝ ነው፡፡ ስለሆነም ከመንግስት በኩል ተስማሚና ሕጋዊ የውል ስምምነት እንዲኖር ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ ደንብና የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣትና ማስተሳሰር፣ የምርምርና የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥን ማጠናከር እና በአምራቹ አካባቢ መሰረታዊ አውታሮችን መዘርጋት ወ.ዘ.ተ አስፈላጊ ነው፡፡

- ☞ የኮንትራት ግብርና አሰራርን ለማጎልበት መከተል ያለብን ቅደም ተከተሎች፡-
- ☞ የኮንትራት ግብርና አሰራርና ሂደት ለማጠናከር የጋራ ውሳኔ መስጠት፣
- ☞ የኮንትራት ግብርና አሰራርና ሂደት ለማጠናከር የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማቀድ፣
- ☞ የኮንትራት ግብርና መፈፀሚያ ቢዝነስ ፕላን ማዘጋጀት፣
- ☞ በድርድር ላይ የተመሠረተ እና ተቀባይነት ያለው የኮንትራት ግብርና እንዲኖር ማድረግ፣
- ☞ የኮንትራት ግብርና የመስክ ሥራዎችን መጀመር፣
- ☞ ክትትል፣ ግብረመልስ እና ልምድ መለዋወጥ ማከናወን፣
- ☞ ዘለቄታዊነቱን ለማረጋገጥ ተከታታይነት ያለው ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎችን መተግበር፣
- ☞ የኮንትራት ግብርና አሰራርን በማስፋት ሁለተናዊ እድገት እንዲመዘገብ ማድረግ፡




ምስል- 6፡-የአርሶ/አርብቶ አደሮችና የካምፓኒዎች/የግል ባለሃብቶች/ፋብሪካዎች የገበያ ትስስር

ከላይ በዝርዝር ለማመላከት እንደተሞከረው የኮንትራት/አውትግሮወር የግብርና አመራራትና ግብይት ስርአት በአምራቹና በምርት ተቀባይ/ገዥ አካላት መካከል በሚመሰረት ውል ላይ የሚገነባ የኢኮኖሚ ትስስር ነው፡፡ ይህ ስርአት ህጋዊ ማእቀፎችንና የኮንትራት ጽንሰ-ሀሰብን ባገናዘበ መልኩ ከተዘረጋና ተዋዋዮች የገቡትን ውለታ በአግባቡ ከፈጸሙና ለዚህም አስፈላጊው የመንግስት ድጋፍ ከተደረገ የሚያስገኘው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከሁለቱም ወገኖች አንጻር ከፍተኛ እንደሚሆን ሀገራዊና የውጭ ልምዶች የሚያረጋግጡ ሲሆን በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ለኮንትራት አርሶ/አርብቶ አደሮች የሚሰጠው ጠቀሜታ፡-** በኮንትራት የአመራረትና የገበያ ስርአት የሚታቀፉ አርሶ/አርብቶ አደሮች ከምርት ተረካቢ/ገዥ ባለሀብቶችና ኩባንያዎች ጋር በሚፈጥሩት ትስስር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በርካታ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን የሚያገኙ ሲሆን በዋናነት፡-

- ☞ አስቀድሞ የታወቀና የተረጋገጠ ገበያ ይኖራቸዋል፤
- ☞ በዋጋ መዋዠቅ ምክንያት ሊደርስ ከሚችለው ስጋት ይድናሉ፤
- ☞ የግብርና ግብአት ብድር አቅርቦትና የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት ያገኛሉ፤
- ☞ ከአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጋር እንዲተዋወቁ አመች ሁኔታ ይፈጠራል፤
- ☞ የመሬት አጠቃቀማቸው ይሻሻላል፣ ምርታማነትና የምርት ጥራት ይጨምራል፣ በውጤቱም የገበያው ተጠቃሚ ይሆናሉ፣ገቢያቸው ያድጋል፡፡

**ለኮንትራት ምርት ገዥ/ተረካቢ አካላት የሚሰጠው ጠቀሜታ፡-**

- ☞ በመሬት ይዞታው ማነስ ጋር ተያይዞ ፍላጎቱ ኖሮት ምርቱን ማስፋፋት ያልቻለ ባለሃብት/ኩባንያ/ በዙሪያው ከሚገኙ አርሶ/አርብቶ አደሮች ጋር በመስራቱ የመሬት ችግርን ያቃልለታል፤
- ☞ አስተማማኝ እና ቀጣይነት ያለው የምርት አቅርቦት እንዲኖር ይረዳዋል፤
- ☞ በሀገር ውስጥናና በውጭ ከሚገኙ የንግድ ሸሪኮቹ ጋር ጠንካራና ቀጣይነት ያለው የገበያ ትስስር እንዲፈጥር ይረዳዋል፤
- ☞ በገበያ ላይ ከሚገዛው ምርት በተሻለ መልኩ በውሉ መሰረት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ምርት በዓይነትና በሚፈለገው መጠን እንዲረከብ ያስችለዋል፤
- ☞በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆን ያደርገዋል /ለሀገርም የውጭ ምንዛሪን ያስገኛል/፡፡

ከላይ በግልጽ ለማመላከት እንደተሞከረው የኮንትራት ግብርና አመራረትና ግብይት ስርአት በአግባቡ ከተዘረጋ ለሁለቱ ወገኖች ከሚያስገኘው ጠቀሜታ ባሻገር በአጠቃላይ ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት በተለይም ደግሞ ለኤክስፖርት የግብርና ዘርፍ መጠናከር የሚኖረው ፋይዳ ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተያያዝነውን የአምስት አመቱን የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳከት የማይታለፍና ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በስፋትና በተቀናጀ መልኩ መተግበር የሚገባው የልማት አቅጣጫ ነው፡፡

ክፍል -4

## የተቀናጀ መስኖ ሰብል እሴት ሰንሰለት በመስኖ ግብርና ምርቶች

የስርዓተ ጾታ ጉዳይ (gender Issue)

- ሴት አ/አደሮች ሁለቱም (እማወራ እና የአ/አደር ሚስት) በመስኖ በሚለሙ ሰብሎች እሴት ሰንሰለት ላይ ቢሳተፉም የሴት አ/አደሮች ተሳትፎ ብዙም የሚታይ አይደለም፡፡
- ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ሰብሎች በማምራት ረገድ አስተዋጾአቸው በቂ እውቅና የለውም፡፡
- በባህላዊ የሥርዓተ-ፆታ ተግባር እና ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ምክንያት ሴቶች በአብዛኛው የሚወስኑት ብዙ ጉልበት በሚጠይቁ እና ከእሴት ሰንሰለት ውስጥ ካሉት የሚሳተፉት ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸውን ነው፡፡
- በዚሁ ዙሪያ ለሴቶች አመቺ የሆኑ አሰራሮችና ደንቦች በማጣታቸው ምክንያት ሴቶች ምርት ለማምረት የሚያስፈልጉ እንደ ግብዓት፣ ብድር እና መሬት የማግኘት እድል የላቸውም ወይም የተለያዩ ሀብቶችን ተጠቅመው እንዲያመርቱ ምቹ ሁኔታ አልተፈጠረላቸውም፡፡
- የባህል እሴት እና ሴቶችን የሚያገሉ/የሚያሳንሱ/ አባባሎች በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ሴቶች በተለያዩ የውሳኔ አሰጣጥ ቦታ እና ሁኔታ እንዳያገኙ ተጭኖታል፡፡
- ሴቶችን ያላማከለ ውክልና እና ተሳትፎ ሴቶች ውሳኔ ሰጪነት ባሉ የተለያዩ ድርጅቶች ያልተገባ ውክልና እና ተሳትፎ የሴቶችን መብትና ጥቅም በእሴት ሰንሰለት ባላቸው አደረጃጀት በቂ የሆነ ግንኙነት እና ትስስር ያለመኖር
- ሴቶች የገበያ መረጃ በጊዜም ሆነ ተገቢ የሆነ መረጃ በማግኘት እጥረት ያላቸው በመሆኑ ምርታቸውን የሚሸጡትን እና ገበያ የሚፈልጋቸውን ምርቶች በማምረት እንዲያቀርቡ ባለሙያዎች ተገቢውን የእሴት ሰንሰለት ሥልጠና የእነርሱን አቅምና ግንዛቤ ያማከለ ስልጠና ያለማዘጋጀት ችግር

### በእሴት ሰንሰለቱ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን እንዴት ማካተት ይቻላል፡፡

- የሴት እና የወንድ አርሶ/አርብቶ አደሮች በእሴት ሰንሰለቱ ያላቸው ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ የሚያስችል መፍትሔ መቅረፅ ያስፈልጋል፡፡
- ሥርዓተ-ፆታን መሠረት ያደረገ ትንተናዎች ላይ ትኩረት በማድረግ በሥርዓተ-ፆታ በእሴት ሰንሰለት የተለያየ ተግባራት  ሥራዎች፣ ፍላጎቶች እና ምርጫ ግንዛቤ እንዳለ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ሥራዎችን መተግባር፤
- በሁሉም የእሴት ሰንሰለት ደረጃዎች የሴቶችን አቅም እና ሀብት በማገናዘብ በእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ ተጠቃሚዎችና ተሳታፊዎች እንዲሆኑ መልካም አጋጣሚ /እድሎችን/ ማሳደግ፤
- ፍትሃዊ/ሴቶችን ያማከሉ/ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ አሰራሮች እና ማበረታቻዎች በመስጠት ሴቶች የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን በወቅቱ እንዲያገኙ ማድረግ፤
- ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች በእሴት ሰንሰለት ውስጥ እኩል ተሰተፎና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ የአመራር ድርሻቸውን እንዲወጡ በማግባባት እንዲሳተፉ ማድረግ እና በእሴት ሰንሰለት ውስጥ የመሪነት ሚናቸውን እንዲጫወቱ የማብቃትና የማበረታታት ስራ መስራት፤
- የሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች ድርጅቶች እና ተቋማት ሴት አምራቾች ማህበሮች ዩኒየን እና

ፌዴሬሽን የግንኙት አግባባቸውን /ትስስርን/ በሴቶች መብት ላይ የሚሰሩ ተቋማት የሴቶች ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በየደረጃው ሴቶች ድምፃቸውን የሚያልራምዱበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት በእኩል ተጠቃሚነትና ተሳትፎ በእሴት ሰንሰለት ውስጥ የራሳቸውን ሚና እንዲጫመቱ ማስቻል፡፡

**በማህበራት (ኅባኤዎች) ውስጥ፡-**

- የሴት አርሶ/አርብቶ አደር አምራቾች/በገበያተኞች/ አቀነባባሪዎች ውክልናና ተሳትፎ ተረጋግጦ እንዲሁም የሴቶችን ተሰሚነት በእሴት ሰንሰለት ስብሰባዎች ውስጥ ማረጋገጥ፡ ፡
- ስርዓተ-ፆታ ተኮር የገበያ ስምምነቶች በቴክኖሎጂ አያያዝና አጠቃቀም፣ በእቅድ አወጣጥና የስራ ሁኔታ ዙርያ እንዲደረጉ ማበረታታት፡፡
- ከታች ወደ ላይ የሆነ አወቃቀር የሴት አርሶ/አርብቶ አደር አምራቾች /ገበያተኞች/ ሰራተኞች ውክልና በኅባኤዎች ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ማበረታታት፡፡
- ሴቶች ወቅታዊና ትክክለኛ የሆነ የገበያ መረጃ አለማግኘታቸው እንዳለ ሆኖ የምርት ጥራት እና ብዛት እንዳይጨምሩ እንከን ይገጥማቸዋል፡፡ የዚህም ምክንያቶች ዝቅተኛ የት/ት ደረጃ፣ ዝግተኛ የሆነ የስራ ከባቢ አየር እውቀት፣ የእለት ተእለት እቅድ ማውጣት፣ በአመዛኙ ከልማድ የተነሳ ከቤታቸው ውጭ ካለው ሁኔታ መነጠል፣ ግን በአጠቃላይ ፆታ ያላማከሉ መረጃ ሲስተሞች እና የጥሩ ልማዶች እና ውጤታማ ልማዶች ማካፈል እውን ካለማድረግ ጋር ግንኙነት አላቸው፡፡
    - ወንዶች እና የሴቶች መረጃ የማግኘት እድል እንዳላቸው በመረዳት የሴቶችን የገበያ መረጃ የማግኘት እድል ማሻሻል፤
    - ሴት አርሶ/አርብቶ አደር አምራቾች የሚያጋጥማቸውን የገበያ እንቅፋት በመለየት መፍትሄ ማዘጋጀት፤
    - ፆታ ተኮር መረጃ ስርዓት መሰረት በማድረግ ተደራሽ ማድረግ፣
    - በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች የእውቀት ተደራሽነት፣ ስኬታማ እና ጥሩ ልማዶች የማግኘት እድል ማሻሻል፤
    - የምርት ጥራት እና ብዛትን በማሻሻል በእሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን ተጠቃሚነት ማሳደግ፡፡

# ምዕራፍ 6. የመስኖ ልማት ስልጠና

አንድ የመስኖ ልማት ሰራተኛ ወይም የመስኖ አርሶ/አርብቶ አደር የ20 ደቂቃ የቀን ውሎውን ዕቅድ ማዘጋጀት ከቻለ ምርታማነትቱን በእጅጉ ለማሻሻል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ የአርሶ/አርብቶ አደር ዓላማ ስኬት የየቀኑ የ20 ደቂቃ ዕቅድ ድምር ውጤት ነው፡፡ የመስኖ ልማት ሰራተኛ ወይም ባለሙያ ወይም አርሶ/አርብቶ አደር በዕቅድ ከተመራ የቀን ውሎ ዓላማውን ሳይሳሳትና የትግበራ መስመሩ የሚፈልገውን አላማ ለማሳካት ይችላል፡፡ ዕቅድ በመረጃ ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፡፡ የሚዘጋጀው ዕቅድ ለሚመራውና ለሚተገብረው አካል ስጋትን የሚቀንስ ሲሆን ቀደም ብሎ መገንዘብ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ሲፈጠሩ በማንኛውም ጉዳይ ላይ እንደገና ተቀምጦ ማቀድ ጠቃሚ ነው፡፡ ባለሙያዉ በዕቅዱ አማካኝነት የትኩረት አቅጣጫዉ ላይ ከተመሠረተ አወንታዊ በሆነ መልኩ ያለዉን ሀይል አስተባብሮ ለውጤት ይሰራል፡፡

ይህን አቅጣጫ በመከተልም ሥራዉን በሰዓቱና በብቃት ለመፈፀም ያግዛል፡፡ በመረጃ ላይ ተመስርቶ የተሰራን ዕቅድን አጥብቆ መያዝ ለመውደቅ የሚኖርን እድል ዝቅተኛ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም ዕቅድ የተለያዩ የመስኖ ተግባራትን በየደረጃቸው በማስቀመጥ ጠቃሚ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንዲደረግ ያደርጋል፡፡ በዚህም የበለጠ ጠቃሚ የሆነውን በማስቀደም እንደ ሁኔታው ይተገበራሉ፡፡

## 6.1. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና አስፈላጊነት

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ለውጥ አስቸጋሪና በረዥም ሂደት እንዲሁም በበርካታ ጥረት የሚመጣ ለውጥ ነው፡፡ ይህ የሆነበት አብይ ምክንያት ደግሞ የኤክስቴንሽን ቁልፍ ተግባር የአመለካካትና ባህሪ ለውጥ ማምጣት ስለሆነ ነው፡፡ ይህ አይነት ለውጥ አርሶ/አርብቶ አደሩ ለዘመናት ከለመደውና ከሚያውቀው የዘልማዳዊ የግብርና ስራ ማላቀቅን፤ አማራጭ/መፈትሄ አቅጣቻዎችን ማመቻቸትንና ኢኮኖሚውን ማሳደግን ይጠይቃል፡፡ ይሁን እንጂ ተለዋዋጭ የአየር ንበረት፣ ያልተረጋጋ የአለም ገበያ እና ታዳጊ የኢኮኖሚ አቅም ባላቸው የኛ አይነቶት ሀገሮች የበለጠ የተወሳሰበ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ የዚህ አይነት ችግርን መቋቋም ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው የሰው ሀብትን በአግባቡ መጠቀም ሲቻልና ይህም ተደራሽ ሲደረግ ነው፡፡ በርካታ የአቅም ግንባታ ዘዴዎች ቢኖሩም በዋናነት የምክርና የስልጠና ድጋፍ ማድረግ የሰው ሀብት ልማትን ከማሳደግ አኳያ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

ስልጠና የሚካሄደው ሁልጊዜ ለዝቅተኛ አፈጻጸም ምላሽ ለመስጠትና ጉድለቶችን ለመሙላት ሳይሆን ከአዳዲስ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች ጋር ለማስተዋወቅ ወይም ለማለማመድ፣ ለውጥን ለመስገንዘብ፣ የጠራ የፖሊሲና ስትራቴጂ ግንዛቤ እንዲኖር ለማስቻል፣ እውቀትና ክህሎት በማጎልበት ምርትና መረታማነትን ለማሳደግ ጭምር ነው፡፡

### 6.1.1 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና ግብ

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና የአርሶ/አርብቶ አደሮችን ልማዳዊ የመስኖ አተገባበር በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን አሳድጎ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ገቢ መጨመርና ኑሯቸውን በዘላቂነት ማሻሻል ነው፡፡ ይህንንም ግብ ለማሳካት የሚከተሉት ግልጽ የሆነ ዝርዝር ተግባራት ተቀምጠዋል፡፡

- ☞ ችግር ፈቺ የሆኑ አዳዲስና የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮችን ማቅረብ፤
- ☞ የመስኖ ልማት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ መልካም ተሞክሮዎችን ማስፋት፤
- ☞ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና መልካም ተሞክሮዎችን መረጃ ማሰባሰብ፣ ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤
- ☞ መልካም ተሞክሮዎችን የማስፋት አተገባበርን፣ ለአሰራር/ቴክኒክ/ ባለሙያዎችና አርሶ/አርብቶ አደሮች የተግባር ስልጠና መስጠት፤
- ☞ ገበያ ተኮር የመስኖ ሰብሎችን መምረጥና ማምረት፤
- ☞ የገበያ ትስስርን መፍጠር፤
- ☞ የእውቀትና ክህሎት ክፍተቶችን መለየትና ድጋፍ ማድረግ፤
- ☞ የልምድ ልውውጥን ማካሄድ፤
- ☞ በቂ መጠንና እና ጥራት ያለው ተወዳዳሪ የመስኖ ምርት ለማምረትና የተቀናጀ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን ለመስጠት የመስኖ ልማት ልማት ፈጻሚዎችን ትስስር መፍጠር፤
- ☞ የሴቶችንና ወጣቶችን የኢኮኖሚ አቅም ለማሻሻል በመስኖ ልማት ያላቸውን ተሳትፎ ማበረታታት፡፡

በአጠቃላይ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና ፕሮግራም ማቀድ በመስኖ ግብርና ስራዎች ላይ አወንታዊ የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የእውቀት፣ ክህሎት እና ተነሳሽነት ችግሮችን ለመቅረፍ ጠቃሚ አቀራረብ ዘዴና አቅጣጫ ነው፡፡

የስልጠና ፕሮግራም ዕቅድ የያዝነውን ተግባር ለማሳካት ከብዙ አቅጣጫ ማሰብና ማገናዘብ፣ የጋራ ውይይትና የተሻለ ዘዴ መምረጥ በኃላ የሚወሰን ሆኖ የኤክስቴንሽን ስልጠና ዕቅዱ አርሶ/አርብቶ አደሩ ጋር ሲደርስ የባለቤትነት ስሜትን የማሳደግ፣

እምነትን የመገንባት፣ ሀብትን የማንቀሳቀስ ወ.ዘ.ተ. መልካም አጋጣሚን ይዞ ይመጣል፡ ፡ በመሆኑም የኤክስቴንሽን ስልጠና ዕቅድ አስፈላጊነት በውሳኔ ሰጪ አካላት ዘንድ ተቀባይነቱ እየጨመረ መጥቷል፡፡

## 6.1.2 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና ሳይክል/ዑደት

ስልጠና ለአቅም ግንባታ ተግባር ከምንጠቀምባቸው ብዙ የአቀራረብ ዘዴዎች አንደኛው ሲሆን በተለያዩ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞችን እውቀትና ክህሎት በማጠናከር የተሰጣቸውን ስራ በላቀ ብቃትና አፈፃፀም ተወጥተው የተቋሙን ግብ/ራዕይ/ እንዲያሳኩ የሚያስችል አሠራር ነው፡፡ አልፎ አልፎ ስልጠናን ደካማ ወይም ዝቅተኛ አፈፃፀም ባለበት ሁሉ እንደ ብቸኛ መፍትሄ የማየትና የመጠቀም አዝማሚያዎች በስፋት ይስተዋላል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ስህተት ያለው አመለካከት ነው፡፡ ለምሳሌ በጉብኝ፣ ፖሊሲ/ስትራቴጂዎችን/ የስራ መመሪያ/ቴክኒካል ማኑሎቸን ማንበብ፣ ከፈጻሚ አካላት ጋር ግልፀኝነት በሰፈነበት አግባብ አብሮ በመስራት፣ በተሻለ የፋይናንስ አያያዝ ብቃት፣ በክትትልና ድጋፍ ወ.ዘ.ተ. ሊሆን እንደሚችልም ግንዛቤ መፈጠር ይኖርበታል፡፡

የስልጠና ዑደት የሥልጠና ፍላጎት መለየት፣ መተንተን፣ የስልጠና ቁሳቁሶች ዝግጅት/ ንድፍ፣ የክፍለ ጊዜ ዕቅድ እና የስልጠና ሪፓርት ማዘጋጀት ተግባራትን ያካትታል፡፡ የስልጠና ዑደት አምስት ክፍሎች የሚኖሩት ሲሆን እነዚህም፡-

- የሥልጠና ፍላጎት ለየታና ትንታኔ፤
- የስልጠና ይዘት፣ ግብዓት ዝግጅትና እና የክፍለ ጊዜ ዕቅድ፤
- የሥልጠና አሰጣጥ ስልት/ዘዴ (የሥልጠና ትግበራ ዜዴ)፤
- ማሰልጠን፤
- የስልጠና ግምገማ፡፡

## 6.1.3 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የስልጠና ሂደት

የኤክስቴንሽን ስልጠና ሂደት በሶስት ምዕራፎች ይከፈላል፡፡ እነርሱም የስልጠና ዝግጅት ምዕራፍ፣ የስልጠና ትግበራ ምዕራፍ እና የስልጠና ክትትልና ግምገማ ምዕራፍ ናቸው፡፡

የስልጠና ዝግጅት ምዕራፍ፡- የስልጠና ዝግጅት ምዕራፍ ማለት ስልጠናውን ከመጀመራችን ቀደም ብሎ የምናከናውናቸው ተግባራት ማለት ሲሆን እነዚህ ተግባራትም ስልጠናው በተሳካ ሁኔታ ለማከናውን አይነተኛ ሚና አላቸው፡፡ የዚህ ምዕራፍ አብይ ተግባራትም የሥልጠና ፍላጎት ልየታና ትንታኔ ማካሄድ፣ የስልጠና ይዘት መንደፍ፣ የስልጠና ግብዓት ማሰባሰብ /የሥልጠና ቁሳቁሶች ዝግጅት/፣ የክፍለ ጊዜ ዕቅድ፣ ተሳታፊዎችን በተደራጀ መልኩ መምረጥ፣ የስልጠና ዝርዝሮችን በማሳወቅ አስፈላጊ ዝግጅቶች ይጠናቀቃሉ፡፡

**የስልጠና ትግበራ ምዕራፍ:-** በዝግጅት ምዕራፍ የተከናወኑትን ተግባራት መሰረት በማድረግ የተዘጋጀውን ስልጠና በተግባር ላይ ማዋል ነው፡፡ በዚህ ምእራፍ ለተሳፊዎች የተረጋጋ አካባቢን በመፍጠር ታዳሚዎች በነጻ እንዲሳተፉና አዳዲስ እውቀትና ክህሎትን እንዲለማመዱ ይደረጋል፡፡ ስልጠናውም በተመረጠው ርዕስና የስልጠና ዘዴ መሰረት በተያዘለት ቦታና ጊዜ ይካሄዳል፡፡ በስልጠናው ወቅት አመቻቹ/አሰልጣኙ የተሳታፊዎችን ምቾት ማለትም አቀማማጥ፣ የመማሪያ ክፍል ንፅህና፣ የስልጠና መርጃ መሳሪያዎች በትክክል መዳረስና ለዕይታ አዳጋች አለመሆናቸውን ወ.ዘ.ተ. ማረጋገጥ ይኖርበታል: : በሁለም የስልጠና ክፍለ ጊዜ ሠልጣኞች (በተለይም ሴት ተሳታፊዎቸን) ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ማበረታታት ይኖርበታል፡፡ የሚጠቀምባቸውን መርጃ መሳሪያዎችና የሚጠቀምባቸው ምሳሌዎች በትክክል ከስልጠናው ርዕስ ጋር የተጣጣሙ/የተያያዙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በቂ የጥያቄና የውይይት ሰዓት መመደብ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በመጨረሻም የስልጠናውን ቁልፍ/ዓብይ ጭብጥ በማስገንዘብ ስልጠናውን መቋጨት ይጠበቅበታል፡፡

**የስልጠና ክትትልና ግምገማ ምዕራፍ:-** የስልጠና ክትትልና ግምገማ ምዕራፍ ማለት የስልጠናው ክፍለ ጊዜ ሲጠናቀቅ ሰልጣኞች ከስልጠናው ምን አንደ ተረዱ የተግባር ወይም እንደሁኔታው የፅሁፍ/ቃል ፍተሻ/ፈተና/ የሚሰጥበት ምዕራፍ ነው፡፡ ይህም የስልጠናውን የመጀመሪያ ደረጃ ተጽዕኖ ልኬት የምናደረግበት ዘዴ ሲሆን ተሳታፊዎችን በሥራ ቦታቸው ላይ ሆነው በስልጠና የወሰዱትን ትምህርት ሲተገብሩ የሚደረግላችውን የድጋፍ አይነትና ይዘትን ጠቋሚ መረጃ ለማግኝትም ጭምር የምንገለገልበት ነው፡፡ ሌላው በዚህ ምዕራፍ አጠቃላይ የስልጠና ሪፖርት የሚዘጋጅበት መረጃ መሰብሰቢያና በቀጣይ ለሚደረጉ ስልጠናዎች ሊወሰዱ የሚገባቸውን ጥናቃቄና ልምድ የምንወስደበት የግብረ መልስ አሰጣጥ ዘዴ ነው፡፡

## 6.2. የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት(Training Need Assesment) (TNA)

በወሳኝ የኤክስቴንሽን ስትራቴጂ ተግባር ቁጥር 10 ላይ በግልፅ እንደተመለከተው የልማት ጣቢያ ሰራተኞች በአርሶ/አርብቶ አደሩ ጥያቄዎች፣ ችግሮችና ፍላጎቶች በየጊዜው የዳሰሳ ጥናት የሚያካሂዱበትንና ግብረ መልሶችን የሚሰበስቡበትን ስልት ተቋማዊ ማድረግን ያሰቀምጣል፡፡ ይህ ማለት የመስኖ ስልጠናን ፍላጎት ዳሰሳ ጥናትና ግበረ-መልስንም ይጨምራል ማለት ነው፡፡

የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማለት አንድ የመስኖ ልማት ተግባርን በብቃት ለመፈፀም የመስኖ ባለሙያ ወይም የመስኖ ልማት ሰራተኛ በአንድ የሥራ ዘርፍ ላይ እየሰራ ስራውን በሚፈለገው የብቃትና ጥራት መስፈርት መስራት ሳይችል ሲቀር ክፍተቱን በትክክል ለመረዳትና የሚስፈልገውን/የጎደለውን እውቀት፣ ክህሎት ወይም ተነሳሽነት ደረጃ አስቀድሞ አውቆ የታዩትን ክፍተቶች ለማሟላት የሚችልበትን ዘዴ /ስልት ለመወሰን የሚደረግ ዳሰሳ ጥናት ነው፡፡

ይህ ማለት አሁን የሚታይ(ያለ) እና የሚፈለግ/መሆን ያለበት የስራ ተግባር ብቃትና ጥራት መካካልና ልዩነት ያለ እንደሆነና ይህም በእውቀት/ክህሎት ማነስ መሆኑ ሲረጋገጥ እንዲሁም ሥልጠና ይህንን ክፍተት የሚሞላ ሆኖ ሲገኝ ይህንኑ ተግባር

በተመለከተ ስልጠና ይዘጋጃል፡፡

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ሂደት ሲሆን በዚህም የስልጠና ፍላጎት ይለያል፣ በደረጃ ይቀመጣል፣ ከዚያም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባር ሆኖ ሲገኝ የስልጠና ፕሮግራም ወጥቶ ስልጠናው ይሰጣል፡፡

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና የመጀመሪያው ዑደት /ሳይክል/ ደረጃ የስልጠና ፍላጎትን መለየት ነው፡፡ ፍላጎት ተለይቶና ተተንትኖ እስካልቀረበ ድረስ ስልጠና ሊሰጥ አይገባም፡፡ ችግሩ አንድ ጊዜ ከተለየ በኋላ በርካታ መፍትሄዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ይሁንና ስልጠና ሁልጊዜ መፍትሄ እንዳልሆነ መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡ በጣም ጠቃሚው ጉዳይ በእውቀት፣ ክህሎትና ተነሳሽነት ላይ እጥረት በተከሰተ ጊዜ የተወሰነ መደበኛ ስልጠና ሊያስፈልግ ይችላል፡ ምን መሰልጠንና ማሰልጠን እንደሚገባን ለመወሰን በቅድሚያ መሰልጠን የማንፈልገውን ተግባርና ርዕስ አስቀድመን መወሰን የግድ ነው፡ ፡ በእርግጥም ስልጠና ከፍተኛ ዋጋ ያስወጣል፡፡ ይህም ማለት የጊዜና ገንዘብ ብክነትን ለመቀነስ ስልጠና በሚገባ ታስቦበትና ታቅዶ መመራት ይኖርበታል፡፡

አዲስ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና ፕሮግራምን በሚመለከት በዕቅድ ሂደት ላይ በመጀመሪያ ደረጃ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት (TNA) ያስፈልጋል፡፡ በአንድ በተወሰነ ቦታ አርሶ/አርብቶ አደሮች ወይም የመስኖ ተጠቃሚዎች በዋናነት አዲስ አሰራርና ቴክኖሎጂን ለማሻሻል፣ ለማስተካከል እና ለማላመድ ጥናቱን ይፈልጉታል፡፡ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የተቀናጀ የስልጠና ዑደት ክፍል የሆነና በሁለንተናዊ የአስተቃቀድ ሂደት ዋነኛ መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም አሁን ምን እንዳለ እና ምን መሆን እንደነበረበት ሲታይ በመካከላቸው ያለውን ክፍተት የመለየትና መሸጋገሪያ የማበጀት አጠቃላይ ግብ የአብዛኛው ስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ፕሮግራም የጋራ የሆነ ጉዳይ ሲሆን በአረዳድና በአፈጻጸም ሂደት ብዙ ልዩነት ይኖራል፡፡

በሥርዓት የተቀረፀ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አጠቃላይ ሂደት ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- ☞ ተጠቃሚዎችን /ታርጌት ግሩፕን/ መወሰን፤
- ☞ ፍላጎትን መለየትና ትርጉም መስጠት፤
- ☞ የብቃት ውስንነቶችን መለየት፤
- ☞ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፤
- ☞ ከዳሰሳ ጥናቱ በመነሳት የስልጠና ግቦችን ማስቀመጥ፡፡

## 6.2.1 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አስፈላጊነት

የስልጠና ዳሰሳ ጥናት በስልጠና የትኛውን ችግር ለመለየትና እና ችግሮቹን እንዴት መፍታት እንደሚገባ የመሰኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያውና የልማት ሰራተኛው እንዲወስን ይረዳዋል፡፡ ይሁንና የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በስልጠና ዑደት ውስጥ ሌሎች ሥራዎችንም እንደሚከተለው ያከናውናል፡፡

- መሠረታዊ መረጃን በማሰባሰብ ለመስኖ ኤክስቴንሽን ዕቅድ ማነሻ ይስጣል፡፡
- ውጤት ተኮር የሆነ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና ፕሮግራም እንዲኖር ይረዳል፡፡
- በተሻለ ሁኔታ ተጠቃሚዎችን በመለየት የስልጠናውን ውጤታማነትን ያሻሽላል፡ ፡ የትኞቹ ችግሮች በስልጠና እንደሚፈቱ እና የትኞቹ ሌላ መልኩ ትኩረት እንደሚፈልጉ በየመልካቸው ለይቶ ያስቀምጣል፡፡ ስልጠና የሚፈልጉ ባለሙያዎች ወይም አርሶ/አርብቶ አደሮች ምን ዓይነት ስልጠና እንደሚፈልጉ ይለያል፡፡
- የስልጠና ዳሰሳ ጥናት ሌላው ጥቅም ከበርካታ የታወቁ ችግሮች መካከል ጥቂቶቹን ለማስወገድና ለመምረጥ ይረዳል፡፡ ለምሳሌ ጥልቅ የሆነ የአፈር ኬሚስትሪ፣ ውስብስብ የውሃ ምህንድስና የሂሳብ ቀመሮችን ከጊዜ አጠቃቀምና ሰልጣኞች ፍላጎት አኳያ አስፈላጊ ላይሆኑ የችላሉ፡፡
- ሰልጣኞች የሚያወቋቸውን ርእሶች በመተው ወይም በመቀነስ የሚጎድላቸው ዕውቀትና ክህሎት ላይ ትኩረት በማደረግ የስልጠና ይዘትን እንድንቀርፅና የስልጠና መርጃ እንድናዘጋጅ ያግዛል፡፡
- የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ለስልጠናው የሚመጥን ሰፋ ያለ የስልጠና ቁሳቁስ (ማቴሪያሎች) ዝግጅትና የተሳካ ስልጠና እንዲኖር የሚከተሉት ላይ ተመርኩዞ ያቀርባል፡፡ እነርሱም፡-
- የሚሰጡ የስልጠና ዓይነቶች፤
- የስልጠና ቦታዎች፤
- የስልጠና ተግባራት መርሀ-ግብር፤
- የሚያስፈልጉ ሀብቶች/Resource
- የስልጠና ቁሳቁስ /ማቴሪያሎችና ዘዴዎች መረጣ፣ ዝግጅት እና ማላመድ

## 6.2.2. የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አተገባበር

የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ አራቱን (4ቱን) መሠረታዊ የስልጠና ዳሰሳ ጥናት ደረጃዎች መከተል ያስፈልጋል፡፡

| |
|---|
| **አራቱ ደረጃዎች፡-** |
| ደረጃ 1፡- የክፍተት ዳሰሳ ጥናትና ትንተና ማካሄድ፤ |
| ደረጃ 2፡- የችግሮችን ደረጃ ማውጣትና ተጠቃሚዎችን (target) መለየት፤ |
| ደረጃ 3፡- የአፈጻጸም ችግሮች ወይም የመልካም አጋጣሚዎችን ምክንያቶች መለየት፤ |
| ደረጃ 4፡- መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉትንና ምቹ አጋጣሚዎችን መለየት፡፡ |

**ደረጃ 1፡-** የክፍተት ዳሰሳ ጥናትና ትንተና ማካሄድ፡- የክፍተት ዳሰሳ ጥናትና ትንተና ማካሄድ ማለት የመስኖ ልማት ማነቆ/ክፍተት የሆኑ ችግሮች የሚለዩበትና የመጀመሪያ ደረጃ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አፈጻጸም ከግቡ አኳያ ያለበትን ደረጃ ማረጋገጥ ማለት ነው፡፡ ይህ በሁለት ክፍሎች ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

- ☞ አሁን ያለውን የመስኖ ልማት ሁኔታ መተንተን፡- አሁን ያለውን የእውቀት፣ የክህሎትና ተነሳሽነት ደረጃ እና ከተቋሙ ዓላማና ግዴታ አኳያ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባራትን መረዳት፡፡

- ☞ የሚፈለግ የመስኖ ልማት ለውጥን ማስቀመጥ፡- ይህ የሚፈለግ የመስኖ ልማት የሥራ ደረጃ በስኬት ለማከናወን የሚያስፈልጉ ክህሎቶች፣ እውቀት እና ችሎታዎች ላይ ያተኩራል፡፡ በዚህ ላይ አሁን በተጨባጭ ያሉ ፍላጎቶችና ግንዛቤ መካከል ያለውን ልዩነት መለየት ይኖርብናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተመለከተው ፍላጎት ስንል አሁን ባለ ሁኔታና (አሁን ያለው ምንድን ነው) እና ተፈላጊ ሁኔታ(ምን መሆን ነበረበት) መካከል ያለውን ክፍተት ነው፡፡ ይህ ግንኙነት እንደሚከተለው ተብራርቷል፡፡

- ምን መሆን ነበረበት = ተፈላጊ ሁኔታዎች
- ፍላጎት = ልዩነት ወይም ከሚገባው በታች ያነሰ/የጎደለ
- ምንድን ነው = አሁን ያለ ተጨባጭ ሁኔታ

ማስታወሻ፡- የመስኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን የኤክስቴንሽን ሥራውን ጥልቀጥና ግንዛቤ በማገናዘብ ከአርሶ/አርብቶ አደሮችን አቅምና ፍላጎት ጋር የተጣጣመ መሆን አልበት፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በተሻለ የስልጠና መረጣ ወይም አቅርቦት ችግሩን መቅረፍ እንችላለን፡፡ በሁለተኛው አካሄድ ደግሞ የመስኖ ሥራውን ከመስኖ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና አርሶ/አርብቶ አደሮች ጋር ማድረግ ደግሞ የመስኖ አሰራሩንና ቴክኖሎጂዎችን እንደገና መንደፍ (redesign) ወይም ተከታታይ የሆነ ተግባር ተኮር የመስክ ድጋፍ በመስጠት ማቅረብ ማለት ነው፡፡

ከላይ የቀረበው ሀሳብ በመስኖ ኤክስቴንሽን የአፈጻጸም ክፍተቶች ላይ የተገነዘብናቸው ችግሮች ሁሉም በስልጠና እጥረት የተከሰቱ እንዳልሆነ ወይም እንደማይሆን እንድንረዳና አልፎ አልፎ በውስጥ ባለ አለመግባባት፣ ዝቅተኛ የስራ ተነሳሽነት ወ.ዘ.ተ. በሆኑ ምክኒያቶች ሊሆን እንደሚችል ለማሳየት ነው፡፡ የመስኖ ስልጠና ከመስጠታችን በፊት ለተፈጠረው የስልጠና ፍላጎት ትክክለኛውን ልዩነት በመግለጽ መሰረታዊ ምክንያቶቸን በማወቅና በመረዳት ሌሎቸ አማራጭ መፈትሄዎችንም ለመየትና ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት ይረዳናል ማለት ነው፡፡

## 6.2.3 የፍላጎት መጠንን መረዳት (Need Level)

ስልጠና ሲሰጥ በተደጋጋሚ ከሚታዩ ችግሮች መካካል አንዱ ሰልጣኞች በሙሉ በሚሰጠው ስልጠና ላይ አንድ ዓይነት እውቀትና ክህሎት አላቸው ብሎ ማሰብና የስልጠናውንም ይዘት በዚሁ ልክ ማዘጋጀትና ስልጠና መስጠት ነው፡፡ በርግጥ ከስልጠናው በፊት የስልጠና ተሳታፊዎችን ዕውቀትና ክህሎት ማወቅ ያስቸግራል፡፡ ይህም በቂና ትክክለኛ የሆነ መሰረታዊ የተሳታፊዎች መረጃ ስለሚቸግረን የሚከሰት ነው፡፡ ነገር ግን በስልጠና ዳሰሳ ጥናት ወቅት የሚከተሉትን መስፈርቶች በመጠቀም የስልጠና ተሳታፊዎች የስልጠና ፍላጎት መጠንን መረዳትና ደረጃን በማወቅ ስኬታማ ስልጠናን ለመስጠት ይረዳል፡፡

ሠንጠረዥ- 1 ፡-የስልጠና ፍላጎት መጠንና ደረጃ

| ተ/ቁ | ያለ እውቀት/ ክህሎት ደረጃ | ትርጉም |
|---|---|---|
| 1 | ግንዛቤ የሌለው/ ባዶ | በተነሳው የስልጠና ርዕስ ላይ ምንም አይነት ግንዛቤ፣ እውቀትና ክህሎት የሌለው |
| 2 | ጉድለት | ጥቂት አጠቃላይ ግንዛቤ ግን በቂ ያልሆነ እውቀት/ክህሎት |
| 3 | በቂ | ለመፈፀም በመጠኑ በቂ እውቀት ወይም ክህሎት ግን የቀልጣፋ አፈጻጸም እጥረት |
| 4 | ትክክለኛ አፈጻጸም | በአፈጻጸም ትክክለኛ የሚፈለገውን ተግባር ለማሳካት የሚፈለገው ደረጃ |
| 5 | ፍጹምነት | የአፈጻጸም ትክክለኛነትንና ከበቂ ፍጥነትና ጥራት ጋር ያለው "በጣም ጥሩ " ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ በብዛት አይገኝም |

## 6.3. የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ደረጃዎች

### ደረጃ 1፡- ክፍተትን መተንተን

የዚህ ተግባር ዋነኛ ድርሻ የአርሶ/አርብቶ አደሮችን ትክክለኛ አፈጻጸም አሁን ካለው ወይም አዲስ ከሚቀረፀው የጥራት ደረጃ አንጻር ማረጋገጥ ነው፡፡ ለዚህ 2 ክፍሎች አሉት፡-

**አሁን ያለ ሁኔታ፡-** በተለይም በአነስተኛ መስኖ፣ የማህበረሰብ ኩሬ፣ ጥቃቅን የመስኖ አውታሮች ላይ አሁን ያሉ የአርሶ/አርብቶ አደር ክህሎቶች፣ የእውቀት እና ችሎታዎች ደረጃ ማወቅ እና

**ተፈላጊ /አስፈላጊ ሁኔታ፡-** ይህ ትንተና የሚያተኩረው በአስፈላጊ የመስኖ ሥራ የጥራት ደረጃና ብቃት ለማሳካት የሚያስፈልጉ ክህሎቶች፣ እውቀት እና ችሎታዎች ላይ ነው፡፡

ከዚህ በታች ያሉት ጥቂት ጥያቄዎች በአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ/የማህበረሰብ ኩሬ ውስጥ ለተገኙ ችግሮች ስልጠና መፍትሄ ስለመሆኑ ለማወቅ ይረዳሉ፡፡

- ☞ በመስኖ አውታሮች ውስጥ የተለዩ ችግሮች በስልጠና ወይም በሌላ የሰው ሀብት ልማት ተግባራት ሊፈቱ የሚችሉ ናቸውን?
- ☞ አሁን ያልታዩ ነገርግን በውጫዊ ለውጥ ምክንያት የሚኖሩ አዳዲስ ሂደቶች እና ቁሳቁሶች፣ ውጫዊ ውድድሮች የመጣ ለውጥ ችግሮች አሉን?
- ☞ አርሶ/አርብቶ አደሮች ስልጠና በመውሰዳቸው ምክንያት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን ለምደው ምርትና ምራታማነታቸውን ጨምረው ያውቃሉ?
- ☞ አርሶ/አርብቶ አደሮች ከድክመታቸው ይልቅ ጥንካሬያቸውን ስራ ላይ ለማዋል እድል ግገኝተው/ተሰጥቷው ያውቃሉ?
- ☞ አርሶ/አርብቶ አደሮች ችሎታቸውን ወደ አዳዲስ የአፈጻጸም ደረጃ በማንቀሳቀስ ተግባራዊ የአቀራረብ ዘዴ ማግኘት ችለዋልን? ለምሳሌ፡-የአርሶ/አርብቶ አደሮች በቡድን መደራጀትና ተያያዥ ተግባራት ምርታማነታቸውን ለማሻሻል ረድቷቸዋልን?
- ☞ ስልጠና እንዲሰጥ አስገዳጅ የውስጥና የውጭ ሀይል አለን? የኤክስቴንሽን ፕሮግራሞች እንዲተገበሩ የሚያስገድዱ ፖሊሲዎችና የአመራር ውሳኔዎች አሉን?

### ደረጃ 2 ፡- ጠቃሚና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የስልጠና ርዕሶችን መለየት

በመጀመሪያው ደረጃ በአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ እንዲሁም በማህበረሰብ ኩሬ ያሉ ፈላጎቶችን በሙሉ መዘርዘርና ቀጥሎም በደረጃ ማስቀመጥ ይገባል፡፡ ይህን ስናደርግ ለተቋማችን ዓላማ/ግብ ስኬት ያለውን ፋይዳና ይህንኑም ለማሳካት

የሚያስከትለው ውስንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደየ አንገብጋቢነታቸው ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

### ደረጃ-3፡- የአፈጻጸም ችግር መንስኤዎችን መለየት

በደረጃ ሁለት ላይ የተቀመጡትን የስልጠና ርዕሶች/ችግሮች በቅደም ተከተል ካወቅን በኃላ መሰረታዊ የችግሩ መንስኤዎች/ምንጮች ምን ምን እንደሆኑ የመስኖ አውታሮቹ ላይ ከሚታየው የስራ ክንውን በመነሳት መደምደሚያ ላይ ለመድረስና ለመወስን የሚከተሉትን ሁለት ጥያቄዎች ማንሳትና መረዳት ተገቢ ነው፡፡ በሚለዩ ፍላጎቶች ሁልጊዜ ሁለት ጥያቄዎችን እንጠይቃለን ይህም፡-

☞ አርሶ/አርብቶ አደሮች/ባለሙያዎች ሥራዎቻቸውን በሚፈለገው ልክ ውጤታማ ሆነው እያከናወኑ ነው?

☞ አርሶ/አርብቶ አደሮች እና ባለሙያዎች ሥራዎቻቸውን እንዴት መተግበር እንደሚገባ ያውቃሉን?

☞ በሁለቱም ማለትም አሁን ለአለው ሁኔታ እና ወደፊት ለሚደረግ ዝግጅት ባለሙያዎችና አርሶ/አርብቶ አደሮችን ሥራዎቻቸውን፣ አፈጻጸማቸውን በጥልቅ መመርመርና መተንተንን ይጠይቃል፡

### ደረጃ-4፡- ምቹ አጋጣሚዎችን መለየትና መፍትሄ መስጠት

ለአርሶ/አርብቶ አደሮች ወይም ባለሙያዎች ሥራዎቻቸውን በትክክልና ውጤታማ ሆነው እያከናወኑ ከሆነ የያዙትን እንዲቀጥሉበት መተው ያስፈልጋል "ካልተሰበረ አትጠግነው" እንዲሉ፡፡ ይሁንና አርሶ/አርብቶ አደሮችንና አፈጻጸማቸውን ወደ አዲሱ አቅጣጫ ለማንቀሳቀስ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ትንሽ ስልጠና እና/ወይም ሌላ የድጋፍ ጣልቃ ገብነት ማስፈለጉ አይቀርም፡፡ ነገር ግን አርሶ/አርብቶ አደሩ ሥራዉውን ውጤታማ ሆኖ እያከናወነ ካልሆነ ስልጠና የሚያስፈልገው በእርግጥም ችግሩ የእውቀትና ክህሎት ውስንነት ነው፡፡ ይህም በስትራቴጂክ ዕቅድ፣ አደረጃጀቱን መልሶ በማዋቀር፣ በውጤታማ የቡድን ምስረታና በጠንካራ አመራር ሊታገዝ ይችላል፡፡ የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ወይም የልማት ሠራተኞች የድጋፍ ጣልቃ ገብነት ያስፈልጋል ማለት ነዉ፡፡

## 6.4. የአርሶ አደሮችን የስልጠና ፍላጎት መለየት

በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ የስልጠና ፍላጎት የሚኖረው በ "አሁን ባለ ተጨባጭ ሁኔታ" እና "ምን መሆን ነበረበት/አለበት" መካከል ልዩነት ሲኖር ነው፡፡ ልዩነቱ ሠልጣኞቹ ሥራዎቻቸውን ውጤታማ ሆነው ለማከናወን የሚፈልጉት እውቀት፣ ተነሳሽነት፣ ወይም ክህሎት ሊሆን ይችላል፡፡ የፍላጎት ትንተና ሂደት በሁለት የተለያዩ ቅደም ተከተል ምዕራፎች ሊከፈል ይችላል፡-

ሀ. አብይ ስራን መተንተን (“ምን መሆን አለበት”ን መለየት) ይህም የሚያካትተው፡-

☞ ተግባር (Activity)፤

☞ ዝርዝር ተግባራት (Task)፤

☞ ድርጊት (Action)፤

☞ የድርጊት ደረጃ (Steps)፤

ለ. ክፍተት ልየታ (“ምንድን ነው?” የሚለውን መለየት)

☞ የሰልጣኝ ክህሎት ግመታ፤

☞ “ምን መሆን ነበረበት/አለበት“ ከሚለው ጋር ማነፃፀር

### 6.4.1 የስራ ትንተና ማካሄድ

አብይ ስራን መተንንተን ማለት በዘርፉ ውስጥ ያሉ ተግባራትን (Activites) መዘርዘር ማለት ሲሆን በአንድ የአብይ ስራ ትንተናም ውስጥ በረካታ ተግባራት (Activites) ይኖራሉ፡፡ እያንዳዱ ተግባር ደግሞ በስሩ በርካታ ቁጥር ያላቸውና የተመረጡ ዝርዝር ተግባራት (tasks) የያዘ ነው፡፡ የእያንዳንዱ ሙያ ዝርዝር ተግባራት ትንተና ለማጠናቀቅ የተፈለጉ በርካታ ቁጥር ያላቸው የድርጊቶች (action) አሉ፡፡ ስለዚህ የእያንዳንዱ ድርጊት ትንተና በርካታ ቁጥር ያላቸው የተካተቱ የነፍስ ወከፍ የድርጊት ደረጃዎች (stpes) ይኖሩታል ማለት ነው፡፡

ከልየታ በኂላ ድግግሞሽ (Frequencey) ፣ተነጻጻሪ ጥቅም (Relative Importance) እና በእያንዳንዱ ዘርፍ የመማማር አስቸጋነት (Learning Difficulty) ይለያሉ፡፡ በሚከተለው የመመዝገቢያ ሠንጠረዦች ወይም ቅጾች በመመዝገብና በማደራጀት ለሚፈለገው ተግባር መጠቀም ይቻላል፡፡

☞ ተግባር መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ፣

☞ የዝርዝር ተግባር መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ፣

☞ የድርጊት ደረጃ መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ፣

☞ የድርጊት ትንተና መመዝገቢያ ቅጽ፣

☞ የደረጃ ትንተና መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ ይገኙበታል፡፡

በመጨረሻ ክፍል ላይ (በዕዝል 11) ባዶ መመዝገቢያ ሠንጠረዦች/ቅጾች ተያይዘዋል፡፡ ስልጠናውን የሚያደራጀው/አሰልጣኙ የሥራ ትንተና ለማካሄድ ሲወስን የመመዝገቢያው ሠንጠረዥ/ቅጽ ፎቶ ኮፒዎች ሊሰራባቸው ይችላል፡፡ ዝርዝር ተግባራት ልየታና ትንታኔ የሚጠቅመዉ፡-

- ለሥራው ምን ሙያ እንደሚያስፈልግ ለማወቅ፣
- ለየትኛው ተግባር በቂ ችሎታ መኖሩን/አለመኖሩን ለማረጋገጥ፣
- በጣም ጠቃሚ የሆነውን ተግባር ለማወቅ/ለመወሰን ሲሆን፤

ድርጊትና የድርጊት ደረጃዎችን መለየትና መተንተን የሚጠቅመው፡-

- ተግባራትን ለመፈፀም የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ ክህሎቶችን እና እውቀቶችን ለመለየት፣
- የስልጠና ርዕሶች/ኮርሶቹ እንዴት እንደሚሰጡና እንደሚዘጋጁ ለማወቅ፣
- ይዘቱ ምን መሆን እንዳለበት እና ለእያንዳንዱ ርዕስ /ኮርስ/ ምን ያህል ጊዜ እንደሚያስፈልግ ለማወቅ/ለመወሰን ነዉ፡፡ የሚከተለው የዚህ ሂደት ምሳሌ ነው፡፡

ሠንጠረዥ- 2፡-የተሟላ የስልጠና ልየታ ሂደት መመዝገቢያ

| አብይ ሥራ/job | ተግባር/Activity | ዝርዝር ተግባር (Task) | ድርጊት (Action) | ደረጃ (Step) |
|---|---|---|---|---|
| አትክልት ማምረት | መሬት ዝግጅት ዘር መረጣ<br>ችግኝ ጣቢያ ዝግጅት<br>መዝራት ችግኝ ጣቢያ እንክብካቤ ማዛመት<br>የውሃ አስተዳደር<br>ማዳበሪያ መጨመር<br>ማረም ተባይና በሽታ ቁጥጥር ማማረት / መቀናበር | የተባይ ቅኝት ተባይ መለየት<br>በሽታ ልየታ<br>የመቆጣጠሪያ ዘዴን መለየት ጥቅም ላይ የሚውል መጠንን መወሰን/ማወቅ<br>ተመጣጣኝ ዋጋን መወሰን/ማወቅ ናፕሳክ<br>መርጫን መጠቀም<br>የቁጥጥር ውጤትን<br>መዳሰስ | (ድርጊቶች)<br>ቁሳቁስን ማረጋገጥ<br>ማስተካከል<br>ማደባለቅ<br>መከላከል<br><br>መርጫ መጠቀም<br>ማጠናቀቅ | (ደረጃዎች)<br>ግፊትን መቆጣጠር<br><br>እርምጃ/ ፍጥነት<br>የመርጫ ጫፍ ከፍታ<br>የሽፋን ስፋት |

- አርሶ/አርብቶ አደሩ የሚተገብራቸውን ሥራዎች ለመተንተን የሚያግዙ ከላይ የተጠቀሱት አራቱን የአቀራረብ ዘዴዎች መጠቀም ይቻላል፡፡ እነዚህም የአቀራረብ ዘዴዎች ተግባር፣ ዝርዝር ተግባር፣ ድረጊት አና ደረጃዎች የሚታወቁ ሲሆን አርሶ/ አርብቶ አደሮችም እነዚህን እንዲገልፁ በማድረግ የምንፈልገውን መረጃ ማግኘት እንችላለን፡፡ የስልጠና ልየታ መመዝገቢያ ባዶ ቅፁን በዕዝል 12 ይመልከቱ.

ይህንንም መረጃ ለመሰብሰብ የሚከተለውን አተገባበር ዘዴዎች (methods) መጠቀም ይችላል፡፡

☞ ከአርሶ/አርብቶ አደር ቡድኖች ጋር ስብሰባ ማካሄድ፤

☞ የመስክ ምልከታ እና ከአርሶ/አርብቶ አደሮች ጋር ቃለ-መጠይቅ ማካሄድ፤

☞ የልምምድ ተግባራትን፣ ዝርዝር ተግባራትን፤ ድርጊቶችንና ደረጃዎችን ዘርዝሮ ለአርሶ/አርብቶ አደሮች ወይም ለልማት ሠራተኞች በማቅረብ እንዲወያዩባቸውና እንዲስማሙባቸው ማድረግ፤

☞ የባለሙያዎች ድጋፍ ሰጭ ቡድን/SMS/ የእንቅስቃሴ መስኮችን እና ዋነኛ ተግባራትን እንዲለዩ እና እንዲዘረዝሩ ማድረግና፤

☞ ድርጊትና ደረጃዎች ናቸዉ፡፡

ተግባራትን መወሰን/መረዳት፡- አብይ ስራን በትክክል ለመረዳት በስሩ ያሉ ተግባራትን በመዘርዘር አንጻራዊ ጠቀሜታቸውን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ለመስራት የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች/ደረጃዎች መከተል ያስፈልጋል፡፡

ደረጃ-1. የዋና/አብይ ስራ ትንተና መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ በመውሰድና ከእያንዳንዱ ሰንጠረዥ ስር/መጨረሻ የዋና/አብይ ሥራውን ስም መጻፍ፤

ደረጃ-2. አርሶ/አርብቶ አደሩን ወይም የልማት ሰራተኛውን በመጠየቅ የአብይ/ዋና ስራውን ተግባራት በሠንጠረዡ/ቅጽ መሰረት መመዝገብ፤

ደረጃ-3. አንዱን ተግባር መውሰድና ለእያንዳንዱ ተግባር ዝርዝር ተግባራትን በሠንጠረዥ/ቅጽ ውስጥ መጻፍ፡፡ ይህን ለሁለም ለተዘረዘሩት ተግባራት መስራት፡፡

ደረጃ-4. እያንዳንዱን ዝርዝር ተግባር ምን ያህል ጊዜ ተደጋገሚ (Frequencey) እንደሆነ የሚከተሉትን መለኪያዎች/መመዘኛዎች በመጠቀም በሠንጠረዡ/ቅጽ መሰረት መመዝገብ፡-

☞ አንዳንዴ፣

☞ አልፎ አልፎ፣

☞ በየቀኑ/በየእለቱ፣

☞ በየሳምንቱ፣

☞ በየወሩ የሚሉትን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ደረጃ-5. የእያንዳንዱን ዝርዝር ተግባር አንጻራዊ ጠቀሜታ(Importance) ማወቅ/መወሰን፡- ይህንንም የሚከተሉትን መለኪያዎች/መመዘኛዎች መጠቀምና በሠንጠረዡ/ቅጽ መሰረት መመዝገብ ይገባል፡፡

- ☞ መጠነኛ ጠቃሚ፣
- ☞ መካከለኛ ጠቃሚ፣
- ☞ በጣም ጠቃሚ ናቸዉ፡፡

ደረጃ-6. የእያንዳንዱ ዝርዝር ተግባር ለመፈፀም/ለመማር አስቸጋሪነቱን (Learning Difficulty) የሚከተሉትን መለኪያዎች/መመዘኛዎች መጠቀም በሠንጠረዥ/ቅጽ መገመት፤

- ☞ ቀላል፣
- ☞ በመካከለኛ ከባድ፣
- ☞ በጣም ከባድ፣
- ☞ እጅግ በጣም ከባድ ናቸዉ፡፡

ደረጃ-7. ለእያንዳንዱ ዝርዝር ተግባር ማለትም ድግግሞሽ (Frequencey)፣ ጠቃሚነት (Importance) እና የመፈፀም/መማር አሰቸጋሪነት(Learning Difficulty) በቀላሉ የውጤት ነጥብን በመደመር ለእያንዳንዱ ዝርዝር ተግባር ጠቅላላ ነጥቡን መደመር ነዉ፡ ፡ ይህንንም በዋና/አብይ ስራ ትንተና ሠንጠረዥ/ቅጽ ተገቢ በሆነው የጎን መስመር ላይ የማጠቃለያ ድምሩን መመዝገብ አለበት፡፡ በድምር ውጤቱ ከፍተኛ ነጥብ ያመጣውን/ ያገኘውን ወሳኝ ዝርዝር ተግባር በመምረጥ ወደ ሚቀጥልው የድርጊት ማወዳደሪያ ስራ መሄድ ይገባል፡፡ ዋና/አብይ ሥራ፡ የአትክልት ማምረት

| ተግባራት | የድግግሞሽ (Frequencey) | ጠቃሚነት (Importance) | የአፈፃፀም/መማር አስቸጋሪነት (Learning Difficulty) | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|
| መስክ መረጣ | 2 | 1 | 2 | 5 |
| ዕቅድ | 3 | 3 | 3 | 8 |
| የማሳ ዝግጅት | 2 | 2 | 2 | 6 |
| የዘር መረጣ | 2 | 2 | 1 | 5 |
| ችግኝ ጣቢያ/መደብ ዝግጅት | 2 | 2 | 2 | 6 |
| መዝራት | 2 | 3 | 1 | 6 |
| ችግኝ ጣቢያ መንከባከብ | 4 | 2 | 1 | 7 |
| ማዛመት | 2 | 3 | 1 | 6 |
| ውሃ ማስተዳደር | 5 | 2 | 3 | 10 |
| ማዳበሪያ መጨመር | 3 | 3 | 3 | 9 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ማረም | 3 | 2 | 1 | 6 |
| ተባይና በሽታ ቁጥጥር | 4 | 3 | 4 | 11 |
| ማምረት/ማቀነባበር | 1 | 3 | 2 | 6 |

**መግለጫ**

| ድግግሞሽ (Frequencey) | ጠቃሚነት (Importance) | የአፈፃፀም/መማር አስቸጋሪነት (Learning Difficulty) |
|---|---|---|
| 1.አንዳንዴ | 1.በመጠኑ ያህል ጠቃሚ | 1.ቀላል |
| 2. አልፎ አልፎ | 2.መካከለኛ ጠቃሚ | 2.በመካከለኛ ከባድ |
| 3.በየቀኑ/በየእለቱ | 3.በጣም ጠቃሚ | 3.በጣም ከባድ |
| 4.በየሳምንቱ | | 4.እጅግ በጣም ከባድ |
| 5.በየወሩ | | |

ከዚህ ናሙና የዋና/አብይ ሥራ ትንተና መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ ማየት እንደሚቻለው “ተባይና በሽታ ቁጥጥር” ጠቃሚ እንዲሁም በየሳምንቱ የሚካሄድ ተግባርና ለመፈፀም/መማርም አስቸጋሪ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህም ማለት ተግባሩ በጣም ጠቃሚ ለመማር/ለመፈፀምም እጅግ በጣም ከባድ እንዲሁም በየሳምቱ የተባዮችንና የበሽታን ያለበት ደረጃ በማወቅ ጉዳት እንዳይደርስ መከታተል እንደሚያስፈልግ ያስገነዝበናል፡፡ በመቀጠልም ውሃን ማስተዳደር እንዲሁ በሁለተኛነት ጠቃሚ፣ ለማማር/ለመፈፀም ግን አስቸጋሪ እንዲሁም ድግግሞሹ ከፍተኛ ነጥብ የተሰጠው ተግባር ነው፡፡  ይህን ነጥብ አሰጣጥ ሂደት በመጠቀም የበለጠ ዋነኛ በሆነው ተግባር ላይ  ስልጠናው ያተኩራል ማለት ነዉ. የየዋና/አብይ ተግባር ትንተና ናሙና ቅጽ በዕዝል 13 ላይ ይመልከቱ፡፡

ዝርዝር ተግባርን መለየት (Task break down)፡- እያንዳንዱ ተግባር በስሩ በርካታ ዝርዝር ተግባራት አሉት፡፡ እነዚህንም ዝርዝር ተግባራ ለይቶ ማወቅ በስልጠና ሂደት ላይ በየትኛው ዝርዝር ተግባር ላይ የበለጠ ማተኮርና ሰፊ ሰዓት መስጠት እንዳለብን ለማወቅ ይጠቅመናል፡፡ ይህንን የምንሰራበት መንገድም ከዋና/አብይ ተግባር ጋር ተቀራራቢ ሲሆን ዝርዝር ተግባራትን ወደ ድርጊት ተገባራት መከፋፈል ያስፈልጋል፡፡

ደረጃ-1. ተግባር መተንተኛ ሠንጠረዥ/ቅጽ በመውሰድ ከፍተኛ ነጥብ የተሰጠውንና የተመረጠውን ተግባር (task) ስም የላይኛው የሰንጠረዥ/ቅጽ መጨረሻ ይጻፋል፡፡ ይህም የእያንዳንዱን ዝርዝር ተግባር ድረጊት/ንዑስ የዝርዝር ተግባር ለመከፋፈል ይጠቅማል፡፡

ደረጃ-2. አርሶ/አርብቶ አደሩን ወይም የልማት ሰራተኛውን በመጠየቅ ዝርዝር ተግባራት በሠንጠረዡ/ቅጽ መሰረት መመዝገብ፡፡

ደረጃ-3-7- ለእያንዳንዱ ዝርዝር ተግባር በሰንጠረዥ 6. የዋና/ዐብይ ተግባር ትንተና

ናሙና ሠንጠረዥ/ቅጽ መጠቀም ድግግሞሽን፣ አንጻራዊ ጠቀሜታን እና የመማር ና መፈፀም አስቸጋሪነትን ነጥብ አሰጣጥ ዘዴን በመከተል ዝርዝር ተግባራትን ማወቅና መወሰን ይቻላል፡፡

ዋና/አብይ ሥራ- አትክልት ልማት
ተግባር- ተባይና በሽታ ቁጥጥር

ሠንጠረዥ- 4፡-ናሙና የዝርዝር ተግባር መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ

| ዝርዝር ተግባራት | የድግግሞሽ (Frequencey) | ጠቃሚነት (Importance) | ጠቃሚነት (Importance) | የአፈፃፀም/መማር አስቸጋሪነት (Learning Difficulty) |
|---|---|---|---|---|
| ተባይ ልየታ | 4 | 3 | 3 | 1 |
| ተባይ ቆጠራ | 2 | 2 | 2 | 2 |
| በሽታ ልየታ | 3 | 3 | 3 | 2 |
| የተመረጡ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች | 2 | 2 | 2 | 1 |
| የተመረጡ የተባይ/በሽታ መከላከያ መድሃኒቶች | 2 | 3 | 3 | 2 |
| ለመጠቀም መጠንን መወሰን/ማወቅ | 2 | 3 | 3 | 2 |
| ተመጣጣኝ ዋጋን ማወቅ/መወሰን | 2 | 2 | 2 | 4 |
| የናፕሳክ መርጫ መሣሪያ መጠቀም | 3 | 3 | 3 | 3 |
| የቁጥጥር ውጤትን መዳሰስ | 3 | 2 | 2 | 3 |

መግለጫ

| የድግግሞሽ (Frequencey) | ጠቃሚነት(Importance) | የአፈፃፀም/መማር አስቸጋሪነት (Learning Difficulty) |
|---|---|---|
| 1.አንዳንዴ | 1.በመጠኑ ያህል ጠቃሚ | 1.ቀላል |
| 2.አልፎ አልፎ | 2.መካከለኛ ጠቃሚ | 2.በመካከለኛ ከባድ |
| 3.በየቀኑ/በየእለቱ | 3.በጣም ጠቃሚ | 3.በጣም ከባድ |
| 4.በየሳምንቱ | | 4.እጅግ በጣም ከባድ |
| 5.በየወሩ | | |

በዝርዝር ተግባራት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ ላይ ባለው ነጥብ/ውጤት "የናፕሳክ መርጫ መሣሪያን መጠቀም" የተባይና በሽታ ቁጥጥር ተግባራትን ለማከናወን በጣም ጠቃሚ የዝርዝር ትግባራት አካል እንደሆነና የነጥብ/ውጤት አሰጣጡም ከሌሎቹ ዝርዝር ተግባራት አኳያ ከፍ ያለ እንደሆነ በሰንጠረዥ 7. ናሙና የዝርዝር ተግባራ መመዝገቢያ ሠንጠረዥ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህም ማለት የተገለው ዝርዝር ተግባር በጣም ጠቃሚ፤ለመፈፀም/ለመማር በጣም ከባድ እንዲሁም የተባይና በሽታ በሚከሰትብት ወቅት በየቀኑ የምንጠቀመው በመሆኑ በስልጠናው ወቅት ትኩረት የሚደረግበት ቁልፍ ዝርዝር የተባይና በሽታ ተግባር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ከተቀመጡት ዝርዝሮች

መካከል ከፍተኛ የድምር ውጤት/ነጥብ በማግኘት የመርጫ መሣሪያ መጠቀም ተቀዳሚ የስልጠናው ትኩረት ይሆናል ማለት ነው፡፡ ናሙና የዝርዝር ተግባር መመዝገቢያ ቅጽ በዕዝል 14 ይመልከቱ፡፡

**ዝርዝር ተግባርን መተንተን፡-** የዋና/አብይ ሥራ ትንተናን እና የዝርዝር ተግባር ቅደም ተከተል አሠራርን በመጠቀም የሚፈለጉ ተግባራትን ለመለየት እና የእያንዳንዱን አንጻራዊ ጠቀሜታ ለመረዳት ተችሏል፡፡ እነኝህን መረጃዎች በክፍተት ትንተና/gap analysis/ ከተገኙት መረጃዎች ጋር በማወዳደር ስልጠናው በየትኛው ተግባር ላይ ማተኮር እንዳለበት ይታወቃል፡፡ አሁን ደግሞ እያንዳንዱን ድርጊት/Action/ በመወሰድና እና ተግባሩን ለማጠናቀቅ የሚጠየቁ ደረጃዎች/steps መከፋፈል አለብን፡፡ ይህ ሂደት የዝርዝር ተግባር ትንተና ይባላል፡፡

የዝርዝር ተግባር ትንተና ለተግባር ተኮር ስልጠና ዕቅድ አስፈላጊ የሆነ ዘርፍ ነው፡ ዝርዝር ተግባራት ትንተና ምን ማለት/ምን እንደሆነ ለመረዳት በክህሎት፣ ተግባርና ድርጊት መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

☞ ክህሎት ማለት አንድን ተግባር ለማከናወን የሚጠየቀው ችሎታ ማለት ነው፡፡

☞ ተግባር ማለት ከዋና/አብይ ተግባር ዓላማ ጋር የተያያዘ እንቅስቃሴ ነው ማለት ነው

☞ ድርጊት ማለት የተግባር አንዱ አካል/ክፍል ነው፡፡

የዝርዝር ተግባር ትንተና ሲባል የተመረጠ ተግባርን ለማቀናጀት ሁሉንም ዝርዝር ተግባሮች መለየት፣ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ እና የድርጊት ደረጃን/ቅደም ተከተልናን ተንተርሶ የክህሎት ማሳደጊያ/ማጎልበቻ ስልጠናን ለመስጠት ይጠቅማል፡፡

የዝርዝር ተግባር ትንተና ከመጀመሩ በፊት ዝርዝር ተግባሩ ምን እንደሆነ አሰልጣኙ/ኟ (የስልጠናው አመቻች) ማወቅ አለበት፡፡ የሚከተሉትን ነገሮች በመጻፍ ይህንን ግልጽ ማድረግ ይችላሉ፡፡

☞ የዝርዝር ተግባሩ ውጤት ምን ይመስላል?

☞ ማን ዝርዝር ተግባሩን ያከናውናል/ ይሸፍናል?

☞ ዝርዝር ተግባሩ የሚከናወኑበት ሁኔታዎች፡፡

አንድ ጊዜ ዝርዝር ተግባሩ በግልጽ ከተለየ በኋላ ተግባሩን እውን የሚያደርጉ ሁሉንም ድርጊቶች መለየትና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው በተግባሩ ላይ ክህሎት ባለው ባለሙያ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ምልከታ ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ስልጠና በሚሰጥበት ጊዜ በዝርዝር ትንተና ስለሚሰጥ የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ትንተናው ከተጠናቀቀ በኃላ መጻፍ ይኖርበታል፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለው የዝርዝር ተግባራት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ በመጠቀም ነው፡፡

የሚከተለው የዝርዝር ተግባር “ናፕሳክ መርጫ መሣሪያን መጠቀም” ድረጊት ደረጃ ዝርዝር ምሳሌ ነው፡፡ ምናልባት ዝርዝር ተግባር ምን እንደሆነ ግልጽ የማይሆኑ ከሆነ

እነዚህ ተግባራት ሁለት ወይስ ከዚያ በላይ በሚል አሰልጣኙ/ኟ ራሱን/ራሷን መጠየቅ አለበት/ባት፡፡

ዋና/አብይ ሥራ ፡- የአትክልት ምርት

ተግባር፡- ተባይና በሽታ ቁጥጥር

ዝርዝር ተግባር፡- የናፕሳክ መርጫ መጠቀም

| ድርጊት | | ደረጃዎች | | |
|---|---|---|---|---|
| ድርጊት 1 | መሳሪያውን ናፕሳኩን መፈተሽ | ደረጃዎች | ሀ | ታንከሩን ማፅዳት |
| | | | ለ | መመርመር/ የመርጫ ጫፍ ጽዳት |
| | | | ሐ | የግፊት ሙከራ |
| ድርጊት 2 | ልኬት ማስተካከያ | ደረጃዎች | ሀ | የሚረጨውን ቦታ ማወቅ/መወሰን |
| | | | ለ | የሙከራ ቦታን ምልክት ማድረግና መለካት |
| | | | ሐ | ሙከራን በውሃ ማድረግ |
| | | | መ | ለሙከራ የተጠቀምነውን ውሃ ማስላት |
| | | | ሠ | የታንከሩን ጠቅላላ ይዘት ለጠቅላላ ቦታው በማካፈ ማስላት |
| | | | ረ | ምልክቱን ማንበብ |
| | | | ሰ | በየታንከሩ ኬሚካሉን ማስላት |
| ድርጊት 3 | መደባለቅ | ደረጃዎች | ሀ | የደህንነት ጥንቃቄዎች |
| | | | ለ | ተስማሚ የመለኪያ መሣሪያ |
| | | | ሐ | መለኪያ (ግምት) |
| | | | መ | መበጥበጥ |
| ድርጊት 4 | መከላከያ | ደረጃዎች | ሀ | የእጅ |
| | | | ለ | የፊትና እራስ |
| | | | ሐ | የእግር |
| | | | መ | የሰውነት |
| ድርጊት 5 | መርጫ መጠቀም | ደረጃዎች | ሀ | ግፊት መቆጣጠር |
| | | | ለ | የእግር እርምጃ/ፍጥነት መቆጣጠር |
| | | | ሐ | የመርጫ ጫፍ ቁመትን ማስተካከል |
| | | | መ | መጠነ ሽፋን መዳረስ |
| ድርጊት 6 | ማጠናቀቅ | ደረጃዎች | ሀ | ቆሻሻን ማስወገድ |
| | | | ለ | መርጫን መፅዳት |
| | | | ሐ | ኬሚካል በአግባቡ ማስቀመጥ/ማከማቸት |
| | | | መ | መታጠብ |

ሠንጠረዥ-5፡-ናሙና የድረጊትና ደረጃዎችን /Action& steps/ መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ

**የድርጊት ትንተና፡-** አሁን ዝርዝር ተግባራትን ወስነናል፣ ለዚህም ስልጠና መስጠት ጠቃሚ ነው (በምሳሌያችን "ናፕሳክ መርጫን መጠቀም") ተግባርን ለመፈፀም የሚያስፈልግ አሁን የለየነውን የእያንዳንዱ እንቅስቃሴ አንጻራዊ ጠቀሜታ መተንተን አለብን፡፡ ይህ በስልጠና ወቅት ከባድና ጠቃሚ እንቅስቃሴ በሆኑት ላይ እንድናተኩር ያግዛል፡፡ ይህ ትንተና ቀድመን በተግባርና እና በዝርዝር ተግባራት ከአካሄድነው ግምገማ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይሁንና በአሁኑ አካሄድ ሁሉም ድርጊቶች የሚስፈልጉና የማይነጣጠሉ በመሆናቸው በዳሰሳችን ወቅት ስለ ድግግሞሽ/Frequencey/ ማሰብ አያስፈልግም፡፡ ናሙና የድረጊትና ደረጃዎችን /Action& steps/ መመዝገቢያ ቅጽ በዕዝል 15 ይመልከቱ፡፡

ደረጃ-1:- የድርጊት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ በመውሰድ የዝርዝር ተግባሩን ስም የሠንጠረዡ/ቅጽ በላይኛው ጫፍ ላይ መመዝገብ:- የዝርዝር ተግባራቶቹ ከተግባር ትንተና መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ/ ከፍተኛ ነጥብ ኖሯቸው የተለዩት መሆን አለባቸው።

ደረጃ-2:- ዝርዝር ተግባርን ለመፈፀም የሚፈለጉ ሁሉንም ድርጊቶች መለየት። በድርጊት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ የደርጊት ደረጃ/ቅደም ተከተል መጻፍ፤

ደረጃ-3:- ለእንዳንዱ ዝርዝር ተግባር አስቀድሞ ተመሳሳይ ነጥብ አሰጣጥ ዘዴን በመጠቀም ድግግሞሽን፣አንጻራዊ ጠቀሜታን እና የመፈፀም/መማር አስቸጋሪነት ማወቅ/መወሰን እና ነጥቦቹን መደመር።

የሚከተለው ምሳሌ/ናሙና የናፕሳክ መርጫን መጠቀም የተባይና በሽታ ቁጥጥርን በማድርግ የአትክልት ምርትን ለማምረት የተሰራ የድርጊት ትንተና ነው።

ዋና/አብይ ሥራ:- የአትክልት አምራች አርሶ አደር

ተግባር:- ተባይና በሽታ ቁጥጥር

ዝርዝር ተግባር:- የናፕሳክ መርጫ መጠቀም

ሠንጠረዥ- 6:-ናሙና የድርጊትና ደረጃዎችን /Action& steps/ መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ

| ትግበራ | ጠቃሚነት(Importance) | የአፈፃፀም/መማር አስቸጋሪነት (Learning Difficulty) | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|
| መሳሪያውን/ናፕሳኩን መፈተሸ | 3 | 2 | 5 |
| ልኬት ማስተካከያ | 3 | 4 | 7 |
| ማደባለቅ | 3 | 1 | 4 |
| መከላከያ | 3 | 1 | 4 |
| መርጫ መጠቀም | 3 | 3 | 6 |
| ማጠናቀቅ | 3 | 1 | 4 |

መግለጫ

| ጠቃሚነት(Importance) | የአፈፃፀም/መማር አስቸጋሪነት (Learning Difficulty) |
|---|---|
| 1.በመጠኑ/ለአመል ያህል ጠቃሚ | 1.ቀላል |
| 2.መካከለኛ ጠቃሚ | 2.በመካከለኛ ከባድ |
| 3.በጣም ጠቃሚ | 3.በጣም ከባድ |
| | 4.እጅግ በጣም ከባድ |

በዚህ ትንተና የትኛው ድርጊት ብዙ የስልጠና ጊዜ እንደሚፈልግ ለመለየት ያስችላል። ይህም የሆነበት ምክንያት የትኛው ድረጊት የበለጠ ለመፈፀም/መማር እንደሚያስቸግር ያመላክታል። በዚህ ምሳሌ ሁሉም ድርገቶች ጠቃሚ እንደሆኑ ያመላክታል፣ ነገር ግን በመማር ረገድ ከባዱን ይለያያሉ። የመርጫ መሣሪያ መጠቀምና ልኬት ማስተካከያን ለመማር ብዙ ጊዜ እንደሚወስዱ እና ብዙ የመማሪያ ዝግጅትና የማስተማሪያ ክህሎት

እንደሚስፈልግ ማየት ይቻላል፡፡ ናሙና የድርጊትና ደረጃዎችን /Action& steps/ መመዝገቢያ ቅጽ በዕዝል 16 ይመልከቱ፡፡

## የደረጃ ትንተና

ድርጊትን ለማጠናቀቅ በርካታ ቁጥር ያላቸው ደረጃዎች (steps) ካሉ የእያንዳንዱን ደረጃ የመማር ክብደት ለማገናዘብ ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡ ይህም ኮርሶቹን ለማቀድ ይረዳል፡፡ ይህ ትንተና አሁንም ቀደም ሲል ከሰራነው ተግባር፣ የዝርዝር ተግባር ዳሰሳ እና ድርጊቶች ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ይሁንና በዚህ ክፍል ሁሉንም ድርጊት ማጠናቀቅ አስፈላጊ ስለሆነ የመፈፀም/መማር አስቸጋሪነትን መዳሰስ ብቻ በቂ ይሆናል፡፡

ደረጃ-1. የደረጃ ትንተና መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ መውሰድና የድርጊቱን ስም በላይኛው ሠንጠረዥ/ቅጽ ጫፍ ላይ መጻፍ፤

ደረጃ-2. ድረጊቱን ለማጠናቀቅ የሚፈለጉ ሁሉንም ደረጃዎች መዘርዝር፡፡ በእያንዳንዱ መስመር አንድ ደረጃ መጻፍ፤

ደረጃ-3፡- በእያንዳንዱ ደረጃ የሚፈልግ ሥራን ለማከናወን የመፈፀም/መማር አስቸጋሪነትን መገምት፡፡ የሚከተለውን ልኬታ ተጠቀም፡-

- ቀላል፣
- በመካከለኛ ከባድ፣
- በጣም ከባድ፣
- እጅግ በጣም ከባድ፡

የሚከተለው ምሳሌ ለዋና/አብይ- አትክልት ማምረት፣ ለተግባር- ተባይና በሽታ መከላከል፣ ለዝርዝር ተግባር-የናፕሳክ መርጫ መሣሪያ መጠቀም፣ለድርጊት- መርጨት የተዘጋጀ ነው፡፡

ዋና/አብይ ስራ፡ ሥራ አትክልት ማምረት

ተግባር፡ ተባይና በሽታ ቁጥጥር

ዝርዝር ተግባር፡ ናፕሳክ መርጫ መሣሪያ መጠቀም

ድረጊት፡ መርጫ መሣሪያ መጠቀም

| ደረጃ | የመማር ችግር |
|---|---|
| ግፊት ቁጥጥር | 3 |
| የጉዞ እርምጃ | 2 |
| የመርጫ ጫፍ ቁመት | 2 |
| ሽፋን | 3 |

- ቀላል
- በመካከለኛ ከባድ
- በጣም ከባድ
- እጅግ በጣም ከባድ

ይህ መረጃ የስልጠና ኮርስ እና የትምህርት ዕቅድ ለማዘጋጀት ይረዳል፡፡ ናሙና የደረጃ ትንተና ቅፅ በዕዝል 17 ላይ ይመልከቱ፡፡

### 6.4.2. የክፍተት ትንተና ማካሄድ

የክፍትት ትንተና (Gap Analysis) ማለት አንድን ተግባር በበቂ ሁኔታ ለመፈፀም የሚስፈልጉ መሰረታዊ የሆኑ ክህሎት/ዕውቀት ብቃቶች/አጠቃላይ ግንዛቤ መረጃ መሰብሰቢያ ስልት ነው፡፡ ይህም ማለት አንደ አርሶ/አርብቶ አደር ወይም የመስኖ ባለሙያ አሁን እያከናወነ ያለው ተግባር ከሚፈለግዉ የተግባር አፈፃፀም አንፃር ሲታይ የአፈፃጸም ብቃቱ (በእውቀቱ ና ክህሎት) አነስተኛ ሆኖ ሲገኝ የእውቀት ክህሎት ክፍተት ይባላል፡፡ ይህንንም ክፍትት ለሟሟላት የሚስፈልጉትን የሚፈለጉ የተለያዩ ተግባራትን ባለሙያውን ወይም አርሶ/አርብቶ አደሩን በመጠይቅና በተግባር ሙከራ የሚያውቀውና የሚችለውን እንዲነግረን በማድረግ ማወቅ እንችላለን፡፡ ሰልጣኙ በአሁኑ ጊዜ መስራት የሚችለው ከሚፈለገው በቂ የተግባር አፈጻጸም ጋር መወዳደር አለበት፡፡ ተግባሩ የሚፈልገውን ክህሎትና እውቀት ሰልጣኙ በአሁኑ ጊዜ እያከናወነ ካለው ከበለጠ “ክፍተት” አለ ማለት ነው፡፡ ይህ ክፍተት ነው በስልጠና መስተካከል ያለበት፡፡

**የክፍተት ትንተና ቅደም ተከተል፡-** የሚከተሉት ደረጃዎች የሰልጣኙን የክህሎት ደረጃ ለመገመት የክፍተት ልየታ አሰራርን/ቴክኒክን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ሂደቱ አጠቃላይ በመሆኑም ወደምንፈልገው አይነትን ሁኔታ መለወጥ እንችላለን፡፡ ይህ ዘዴ በመጀመሪያ በዝርዝር ተግባራት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ ውስጥ የተዘረዘሩትን ዝርዝር ተግባራት በመውሰድ እነዚህን ተግባሮች የመፈፀም ብቃት/ችሎታ ትንተና በሥራ ላይ መዋል አለበት፡፡ በዚህ ክፍል መጨረሻ በዕዝል 18 ላይ ተያይዟል፡፡

**ደረጃ 1፡-** በዝርዝር ተግባራት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ-8 ላይ ያሉትን ተግባራት ከከፍተኛ ነጥብ በመነሳት ወደ ዝቅተኛ ነጥብ በቅደም ተከተል መዘርዘር፡ - ይህም የበለጠ አሳሳቢ የሆኑትን ተግባራት ትንተና ላይ እንድታተኩር ይረዳል፡፡

**ደረጃ 2፡-** ቀጥሎ ደግሞ በዚሁ ሰንጠረዥ ዝርዝር መሰረት በአሁኑ ጊዜ ሰልጣኞች በብቃት ከማጠናቀቁትን ተግባር ደረጃ ማውጣት፡- ይህ ደረጃውን ከ1-5 በመስጠት መከናወን አለበት፡፡

ማንኛውም ክፍል መጠናቀቅ አይችልም፡፡

- ሁሉንም ዝርዝር ተግባር ማከናወን አይችልም፤
- ዝርዝር ተገባሮቹን ከግማሽ በታች ማከናወን ይችላል፤

- ከጠቅላላው ከግማሽ በላይ ማከናወን ይችላል፤
- ሁሉንም ተግባር ማከናወን ይችላል ግን በጣም ረጅም ጊዜ ይወስዳል፤
- ተግባሩን በትክክል እና በተቀላጠፈ መፈጸም ይችላል በሚሉት ሊሰራ ይገባል፡፡

ደረጃ 3፡- የብቃት ደረጃን መከለስና እና ዝቅተኛ ብቃት ያለው ተግባር ላይ ምልክት ማድረግ ፡-, ዝቅተኛ ብቃት ማለት በሚፈለግና አሁን ባለው ብቃት መካከል ክፍተት አለ ማለት ነው፡፡

ደረጃ 4፡- የተለዩት የተግባር ብቃት ማነስ ችግሮች በስልጠና ሊስተካከሉ እንደማይችሉ ታሳቢ በማድረግ በስልጠና ሊሞላ የሚችል ክፍተትን መለየት፡- ለምሳሌ፡- ተግባሩ የሚፈልገው ውስብስብ የሆነውን የኬሚካል ትንተና ማጠናቀቅ ከሆነ በአጭር ስልጠና ውጤታማ እንደማይሆን መረዳት በጣም ይቻላል፡፡

ደረጃ 5፡- በስልጠናው ተግባር ላይ የተካተቱ የዘርፉ ሙያተኞች ከሆኑ ከአንድና ከዚያም በላይ ከሆኑ ሰዎች ጋር በክፍተት ትንተና ውጤት፣ በብቃት ደረጃ እና በክፍተት መለኪያዎች ላይ መወያየት፤

የሚከተለው የድረጊት ክፍተት ትንተና መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ/ ምሳሌ ነው፡፡

ማስታወሻ፡- የዚህ ስራ ዝርዝር ተግባራት መውሰድ ያለት ድርጊት ሰንጠረዥ ውስጥ ከፍተኛ ነጥብ ወደ ዝቅተኛ በመጣው ቅደም ተከተል ላይ ነው፡፡

ዋና/አብይ ሥራ ፡- አትክልት ማምረት

ተግባር ፡- ተባይና በሽታ ቁጥጥር

ሠንጠረዥ- 7፡-የተግባር ክፍተት ትንተና መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅ

| ዝርዝር ተግባራት | የብቃት ደረጃ | ብቃት | ክፍተቱ በስልጠና ይፈታል |
|---|---|---|---|
| የናፕሳክ መርጫ መሣሪያ መጠቀም (9) | 1 | (X) | ✓ |
| ተባይ ልየታ(8) | 3 | (X) | ✓ |
| ውድ ባልሆነ ዋጋ መሆኑን ማረጋገጥ (8) | 2 | (X) | ✓ |
| በሽታ ልየታ(8) | 2 | (X) | ✓ |
| የቁጥጥር ውጤቱን ማገዝ(8) | 4 | (X) | ✓ |
| ተባዩን መለየት(7) | 3 | (X) | ✓ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጥቅም ላይ የሚውለውን መጠን ማወቅ/መወሰን(7) | 4 | (X) | ✓ |
| ተባይ ቆጠራ (6) | 4 | (X) | ✓ |
| የቁጥጥር ዘዴዎችን መምረጥ (5) | 5 | ✓ | ✓ |

**መግለጫ**

- ሁሉንም ዝርዝር ተግባር ማከናወን አይችልም፣
- ዝርዝር ተገባሮቹን ከገማሽ በታች ማከናወን ይችላል፣
- ከጠቅላላው ከግማሽ በላይ ማከናወን ይችላል፣
- ሁሉንም ተግባር ማከናወን ይችላል ግን በጣም ረጅም ጊዜ ይወስዳል፣
- ተግባሩን በትክክል እና በተቀላጠፈ መፈጸም ይችላል፣

| ብቃት አለው | ችግሩ በስልጠና ይፈታል |
|---|---|
| ✓አዎ / X የለውም | ✓አዎ / X አይፈታም |

የድርጊት ክፍተት ትንተና ደረጃ/ቅደም ተከተል (steps) ለእያንዳንዱ ተግባር በሰጠነው የተግባር ክፍተት ትንተና የብቃት ደረጃን ለማወቅ እንዲረዳ የድርጊት ክፍተት ትንተና መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ/ መጠናቀቅ አለበት፡፡ የድርጊት ክፍተት ትንተና መመዝገቢያ ቅጽ ዕዝል 19 ላይ ይመልከቱ፡፡

ደረጃ 1፡- በድርጊት የክፍተት ልየታ መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ/ ላይ የድርጊት ትንተና መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ/ የተለዩትን ድርጊቶችን መለየት፡- በድርጊት ትንተና ልምምድ ጊዜ የተለዩትን ድርጊትቶች ከከፍተኛ ነጥብ ወደ ዝቅተኛ መዘርዝር አለበት፡፡

ደረጃ 2፡- በዚሁ ሰንጠረዥ ዝርዝር መሰረት በአሁኑ ጊዜ ሰልጣኞች በብቃት የሚያጠናቅቁትን ተግባር ደረጃ ማውጣት፡- ይህ ደረጃውን ከ1-5 በመስጠት መከናወን አለበት፡፡

ማንኛውም ክፍል መጠናቀቅ አይችልም፡፡

- ☞ ሁሉንም ዝርዝር ተግባር ማካናወን አይችልም፡
- ☞ ዝርዝር ተገባሮቹን ከገማሽ በታች ማከናወን ይችላል፡
- ☞ ከጠቅላላው ከግማሽ በላይ ማከናወን ይችላል፡
- ☞ ሁሉንም ተግባር ማከናወን ይችላል ግን በጣም ረጅም ጊዜ ይወስዳል፡
- ☞ ተግባሩን በትክክል እና በተቀላጠፈ መፈጸም ይችላል፡

ደረጃ 3፡- በድርጊት የክፍተት ትንተና መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ/ ላይ ለተግባር የብቃት ነጥብን ለመወሰን ይህን መረጃ መጠቀም ይገባል፡፡

ዋና/አብይ ሥራ ፡- የአትክልት ማምረት

ተግባር፡- ተባይና በሽታ ቁጥጥር

ዝርዝር ተግባር፡- የናፕሳክ መርጫ መሣሪያ መጠቀም

ሠንጠረዥ- 8፡-የድርጊት ክፍተት ትንተና መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ቅጽ/

| ድርጊቶች | የብቃት ደረጃ | ብቃት | ክፍተቱ በስልጠና ይፈታልን? |
|---|---|---|---|
| (7) ማስተካከል | 1 | (X) | (✓) |
| (6) መርጫ መጠቀም | 2 | (X) | (✓) |
| (5) ቁሳቁስ ማረጋገጥ | 1 | (X) | (✓) |
| (4) ማደባለቅ | 2 | (X) | (✓) |
| (4) መከላከል | 5 | (X) | (✓) |
| (4) ማጠናቀቅ | 4 | (X) | (✓) |

መግለጫ

- ሁሉንም ዝርዝር ተግባር ማካናወን አይችልም፡
- ዝርዝር ተገባሮቹን ከግማሽ በታች ማከናወን ይችላል፡
- ከጠቅላላው ከግማሽ በላይ ማከናወን ይችላል፡
- ሁሉንም ተግባር ማከናወን ይችላል ግን በጣም ረጅም ጊዜ ይወስዳል፡
- ተግባሩን በትክክል እና በተቀላጠፈ መፈጸም ይችላል፡

ብቃት አለው — ✓አዎ / X የለውም

ችግሩ በስልጠና ይፈታል — ✓አዎ / X አይፈታም

## 6.5 ውጤታማ የኤክስቴንሽን ስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት

በተጨባጭ ውጤታማ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ዝግጅትንና ተግባራዊነቱን በርካታ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሊያስተጓጉሉት የሚችሉ ሲሆን በኤክስቴንሽን ስልጠና ፕሮግራም ከሚከሰቱ የሀብት ውስንነቶች ባሻገር በርካታ ችግሮች ይነሳሉ፡፡ ብዙዎቹ ችግሮችም የፅንሰ ሀሳብና የተቋም ባህሪ ያላቸው ናቸው፡፡ በመስኖ ግብርና ኤክስቴንሽን ላይ የግንዛቤ ውስንነት በመኖሩ በስፋት የመስኖ ኤክስቴንሽንን ከዝናብ ግብርና ኤክስቴንሽን አሰጣጥ ጋር ማዘበራረቅ የታያል፡፡ ለእነዚህ ጉዳዮች ቀደም ብሎ ግንዛቤ መፍጠርና በአጠቃላይ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ልምምድን ለመንደፍ ያግዛል፡፡

### 6.5.1 ፍላጎትን መረዳት

አንድ ግልጽ የሆነ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት መሰናክል ፍላጎትን መረዳት ያለመቻል ችግር ነው፡፡ ይህን ችግርን ለማቃለል ተለይተው የሚታወቁና ያልተለዩ ፍላጎቶችን መለየት ወሳኝ ነው፡፡ የመጀመሪያው ፍላጎት የመስኖ አርሶ/አርብቶ አደሮች የተቀበሉት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በስፋት ያልተተገበረ/ያልተገለፀ ፍላጎት ነው፡፡ ተቀባይነት ያገኘው ፍላጎት የሚበረታታ ወይም ክፍተትን ለመሙላት በፍጥነት ወደ ትግበራ የሚገባበት ነው፡፡ ሆኖም ግን በሰልጣኙ ዘንድ ሰፊ የእውቀትና ክህሎት ክፍትት ሆኖ ሲገኝ ለመስኖ ኤክስቴንሽን ስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የሚያስቸግር ነው፡፡

☞የስልጠና ፍላጎትን መረዳት መቻል

☞ ያልተለዩ ፍላጎቶች (unfelet needs)

- ☞ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አፈጻጸም ችግርን በአጠቃላይ አለመገንዘብ፤
- ☞ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች አፈጻጸም ችግርን መገንዘብ ነገር ግን ችግሩ የስልጠና እጥረት መሆኑን አለማወቅ፡፡

☞ የተለዩ ፍላጎቶች (feelt needs)

- ☞ የአፈጻጸም ችግርን መረዳት፣ የሚፈለገውን የስልጠና ዓይነት መለየት፣ ነገር ግን መጠኑን አለማወቅ፤
- ☞ የአፈጻጸም ችግርን መረዳት፣ የስልጠና መጠንንና ዓይነትን መለየት መቻል፡፡

### 6.5.2 የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የአቀራረብ/ ዘዴ (Need Assessment Approaches)

የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የሚፈለገውን የስልጠና ዓይነት መለየት ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ፍላጎትም የባለሙያ፣የተቋማትና እና በስራቸው ያሉ አካላትን (መምሪያዎች፣ ክፍሎች እና ግለሰቦች) ያካትታል፡፡

1. ተቋማዊ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አቀራረብ፡- በተቋም ወይም በቡድን እና በቢሮዎች ውስጥ የሚፈለጉ የስልጠና ዓይነቶችን መለየት ይጠቅማል፡፡ ለምሳሌ የኤክስቴንሽን የስራ መምሪያ/የስራ ክፍል፣ የዕቅድና ክትትል መምሪያ/የስራ ክፍል፣ የገበያ መምሪያ/የስራ ክፍል ወ.ዘ.ተ.

2. የሙያ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አቀራረብ፡- በአንድ የሙያ ዘርፍ ውስጥ አንድን ሥራ ወይም ተግባር ለማከናወን ባለሙያዎችን ያላቸውን አመለካከት እና ዕውቀት ማጎለበትን/ማሳደግን ያካትታል፡፡ የተለየ ዓይነት ሥራ ለማከናወን ያለዉን የእውቀት ክፍተትን ለመተግበር ይጠቅማል፡፡

3. የተናጠል የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አቀራረብ፡- ከላይ የተገለፁት የተቋምና የሙያ ክፍተት ዳሰሳ ጥናቶች ማን ምን አይነት ስልጠና ያስፈልገዋል ወደሚል ድምዳሜ ይመጣና የዳሰሳ ጥናቱ በእያንዳንዱ ባለሙያወይም አርሶ/አርብቶ አደር ደረጃ ይተነተናል፡፡ የዚህ አይነቱ አቀራረብ የተናጠል የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አቀራረብ ይባላል፡፡ ይህም የትኛው ባለሙያ ወይም አርሶ/አርብቶ አደር ምን አይነት ስልጠና ቢደረግለት የአሰራርና ቴክኒካል እውቀቱንና ክህሎቱን አሳድጎ ተቋሙን ከእርሱ ተጠቃሚ ያደርጋል የሚለውን ለመመለስ ይጠቅማል፡፡

ይሁንና የፍላጎት ልየታ የሚካሄድባቸው እያንዳንዱ የሚወከልበት የተለየ እይታ ወይም ገጽታ አለው፡፡ ተቋሞች ውስጥ በእውቀትና ክህሎት እጥረት ምክንያት ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የዚህ ውጤትም የሥራ መጓተትና ቶሎ አለመጠናቀቅ፣ ተደጋጋሚ ስህተቶች፣ በሪፖርት ያለመርካት፣ ግልጽ ያልሆነ የአሠራር ሥርዓት ወይም በብዛት ከሥራ መቅረት ናቸው፡፡

- ☞ አዳዲስ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች፣ ተሞክሮዎች፣ ሂደቶች እና ቁሳቁስ በሚፈለገው ፍጥነትና ስፋት ሳይደርሱ ሲቀሩ በስልጠና የአቅም ግንባታን ፍላጎትን ሊያግዱ ይችላሉ፡፡

- ☞ አልፎ አልፎ የግዴታ ስልጠና ሊሰጥባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ፡ -ፖሊሲዎች ወይም የአመራር ውሳኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ስልጠና መሰጠትና ብዥታዎችን ማስወገድ ያስገልጋል፡፡

## 6.5.3 የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ቴክኒክ

ትክክለኛ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ የጥናት ስዕል ለማግኘት በርካታ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ዘዴዎችን መጠቀም የበለጠ ጠቃሚ ነው፡፡ ብዙ ዓይነት የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ቴክኒኮች አሉ፡፡ ቀደም ሲል ከነበሩት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናቶች በመነሳት፣ የኤክስቴንሽን ባለሙዎች በሥራ አካባቢዎች ተገኝተው በቀጥታ ምልከታ ማካሄድ፣ መጠይቆችን፣ ሥራ ቦታ ላይ ሰዎችን ማማከር፣ ተገቢ ጽሁፎችንና ሰነዶችን መቃኘት፣ ቃለ መጠይቅ ማካሄድ፣ የቡድን ውይይት ማካሄድ፣ መፈተን ወይም ሙከራ በመስጠት፣ መዝገቦችን ማገላበጥ (የተቀጣሪዎችን ወይም የሠራተኞችን ፋይል)፣ የሥራ መዘርዝርን ማየት እና የሪፖርት ጥናትና ወካይ ሥራዎችን መዳሰስ ያስፈልጋል፡፡

## 6.5.4 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠናዎችን ቅደም ተከተል መለየት

ካሉት ሰፊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክህሎት እና ሌሎች ብቃቶች ውስጥ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እንደ ሁኔታው ለስልጠና ቅድሚያ መስጠቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ስልጠናዎችን ቅድሚያ ለመስጠት የሚከተሉትን መስፈርቶች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

☞ **ጠቃሚ/አስፈላጊነት (Essential/Desirable) የስልጠና ማወዳደሪያ፡-** ለመስኖ ኤክስቴንሽን የሥራ ዓላማ እና ተቋማዊ የሥራ ክንዋኔ አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ እያንዳንዱን እንቅስቃሴ (ክህሎት/skill/፣ችሎታ/compettency) ለይቶ ማስቀመጥ፡፡ የመስኖ ኤክስቴንሽን ስልጠና ቅድሚያ የሚሰጠው አስፈላጊ ብቃቶችን ለማሳደግ እንደሆነ ግልጽ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

☞ **ጠቃሚ/ችሎታ የስልጠና ማወዳደሪያ፡-** ከፍተኛውን የክህሎት ቅደም ተከተል የሚያመለክቱ ሲሆኑ ለተቋማዊ ተግባራት ክንውን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውና ለመተግበር ግን ዝቅተኛ ችሎታ የሚታይባቸውን ጉዳዮች የስልጠናው ተቀዳሚ ትኩረት ይሆናሉ፡፡

☞ **የከባድ፣ ጠቃሚ እና ተደጋጋሚነት የስልጠና ማወዳደሪያ፡-** ይህ ከ3ቱ እይታዎች ማለትም ከባድ፣ ጠቃሚነት እና ተደጋጋሚነት አኳያ ለስልጠና ፍላጎትና ለስልጠና ቅድሚያ መስጠት ውስብስብና በጣም የተዘበራረቀ የአፈጻጸም ዳሰሳ ጥናት ዘዴ ነው፡፡

ይህ ዘዴ የሚመለከተው ልማትን ከግለሰብ ባህሪ አኳያ ሳይሆን ተግባራትንና ዝርዝር ተግባራት (ክህሎትና ብቃትን) ነው፡፡ ከባድ፣ ጠቃሚነት እና የተደጋጋሚነት ትንተና በተለያዩ መንገዶች ሊጠቅም ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡-እንደ ስዕላዊ መግለጫ ፍሰት ለ3ቱ ነገሮች በተከታታይ ከባድ (አዎ/አይደለም)፣ ጠቃሚነት (አዎ/አይደለም) እና ተደጋጋሚነት (አዎ/ አይደለም) በቀላሉ አዎ/አይደለም የሚለውን በመጠቀም እያንዳንዱ ተግባር ላይ ለማተኮር 8 ህብረት የመሆን አድልን ያጎለብታል፡፡ በሁሉም 3 መለኪያዎች በቀላሉ ዝቅተኛ ነጥብ ያለው ተግባር ዝቅተኛ ቅድሚያ ሲሰጠው በሁሉም 3 መለኪያዎች በቀላሉ ከፍተኛ ነጥብ ያለው ተግባር ከፍተኛ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ በአብዛኞቹ የከባድ፣ ጠቃሚነት እና የተደጋጋሚነት ትንተና በቀጥታ የግለሰብ ምርጫዎችንና ያለውን ብቃት ምክንያት የማያደርግ ነው፡፡

### ሌሎች ዘዴዎች፡-

☞ **የስልጠና ማወዳደሪያ እንደ ሁኔታዎች (ማለትም የጊዜ፣ የሰው ኃይል፣ የገንዘብ ወ.ዘ.ተ.) የሚቀያየር ነው፡፡** ይህ የሆነበትም አብይ ምክንያት ስልጠና በባህሪው ከሌሎች የአቅም ግንባታ ዘዴዎች በጣም ውድ ስለሆነ ነው፡፡ ስለጠናን በቀላሉ ለመወሰን የተሻለ መንገድ ሊሆን የሚችለው ከስልጣኞች ጋር በቀላሉ መስማማት ነው፡፡

☞ **አሳታፊ የገጠር ምዘና/ግመታ (PRA)፡-** በኤክስቴንሽን አካሄድ ይህ ማለት ስለ አርሶ/ አርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ችግሮችን ጨምሮ በርካታ መረጃዎች የምናሰባሰብበት አሰራር/ቴክኒክ ነው፡፡ ይህም ከቁልፍ መረጃ ሰጪዎች/አቀባዮች ጋር ቃለ-መጠይቅ ማካሄድ፣ መረጃ ምንጮችን መዳሰስ፣ በእይታ፣ ከግል ወይም የአርሶ/አርብቶ አደር ቡድኖች ጋር በከፊል በተደራጀ ቃለ-መጠይቅ ማካሄድ ናቸው፡፡

☞ **ከልማት ሠራተኞች የቀን ማስታዎሻ(Diary)፡-** ይህ የአርሶ/አርብቶ አደር ችግሮችን፣ ፍላጎቶች፣የችግሮችና መንስኤ ተመዝገቦ የሚገኝበት ስለሆን ለስልጠና ዝግጅት በቂ መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡

☞ **የእውቀት፣ ፍላጎት እና አመለካከት ጥናት፡-** በተወሰነ ተግባር ላይ የተሰማሩ አርሶ/

አርብቶ አደሮችን እውቀት፣ ፍላጎትና አመለካከት ጥናት የስልጠና ፍላጎታቸውን ለመለየት ያግዛል፡፡ በአብዛኛዉ ይህ ተግባራዊ የሚደረገው ቃለ-መጠይቅ በማዘጋጀት ነው፡፡

☞ **ከአርሶ አደር ጋር ቃለ-መጠይቆችን ማካሄድ፡-** ከግለሰብም ሆነ ከቡድን አርሶ/አርብቶ አደሮች ጋር የሚካሄዱ ቃለ-መጠይቆች የስልጠና ፍላጎታቸውን ለማወቅ ይረዳሉ፡፡ ቃለ-መጠይቆች በርካታ አርሶ/አርብቶ አደሮች የሚሳተፉበት ጥቅም/ዋጋ ያላቸውና ለስልጠና የሚኖረው ግለሰቦችን አቅም ለማጎልበት ዓላማ ያደረገ ነው፡፡

☞ **የአርሶ/አርብቶ አደሮች ባህሪን ማስተዋል፡-** የአርሶ/አርብቶ አደሮች ባህሪ በቀጥታ የማስተዋል ጉዳይ በመስኖ ልማት ሰራተኞች/ሱፐርቫይዘሮች/ መከናወን የሚችል ነው፡፡ ይህም የትኛው አርሶ/አርብቶ አደር የተሻለ ግንዛቤ እንዳለው፣ ያለውን ግንዛቤ ተግባራዊ ያደርጋል ወ.ዘ.ተ. የሚሉትን ከአርሶ/አርብቶ አደሮች በቀላሉ ሊያገኝ ይችላል፡፡

☞ **የክህሎት ፈተና፡-** የሙያ ክህሎት እና የመሠረታዊ ሥራ እውቀት የችሎታ ፈተና ሊሰጥ ይችላል፡፡

☞ **የፖሊሲ መግለጫዎች፡-** ጥቂት የስልጠና ፍላጎቶች የሚለዩት የተቀረፁ ፖሊሲዎችን ሥራ ላይ ለማዋል ነው፡፡

**ክፍል 6**
**የመስኖ ኤክስቴንሽን እቅድና ስልጠና እና የስልጠና ፍላጎቶችን መለየት**

| በኤክስቴንሽን ስልጠና እቅድ ውስጥ የሚታዩ የፆታ ችግሮች | ችግሮች እንዴት ይቀረፋሉ? | ችግሮቹ ሲፈቱ ምን ጥቅም ያስገኛሉ? |
|---|---|---|
| 5 የኤክስቴንሽን ስልጠና ዕቅድ ሲዘጋጅ የሴቶችን ነባራዊ ሁኔታ ለስርዓተ-ፆታ ትኩረት አለመስጠት፡፡<br>6 ለኤክስቴንሽን አገልግሎት ስልጠና ግብዓት አቅርቦት፣ ድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ እና የገበያ ክፍፍል ላይ ሴቶችን ኢላማ አያደርጉም፡፡<br>7 ብዙውን ጊዜ ስልጠና የሚሰጥበት ጊዜ፣ ቦታ እና የአሰለጣጠን ዘዴ ለሴት አርሶ አደሮች ምቹ አይደለም፡፡<br>8 የኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰራተኛ በስርዓተ-ፆታ እና ፆታ ተኮር ዕቅድ አወጣጥ ላይ በብቁ/የሰለጠኑ አይደሉም፡፡ | • በዕቅድ ጊዜ ከፆታ ረገድ የሚጠበቁ ለውጦች ማን፣ ምን፣ የት እና መቼ ጭምር መለየት አለባቸው፡፡<br>• በሴቶች፣ ወንዶች እና በሁለቱም ደረጃ የሚገኙ ወጣቶችን በማካተት በዕቅድ የተያዙትን ወደ ተግባር መለወጥ፤<br>• ለስልጠናው አስፈላጊነት በሚደረገው የዳሰሳ ጥናት ወቅት የሴቶች ልዩ ፍላጎት፣ ዝንባሌ እና ሌሎች ተግዳሮቶችን መለየት፤<br>• ሴቶች እና ወንዶች እኩል መረጃ፣ ስልጠና፣ ቴክኖሎጂ እና የተለያዩ ግብዓቶች ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤<br>• የኤክስቴንሽን አገልግሎት ሴት አርሶ አደሮች ተገቢውን የመስኖ የግብርና ዘዴ እውቀት ማግኘታቸውን እና መተግበራቸውን አትኩሮት መስጠት አለበት፡፡<br>• ቢያንስ 30% ለሚሆኑ ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች የመስክ ላይ ገለፃ፣ የግብርና ምክር እና ስልጠና መስጠት፤<br>• በዘመናዊ መስኖ ግብርና ተግባራት ዙሪያ በአባወራ ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች አትኩሮት መስጠትና ግንዛቤያቸውን ከፍ ማድረግ፤ | ለስርዓተ-ፆታ ጥያቄዎች መልስ ሰጪ የሆነ የመስኖ የኤክስቴንሽን ስልጠና ዕቅድ እና የስልጠና አስፈላጊነት የሴቶችንም ሆነ ወንዶችን ምርታማነት ከፍ ያደርጋል፡፡ |

# ምዕራፍ-7 የመስኖ ልማት ሰራተኞች ተግባርና ሚና

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሂድቶች ሁለንተናዊ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የመስኖ ስራዎች ስኬታማ እንዲሆኑ ይረዳል፡፡ በተለይም በክልል፣ ዞን እና ወረዳ ሁለንተናዊ የሆነና የተሳሰረ ሙያዊ ድጋፍ ሲኖር የበለጠ ፍሬያማ ይሆናል፡፡ በአብዛኛው የክልልና የዞን ቢሮዎች ወይም መምሪያዎች ቁልፍ ሚና የተለያዩ የመስኖ ልማት ፓኬጆችንና ማንዋሎችን ማዘጋጀት፤ የአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ አውታሮች ማደራጀትና መምራት፣ የመስኖ አግሮኖሚ፣ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ፣ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት አመራር፤ የማሳና የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ሠርቶ ማሳያዎች ቴክኒክ ስልጠና መስጠት፤ የመስኖ ተግባራትን በሚመለከት መመሪያዎችን ማውጣት፤ ማጣቀሻ ማቴሪያሎችና፤ የስልጠና ማንዋሎችንና ዓመታዊ የሥራ እቅዶችን ማዘጋጀት ነውበተጨማሪም ተቋማዊ አደረጃጀትን ማስተባበር፤ ገበያና የእሴት ሰንሰለት ልማትን ማጎልበት፤ ሥርዓተ ጾታ፣ ወጣቶችና ሥርዓተ ምግብ በሁሉም ዘርፎች መደገፍና ማጎልበት ይገኙበታል፡፡

## 7.1. የመስኖ ልማት ሰራተኞች ተግባርና ኃላፊነት

ውጤታማ የሆነ የመስኖ አሠራር/ሲስተም መንግሰት ያወጣውን ስትራቴጂ ከግብ ለማድርስ አይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የመስኖ መስኩን ኤክስቴንሽን አተገባበርና በትክክል በሚተገብሩ የልማት ሰራተኛ አማካኝነት መሆኑ ጥርጥረ የሌለው ቢሆንም የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ዘንድ አወንታዊ ተነሳሽነት ሲኖርና ወደ ተግባር ሲለወጥ ነው፡፡ እንደ ግብርና ቢሮ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሠራር አንድ የቀበሌ የመስኖ ልማት ሰራተኛ ዘመናዊና ባህላዊ የመስኖ አውታሮችን አካቶ በቀበሌው ውስጥ ቢያንስ 50 ሄክታር ለሆነ የመስኖ ልማት ሙያዊ ድጋፍ፤ ስልጠናና ምክር አገልለግሎት ይሰጣል፡፡ የመስኖ ልማት ሰራተኛው የቀን ተቀን ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ☞ የመስክና መስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ
- ☞ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበርን እና የውሃ ተጠቃሚዎች ንዑስ ቡድን ሙያዊ መደገፍ
- ☞ ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች ተግባር ተኮር ሥልጠና መስጠት
- ☞ የመስኖ ተጠቃሚ ማህበራን በማወያየት ዓመታዊ የመስኖ ልማት ዕቅድ ማዘጋጀት
- ☞ ፍትሀዊ የውሃ ስርጭት እንዲኖር የውሃ ተጠቃሚ ማህበራትንና፣ እና የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ንዑስ ቡድኖችን መማሰልጠን/መምክር
- ☞ በመስኖ መሠረተ ልማት ተገቢ የሆነ ጥገና እንዲካሄድ የውሃ ተጠቃሚዎችን መምክር
- ☞ ለተፋሰስ ልማት የአርሶ/አርብቶ አደሩንና የውሃ ተጠቃሚዎችን ንቅናቄ መደገፍ
- ☞ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን ከሌሎች የመስኖ ልማት አጋር አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር ማስተሳሰር

- ☞ የመስኖ ሠርቶ ማሳያዎችን፣የመስክ ቀን፣ የአርሶ/አርብቶ አደር ስብሰባን፣የልምድ ልውውትን ማካሄድ
- ☞ በሙያዊ ስልጠናዎች ላይ መገኘትና ልምድን/ ተሞክሮን ማካፈል
- ☞ የዕለት ውሎን ወይም ዋና ዋና ተግባራትን በልማት ሰራተኛ የዕለት ተዕልት የስራ እንቅስቃሴ መመዝገቢያ ማስታዎሻ ደብተር/ዲያሪ ላይ መመዝገብ
- ☞ ለወረዳ ጽ/ቤት ሳምንታዊ እና ወርሀዊ ሪፖርቶችን ማቅረብ

### 7.1.1 መረጃ መያዝና የስራ አከባቢን ማወቅ

አንድ የመስኖ ልማት ሰራተኛ የመስኖ ስራ አገልግሎትን ለአርሶ/አርብቶ አደሮች ከመስጠቱ በፊት የስራ ድርሻውን ማለት ያለበትን ኃላፊነትና ግዴታውን ጠንቅቆ ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡ በዚህም መሰረት የመስኖ ልማት ሰራተኛው የተመደበበትን ቀበሌ መሰረታዊ መረጃ የመያዝና የመመዝገብ ግዴታ/ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህም የቀበሌውን የአባወራና እማወራ ብዛት፤ የመስኖ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደር ብዛት፤ የመሬት ይዞታና አጠቃቀም፤ የአፈር ዓይነትን፣ የመልከዓ ምድር ሁኔታና የተፈጥሮ ሀብት ዓይነት፤ የገፀ ምድርና ከርሰ ምድር ውሃ አቅም፤ የመስኖና ማፋሰሻ ዘዴዎች፣ በመስኖ የሚለሙ ዋና ዋና የሰብል ዓይነቶች፤ ዋና ዋና የመስኖ ልማት ችግሮች፤ የገበያ ቦታዎች፤ የተቋሞች ብዛትና የህብረተሰቡን አጠቃቀም ሁኔታ፣ ግብዓት አቅራቢዎችን እና ሌሎች የግብርና መረጃዎችን መረዳት ማለት ነው፡፡ የመስኖ ልማት ሰራተኛው/ዋ በአካባቢው ያሉ ማለትም የቀበሌውን የመስኖ ልማት ቡድኖች፤ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች፤ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እንዲሁም የአርሶ/አርብቶ አደሮች ድርጅቶችን ማለትም የውሃ ተጠቃሚ ማህበራት፣ ሁለገብ ህ/ሥራ ማህበራትን በሚገባ ማወቅ አለበት፡፡

### 7.1.2 የመስኖ ልማት ሰራተኞች የሥራ መርሀ ግብር ይዘትና ቅርፅ

የመስኖ ልማት ሠራተኛ የሥራ መርሀ ግብር በአራት ሳምንታት የተከፋፈለ 28 የስራ ቀናት ሲኖሩት በነዚህ ቀናትም ውስጥ የልማት ሰራተኛው ንዑስ የመስኖ ቡድን/ የብሎክ አባላትን ቢያንስ በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ ማግኘትና ሙያዊ ድጋፍ ማደረግ ይኖርበታል፡፡ ይህም ድጋፍ ተግባር ተኮር የመስክ ስልጠናን፣ የመስኖ ሰብል የውሃ ፍላጎት ተግባራዊ መሆንን፣ ፍትሀዊ የውሃ ክፍፍልና ስርጭትን፣ የመስኖ ውሃ ቁጠባ ቴክኖሎጂ ስርጭትንና አተገባበርን፣ ተቋማዊ ችግሮችን መለየትን፣ የቡድን ሥራዎችን፣ የመስኖ አውታሮች ጥገናና የመስኖ ቦዮች ፅዳትን፣ የግበዓት አጠቃቀምን፣ የተባይ መከሰትን፣ የገበያ መረጃ ማቀበልን እና ሌሎች ተግባራትን ያጠቃልላል፡፡ በአከባቢው የሚገኙ የመስኖ ልማት አጋር አካላትም ይህንን የመስኖ ልማት ሠራተኛ ፕሮግራም በመለየትና በማወቅ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል፡፡ ዝርዝር የመስኖ ልማት ሰራተኛ የኤክስቴንሽን ወርሃዊና ሳምንታዊ የተግባር መርሀ ግብር ምሳሌ በዕዝል 3 ይመልከቱ፡፡

ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ሥራ ያልተከናወነባቸው ቀናት ካሉ የመስኖ ልማት ሰራተኞች እንደ አስፈላጊነቱ ቅዳሜና እሁድን ወይም የበዓላት ቀናትን ተጠቅመው

ያካክሳሉ። የመስኖ ልማት ሠራተኞች የቀበሌ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች፤ አስተዳዳሪዎች ወይም የንዑስ ቡድን አባላትና የሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች የሚገኙበትን በማመቻቸት የሥራ ቀናትን እንደ ሁኔታው መቀያየር ይችላሉ። ለመስኖ ልማት ሠራተኞች የሥራ መርሀ ግብር ተግባራዊነት የመስኖ ልማት ሠራተኞች የዘወትር ፕሮገራም ከአርሶ/ አርብቶ አደሩ (በተለይም ከሴቶች)ና ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ጋር ለውይይት መዘጋጀት ይኖርበታል።

## 7.2. የመስክ ጉብኝቶችና ስብሰባዎችን ማዘጋጀት

የመስኖ ልማት ሠራተኞች የመስክ ጉብኝት መርሀ ግብር በጣም ጠቃሚ ነው። የልማት ሰራተኞች የመስኖ አርሶ/አርብቶ አደሮችን የሚጎበኙት በታቀደና ቀድሞ በተወስነ ቀን፤ ሰዓትና ቦታ ታውቆ በመሆኑ ሁሉም የመስኖ አርሶ/አርብቶ አደሮች በማሳቸው/ በተመረጠው ቦታ በመገኘት የልማት ሰራተኛው የሚሰጠውን ስልጠና/መመሪያ መቀበልና መተግበር ይኖርባቸዋል። ሌሎች የውሃ ተጠቃሚዎችን ለማግኘት ጥረት በማድረግ ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናሉ።

የልማት ሰራተኞች ያለውን ጊዜ በሙሉ ተጠቅመው በዋናነት በመስኖ ላይ የሚያደርጉት ጥረቶችን ለመስኖ ውሃ አመራር እና ለውሃ ተጠቃሚዎች የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። በጉብኝት ወቅት የመስኖ ልማት ሰራተኞች፡-

- ☞ ምክረ ሀሳብ የተሰጠባቸው አዳዲስ የመስኖ ተሞክሮዎችን ትግበራ መከታተል
- ☞ ቴክኒክ ነክ የሆኑ (የችግኝ መደብ ዝግጅት፣ በመስመር መዝራት፣ ማረም፣ የውሃ መገኘት፣ ተባይና በሽታ መከላከል) እና ቴክኒክ ነክ ያልሆኑ (የግብዓትና ብድር መገኘት፣ የግብርና ምርት ዋጋ፣ ግብይት) የውሃ ተጠቃሚ ችግሮችን መመርመር
- ☞ በምክረ ሀሳቡ መሠረት ተግባራዊ የሆኑ እና በባህላዊ ተሞክሮዎች መካከል በሰብሎች እድገት ላይ ያለውን ልዩነት መመዝገብ
- ☞ ፍትሀዊ የመስኖ ውሃ ክፍፍል መኖሩን መቆጣጠር
- ☞ የአሰራርና ውጤት ሠርቶ ማሳያ ብሎኮችን መቆጣጠር

የመስኖ ልማት ሰራተኞች የአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ አውታሮች እንዲሁም የማህበረሰብ ኩሬ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁልፍ የኤክስቴንሽን ምክሮችን ለማስተላላፍ በቂ እድል ያገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪም በስልጠና የተገኘውን ዕውቀት አርሶ/አርብቶ አደሮች በተግባር መስክ ላይ ሲሰሩ ለማየትና የክህሎት ክፍተትም ሲኖር ድጋፍ ለማደረግና ማሳየት ጥሩ አጋጣሚ ይፈጥራል። ከጉብኘቱም በኃላ የልማት ሰራተኛ ከውሃ ተጠቃሚዎች ግብረ መልስ ይቀበላል።

ያልተፈቱ ጉዳዮች/ጥያቄዎችን በመመዝገብ የወረዳ/ዞን የመስኖ ባለሞያዎች እንዲመልሱ ያደርጋል። የውሎ ተግባራቱን ቁልፍ መረጃዎችን በኤክስቴንሽን የውሎ መመዝገቢያ ማስታዎሻን ያሰፍራል።

### 7.2.1. የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች የቤት ለቤት ጉብኝት

በተለዩ ቴክኖሎጂዎች ወይም ሀሳቦች ላይ መረጃ ለመለዋወጥ በመስኖ አውታሩ ውስጥ ወይም ራቅ ባለ ቦታ ተገኝተው ሌሎች አርሶ/አርብቶ አደሮችን ቤት ለቤት መጎብኘት ጠቃሚ መረጃዎችን  ለመለዋወጥ አይነተኛ የኤክሰቴንሽን ዘዴ ነው፡፡

ይህ ከስልጠና በኋላ የሚካሄድ ከሆነ የዚህ ጉብኝት ዋና ዓላማ የሚሆነው የተማሩትን በተግባር እንዲያዩ ለማስቻል ነው፡፡ ይህ ዘዴ በተለይ የአርሶ/አርብቶ አደሮችን በራስ መተማመንን ለማዳበርና በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ይረዳል፡፡ የቤት ለቤት/ማሳ  ጉብኝቶች የሰፋፊ መስኖ ስራዎችንም ያካትታል፡፡ ይህ ተግባርም የመደበኛ የቡድን ኤክስቴንሽን ተግባራት አካል ነው፡፡

**ጥቅም**

- ☞ አርሶ/አርብቶ አደሮች የተሸሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን በቀላሉ ይማማራሉ፡፡
- ☞ አርሶ/አርብቶ አደሮች ሌሎች አርሶ/አርብቶ አደሮችን የማመን ዝንባሌ ያድርባቸዋል፤ ስለሆነም የሚሰራጨው ክህሎት እና ሀሳብ ከመደበኛው ኤክስቴንሽን የፈጠነ ነው፡፡
- ☞ ስኬታማ ምሳሌዎችን ማየት የአርሶ/አርብቶ አደሮችን ጉብኝት የሚያነሳሳ ሲሆን በራሳቸው የተሻለ ለመስራት እንዲሞክሩ ያደርጋቸዋል
- ☞ ጉብኝቱ በአርሶ/አርብቶ አደሮች መካከል ግንኙነትን ለማዳበር ይረዳል
- ☞ ጉብኝቱ ሠርቶ ማሳያ የሚሰሩ አርሶ/አርብቶ አደሮችን በራስ መተማመን ያጎለብታል
- ☞ የተወሰኑ ቴክኖጂዎችን ለማየት የመጡ አርሶ/አርብቶ አደሮች ከዚህም በላይ ብዙ ያያሉ፣ይማራሉ

### 7.2.2. የመስክ ቀን ማካሄድ

የመስክ ቀን አንዱ የቡድን ኤክስቴንሽን ሲሆን ማሳ ላይ የተግባር/ውጤት ሠርቶ ማሳያ የሚካሄድ ነው፡፡ የመስክ ቀን የሰርቶ ማሳያ ቦታዎችን ለመጎብኘት ከ20-30 ወይም ከዛ በላይ አርሶ/አርብቶ አደሮች የሚገኙበት ፕሮግራም ሆኖ በጉብኝቱም ለመማር፣ ለመጠየቅ እና አዲሱን ቴክኖሎጂ በራሳቸው ማሳ ላይ መሞከር የሚፈልጉ አርሶ/አርብቶ አደር አንድ አንድ ጥያቄዎችን በማንሳት የሚማማሩበትን መልካም አጋጣሚ የሚሰጥ ነው፡፡

ስዕል-12፡-በመስኖ ልማት ሥራ የመስክ ቀን ላይ አርሶአደሮችን ማሳተፍ አርሶአደሮችን ያበረታታል፡



### 7.2.3. የልምድ ልውውጥ/ በተነሳሽነት የቡድን ጉብኝት ጉዞ ማድረግ

የልምድ ልውውጥ በተነሳሽነት ላይ የተመሠረተ የቡድን የጉብኝት ጉዞ ሲሆን እስከ 30 የሚሆኑ አርሶ/አርብቶ አደሮችን የሚያካትት ነው፡፡ ጉብኝቱም ከአንዱ የመስኖ አውታር/ኩሬ/ጥቃቅን የመስኖ ቴክኖሎጂ ወደ ሌላው በመሄድ ያላቸውን ተሞክሮና አሰራር ሂደት እርስ በራሳቸው የሚማማሩበት ዘዴ ነው፡፡

### 7.2.4. በወረዳ የሚደረግ ወርሀዊ የመስኖ ስራ የትኩረት አቅጣጫና ስልጠና

እንደ ሌሎች ተግባሮች የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ወራዊ የትኩረት አቅጣጫን ለልማት ሰራተኞች ማሳወቅ/ማሰልጠን ጠቃሚ ነው፡፡ ለመስኖ ልማት ሰራተኞች የሚሰጥ ስልጠና ሥራን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመፈፀም ስለሚረዳ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስራዎችን ለውሃ ተጠቃሚዎች በሰዓቱ መድረስ ይችል ዘንድ ለመስኖ ልማት ሰራተኞች ተደጋጋሚ ስልጠና/የትኩረት አቅጣጫዎችን ማወያየትና ማስገንዘብ ለመስኖ ግብርና ድጋፍ ሚናው የጎላ ነው፡፡ ምክንያቱም የመስኖ ስራ በባህሪው ወቅታዊና ፋታ የማይሰጥ የግብርና መስክ ስለሆነ ነው፡፡ ስልጠና/ገለፃው የሚያካትተው የክፍል ውስጥ ውይይትን፣ ስዕሎች/ፖስተሮችን፣ በመስክ የተግባር ሥራዎችን ወዘተ ነው፡፡ የስልጠና ቦታው በወረዳ መስኖ ግብርና/አጋር አካላት አዳራሽ ሲሆን ስልጠናውም በወረዳና በዞን ባለሙያዎች የሚቀርብ ይሆናል፡፡ ይህን ስልጠና/የትኩረት አቅጣጫ የማዘጋጀት የወረዳው ሀላፊነት ይሆናል፡፡

የስልጠናው መጀመሪያ ክፍል የሚያተኩረው በገለጻና ውይይት ላይ ነው፡፡ ስልጠናው እስከሚጠናቀቅ 3 ወይም 4 ወቅታዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባራት ወይም

የመማሪያ ርዕሶች ብቻ ይሸፈናሉ፡፡ ይህ በአንድ ዓይነት ወይም በተለያዩ ሰብሎች የሚተገበር ሲሆን በሚቀጥለው አንድ ወር ከውሃ ተጠቃሚዎች ወቅታዊ ሁኔታ ጋራ ተገናዝቦ መሆን አለበት፡፡

የወሩ የመስኖ ስራ የትኩረት አቅጣጫ በተደጋጋሚ የሚነገር ቃል መሆኑ ማብራሪያ ነጥቦችን ለማስታወስ ይረዳል፡፡ ከገለጻና ውይይት በኋላም የመስኖ ልማት ሰራተኞች የተግባር ልምምድ እንዲያደርጉ ጊዜ ሊኖር ይገባል፡፡ ለምሳሌ የመደብ ዝግጅት/የመስኖ ቦይ/Furrow ሊሆን ይችላል፡፡ ከተግባር ስልጠናው በኋላ ስልጠናው መጠናቀቅ ያለበት እያንዳንዱን የትኩረት አቅጣጫ ነጥብ እና እያንዳንዱ የመስኖ ልማት ሰራተኛ ለውሃ ተጠቃሚዎች የሥራ ላይ ስልጠና በሚሰጡት ስልጠና ላይ አጽንኦት እንዲሰጡት አጭር ማጠቃለያ ሊሰጥ ይገባል፡፡

እያንዳንዱ የመስኖ ልማት ሰራተኛም ለአንድ ወር የተመረጠ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የትኩረት አቅጣጫ መልዕክት ማጠቃለያ የያዘ ትምህርት አዘል ትንሽ በራሪ ወረቀቶች እዲደርሰው ይደረጋል፡፡ በዚህም የልማት ሰራተኛው በመስክ ጉብኝቱ ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ይህንኑ ያስተላልፋል/ያስተገብራል፡፡

## 7.2.5. የመስኖ ኤክሰቴንሽን የትኩረት አቅጫ ነጥቦች መረጣና ማብራሪያ

የመስኖ ኤክሰቴንሽን የትኩረት አቅጫ ነጥቦች መረጣና ማብራሪያ የመስኖ አምራች አርሶ/አርብቶ አደሩ ምርትና ገቢ እንዲጨምር የምረት ሰንሰለቱን ተከትለው በጥንቃቄ የተመረጡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መልዕክቶች ናቸው፡፡ መልዕክቶቹ በመጀመሪያ የተወሰኑ፣ቀላል የሆኑና በመስኖ ግብርና የተለያዩ ደረጃዎችን የሚሸፍኑ ናቸው፡፡ እነኝህ በቀላሉ የሚገኙ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ሀብቶችን ለማቀናጀትና መጠቀም በዕይታ የተመረጡ ናቸው፡፡ የወረዳ መስኖ ግብርና ልማት ባለሙያዎች ለተመረጡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መልዕክት ትምህርት አዘል ወረቀት ያዘጋጃሉ፡፡ይህም ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርበቶ አደሮች ውይም ማህበራት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት ለልማት ሰራተኞች የሚመች አካሄድ ነው፡፡ በተመረጡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መልዕክቶች መደበኛው ሂደት የሚከተሉትን ደረጃዎች በመከተል ያዘጋጃል፤-

- ☞ የመስኖ ሰብል ቅደም ተከተል አመራረት ልየታ
- ☞ ገበያ ተኮርና ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ሰብሎች መረጣ
- ☞ ለንዑስ መስኖ ቡድን/ የመስኖ ብሎክ አርሶ/አረብቶ አደሮች በተመረጡ ሰብሎች የተግባር ቅደም ተከተሎች ላይ ያተኮረ የኤክስቴንሽን መልዕክት/የትኩረት ማበራሪያ ነጥብ ዝግጅት
- ☞ በመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደር ማሳና ማሰልጠኛ ማዕከል ተግባር ተኮር ሥልጠና ለመስጠት ያስችል ዘንድ ለውሃ ተጠቃሚዎች የስልጠና ፕሮግራም ማዘጋጀት

☞የስልጠና መስጠት

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መልዕክቶቹ/ የትኩረት ነጥቦቹ ከተመረጡ ስልጠና ፍላጎቶች ጋር እንዲጣጣሙ ተደረገ በወረዳ የመስኖ ልማት ባለሙያዎች መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡ ፡ የትምህርት አዘል በራሪ/ትንንሽ ወረቀት እና የተመረጡ የመስኖ ኤክስቴንሽን መልዕክቶች ምሳሌ ዕዝል-4 ይመልከቱ፡፡

## 7.3. የመስኖ ተጠቃሚዎች ሥልጠና ማዘጋጀት

ስልጠና ዓይነተኛ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባር ሲሆን የመስኖ ስራዎችን በትክክል እንዲከናወኑ የአረሶ/አርብቶ አደሮችን፤ የመስኖ ልማት ሰራተኛና ሌሎች አጋር አካላትን ዕውቀትና ክህሎት በማዳበር የማይተካ ሚና አለው፡፡ ይህ አይነቱ ትመህርትና ስልጠና በሂደት የአመለካካትና የባህሪ ለውጥ የመጣል ዘላቂ የመስኖ ልማት፤ የመስኖ አውታሮች አጠቃቀም፤ በቴክኖሎጂ የመጠቅም ልምድ ይዳብራል፡፡

ለአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ ልማት ማህበራት አባሎችና የውሃ ኮሚቴዎች የሚሰጥ ስልጠና የውሃ ተጠቃሚዎች የመስኖ ማህበራትን አቅም በመገንባት የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ተቀብሎ ሥራ ላይ ለማዋልና የተሻሻሉ የውሃ ማኔጅመንት እንዲኖር ይረዳል፡፡ ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት የሚሰጡ የመሰኖ ኤክስቴንሽን ሥልጠናዎች ዓላማ፡-

- ☞ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር አባላትና የመወሰን አቅም ማጎልበትና የሚወሰኑ ውሳኔዎችን በአማራጭ ሃሳብና ሀብት አጠቃቀም ላይ እንዲመሩ ለማገዝ
- ☞ የውሃ ተጠቃሚዎች የተሻለ የግብርና ተሞክሮ እየተከተሉ መሆኑን ለማረጋገጥ
- ☞ የውሃ ተጠቃሚዎች ያላዳበሯቸውን የመስኖ ቴክኒኮችን እንዲጠቀሙ የሚያስችል ሠርቶ ማሳያዎችን ለማካሄድ
- ☞ የመስኖ ልማት አርሶ/አርብቶ አደሮችን ለአከባቢው ተስማሚ የሆኑ አዳዲስ/የፈጠራ ሀሳቦችና እውቅና መስጠትና ከኤክስቴንሽን ሁኔታ ጋር ማጣጣም
- ☞ ከመስኖ ተግባራት ጋር በተያያዘ የውሃ ተጠቃሚዎች ተስማሚ የመስኖ እርሻ መሣሪያዎችንና ግብዓቶችን እንዲጠቀሙ ማሰልጠን
- ☞ የውሃ ተጠቃሚዎችን ከአካባቢ ጋር የተስማሙ ቴክኒኮች ላይ ማሰልጠን

ጥሩ ስልጠና የጥሩ ዝግጅትና ውጤታማ የስልጠና መርሀ ግብር መገለጫ ነው፡፡ ወቅዊ የሆነ በንደፈ ሃሳብና ተግባር የተደገፈ ስልጠና የሰልጣኞችን የማወቅ ፍላጎት ከማነሳሳቱም ባሻገር ያአረዳድ ደረጃንም ያሳድጋል፡፡ በአጠቃላይ የስልጠና ዕቅድ ማለት በተመረጡና በተወሰኑ የስልጠና ርእሶች ላይ በወቅቱ የሚሰጥና የተለያዩ የስልጠና መረጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም የንደፈ ሃሳብና የተግባር ክፍል ጊዜን ያካተተ ከስልጠና በፊት የሚዘጋጅ ንድፍ/መር ግብር ማለት ነው፡፡ የሚዘጋጀው የስልጠና ዕቅድ/ንደፍም ዝርዝር የስልጠና ተግባራትን፣ የስልጠናውን ዓላማ፣ የስልጠናውን ጊዜና፣ ማቴሪያሎች ዝርዝርና ብዛት፣ የተሳታፊዎቸ ብዛት ወዘተ ያካትታል፡፡ በትምህርት ክፍለ ጊዜ ዕቅድ

ዝግጅት የሚካተቱ ደረጃዎች፡-

የስልጠና ዕቅድ ፎርማት/ሠንጠረዥ/ በዕቅድ ወይም በፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ላይ በመመስረት ለውሃ ተጠቃሚዎች በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል ወይም በሥራ ላይ ያለውን ስልጠና ለመስጠት ለመስኖ ልማት ሰራተኞች ይረዳቸዋል፡፡ ስልጠናን ከማቀድ ቀደም ብሎ በውሃ ተጠቃሚዎች/ሠልጣኞች/ ዘንድ የትኛው ዕውቀትና ክህሎት ላይ ክፍተት እንዳለ በትክክል መለየት፣ ለዚሁም የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ ለመስኖ ልማት ሰራተኞች ጠቃሚ ነው፡፡

በመስኖ ስልጠናው ዓይነት የዕውቀትና ክህሎት ክፍተትን መሠረት አድርጎ የስልጠናው ርዕስ/ትምህርት/ይነደፋል፡፡ ከዚህ በታች እንደተመለከተው የስልጠና ርዕስ/ትምህርት/ ፎርማት (ሠንጠረዥ) በየክፍሎች ተከፋፍሏል፡፡

- ☞ የዳሰሳ ጥናት
- ☞ ስልጠናው የሚሰጥበት ዝርዝር የስልጠና ጊዜ ይዘጋጃል (ቀን እና ቦታ)
- ☞ የትምህርቱ ግብ
- ☞ የስልጠና ፕሮግራሙን ዝርዝር ንደፍ (ጊዜ፣ቪዥዋል ኤድስ፣እና የሠርቶ ማሳያ ማቴሪያሎች)
- ☞ የስልጠናው ዕቅድ ከመጠናቀቁ በፊት ከወረዳ ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጠበት መጠየቅ፡

ዝርዝር የስልጠና ትምህርት ክፍለ ጊዜ ዕቅድ/ናሙና ዕዝል 5 ላይ ይመልከቱ፡፡

## 7.4. መረጃ መመዝገብና እና የውስጥ ሪፖርት ማዘጋጀት

የመስኖ ልማት ሰራተኞች መደበኛና ወቅታዊ ሪፖርቶችን፤ የተከናወኑ ስራዎችን መረጃ በመያዝና በወቅቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡ በሪፖርቱ ውስጥ የመስኖ ሰብል እድገት ሁኔታን፣ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መልዕክቶችና የመጣውን ለውጥ፣ የተሰራጩ ስራ ላይ የዋሉ ቴክኖሎጂዎች አይነትና ብዛት፣ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችና ልምዶች፣ የመስኖ ተጠቃሚዎች ግብረ መልስ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና በቀጣይ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ማመላከት ይኖርበታል፡፡ የወረዳ ባለሙያዎችም የመስኖ ልማት ሰራተኞች ባቀረቡት ሪፖርት ላይ በመመርኮዝ የመጣውን ለውጥ በቅርብ እንዲያውቁትና ስታትስቲካዊ ትንተናን ለመስራት ያስችላቸዋል፡፡ የመስኖ ልማት ሰራተኞች ሁለት ቁልፍ መረጃዎችን ማለትም የስራ መርሃ ግብር (ቻርት) እና የዕለት ውሎ መመዝገቢያ ማስታወሻ መያዥያ መያዝና ማስቀጠል ይኖርበታል፡፡ ቻርቱ የመስኖ ልማት ሰራተኞች የቀናት መርሀ ግብር በስዕልና በጽሁፍ የሚያሳይ ነው፡፡ የዕለት ውሎ መመዝገቢያ ማስታወሻው/ዲያሪ ደግሞ አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴን መረጃ የሚይዝ ይሆናል፡፡ ናሙና ወርሃዊ ሪፖርት ማሳያ ቅጽ ዕዝል 6. ላይ ይመልከቱ፡፡

ክፍል 7

## የመስኖ ልማት ባለሙያዎች ወርሃዊ የትኩረት አቅጣጫ አወጣጥና የስልጠና ርእስ መረጣ እስታንዳርድ ጉዳዮች

- ሴቶች ማለትም እማወራ እና የአ/አደር ሚስት የተሻሻለ መስኖ ለማስፋፋት በቂ እውቀትና ክህሎት ሊጎድላቸው ይችላል። በተግባርም የሴቶች ንዑስ ኮሚቴ ለሴቶች ውሃ ተጠቃሚ እንደ ግንባር ቀደም ካደረግናት ለውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ጠቃሚ ሞዴል መሆን ትችላለች፤
- የመስክ በዓል ለማዘጋጀት የሚመረጠው የተሳታፊ መጠን እና ንቅናቄ በፆታ የተለየ ያለመሆኑ እና ለሴቶች ተገቢውን ትኩረት ያለመስጠት፣ ሴቶች በውሃ ተጠቃሚ ማህበር በመሪነት ካልተመረጡ ሴቶች በቴክኒክ ረዳት እና በሥራ ላይ በሚሰጥ ስልጠናዎችን ላይ ሳተፉ መሆን ይችላሉ።
- በኤክስቴንሽን የሚተላለፍ መልዕክቶች ሲቀረፅ የትምህርት ደረጃን እና ሴቶችን ማዕከል ያደረገ እና ወደ ሴቶች ሊተላለፍ የሚችል ልምድ /ምልከታ/ ታሳቢ ያደረገ አይደለም።
- ሥርዓተ-ፆታን ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ ተጠያቂነት አሰራር ያለመኖሩ በመስኖ ልማት ባለሙያ የሥራ ተግባር የተበነተነ አይደለም።

## እንዴት ውጤታማ ማድረግ ይቻላል

- የመስኖ ልማት ባለሙያ እና የሚመለከታቸው ኃላፊነት ያላቸው አካላት የውሃ ተጠቃሚ ማህበር የሴቶች ንዑስ ኮሚቴ ግንባር ቀደም እንዲሆኑ በማበረታታት እና ሴቶች ውሃ ተጠቃሚዎች በማስተባበር ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው መስራት አለበት።
- ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ ሴቶች ተሳታፊ እንዲሆኑ በግል እና በንቅናቄ ጉዞ እማወራ እና የአ/አደር ሚስት በንቃት እንዲሳተፉ በሁሉም ደረጃ የሚገኙ ባለሙያዎች አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ መስራት ይኖርባቸዋል።
- የመስኖ ልማት ባለሙያ የስልጠና ዕቅድ በሚቀረጽበተ ወቅት ምቹ የድርጊት መርሃ ግብር ዕቅድ ሲያዘጋጅ ሴቶችን ያማከለ ስልጠና፣ የሥልጠና ቦታ ለሴቶች ምቹ መሆኑን ቀድሞ መለየትና በቂ የሴቶች ተሳትፎ እንዲኖር ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ የሴቶችን አቅም እና ተሳትፎ ያገናዘበ ሥልጠና በማዘጋጀት ውጤታማ ሥልጠና መስጠት ይቻላል።
- በመስኖ ልማት ባለሙያ የሥራ ተግባራት /ዝርዝር/ ውስጥ በሥርዓተ-ፆታ ተያያዥነት ያላቸው ሀሳቦችን እንዲካተት ማድረግ።

## የሚገኝ ውጤት ጥቅም

- የመስኖ ልማት ባለሙያ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ የድርጊት መርሃ-ግብር እቅድ ለማዘጋጀት ተጠያቂነት ይወስናል፤
- ሥርዓተ-ፆታን ያማከለ የኤክስቴንሽን መልዕክት ያዘጋጃል፤
- የሴቶች ንዑስ ኮሚቴ ለውሃ ተጠቃሚ ማህበር አስፈላጊ መሆኑ ግምት ውስጥ የማስገባት እና እማወራ እና የአ/አደር ሚስቶች ቴክኒክ ድጋፍ እና የሥራ ላይ ስልጠና እና ግንኙነት የተሻሻለ መስኖ ተግባርን እና ቴክኖሎጂ ያስፈልጋል ይህ በመሆኑ ምርትና ምርታማነታቸው እንዲጨምር ይረዳቸዋል።

# ምዕራፍ-8 የተቋማት ትስስር/ ግንኙነትና ትብብር

ባህላዊ የመስኖ ልማት አሠራሮች በሚካሄዱባቸውና የዝናብ ጥገኛ በሆኑ ቦታዎች ላይ የምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ በስፋት ይስተዋላል፡፡ ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ የአነስተኛ መስኖ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደር ምርትና ምርታማነቱን ማሳደግ እንዲችል የተሻሻሉ የመስኖ አሠራሮችንና ቴክኖሎጂዎች መተዋወቅና መላማመድ ከፍተኛ አስተዋጽኦና ጠቀሜታ አለው፡፡ ስለሆነም የምርት እድገትን ለማስመዝገብና ድህነትን ለመቀነስ በሚደረግ ጥረት ውስጥ የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ተቀብሎ ሥራ ላይ ለማዋል አንደኛው መንገድ የኤክስቴንሽን አገልግሎትን አጠናክሮ ማስቀጠል ሲሆን ለውጤታማነቱም የሁሉንም ፈጻሚ አካላት ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይጠይቃል፡፡ የሚመለከታቸው ፈጻሚ አካላት የምርምር ተቋማትን፣ የግብዓትና ብድር አቅራቢዎችን፣ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪዎችን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ያጠቃልላል፡፡

የድጋፍ ሰጭ ተቋማትን ትስስር መፍጠር በመስኖ ማምረት ተግባር ላይ የተሰማሩ ፈጻሚ አካላትን ወደ አንድ በማምጣትና በጋራ እንዲሰሩ በማድረግ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት ተደራሽ ለማድረግ ይረዳል፡፡ የትስስሩ ዋና ዓላማ በአጠቃላይ በመስኖ ልማት እየተደረገ ባለው ጥረት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑትንና ድጋፍ እየሰጡ ያሉ ወሳኝ ተቋማትን/ አጋር አካላትን ቅንጅታዊ አሰራር በማጠናከር የአነስተኛና ሠፋፊ መስኖ ተጠቃሚዎችን ዘርፈ ብዙ ፍላጎት ተደራሽ ለማድረግና የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ነው፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የፌደራል ግብርና ሚ/ር በአዲሱ የግብርና ኤክስቴንሽን ስትራቴጂ ላይ አምድ-7 ሥር ባሉት ተቋማት መደራጀት እና ቁልፍ በሆኑ የግብርና ልማት ፈጻሚ አካላት ግንኙነትና ትስስር ላይ አጽንኦት ይሰጣል፡፡ ከዚህ አንፃር የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ሥራ ላይ ለማዋል የነዚህ አጋር አካላት ድጋፍ፤ ቅንጅትና ትስስር ጠቀሜታ ያለው መሆኑን በማመን የግብርና ልማት አጋር አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስል (ADPLAC) በስሩ የመስኖ አማካሪ ካውንስል ተጠሪ ሆኖ ከፌደራል ግብርና ሚኒቴር እስከ ወርዳ ግብርና ጽ/ቤት ድረስ በየደርጃው ንዑስ መድረክ (Sub-platform) በመዘርጋት የመስኖ ምርምር- ኤክስቴንሽን-አርሶ/አርብቶ አደር ግንኙነት እንዲጠናከር ጥረት መደረግ አለበት፡፡ በተለይ ለመስኖ ግብርና ውጤታማነት የቴክኖሎጂ ልማት በማካሄድ ለአርሶ አደሩ ለማቅረብ በዋናነት የካውንስሉ ሚና በምርምር-ኤክስቴንሽን-አርሶ/አርብቶ አደር ግንኙነት ላይ በጣም ትልቅ ነው፡፡ ይህ ካውንስል በተዋረድ በግብርና ቢሮ ወይም በውሃ ሃብት ልማት ቢሮ እንደየክልሎች የመስኖ ልማት ጽ/ቤት አደረጃጀት በሰብሳቢነትና በግብርና ምርምር/በአቅራቢያው በምርምር ላይ የሚገኙ ተቋማት/ ፀሓፊነት የሚመራ ይሆናል፡፡

የካውንስሉ አወቃቀር እንደሚከተለው ይሆናል በሚከተለው ስዕላዊ መግለጫ ቀርቧል፡፡




ምስል- 7፡-የመስኖ ንዑስ አጋር አካላት ግንኙነት

በጀት መመደብ/መደገፍ　　　　አገልግሎት መስጠት

ዝርዝር የካውንስሉን የአቅም ግንባታ ድጋፎችን በሠንጠረዥ-1 እና ዕዝል 1 ላይ ይመልከቱ፡፡

| ተግባር | የአቅም ግንባታ ድጋፍ ስትራቴጂ/ድርጊት |
|---|---|
| ዕቅድ ክለሳና ግምገማ | በክልል ደረጃ የመስኖ ልማት ዕቅድ አውደ ጥናት ላይ፡<br>5 በመስኖ ልማት ዕቅድ ላይ የጋራ የክለሳ ግምገማ ማካሄድ፤<br>6 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድን በጋራ ማዘጋጀት፤<br>7 ዕቅዱ በግብርና ልማት አጋር አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስል (ADPLAC) ማፅደቅ፤<br>8 የመስኖ ልማት ስልጠና አተገባበርን በጋራ ማቀድ፤<br>9 የመስኖ ባለሙያዎችን ዋና አሠልጣኞች ሊሆኑ ይገባል፤ |
| የፕሮግራም ዝግጅትን በደርጃ ማስቀመጥ | የፕሮግራም ደረጃ የሚቀረፀው በሁኔታዎች ትንተና ላይ ነው፡፡ ይህም በመስኖ ልማት ላይ ቅድሚያ ለሚሰጠው ጉዳይ ውሳኔ ለማስጠት በመሠረታዊነት ያገለግላል<br>• በሁኔታዎች ትንተና እና ደረጃ አቀማመጥ ቴክኒክ ላይ የዕቅድ ንድፍ ማዘጋጀት፤<br>• ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችን ለመወሰን የሚያስችሉ መረጃዎችን በተከታታይ መመርመር እና መተንተን፤<br>• ተግባር ተኮር ስልጠናና ድጋፍ መስጠት፤ |
| የሙያ ትምህርት | የሙያ ትምህርት ትግበራ ለሙያ ሰልጣኙ እውቀትና ክህሎትን ለመጨበጥ ይረዳዋል፡፡ በዚህም፡-<br>• ባለሙያዎች ተግባሮቻቸውን በመፈተሽ ያሻሽላሉ፤<br>• ሙያዊ እውቀትንና ክህሎትን ለማዳበርም መጽሐፍ ማንበብ፣ የባለሙያን ሥራ መመልከት፣ትምህርታዊ ጉብኝትና ትምህታዊ ጥናቶችን ማደርግ እንዲሁም ሙያዊ ግብን ላማሳካት የራስ ተነሳሽነትን ማሳደግ፤<br>• አርሶ/አረብቶ አደሮች ያገኙትን ትምህርት መገምገም፤ |
| የሃሳብ ልውውጥና እና የሀብት ማዳበር ልምድን ማሳደግ | የሃሳብ ልውውጥና እና የሀብት ማዳበር ልምድን ማሳደግ ልምድ ካላቸው አካላት ጋር የረጅም ጊዜ ውይይቶችን ማድረግ እነርሱም፡-<br>a) ጥናታዊ የመስክ ጉዞን ማዘጋጀት (የሀገር ውስጥና የውጭ)፤<br>b) የክህሎት እና የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናን ማድረግ፤<br>c) የግል/ፕራይቬት/ እና ጋራ ፐብሊክ አጋርነትን(PPP) ማበረታታት፤<br>d) የአካባቢ/የማህበረሰብ ማህበራትን ማጠናከር፤ |
| የመስኖ ልማት ስራ መረጃንና ወቅታዊ ግንዛቤን ማሠራጨት | የመስኖ ልማት ስራ መረጃንና ወቅታዊ ግንዛቤን ማሠራጨት ረገድ የሚከተሉትን ተግባራት እንደ አስፈላጊነቱ መጠቀም<br>▪ የተጻፉ የመረጃ ማቴሪያሎችን ለምሳሌ በራሪ ጽሁፎችን፣ ጋዜጦች፣ ትንንሽ መጽሀፍት፣ ተፈላጊ መረጃ የያዘ ሰነድ፣ የሀብት መመዘኛ፣ የምርምር መጽሄት፣ ሳይንሳዊ ሪፖርቶች፣ ወ.ዘ.ተ...፣<br>▪ የኤሌክትሮኒክ እቃዎች ማለትም ዲቪዲ/ ሲዲ ሮም፣ የኢሜይል መልዕክቶች፣<br>▪ በኢንተርኔት የሚገኙ የእውቀት ማቴሪያሎች፣ የምርምር ፍንጮች፣ ትክክለኛና የተመጠኑ መልዕክቶች፣ ዌብ ኮንፈረንስ፣ እና ዌብ ሳይትስ፤<br>▪ የአጋር አካላት ሽርክና እና ጉባኤዎች/አውደ ጥናቶች፤ |
| የሙያ ተግባራትን ማስተባበር | የአርሶ አደር ድርጅቶችን ጨምሮ የአካባቢ የሙያ ድርጅቶችን ለመደገፍ የትብብር ስትራቴጂን ማሳደግ፤<br>■ ያሉትን የሙያ ድርጅቶች መለየት (የአርሶ አደር ድርጅቶች፣ ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች፣ የግብርና ማህበራት ወ.ዘ.ተ)፣<br>■ አዳዲስ የሙያ ድርጅቶችን መመስረትና መደገፍ፣<br>■ የድርጅቶችን የልማት አጭር የሥራ ዕቅድ እና መተዳደሪያ ደንብ ማውጣት፣<br>■ የሙያ ማህበራትን አቅም ግንባታ መደገፍ፤ |

ሠንጠረዥ- 9፡-ግንኙነትን ለማጠናከር የሚደረግ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ዝርዝር

የግብርና ልማት አጋር አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስል (ADPLAC) በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ የግብዓት አቅርቦት፣ የቴክኖሎጂ ማውጣት፣ማስተዋወቅና ማስተላለፍ፣ የገበያ ምርቶችን አመራረት እና ጥቅም ላይ የማዋል ሂደት ችግሮችን ለይቶ ለማውጣት አግባብነት ያላቸውን አጋር አካላት/ተቋማት በመሰብሰብና በማወያየት ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የመፍትሄ አቅጣጫዎች ያስቀምጣል፡፡ በዚህ መድረክ ከሚነሱ የውይይት አጀንዳዎች መካከል አንዱና ዋናው የመስኖ ልማት ሲሆን በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የጋራ ዕቅድ፣በማላመድ ሙከራዎችና ሠርቶ ማሳያዎች የጋራ አፈፃፀምና ግምገማ፣ የመስክ ቀንና አውደ ጥናት ማካሄድ፣ አዳዲስ የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅና በማላመድ ተግባራት ላይ በየደረጃው ባሉ የግብርና ልማት አጋር አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስል (ADPLAC) መድረክ ውይይት ወይም ምክክር ይደርጋል፡፡

ስለዚህ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የተለየ ዓላማ ያለው ሳይሆን የታቀዱ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባራትን ውጤታማ ለማድረግ ከአጠቃላዩ ዓላማ ጋር የተስማማ የኤክስቴንሽንና የመስኖ ማኔጅመንት ሀሳብ ኖሮት ጠንካራ የጋራ ትስስር በመፍጠር የድጋፍ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል በትስስሩ ውስጥ ድጋፍ የሚፈለግባቸውን ሌሎች የሥራ ሂደቶች ወይም አጋር አካላት፤ ለምሳሌ፡-የመስኖ ልማት ግብዓት አቅራቢዎች፣ ግብይት፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የገበሬ ማህበራት፣ የግብርና ምርምር፣ የብድር ተቋማት፣ የመስኖ ማህበራትና የውሃ ተጠቃሚዎችን ማካተት ይኖርበታል፡፡ ለመስኖ ልማት መሠረታዊ ድጋፍና ትስስር የሚፈለግባቸው ዋና ዋና አጋር አካላት የሚከተሉት ናቸው፡፡

☞ **የመስኖ ግብዓት አቅራቢዎች፡-** በመስኖ ልማት ሂደት ውስጥ የመስኖ ግብዓት አቅራቢ አካላት ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡ የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች በወረዳ፣ በዞን፣ በክልልና በፌደራል ደረጃ ያለውን የግብርና ግብዓት አቅርቦትና የገበያ ሂደት በማመቻቸት አርሶ/አርብቶ አደሩ የሚፈልጋቸውን ግብዓቶች እንደ ምርጥ ዘር፣ማዳበሪያ፣ የግብርና ኬሚካል እና የመስኖ እርሻ መሳሪያዎች ማለትም የርጭት መስኖ መሳሪያ፣ የውሃ ታንከር፣የውሃ መሳቢያ ሞተር፣ የውሃ መሳቢያ ቱቦ/ጎማ፣ የጠብታ መስኖ፣ መለዋወጫ መሳሪያዎች፣ወዘተ የመሳሰሉትን በወቅቱ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዋናነት በአቅራቢነት የሚሳተፉ አጋር አካላት ወይም ድርጅቶች የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ፣ የግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን፣ ማህበራትና ግለሰቦች ሲሆኑ እነዚህን አካላት በማደራጀትና በመደገፍ ግብዓቶቹን ለአርሶ/አርብቶ አደሩ በቅርበትና በወቅቱ እንዲገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

☞ **የመስኖ ልማት ምርት ገበያ፡-** በዋናነት በወረዳም ሆነ በክልል ደረጃ የምርት ገበያ የግብርና ግብዓት እና ግብይት ሂደትን ያካትታል፡፡ ኃላፊነቱም በግብርና ምርትና ሸቀጥ ዋጋዎች ላይ የገበያ ፍላጎትን ለመተንበይ የገበያ መረጃን መሰብሰብ፣መተንትንና ማቅረብ፤እንዲሁም መቆጣጠር ነው፡፡ በተጨማሪም ገበያ ተኮር ምርቶች እንዲመረቱ መደገፍና አምራቹን ከገበያ ጋር ማስተሳሰር ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ ረገድ ሌሎች አጋር አካላት መሆን የሚችሉት የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ፣ የግል ነጋዴዎች፣ የትራንስፖርት እና መጋዘን አገልግሎት ሰጪዎች ወዘተ ናቸው፡፡

☞ **የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን፡-** በየደረጃው ከወርዳ ጀምሮ ባሉ የግብርና ልማት ተቋማት ውስጥ የመስኖ እክስቴንሽን እምብርት ወይም ማዕከላዊ ክፍል ነው፡፡

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን በግብርና ቢሮዎች፣ በምርምር፣ በግብዓት ቅራቢዎች፣ በሰፋፊ የገበያ ማዕከላት እና የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች መካከል ለሚፈጠሩ ትስስሮችና ድጋፎች የማይተካ ሚና የሚጫወት ሲሆን በሰው ኃይል ማደራጀትና ማብቃትም አስፈላጊ ነው፡፡

☞ **የመስኖ አሠራርና ጥገና፡-** በዋናነት የመስኖ አሰራርና ጥገና በመስኖ አውታርና በጥቃቅን የቤተሰብ መስኖ፤ እንዲሁም በማህበረሰብ ኩሬ አሠራርና ጥገና ላይ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ በዚህም መሰረት የመስኖ ቦይ እድሳት፣የውሃ መቀልበሻ ቦዮች ጥገና፣ የኩሬ ውሃና አከባቢ ፅዳት፣ የወንዝ ጠለፋና ሌሎች የቁጥጥር ሥራዎች ሀላፊነት የሚከናወኑት በግብርና ቢሮ በአነስተኛ የመስኖ ልማት ቡድን፣ በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት፣ በመስኖ ኤክሰቴንሽንና የመስኖ ኢንጂነሮች ነው፡፡

☞ **የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ንዑስ ቡድን፡-** የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን በንዑስ ቡድን ማደራጀት ጠቀሜታው የተለያዩ የኤክስቴንሽን ዘዴዎችን ተጠቅሞ የተሻሻሉ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ተቀብሎ ለውሃ ተጠቃሚዎች ለማስተላለፍና ሥራ ላይ ለማዋል፣ የመስኖ አውታሮችንና የውሃ ማሰባሰብ ሥራዎችን ለማስተዳደር ወሳኝ አሰራር መንገድ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የመስኖ ንዑስ ቡድን ሚና የተሻሻሉ የጥቃቅን መስኖ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋዎቅና ተቀብሎ ሥራ ላይ ለማዋል ነው፡፡ ስለዚህ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበርና የንዑስ ቡድኑ ግንኙነት ጠቃሚ ነው፡፡

☞ **የግብርና ምርምር ውጤት፡-** በዋናነት የግብርና ምርምር ለውሃ ተጠቃሚዎች ተገቢውን የመስኖ ሰብል ምርት ቴክኖሎጂ ፓኬጅ ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመላከታችው አካላት ጋር በመሆን ያዘጋጃል፡፡ የምርምር ማዕከላት ከኤክስቴንሽን አገልግሎት ሠራተኛ ጋር ተቀናጅቶ በመስራት አሁን ባለው እና እየተለወጠ ባለው የአየር ንብረት ሁኔታ ላይ በመመስረት ለአካባቢው ተስማሚና ዘላቂ የሆኑ የመስኖ ግብርና/ አግሮኖሚ ቴክኖሎጂዎችን መገምገምና ማሻሻል ይጠበቅበታል፡፡ በሌላ በኩል ፍላጎትና አቅም ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የምርምር ተግባራትን እንዲደግፉ ያስፈልጋል፡፡

☞ **የብድር ተቋማት፡-** የብድር ተቋማት ለወረዳ የምግብ ዋስትናና ተዘዋዋሪ የብድር ፈንድ፣ ለውሃ ማህበራት፣ ለወንድና ሴት መስኖ ተጠቃሚ አርሶ/አረብቶ አደሮች እና ሌሎች ግለሰቦችን ጨምሮ ውሃ ተጠቃሚዎች ብድር እንዲሰጣቸው ምቹ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ/ይፈጥራሉ፡፡

☞ **የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ፡-** በመስኖ አውታሮች ውስጥና ውጪ የአፈር መሸርሸር የሚያደርሰውን መጠነ ጉዳት በማስላት በየደረጃው ካሉ የተፈጥሮ ሀብት ማኔጅመንት የሥራ ሂደት ጋር በመስራት በመስኖ አውታሮች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት በማቆም የመስኖ አውታሩን በዘላቂነት ለመጠቀምና ላላስፈላጊ ጥገና የሚውጣውን ወጪ ለመቀነስ ይረዳል፡፡ ስለዚህ የአፈር መሸርሸርን በመቆጣጠርና የተፋሰስ ልማትና

ጥገና ሥራን ለመስራት የተፈጥሮ ሀብት ማኔጅመንት የሥራ ሂደት ሚና ወሳኝ ነው፡፡

☞ **የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር፡-** የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ሕጋዊ እውቅና ያለው የአርሶ/አረብቶ አደሮች ተቋም ሲሆን ሁለንተናዊ የመስኖ አውታርና የማህበረሰብ ኩሬ አስተዳደርና አገልግሎት ሀላፊነት የተሰጠውና ለመስኖ ተጠቃሚ አርሶ/አረብቶ አደሮች አገለግሎት የሚሰጥ ነው፡፡ ማህበራቱ ለተፋሰስ ጥበቃ፣ ለመስኖ አውታር ጥገናና ለአካባቢ ቁሳቁስ ማቅረብ አርሶ አደሮችን በማነቃነቅ (mobilization) የመስኖ ሰብል ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ለማድረግ ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር ሆነው ዕቅድ በማቀድና ውሳኔ መስጠት በኩል ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡

☞ **የአካባቢ አስተዳደር፡-** የአካባቢ አስተዳደር የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ አስተዳደሮችን የሚያካትት ሲሆን ሚናቸውም የመስኖ ልማት ዕቅድን መሰረት አድርጎ ውሳኔ መስጠት፣ በጀት መመደብና በተያያዥ ጉዳዮችና ትግበራ በዘላቂነት የተቋማት ግንኙነትን ይደግፋሉ፡፡

## 8.1 የተቋማት ድጋፍና ትስስር ዓላማዎች

እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል የራሱ የሆኑ የተለያዩ ኃላፊነቶችና የሥራ ድርሻዎች እንዳሉት ይታወቃል፡፡ በዚህም መሰረት የካውንስሉ ግንኙነት ስትራቴጂ አጠቃላይ ግብ ውጤታማ የድጋፍና ግንኙነት አሠራር ዘዴ በመመስረት አርሶ/አርብቶ አደሩ የተሻሻሉ የመስኖ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ተቀብሎ ሥራ ላይ በማዋል ምርትና ምርታማነቱን ማሳደግና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥ/ማሳደግ ነው፡፡ ይህም ሊሳካ የሚችለው በተለያዩ ደረጃዎች በርካታ የተቀላጠፈ የግንኙነት ስትራቴጂ ሥራ ላይ ውሎ በአጠቃላይ በቴክኖሎጂ ልማት ሂደት፣ በግብዓት አገልግሎት ማቅረብና ምላሽ መስጠት ረገድ ሁሉንም አጋር አካላት ወደ አንድ ማምጣት ሲቻል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የተቋማት ድጋፍ ግንኙነት ዝርዝር ግቦች እንደሚከተሉት ናቸው፡-

☞ ተመራማሪዎችና የምርምር ፕሮግራሞች የመስኖ ልማት ፍላጎትን ያማከሉና ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂዎች መሆናችውን፤ እንዲሁም ለኣከባቢ ተስማሚ መሆቸውን ማረጋገጥ፣

☞ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በወቅቱና በሚፈለገው ልክ/መጠን መባዛታቸውንና መሰራጨታቸውን ማረጋገጥ፣

☞ የመስኖ ልማት ስልጠና ሲሰጥ የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂ ስርጭትና ውጤታማነት መረጋገጥ ይኖርበታል፣

☞ ለመስኖ ልማት በቂ የመስኖ ግብዓቶች ማለትም እንደ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ ኬሚካሎች፣ የጥገናና መለዋወጫ መሳሪያዎች፣ የእርሻ መሣሪያዎች፣ወዘተ በወቅቱ መቅረባቸውን ማረጋገጥ፣

- የመስኖ ልማት ማህበራት ፈትሃዊ የመስኖ ውሃ ክፍፍል መኖሩንና በአጠቃቀም ረገድ የሚከሰቱ አለመግባባትቶችን መፍታት፣ የገበያ አማራጮች እንዲኖሩ ማስቻላቸውን ማረጋገጥ፣

- የመስኖ ውሃ መስመር ጥገና፣ የመስኖ አውታር አሠራርና ጥገና ወቅታዊ መሆን፣ የተፋሰስ ጥበቃ፣ ወንዝ ጠለፋ እና በሌሎች የቁጥጥር ሥራዎች አገልግሎት እየተሰጡ መሆኑን ማረጋገጥ፣

- የቴክኖሎጂ መረጃዎችን በየጊዜው ማደስ/ማስተካከል፣ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ምክረ ሀሳቦችን ማቅረብ፣ ቴክኖሎጂዎችን ማስተላለፍና ተቀብሎ ሥራ ላይ ማዋል፣ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ መከታተልና መቀበል፣

## 8.2 የግንኙነት አሠራር ዘዴ

የተቋማትን ግንኙነት በማሳደግ ረገድ የመንግስትን ስትራቴጂ ተከትሎ ሙያዊ ንዑስ መድረኮችንና ውይይቶችን በየደረጃው ማካሄድ ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያን/አብይ እና ንዑስ የምክክር መድረኮችን፣ በፌደራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ በማቋቋም ቁጥጥር/ክትትል ማድረግ፣ በወቅቱ ስብሰባዎችንና አውደ ጥናቶችን በማካሄድ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ለማውጣትና ለማስተዋወቅ እና ያጋጠሙ ችግራችን ለይቶ አቅጣጫ ለመስጠት ያስችላል፡፡ መድረኩን የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ካውንስሉ ሰብሳቢ ሆኖ በየደረጃው ባሉ የግብርና ቢሮዎች ወይም ጽ/ቤቶች ይመራል፡፡ የተገኙ ተሞክሮዎቸንና ምክረ ሃሳቦችን በየደረጃው ላሉ የግብርና ልማት አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስል (ADPLAC) ሪፖርት ይደረጋል፡፡

### 8.2.1 በክልል ደረጃ

እንደ መጀመሪያ እርምጃ የክልሉ ግብርና ቢሮ ግንኙነቱን ለማዳበር የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያን መስርቶ የመጀመሪያውን የስብሰባ መድረክ ያካሄዳል፡ ፡ በስብሰባውም ላይ ቁልፍ የሆኑ አጋር አካላትና ተቋማት እንዲሳተፉ ተጋብዘው በመስኖ አገልግሎት ተቋማት ድጋፍና ግንኙነት ዙሪያ ይወያያሉ፤ ያቅዳሉ፡፡ በመስኖ አገልግሎት ማስተባበሪያ አነስተኛ መድረክ አባላት የሚሆኑት በግብርና ቢሮ የአነስተኛ መስኖ መሠረተ ልማት የሥራ ሂደት/ዳይሬክቶሬት፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎት የሥራ ሂደት/ዳይሬክቶሬት፣ የክልሉ የውሃ ሀብት ቢሮ፣ የተፈጥሮ ሀብት የሥራ ሂደት/ ዳይሬክቶሬት፣ የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት የሥራ ሂደት/ዳይሬክቶሬት፣ የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ፣ የክልሉ የግብርና ምርምር ተቋም፤ የክልል የምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም የግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት ተወካዮች እና ሌሎችም አስፈላጊ ተቋማት ናቸው፡፡

- የክልል የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ተግባራት፡-

## ዋና ዋና ተግባሮቹ፡-

- ☞ የመስኖ ልማት ምርምር እና የኤክስቴንሽን ፕሮግራም ውጤቶችን ወይም ውጤታማነትን ይገመግማል፣
- ☞ አሳታፊ የቴክኖሎጂ ልማት አቀራረብ ዘዴን እና አነስተኛና ጥቃቅን የመስኖ አውታሮችን የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስትራቴጂ በመጠቀም በማሳ ውስጥ በመስኖ መርምር ፕሮግራም ውጤት ላይ ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፣ በጋራ ያቅዳል፣
- ☞ ዓመታዊ የተጠቃለለ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድን ይገመግማል፣ ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፣ አፈጻጸሙንም ያረጋግጣል፣
- ☞ ዓመታዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድን መሠረት በማድረግ የመስኖ ግብዓቶች ማለትም ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የበሽታ/ተባይ መከላከያ መድሀኒት ፍላጎትን ይገመግማል፣ የሚገኙበትን ስትራቴጂ ይቀይሳል፣
- ☞ ለውሃ ተጠቃሚዎች ብድሮች መመቻቸታቸውን፣ የገበያ አማራጮችን እና ምቹ የመስኖ ልማት አተገባበር መኖሩን ይገመግማል፣
- ☞ በክልል ደረጃ የጋራ ግምገማ፣ አውደ ጥናት እና ዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል፣

**ወቅታዊ አውደ ጥናት ማካሄድ፡-** ክልላዊ የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ/ ምክክር መድረክ/ በዓመት ሁለት ጊዜ አውደ ጥናት ያካሄዳል፡፡ የመጀመሪያው አውደ ጥናት የመስኖ ልማት ምርምር ተግባራትን፣ የግብዓቶች አቅርቦትን እና የቀረቡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ምክረ ሀሳቦችን ለመገምገም ከመስኖ ሰብል ልማት ወቅት በፊት ይካሄዳል፡፡ የክልሉ የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ አውደ ጥናት ከዞኖች የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ አውደ ጥናት በፊት መካሄድ የሚችል ሲሆን በዞኖች የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ አውደ ጥናት ምክረ ሀሳብ ውጤቶች ላይ ይወያያል፡፡ሁለተኛው አውደ ጥናት በመስኖ ሰብል ልማት ማጠናቀቂያ ወቅት የሚካሄድ ሲሆን በክልሉ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተቋማዊ ድጋፍ አፈጻጸምና ሌሎች በድንገት በተከሰቱ ጉዳዮችና ጉድለቶች ላይ ይወያያል፤በተጨማሪም የክልሉ መድረክ/አውደ ጥናት ከዞኖች የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ አውደ ጥናት በኋላ ሊካሄድ ይችላል፡፡ የክልል የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ አውደ ጥናትን አጀንዳ አዳብሮ በተግባር ተኮር ዕቅድ ውስጥ ማካተት እንዲቻል ተጨማሪ የመወያያ ጽሁፎችን ለማግኘት ተሳታፊዎችን የዞኖች የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያን ጨምሮ ይጋብዛል፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ የወንድና የሴት አርሶ/አረብቶ አደሮች ተሳትፎ መኖር ዋና ተግባር ሲሆን አርሶ/አርብቶ አደሮች በተገኙበት ውይይት መካሄዱ የአነስተኛና የጥቃቅን መስኖ ተጠቃሚ አባዎራዎች እና እማወራዎች በማህበረሰቡ አሳሳቢ በሆኑ ጉዳዮች፣በመስኖ ቴክኖሎጂዎች፣ በኤክስቴንሽን ተግባራት፣በግብዓት አቅርቦት፣ሳይታሰብ በመጡ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የውሃ ተጠቃሚዎች ግብረ መልስ እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ቁጥር ከ30 እንዳይበልጥ የሚመከር ሲሆን ሴቶችን ጨምሮ በአነስተኛ እና በጥቃቅን መስኖ ተግባራት ላይ የሚሳተፉ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ቁጥር ማብዛቱ ይመረጣል፡፡

### 8.2.2 በዞን ደረጃ

የዞን የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ መለስተኛ መድረክ የሚካሄድ ሲሆን ያስፈለገበትም ምክንያት ከክልል የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ጋር ተመሳሳይ ዓላማ ስላላቸው ነው፡፡ የዞን የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ሰብሳቢና ፀሐፊ ይኖሩታል፡፡ የዞን የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ሁሉን አቀፍ በሆኑ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራሞች፣ በምርምር፣ በግብዓት አቅርቦትና ግብይት፣ በግንኙነት ማኔጅመንት ላይ በዞን ደረጃ መመሪያ ይሰጣል፡፡ በአጋር አካላትም/ተቋማትም ደረጃ የተከናወኑ የግንኙነት ተግባራትን የመቆጣጠር ሀላፊነት አለበት፡፡

የዞን የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ የሚያቅፋቸው አካላት የግብርና ጽ/ቤት፣ የኤስቴንሽን የሥራ ሂደት፣ የመስኖ ልማት ዲዛይን ሥራ ሂደት፣ የግብርና ግብዓትና ግብይት የሥራ ሂደት፣ የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ጽ/ቤት፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማት የሥራ ሂደት፣ የግብርና ምርምር ማዕከል፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ዘር ኢንተርፕራይዝ ተወካዮች፣ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን፣ የአርሶ/አርብቶ አደር ማህበራት/ድርጅቶች እና ሌሎችም አስፈላጊ ተቋማት ናቸው፡፡

### የዞን የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ተግባራት፡-

### ዋና ዋና ተግባሮቹ፡-

- ☞ በመስኖ ልማት ምርምር ግምገማ ስብሰባ ላይ አግባብነት ባላቸው ኤጀንሲዎች፣ መ/ቤቶች እና የውሃ ተጠቃሚዎች የተለዩ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባራት፣ የምርምር ተግባራት፣ የግብዓት አቅርቦት ችግሮችን ይገመግማል፣
- ☞ በቀበሌ ውስጥ በመስኖ የመልማት አቅም እና መሰናክሎች ጋር በተያያዘ የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂን ተቀብሎ ሥራ ላይ ለማዋል ያለውን ሁኔታ፣ በዞኑ ያለውን የመስኖ ፕሮግራም ሁኔታን ይገመግማል፣
- ☞ የወረዳዎችን መነሻ ዓመታዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ በመገምገም አስተያየት ታክሎበት መነሻ እቅዱ ወደ ክልል የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ይልካል፣
- ☞ በአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ አውታሮች ላይ ውጤታማ የመስኖ አግሮኖሚ ዘዴን እና የውሃ ተጠቃሚዎች የሀብት ማኔጅመንት መሻሻልን ዓላማ በማድረግ ለዞን ግብርና መምሪያ እና የግብርና ምርምር ማዕከላት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስትራቴጂን በመጠቀም በማሳ ላይ በሚካሄድ የመስኖ መርምር ፕሮግራም ላይ ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፣ በጋራ ያቅዳል፣
- ☞ ዓመታዊውን የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ መሠረት በማድረግ የመስኖ ግብዓቶች ማለትም ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የበሽታ/ተባይ መከላከያ መድሀኒት ፍላጎትን ይገመግማል፣ የሚገኙበትን ስትራቴጂ ይቀይሳል፣
- ☞ ለውሃ ተጠቃሚዎች ብድሮች መመቻቸታቸውን፣ የገበያ አማራጮችን እና የመስኖ ልማት አተገባበር መኖራቸውን ይገመግማል፣
- ☞ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን አደረጃጀት ለማጠናከር ድጋፍ ያደርጋል፣

☞ የመስኖ ልማት ምርምር አፈጻጸምን፣ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎትን፣ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበርንና ህብረት ሥራ ማህበራትን ለመዳሰስ/ለማየት የመስክ ጉብኝት ያካሂዳል፣

☞ በዞኑ ውስጥ የጋራ ግምገማ፣ አውደ ጥናትና ዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል፣

☞ ዓመታዊ ሪፖርት ለክልሉ የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ያቀርባል፣

☞ወቅታዊ አውደ ጥናት፡- የዞን የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ በዓመት ሁለት ጊዜ አውደ ጥናት ያካሂል፡፡ የመጀመሪያው አውደ ጥናት የመስኖ ምርምር ተግባራትን፣ የግብዓት አቅርቦትን እና የቀረቡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ምክረ ሀሳቦችን ለመገምገም ከመስኖ ሰብል ልማት ወቅት በፊት ሊካሄድ ይችላል፡፡ ሁለተኛው አውደ ጥናት በመስኖ ሰብል ልማት ማጠናቀቂያ ወቅት የሚካሄድ ሲሆን የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተቋማዊ ድጋፍን አፈጻጸምና ሌሎች በድንገት በተከሰቱ ጉዳዮች ወይም ጉድለቶች ላይ ይወያያል፡፡ የዞኑ የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ የአውደ ጥናት አጀንዳን አዳብሮ በዕቅድ ውስጥ ለማካተት የመወያያ ጽሁፎችን ከተሳታፊዎች ይሰበስባል፡፡

የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊና እና የመስኖ ልማት የሥራ ሂደት ኃላፊዎች ከሌሎች የወረዳ ኃላፊዎችና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ጋር በመሆን በአውደ ጥናቱ ላይ መሳተፋቸው በመስኖ ቴክኖሎጂዎች፣ በኤክስቴንሽን ተግባራት፣ በግብዓት አቅርቦት ላይ ግብረ መልስ እንዲያገኙ ስለሚያደርግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በአውደ ጥናቱ የአርሶ/አረብቶ አደሮች ተሳትፎ መኖር ዋና ተግባር ሲሆን አርሶ/አረብቶ አደሮቹ በተገኙበት ውይይት መካሄዱ የአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ አባዎራዎች እና እማወራዎች በማህበረሰቡ ዘንድ አሳሳቢ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በመስኖ ቴክኖሎጂዎች፣ በኤክስቴንሽን ተግባራት፣ በግብዓት አቅርቦት፣ ሳይታሰብ በመጡ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የውሃ ተጠቃሚዎች ግብረ መልስ እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡ የአውደ ጥናቱ የተሳታፊዎች ቁጥር ከ30 እንዳይበልጡ ይመከራል፡፡ ይህ መሆኑ የኮሚቴውን የቴክኒክ አካሄድና የቡድን ሥራዎችን ለመቆጣጠር በሚያግዝ መልኩ ለማመቻቸት ይረዳል፡፡

## 8.2.3. በወረዳ ደረጃ

በክልልና በዞን ደረጃ ከሚካሄደው የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ መለስተኛ መድረክ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በተመረጡ የወረዳ ግብርና ልማት አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስል (ADPLAC) መድረክ ስር ሆነው የወረዳ አገልግሎት ማስተባበሪያ መለስተኛ መድረክ ያካሄዳሉ፡፡ የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ለወረዳው የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ሁለንተናዊ መመሪያ መስጠትና በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ኃላፊነት አለበት፡፡ የወረዳ የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ የኤክስቴንሽን ፕሮግራምን፣ ምርምርን፣ የመስኖ ልማትን፣ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝን፣ የግብዓት አቅርቦትንና ግብይትን፤ እንዲሁም የግንኙነት ማኔጅመንቱን ይቆጣጠራል፡፡ አንዳንድ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮችም ሲኖሩ ማስተባበሪያው ለወረዳ ካቢኔ አቅርቦ ያስወስናል፡፡

☞ በተወሰነ ጊዜ የሚካሄዱ ስብሰባዎችና አውደ ጥናቶች፡- በአጠቃላይ የወረዳ የመስኖ

ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ እንደ ሥራው ባህሪ አስፈላጊ ስብሰባ ያካሄዳል፡ ፡ በወረዳ የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ በኩል መደበኛ የሆነ የስብሰባ ጊዜ አይኖርም፡፡ይሁን እንጂ የአነስተኛ እና ጥቃቅን መስኖ ልማትን ጠቃሚነት በማገናዘብ የወረዳ መስኖ አገልግሎት ማስተባበሪያ በመስኖ ወቅት ቢያንስ 3 ጊዜ ስብሰባ ያከሄዳል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የወረዳ መስኖ አገልግሎት ማስተባበሪያ የስብሰባ ድግግሞሽን አስፈላጊነት የሚወስነው በመስኖ ላይ የሚደረገው ጥረት አስቸኳይ በመሆኑ ነው፡፡ በወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የሥራ አጀንዳ መሠረት የወረዳው የኤክስቴንሽን የሥራ ሂደት በመስኖ ልማት ዕቅድ ዝግጅትና አተገባበር፣ በክትትል እና ግምገማ፤ እንዲሁም በመስኖ አውደ ጥናት ሂደት ላይ በቅደም ተከተል ለሚከናወኑ ሥራዎች ውይይት እንዲካሄድ መነሻ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

የምክክር መድረክ የመስኖ ወቅት ከመድረሱ በፊት አግባብ ያላቸውን አጋር አካላት ማለትም የምርምር ማዕከላትን፣ የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶችችን፣ በአካባቢው ያሉ የህ/ሥራ ማህበራትን፣ የብድር ተቋማትን፣ የኢትዮጵያ የግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽንን፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ የሥራ ሂደትን፣ የውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን እና የአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ የውሃ ተጠቃሚዎችን በማሳተፍ በወረዳ ደረጃ የመስኖ ልማት ዕቅድ አስቀድሞ ሊዘጋጅና የጋራ ሊደረግ ይገባል፡፡

አውደ ጥናቱ ቅድሚያ ለየሚሰጣቸውን የመስኖ አግሮኖሚ ተግባራትን አካቶ ለግብዓት ተደራሽነትና የድጋፍ አገልግሎት በቁልፍ ባለድርሻ አካላት መካከል ያለውን ግንኙነት ያሳልጣል፡፡ እንዲሁም ለተረጋጋ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ የቁርጠኝነት ስሜትን ያሰርጻል፡፡ በመጨረሻም አውደ ጥናቱ በቀበሌ ደረጃ ያለውን የመስኖ ልማት ዕቅድ ከወረዳ የመስኖ ልማት ዕቅድ ጋር ያጠቃልላል፣ እንዲሁም ዕቅዱን ለዞን የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ አቅርቦ እንዲፀድቅ ያደርጋል፡፡

## 8.3. ተግባራዊ የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ንዑስ መድረክ አወቃቀር

ተግባራዊ የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ንዑስ መድረክ በመስክ ደረጃ ያለ ግንኙነትና የማስተባበር ሂደት ሲሆን የኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ ተመራማሪዎች፣ የህ/ሥራ ማህበራት ሠራተኞች፣ የውሃ ተጠቃሚዎች በመስክ ደረጃ ተሰባስበው የመስኖ ልማት ሰራተኞችን አገልግሎትና የቀን የስራ ዕቅዶችንና ክንውኖችን ይገማግማሉ፡፡ ዕዝል 2- የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ መለስተኛ መድረክ አውታር የስራ ዝርዝር ይመልከቱ

**ሠንጠረዥ- 1፡-የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ መለስተኛ መድረክ**

| ዝርዝር | የድጋፍ ተግባራት | የድጋፍ /የአሠራር ዘዴ | ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም |
|---|---|---|---|
| የመስኖ ቴክኖሎጂ ልማት | የመስኖ ልማት ምርምር አጀንዳ መቅረጽ | ችግሮችን በጋራ መለየትና በደረጃ ማስቀመጥ፣ የአፈጻጸም ግምገማን በጋራ ማካሄድ | የምርምር ተቋማትና የሚመለከታቸው የትምህርት ተቋማት/ዩኒቨርስቲዎች |
| | በተለዩ የአነስተኛና ጥቃቅን የመስኖ ቴክኖሎጂዎች ላይ ግንዛቤ መፍጠር | የአርሶ/አረብቶ አደር ንቅናቄ፣ የተለያዩ ብዙሀን መገናኛ | ግብርና ቢሮና የግብርና ምርምር ተቋም |
| | የቴክኖሎጂ ማረጋገጫ | አሳታፊ የቴክኖሎጂ ልማት ሙከራዎችና ሠርቶ ማሳያዎችን በመጠቀም በጋራ የማላመድ ሥራ ማከናወን | ምርምር፣ ግብርና ቢሮ፣ የግል ሴክተር |
| ቴክኖሎጂ ማባዛት | ቴክኖሎጂ ማባዛት | ቴክኖሎጂውን የሚያባዛ ተቋም መስራች ዘር፣ ማባዥያ ማዕከል | የምርምር ማዕከላት እና ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ/ድርጅት |
| | ፍላጎት መፍጠርና ግብረ መልስ | የዳሰሳ ጥናት ማካሄድና የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች የቴክኖሎጂ ፍላጎት መለየት | የዞን ግብርና ጽ/ቤትና የምርምር ጣቢያ |
| ቴክኖሎጂ ማሰራጨት | የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ማዘጋጀት | የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ምክረ ሀሳብ በጋራ ማዘጋጀት፣ ስልጠና መስጠት፡ ክትትልና ግምገማ ማድረግ | የክልልና የዞን የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ፣ የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት፣ የምርምር ማዕከላት |
| የመስኖ ልማት ግብዓቶች | የመስኖ ልማት ተጠቃሚዎችን የግብዓት ፍላጎት መለየት | ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ ፀረ-ተባይ ኬሚካል፣ብድር፣የእርሻ መሳሪያዎች አቅርቦት | የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ፣ የግብርና ግብዓት አቅርቦት ኢንተርፕራይዝ ህ/ሥራ ማህበራት |
| ብድር | ለአነስተኛና ሰፋፊ መስኖ ልማት ተጠቃሚዎች የመስኖ ልማት አገልግሎት ብድር ማፈላለግ | የመስኖ ልማት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የብድር አቅርቦት እንዲኖር ማስቻል | ህ/ሥ/ማህበራት፣ የገጠር ባንክ |
| የውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር | የአቅም ግንባታ | የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበርን/ቡድን ለማጠናከርና የተቀናጀ ስልት መቀየስ | ህ/ሥ/ማስፋፊያ ኤጀንሲ፣ የመስኖ ልማት ማህበራት |
| | የመስኖ ውሃ አስተዳደር | በየደረጃው ላሉ የመስኖ ውሃ ንዑስ ቡድኖች ፍትሃዊ የመስኖ ውሃ ሀብት ክፍፍል፣የመስኖ ውሃ ቁጠባ መተዳደሪያ ደንብ | ህ/ሥ/ማስፋፊያ ኤጀንሲ፣ የመስኖ ልማት ማህበራት |
| | ገበያ ማመቻቸት | ገበያ ተኮር ሰብሎችን ማማረት የገበያ ቦታዎችን ማማቻቸት | የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት፣ ህ/ሥ/ማስፋፊያ ኤጀንሲ |
| የጥገና አጋልግሎት | ለአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ እና ለማህበረሰብ ኩሬ ውሃ ተጠቃሚዎች | የመስኖ መስመር ጥገና፣ የመስኖ ቦይ ፅዳት፣ ማንጣፈፍና ሌሎች የማስተካከያ ሥራዎች | የመስኖ ውሃ ማህበራት የጥቃቅን መስኖ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች የወረዳ የመስኖ ጽ/ቤት፣ በሁሉም ደረጃ የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ መለስተኛ መድረኮች |
| ክትትልና ግምገማ | ክትትልና ግምገማ | የጋራ ክትትል፣ ግምገማ፣ መማማር፣ ግብረ መልስና እና ወቅታዊ ሪፖርቶች | በሁሉም ደረጃ የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ መለስተኛ መድረኮች ይከናወናል |
| የመስኖ ልማት አውደ ጥናቶች | ፌደራል፣ክልል፣ በዞን፣ በወረዳ ደረጃ የሚካሄዱ አውደ ጥናቶች | ፌደራል/ክልል/ዞን/ወርዳ የመስኖ ልማት ዕቅድ ክለሳ/ግምገማ የግብዓት አቅርቦትን ማረጋገጥ | የፌደራል/ክልል/ዞን/ወርዳ ዳይሬክቶሬት መስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ፣ ግብርና ቢሮ፣ የውሃ መስኖና ኢነርጂ ቢሮ፣ ግብርና ምርምር፣ ህ/ሥ/ማስፋፊያ ኤጀንሲ |

## 8.4. በየደረጃው ያሉ የመስኖ ልማት አጋር አካላት የሥራ ድርሻ

### 8.4.1 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የሥራ ሂደት (ዳይሬክቶሬት)

- ☞ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የሥራ ሂደት(ዳይሬክቶሬት) የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂ ፓኬጅ ዝግጅትን ለማገዝ በህብረተሰብ ፍላጎትና በመስኖ ቴክኖሎጂ ክፍተት ላይ መረጃ በመሰብሰብ ለመስኖ ልማት አጋር አካላት ማስተባበሪያ ማስተላለፍ፣
- ☞ ግብርና ቢሮ በመስኖ ወቅት የአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ የውሃ ተጠቃሚዎችን ለመደገፍ ይረዳ ዘንድ በተመረጡ ወረዳዎች/የመስኖ አውታሮች/የማህበረሰብ ኩሬ የመስኖ ልማት ሰራተኞች መኖራቸውን ማረጋገጥ፣
- ☞ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የሥራ ሂደት/ዳይሬክቶሬት/ በአርሶ/አረብቶ አደሮች ማሰልጠኛ ተቋም፣ በአነስተኛና ጥቃቅን የመስኖ አውታሮች የመስኖ ሥራ፤የመስኖ ሠርቶ ማሳያዎችን፣ የመስኖ ቴክኒሎጂ ልማት ጉዳዮች፣ የመስኖ ውሃ መሳቢያ መሣሪያዎች፣ የጠብታ መስኖ፣ ወዘተ ላይ በስልጠና፤ ተግባር ተኮር የአሠራር እገዛዎችን ማድረግ፣
- ☞ የመስኖ ባለሞያዎች ኤክስቴንሽን የሥራ ሂደት/ዳይሬክቶሬት/ ከመስኖ የልማት ሰራተኛው ጋር በመሆን በተመረጡና ወቅታዊ በሆኑ የመስኖ ርዕሶች ላይ ወርሀዊ ሥልጠናዎችን ማመቻቸት፣
- ☞ ለመስኖ ስራ አመቺ ሆኖ የተመረጠውን/የተቀረፀውን የኤክስቴንሽን ዘዴን ከአከባቢውና ከክልሉ/ዞኑ/ወረዳው ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም በየደረጃው አፈጻጸሙን መከታተልና እንደ አስፈላጊነቱ ግምገማ ማካሄድ፣፣
- ☞ ተግባረዊ የሆነ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ለመቅረፅ በክልል፤ በዞንና ወረዳ (ከቀበሌ) ውስጥ ያለውን ልምድ/ተሞክሮ፤የመስኖ ቴክኖሎጂና ጉድለቱን፤የአፈፃጸም ደርጃውን መረጃ ማሰባሰብና መተንትን፣
- ☞ የክልሉን/ዞኑን/ወረዳዎችን የመስኖ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ችግር በቅደም ተከተል መለየትና ለግብርና ልማት አጋር አካላት አማካሪ ካውንስል ግብረ መልስ ለመስጠት፣
- ☞ በአከባቢው ላሉ አነስተኛና/ሰፋፊና አርሶ/አርብቶ አደሮች አስፈላጊና ወቅታዊ የመስኖ ልማት፣ ገበያ፣ ግብዓት ወዘተ መረጃ ለመስጠት የሚያስችሉ የተለያዩ የኤክስቴንሽን መልዕክቶችንና ዘዴዎችን ማውጣት፣
- ☞ የክልል፤ዞንና የወረዳ የመስኖ ባለሙያዎችንና የመስኖ ልማት ሰራተኞችን ዕውቀትና ክህሎት አቅም በስልጠና፣ አውደ ጥናቶች፤ የልምድ ልውውጦች ወዘተ ማዳበር፣
- ☞ በክልሉ ውስጥ ከመስኖ ኤክስቴንሽን አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ችግሮችን ማጥናት፣ አማራጭ መፍትሄዎችን ማስቀመጥና አፈጻጸሙን መከታተል፣
- ☞ የክልሉን ዓመታዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አፈጻጸም ግምገማ ማካሄድ፤ በተገኙ ምርጥ ተሞክሮችና በገጠሙ ችግሮች ላይ በመመርኮዝ የቀጣይ ዓመት ዕቅድ/መርሀ-ግብር በማዘጋጀት ለዞንና ወረዳዎች ግብረ መልስ መስጠት፣

- ☞ በዞንና ወርዳ ለሚገኙ የመስኖ ልማት ባለሙያዎች ተግባር ተኮር የመስክ ድጋፍ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣
- ☞ በክልሉ ውስጥ ውጤታማ የሆኑ የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን ስኬት በመለየት የአነስተኛ/ጥቃቅን መስኖ ሠርቶ ማሳያዎችን ምርጥ ተሞክሮ ማሰባሰብና ማዘጋጀት፤ ለሌሎች የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ተሞክሮን ማስፋት፣
- ☞ የክልል የግብርና ቢሮ ከልማት አጋር አካላት አማካሪ ካውንስል ጋር በመቀናጀት ሁለንተናዊ የመስኖ ልማት ተግባሮችን ማስተባበር፣
- ☞ በክልል ደረጃ የመስኖ ባለሙያዎች የቴክኒክ ቡድንን መመስረትና መደገፍ፣
- ☞ በመስኖ ኤክስቴንሽን የስራ ሂደት/ዳይሬክቶሬት ውስጥ ለሚሰሩ የተለያዩ የመስኖ ፕሮጀክቶች ጠንካራ ፎካል ፐርሰን በመመደብ አተገባበርን መከታተል፣
- ☞ ከፌዴራል ግበርና ሚኒስቴር ጋር በቅርበት በመመካከር የወጡ መመሪያዎችንና የሚነበቡ ማንዋሎችን ከመስኖ ኤክስቴንሽን ሲስተምና ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር እንዲስማማ ማድረግ እና አተገባበሩን መከታተል፣
- ☞ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ስኬታማነትን ለመገምገም ከክልሉ የባለሙያዎች ቡድን ጋር ግምገማዊ ስብሰባ ማካሄድ፣
- ☞ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ፕሮግራምና የሰብል ስብጥር ስርዓትን ማሰልጠን፣መንደፍና ማስተዋወቅ፣
- ☞ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሥራው ያመጣውን ለውጥ በየጊዜው በመገምገም በክፍተቶች ላይ ማሻሻያ በማድረግ የኤክስቴንሽን አገልግሎቱ እንዲጠናከር ማድረገ፤

## 8.4.2 የመስኖ ልማት ግብዓት አቅርቦት እና ግብይት

የመስኖ ልማት ግብዓት አቅርቦትና ግብይት በሁሉም ደረጃ ላሉ የመስኖ ሰብል ልማት አምራቾች ትልቅ ሚና ይጫዎታል፡፡ የመስኖ ግብዓት አቅርቦትና ግብይት ትኩረት የሚጀምረው በአከባቢው ባለ የገበያ ፍላጎት መረጃ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህም ማለት አርሶ/አርብቶ አደሩ ገበያ ተኮርና ከፍተኛ የምግብ ይዘት ያላቸውን የመስኖ ሰብሎች እንዲያመርት ቁልፍ ተግባር ሲሆን የክልሉ፣ዞኑና ወረዳው የግብዓት አቅርቦትና ስርጭት እንዲሁም የመስኖ ሰብል ምርትን ለመጨመርና ዘላቂ ለማድረግ ግብዓትና ግብይት ማመቻቸት ቀዳሚ ተግባር መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡

- ☞ በወረዳ ጽ/ቤቶች የተሰበሰቡ ዓመታዊ የመስኖ ግብዓቶችን ፍላጎት ማደራጀትና ግብዓት ለሚፈልጉ አርሶ/አርብቶ አደሮች የአቅርቦትን ሰንሰለቱን/ስርጭቱ ተግባራዊነት ማረጋገጥ
- ☞ ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች የመስኖ ልማት ብድር፣ የመስኖ እርሻ መሣሪያዎችና መለዋዎጫዎች፤ግብዓት አቅርቦትነ ማግኘት እንዲችሉ ማመቻቸት
- ☞ የገበያ መረጃ ማሰባሰብ፣ማደራጀት፣ መተንተን እና ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣ የገበያ እውቅና ካላቸው አካላት ጋር ማስተሳሰር

- ☞ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን ከምግብ አቀነባባሪዎችና ምግብ አምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ማመቻቸት እና የመስኖ ምርቶችን የእሴት ሰንሰለትና እሴት መጨመር ልምድን ማጠናከር፣
- ☞ ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመተባበር የመስኖ ልማት ሰራተኞች፣ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት እና ሴት አርሶ አደሮች በመስኖ ምርት ጥራትና ግብይት ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ☞ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን አቅርቦት፣አጠቃቀምና አያያዝ ፓኬጅ ማሰልጠን
- ☞ በዝናብ ወቅት በአቅርቦት ደረጃ እጥረት የሚታይባቸውን ምርጥ ዘሮች መስኖን በመጠቀም እንዲለሙ አርሶ/አርብቶ አደሩን በማደራጀት የምርጥ ዘር አቅርቦትን መጨመር፤

## 8.4.3. የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ የሥራ ክፍል

- ☞ የተፋሰስ ልማት ማለትም በመስኖ አውታር ውስጥና ውጪ፣ በማህበረሰብ ኩሬ፣ ግድብና የውሃ ማከማቻዎቸን ለመንከባከብ አርሶ/አርብቶ አደር ንቅናቄ መደገፍ፣
- ☞ በአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ አውታሮች ላይ አካላዊና ሥነ ህይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችና የችግኝ ተከላ ስራዎችን እንዲከናወኑ ሞያዊ እጋዛ ማድረግና ማስተባበር፣
- ☞ የተፋሰስ ልማት ማለትም በወንዝ እና ምንጭ ለተጠለፉ የመስኖ ልማት አውታሮች የታችኛውና የላይኛው ተፋሰስ አካላት ብዛህ ህይወት ጥበቃን ማዕከል ያደረገ መሆን ስለሚገባው አጠቃቀሙን ይከታተላል፣ይመራል፤
- ☞ በተፈጥሮ የሚገኙ ኩሬ እና ሀይቅ ለመስኖ አገልግሎት የሚጠቀሙት የውሃ መጠን በተፋሰሱ ወደነዚህ አካላት ከሚገባው የውሃ መጠን መብለጥ እንደሌለበት እና የውሃ መጠን ሊጨምሩ የሚችሉ የአፈርና ውሃ መጠበቂያ ዘዴዎች እንዲተገበሩ ያስተባብራል፣ ይመራል።

## 8.4.4 የመስኖ ህብረት ሥራ ማህበራት

- ☞ ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበርና የመስኖ ማህበራት የሰነድና መዝገብ አያያዝ ዘዴ ስልጠና መስጠት/መደገፍ፣
- ☞ ግብዓትና ብድር አቅርቦትን በመስኖ ማህበራት ወይም ሁለገብ ህ/ሥራ ማህበራት በኩል ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ማመቻቸት፤
- ☞ በመስኖ ልማት የኩታገጠም አመራረት ዘዴን በተለይ በጥራት እና መጠን የሚፈለጉ ሰብሎች ማስፋፋት እንዲችሉ (የፍጆታ፣ የኢንዱስትሪ እና የኤክስፖርት) በጅምላ ከሚወስዱ አካላት (በአገር ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት እና ወደ ውጭ ከሚልኩ ተቋማት) ጋር ቅድሚያ የገበያ ትስስር ይፈጥራል(ሽጦ ማምረት)፤
- ☞ የመስኖ ልማት ሕ/ሥራ ማህበራት ወደ ዩኒየን ደረጃ የሚያድጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡

## 8.4.5 የግብርና ምርምር ተቋም/ማዕከላት

በምርምርና በኤክስቴንሽን መካከል የሚኖረው ግንኙነት ውጤታማና የተሸሻሉ የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎችን ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ለማድረስ ይጠቅማል፡፡ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ በግብርና ምርምር ማዕከላት እና በግብርና ኤክስቴንሽን አካላት እንዲሁም በሌሎች አጋር አካላት መካከል የሥራ ግንኙነትን የማስተባበር ዘዴ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ አሁን ያለው የግብርና ልማት አጋር አካላት ትስስር አማካሪ ካውንስል መድረክ በሁሉም ደረጃ የምርምር ተቋማትን፣ የግብርና ኤክስቴንሽን ፈጻሚ አካላትን፣ ከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማትን፣ የግብዓትና ብድር አቅራቢ ድርጅቶችን፣የአገልግሎት ሰጪና ተጠቃሚዎችን ያካትታል፡፡ ስለሆነም የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ መለስተኛ መድረክ ሚና በእነኚህ ተቋማት መካከል ያልተቋረጠ የማስተባበር ሥራ መኖሩን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህም በዋናነት የግብርና ልማት አማካሪ አካላት እና የመስኖ ልማት አጋር አካላት በኤክስቴንሽን ስርዓት/ሲስተም ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር የአርሶ/አርብቶ አደር ችግሮች በአግባቡ ስለ መለየታቸውና ለተመራማሪዎች ስለመቅረባቸው፣ በሌላ በኩል የተገኙ መፍትሄዎች በአግባቡ ወደ አርሶ/አርብቶ አደሮች የደረሱ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡

## 8.4.6. የአጋር አካላት ሚና

በሁሉም ደረጃ ያሉ ግብርና ጽ/ቤቶች እና መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል ያለው የማስተባበር ዘዴ በአነስተኛና ጥቃቅን የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በመግባት ለመስኖ ልማት ስኬታማነት ትልቅ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪዎች (የመንግስታዊ/መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የግሉ ሴክተር፣ ግብዓት አቅራቢዎች፣ ነጋዴዎች፣ ህ/ሥራ ዩኒየኖች ወዘተ) መካከል ያለው ግንኙነት የአርሶ አደሮችን ችግሮች ለመለየት፣ በጋራ መፍትሄ ለመፈለግና ተግባራዊ ለማድረግ እና ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ለማሳካት ይረዳል፡፡

ስለዚህ ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠርና በጋራ በማቀድ፣ተግባራትን በማከናወንና በመገምገም ሂደት የሚከተሉት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡-

- ☞ በመስኖ ግብርና ላይ ንቅናቄና ዝግጁነት መኖር፣
- ☞ በመስኖ አገልግሎት ማስተባበሪያ መለስተኛ መድረክ ላይ በንቃት መሳተፍ፣
- ☞ ተከታታይ ክትትል ማድረግ፣
- ☞ በመስኖ አገልግሎት ማስተባበሪያ ስብሰባዎች የመንግስታዊ ያልሆኑና የግል ድርጅቶችን አስተዋጽኦ ማገናዘብ፣
- ☞ በመስኖ አገልግሎት ማስተባበሪያ በኩል የተሰጡ ውሳኔዎችን በጥብቅ መከታተል፣
- ☞ በሚመለከታቸው አካላት መካከል ቋሚ ግንኙነት መኖር፣

## ክፍል 8 ፡- ተግባራዊ ድጋፍ ትብብር እና ቅንጅታዊ አሰራር

የተዛባ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች

በግብርና ግንኙነት አማካሪ ካውንስል/አድብላክ/የሴቶች አደረጃጀት ተወካይ አቅም ያላቸው የሥርዓተ - ፆታ አባላትን በመስኖ ግብርና ለማካተት እንዲሁም ሥርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የኤክስቴንሽን ዘዴ ለመገንባት የሚያስችል የአመለካከትና የክህሎት ክፍተት አለ ፡፡ በተለምዶ ሥረዓተ ፃታ የእያንዳንዱ ሥራ አካል ያለማድግ እና በውይይት እንዲዳብር ትኩረት እየተሰጠው አይደለም፡፡

- የልማት ፍላጎት እና የቴክኖሎጂ ክፍተትን በመለየት እና ቅደም ተከተል በማስያዝ ረገድ በተለምዶ በአጠቃላይ ለአርሶ አደር በሚል እንጂ የወንዶች እና የሴቶች ፍላጎት ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም ማለትም የእማወራ እና ባለትዳር ሴት
- ለአማካሪ ካውንስል ስብሰባ የአርሶ አደር ውክልና ላይ ሴቶች እና ወንዶች እኩል ውክልና የላቸውም
- የፕሮግራም ቅደም ተከተል ለመወሰን የሚያስችል የነበሩ ሁኔታዎች ትንተና በሚሰጥበት ወቅት አ/አደሮች ተመሳሳይ ናቸው በማለት የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ይዘለላሉ፣
- የስልጠና መመሪያዎች እና በአ/አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የሚዘጋጁ ስልጠናዎች ወይም ስልጠናው ሲዘጋጅ የሴት አ/አደር አቅም፣ የትምህርት ደረጃ፣ ቋንቋ እና የመገንዘብ ችሎታ ግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም፡፡
- እንዲሁም ወንዶች እና ሴቶች የተለየ ፍላጎት እና ቀዳሚ ተግባር አላቸው፡፡ የተችውም የኤክስቴንሽን ቴክኖሎጂ አቀራረብ ተፅዕኖ በወንዶች እና በሴቶች የተለየ ተልዕኮ ሊኖርው ይችላል፡፡ ነገር ግን የኤክስቴንሽን ዘዴው ወይም አቀራረብ ውጤታማነትም ሆነ ዕውቀታቸው በሚገመገምበት ሰዓት ሁሉም አርሶ አደሮች ተመሳሳይ ናቸው ብሎ የመወሰድ እና የሚገኙ ግኝቶችም በወንዶች እና በሴቶች በሚል በጾታ የተተነተነ አይደለም፡፡

## የሥርዓተ-ፆታን ጉዳዮች እንዴት በአግባቡ ማዳረስ ይቻላል፡፡

- ሥርዓተ ፆታን በመስኖ ግብርና ለማስረጽና ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ የሆነ የኤክስቴንሽን አቀራረብ ለማስረጽ ከሴቶች አደረጃጀቶች ጋር ትስስር መፍጠር እና የሥርዓተ ፆታ ኤክስፐርቶች እንዲሳተፉ ማድረግ ያስፈልጋል
- የግብርና አማካሪ ካውንስል ስብሰባ አጀንዳዎች ሲቀረጹ የሥርአተ ፆታ ጉዳዮች እንዲካተቱ በማድረግ የሚጠበቀውን ግብ ማሳካት ይቻላል፡፡
- የልማት እቅዶች የቴክኖሎጂ ክፍተት እንዲሁም ቀዳሚ ተግባር የወንዶችና የሴቶችን አገራዊ ሁኔታ በተለየ መንገድ የእማወራ አ/አደር ፍላጎት በስብሰባ ውስጥ የውሳኔ አሰጣጥ ደረጃ እድል የሚሰጥና የሚፈጥር የኤክስቴንሽን አገልግሎት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ነባራዊ ሁኔታ በሚጠናበት ሰዓት የግድ የሥርዓተ ፆታ ትንተና ማካተት አለበት፡፡ ይህም የሴቶች፣ የወንዶች፣ የወጣቶች ፍላጎት እኩል እና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ በማየት ፍላጎታቸውን እንድንጠብቅ ያግዛል፡፡ በአጠቃላይም ማህበረሰቡንም ለማየት የሚያስችል ሁኔታ ይፈጥራል፡፡
- በአማካሪ ካውንስል ስብሰባ ወንዶች እና ሴቶች እኩል ውክልና ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህም ጉዳያቸውን በተጨባጭ ያላቸውን ምልከታ ለማየት ያስችላል፡፡
- የስልጠና መመሪያዎች እና የአ/አደሮች ማሰልጠኛ ማዕከላት የስልጠና ትምህርት/ርዕስ በሚዘጋጅበት ሰዓት የሴቶች የትምህርት ደረጃ፣ የቋንቋ ምርጫቸውን፣ የአቀባበል ደረጃቸውን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡ በአብዛኛው ሴቶች ያልተማሩ እና የአከባቢያቸውን ቋንቋ የሚመርጡ እና የተግባር ስልጠና ይመርጣሉ፡፡
- ለሴቶች ተስማሚ የሆኑ የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂ እንዲፈልጉ ማበረታታት ላይ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡ ፡
- የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ ክትትልና ግምገማ ለማድረግ ውጤቶችን ከሴቶች እና ከወንዶች አንፃር ለማየት የሚያስችል ስትራቴጂ ትስስር መፍጠር እና የኤክስቴንሽን አገልግሎቱን አፈፃፀም በወንዶችና በሴቶች በእማወራ እና በባለትዳር ሴቶች ለይቶ ማየት፡፡

## የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ቢተገበሩ የሚያስገኘው ጥቅም

የአማካሪ ካውንስል እና ሌሎችም ግንኙነት/ትስስር ለስርዓተ ፆታ ምላሽ ሰጪ የኤክስቴንሽን አገልግሎት እና ለሴቶች የተሻለ ተሳትፎ ከፍተኛ እገዛ አለው፡፡ ግንኙነቶችና አሰራሮች ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በሆነ አግባብ የሚተገበሩ ከሆነ የተቀረፀው የኤክስቴንሽን መመሪያ የሴቶችንና የወንዶችን ቀዳሚ ተግባር መፈጸም ይችላል፡፡

- የአገልግሎት እና የልማት ዘዴዎች የሚተገበርበት የወንድ እና የሴት አ/አደሮች ፍላጎት እና ምርጫ መሰረት ያደረገ ሆኖ ዘላቂ እና የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት ያስችላል፡፡ ይህ ማለት የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ የሴቶች እና የወንድ አ/አደሮች እኩል እድል የማግኘት፣ የመስጠት እና አገልግሎትን እኩል የመወሰን መብት በመፍጠር አከባቢ እና የወንድ እና የሴት አ/አደር የኑሮ ሁኔታ ይሻሻላል፡፡

# ምዕራፍ-9 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ ሂደቶች

ተገቢነት ካላቸው አጋር አካላት ጋር ብቻ ከማቀድ ከውሃ ተጠቃሚዎች ጋር የመስኖ ኤክስቴንሽንን ማቀድ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ አንዱ ጠቃሚ ክፍል ሲሆን ወደ ዘላቂ የመስኖ አውታር ዕቅድ ለመምራት ያግዛል፡፡ የአውታሮቹ ስኬት በዋናነት የሚወሰነው የአስተቃቀድ ደረጃዎችን ተከትሎ የታቀዱት ተግባራት በወቅቱ መከናወናቸዉ ላይ ነው፡፡

የመስኖ ልማት ተግባራትን ለማከናወን በእያንዳንዱ ዓመት ወረዳዉ የውሃ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት መረጃ ይለያል፤ እንዲሁም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡ በአጠቃላይ ዓመታዊ የኤክስቴንሽን ዕቅድ የሚያጠቃልለው ዋና ዋና ዝርዝር ተግባራትን ማለትም የማሳ ውስጥ ፕላን ማዘጋጀት፣ ክለሳ ወይም የውሃ ተጠቃሚ ማህበራት ማቋቋም፣ የሚለሙ ሰብሎች መለየት፣ የአሰራርና ጥገና ስትራቴጂ፣ ምርት መሸጫዎች፣ ግብዓት ግዥ፣ የመስክ ቀናትንና ስልጠናን ያካተተ መሆን አለበት፡፡ በመስኖ ወቅት ከዓመታዊው የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ ተግባራትን በማከናወን ረገድ የመስኖ ልማት ወኪሎች ከውሃ ተጠቃሚዎች ጋር አብሮ የሚሠራ ሲሆን የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን እና የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ቡድኖችን ያግዛሉ፡ ፡ በሌሎች ጉዳዮችም እነኝህን ተግባራት ማከናወን የኤክስቴንሽን ተግባራት አፈጻጸምን ለመከታተል እና ወደ አዳዲስ አስተሳሰብ ለመምራት ያስችላል፡፡

የመስኖ ልማት ወቅት ከመጀመሩ በፊት ከታች ወደ ላይ በሆነ ዕቅድ ከመስኖ አውታር ምድብ ደረጃ ጀምሮ የውሃ ተጠቃሚዎች ቡድንን በማካተት ዓመታዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ላይ የመስኖ ልማት ወኪሎች እንደ አመቻች ሆነው የሚሰሩ ሲሆን ለውሃ ተጠቃሚዎች ቡድን የዕቅድ ክህሎት ያስታጥቃሉ፡ ፡ ረቂቅ የመስኖ የማሳ ምድብ (block) እቅዶች ከመጠቃለላቸው በፊት በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር የኮሚቴ አስፈጻሚዎች አማካኝነት በሁሉም የመስኖ አውታር የተጠቃለለው ፕላን ለቀበሌው አስተዳደር ለክለሳ ይቀርባል፡፡ በመጨረሻም የፀደቀው የቀበሌ መስኖ አውታር ዕቅድ ለተጨማሪ ክለሳ እና ዋና(መሪ)ዕቅድ ዝግጅት ወደ ወረዳ ጽ/ቤት ይላካል፡፡ በሁሉም ደረጃ መነሻ ዓመታዊ የመስኖ ዕቅድ በሚዘጋጅበት ጊዜ የሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ይደረግባቸዋል፡፡

- ☞ ባህላዊና ዘመናዊ የመስኖ አውታር፣የቤት ውስጥ አነስተኛና ጥቃቅን መስኖ፣የማህበረሰብ ኩሬና ሌሎች የባለአነስተኛ ይዞታ የአርሶ/አርብቶ አደር የሚለማ የመስኖ ልማት፤
- ☞ አግባብነት ያላቸው አጋር አካላት ማለትም ማህበራት፣ ግብዓት አቅራቢ ነጋዴዎች፣ የብድር ድርጅቶች፣ የመስኖ እርሻ መሣሪያ አቅራቢዎች፣ ምርት መሸጫዎች እና የመስኖ ተጠቃሚዎች ዝርዝር ልየታ፤
- ☞ ለግንባታ፣ ካስፈለገም ትንንሽ መስኖዎች ማለትም ወንዝ/ምንጭ ጠለፋ፣ ግድቦች፣ የጉድጓድ ውሃ፣ ፓምፖች፣ የችግኝ መሠረተ ወ.ዘ.ተ. እንዲያገግሙ የሚያግዝ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፤
- ☞ የመስኖ ውሃ መሄጃ ቦይ (ካናል) እና የማሳ ላይ ሥራዎችን ማሻሻል፣

- ☞ በመስኖ አውታሮች ውስጥ የሚለማ መሬትን ማዘጋጀት፤
- ☞ ለአነስተኛ መስኖ አውታሮች የስበት ወይም የግፊት ኃይልን በመጠቀም ወንዝ ጠለፋን ማጎልበት፤
- ☞ በመስኖ ውሃ አጠቃቀም ለውሃ ተጠቃሚ ቡድን መሪዎች (አገናኝ ገበሬ) እና ለመስኖ ልማት ወኪሎች የስልጠና አውደ ጥናት በማዘጋጀት የማዳበሪያ፣ የሰብል ተባይና በሽታ መከላከያ መድሀኒት፣ የዘር፣ የመስኖ እርሻ መሣሪያዎችን ለማቅረብ የማህበራትና ግብዓት አቅራቢ ነጋዴዎችን ተሳትፎ ማሳደግ፤
- ☞ ለመስኖ ልማት ወኪሎችና ለውሃ ተጠቃሚዎች የስልጠና ፕሮግራም ማዘጋጀት፤
- ☞ ነባራዊ ያለውን የመስኖ ውሃ መጠን አለካክና የመስኖ ማልማት አቅም የክህሎት ስልጠና መስጠት፤
- ☞ የመስኖ ሰብል ስብጥር ፕሮግራም በማዘጋጀት የዕቅድ ትውውቅ ስራ መስራት፤
- ☞ የመስኖ ሰብል ሠርቶ ማሳያዎችን መቋቋም፤
- ☞ በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር የሚመራ ማለትም የመስክ ቀን፣ የተሻሻሉ የአተካከል ዘዴን፣ በአካባቢ ማቴሪያል ብስባሽ ዝግጅትን፣ አካቶ የኤክስቴንሽን ትምህርታዊ ጉዞ፣ የኤክስቴንሽን ጥረትን ከፍ ማድረግ፤
- ☞ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ሰብሎች ልማትን ማስተወቅና ከፍ ማድረግ፤
- ☞ ከምርት በኋላ ቴክኖሎጂንና ለገበያ የሚሆን የምርት እሴት መጨመርን ከፍ ማድረግ፤
- ☞ ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች የገበያ መረጃ (market information system) ማዘጋጀት;
- ☞ ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት እና የው ተጠቃሚዎች ጋር በቀበሌ ደረጃ የሚካሄድ ውይይት፤
- ☞ የተሻሻሉ የሰብል ልማትና መስኖ ቴክኖሎጂ ፓኬጆችን ማዘጋጀት፤
- ☞ ወቅታዊ ሰብሎችን፣ የሚፈለጉ ግብዓቶችን፣ የአቅራቢዎች አሠራር ዘዴን ማቀድ፤
- ☞ የተለያዩ የመስኖ ውሃ ስርጭትና ክፍፍል ስርዓት መተግበሪያ ደንብ ማውጣት፤
- ☞ የተሻሻሉ የመስኖ ውሃ ማጠጫ ዘዴዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፤
- ☞ የተለያዩ የመስኖ ውሃ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችንና ፓኬጆች ማዘጋጀትና ስልጠና ማዘጋጀት፤
- ☞ የተለያዩ የመስኖ ትርፍ ውሃ ማስወገጃና ማጠንፈፊያ ቴክኖሎጂዎችን ፓኬጅ ማዘጋጀትና ስልጠና መስጠት፤
- ☞ የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂ ጥገናና አጠቃቀም መመሪያ ማዘጋጀት

☞ የመስኖ ውሃ ፍላጎትንና አቅርቦትን ማጣጣም፣

☞ በውሃ ሥርጭት የመስኖ ቅደም ተከተል ማዘጋጀት፣

☞ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ማስተዳደር፡፡

ሠንጠረዥ- 11፡-አጠቃላይ ዓመታዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አስተቃቀድ ደረጃዎች

| ደረጃ | ተግባር | የተግባራት ገለፃ | ኃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1 | የውሃ ተጠቃሚ ፍላጎት መረጃ ዳሰሳ ጥናት | ችግሮችን በመመዝገብ፣ አሳታፊ የገጠር ዳሰሳ ጥናት፣ በስብሰባና የመስኖ ልማት ወኪሎች የውሎ ማስታዎሻን በማየት፣ በመስኖ አውታሮች ከወንዶችና ሴቶች የመስኖ ተጠቃሚዎች ጋር አብሮ በመስራት የውሃ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት መረጃ መለየት፣ነባራዊ ያለውን የመስኖ ውሃ መጠን አለካክና የመስኖ ማልማት አቅም የክህሎት ስልጠና መስጠትና መለየት | የመስኖ ልማት ወኪሎች እና የመስኖ ባለሙያዎች |
| 2 | ለመስኖ ልማት ዕቅድ ዝግጅት የመስኖ አውታር የማሳ ምድብ (block) የውሃ ተጠቃሚ ቡድን | ለመስኖ አውታር የማሳ ምድብ (block) ዕቅድ ዝግጅት ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ቡድን መሪዎች ጋር አብሮ መስራት፡፡ የሁሉም መነሻ ዕቅድ በውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ተከልሶ ይጠቃለልና በቀበሌ አስተዳደሩ ተከልሶና ተስማምቶበት ወደ ወረዳ ይላካል፡፡ የመስኖ ሰብል ስብጥር ፕሮግራም በማዘጋጀት የዕቅድ ትውውቅ ስራ ይሰራል፡፡ | የመስኖ ልማት ወኪሎች፣ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት እና ቀበሌ አስተዳደር |
| 3 | የወረዳ መስኖ ማኔጅመንት ኮሚቴ | ስለ ውሃ ተጠቃሚዎች ፍላጎት፣ ስላለው ሀብት፣ እና በወረዳ ደረጃ ስላለው የትብብር ሁኔታና ስምምነት፣ እንዲሁም በወረዳ ስላለው የመስኖ ዕቅድ ዝግጅት አውደ ጥናት መረጃ መለዋወጥና የመስኖ መሰረተ ልማት ፍላጎትና ነበራዊ ሁኔታዎች መለየት እና የመስኖ ልማት ፈንድ እንድቋቋም ድጋፍ ማድረግ | የወረዳ መስኖ አስተዳደር ኮሚቴ |
| 4 | ለመስኖ ኤክስቴንሽን ዕቅድ ዝግጅት መረጃዎችን ወደ አንድ ማሰባሰብ | የወረዳ የመስኖ ልማት ዕቅድ ዝግጅትን ለማገዝ የነባራዊ ሁኔታ መረጃ ፣ ክትትልና ግምገማ ጥሬ መረጃ፣ የጥናት ውጤቶችን፣ የውሃ ተጠቃሚዎች መረጃ ዳሰሳ ጥናት ውጤትን ማሰባሰብ፣ በወረዳ ደረጃ ለሚቋቋሙ የመስኖ ልማት ፈንድ ዩኒት ድጋፍና ክትትል ማድረግ | የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት |
| 5 | የወረዳ መስኖ ልማት ዕቅድ ዝግጅት | የቀበሌ የመስኖ ዕቅድ ዝግጅት መረጃን መሠረት በማድረግ መነሻ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ ማዘጋጀት | ወረዳ |
| 6 | የወረዳ መስኖ ልማት ዕቅድ ማጠናቀቅና በጀት | መነሻ የወረዳ መስኖ ዕቅድ ዝግጅት ውጤትን ማጠቃለልና በወረዳ ደረጃ የመስኖ ልማት ወኪሎች፣ ሌሎች የሚመለከታቸው የሥራ ሂደቶች እና ሌሎችንም አጋር አካላት በመጋበዝና የውሃ ተጠቃሚዎችንም በማካተት የበጀት ሰነድ ማዘጋጀት | የወረዳ መስኖ ኮሚቴ፣ ወረዳ |
| 7 | የዞን ተቋማዊ ድጋፍ ማስተባበሪያ (ISC) | የወረዳ መስኖ ኤክስቴንሽን ዕቅድ መከለስና የኤክስቴንሽን ምክረ ሀሳብ መስጠት | ዞን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8 | የዞን ዓመታዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ ማጠቃለያ | የወረዳ መስኖ ኤክስቴንሽን ዕቅዶችን ማጠቃለል እና የተሰጡ አስተያየቶችን ጨምሮ ወደ ክልል አሳታፊ የመስኖ ልማት ልማት ጽ/ቤት መላክና ማስፀደቅ እንዲሁም በወረዳ ደረጃ ለሚቋቋሙ የመስኖ ልማት ፈንድ ዩኒት ድጋፍና ክትትል ማድረግ | ዞን |
| 9 | የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕላን የቴክኒክ ክለሳ | የቢሮው የሥራ ሂደቶች/ዳይሬክቴሬቶች፣ ግብርና ምርምር ተቋም፣ የውሃ መስኖና ኢነርጂ ቢሮ፣ ህ/ሥ/ማ/ማስፋፊያ ኤጀንሲ፣ የውሃ ተጠቃሚዎች እና የድጋፍ አገልግሎት ሰጪ አጋር አካላት በተሳተፉበት የተጠቃለሉ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅዶች ላይ የቴክኒክ ክለሳ/ግምገማ/ ማካሄድና የመስኖ ልማት ፈንድን ለማቋቋም ተገቢዉን የፋይናንስና የተክኒክ ድጋፍ ማድረግ | የክልል ግብርና ቢሮ |
| 1010 | የፀደቀ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ | የወረዳን ዕቅድ በማካተት በዞን የተጠቃለሉ የመስኖ ዕቅዶችን ማስፀደቅ እና መልሶ ለዞኑ በመላክ እነርሱ ወደ ወረዳ እንዲያስተላልፉ ማድረግ | የክልል ግብርና ቢሮ |
| 11 | የመስኖ እና የቴክኒክ ስልጠናዎች የአሰልጣኞች ስልጠና | በመስኖ ኤክስቴንሽን፣ በውሃ ቆጣቢና ሌሎች የመስኖ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀምና ጥገና፣ መስኖ አግሮኖሚ እና መስኖ ምህንዲስና አሠራር ላይ ለዞንና ወረዳ ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት | የክልል ግብርና ቢሮ |
| 12 | በኤክስቴንሽንና በቴክኒክ አሠራሮች የመስኖ ልማት ወኪሎች ስልጠና | የመስኖ ተግባራት ከመጀመሩ በፊት ለመስኖ ልማት ወኪሎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት | ወረዳ |
| 13 | የአፈጻጸም ስትራቴጂ ክትትል | የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባራትን በታቀደው መሠረት ማከናወን፣ መከታተልና መቆጣጠር | ወረዳ |
| 14 | የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መርሀ ግብር ግምገማ | የእውቀት፣ የተነሳሽነትና የልምምድ ጥናት በማካሄድ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን መገምገም | ወረዳና ዞን |
| 15 | የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን መርሀ ግብር ወቅታዊ ሪፖርት ዝግጅት | በመስኖ ኤክስቴንሽን ተግባራት ውጤቶች ላይ አጭርና ግልጽ ወርሀዊ እና ዓመታዊ ወቅታዊ ሪፖርት ማዘጋጀት | ወረዳ |

### የውሃ ተጠቃሚዎች መረጃ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት (WUINA)

- ☞ ዓመቱን በሙሉ የመስኖ ልማት ወኪሎች አሳታፊ የገጠር ግመታ/የማመዛዘን ሥራ/ (PRA)፣ ችግር ልየታ፣ ከውሃ ተጠቃሚዎች ጋር ስብሰባ እና ውይይት፣ በኤክስቴንሽን የውሎ ማስታወሻ ደብተር ላይ ይመዘግባሉ፤
- ☞ የውሃ ተጠቃሚዎች መረጃ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ውጤት በዓመታዊ የአስተቃቀድ ክለሳ ሂደት ላይ ይጠቅማል፡፡

### የመስኖ ምድብ /ብሎክ/ የውሃ ተጠቃሚዎች (IWUG)

- ☞ የመስኖ ልማት ወኪል (IDA) በመስኖ አውታሩ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችን የአስተቃቀድ ስብሳባ በአርሶ አደሮች ማሠልጠኛ ማዕከል ውስጥ ያደራጃል፤
- ☞ የውሃ ተጠቃሚዎች ቡድን መሪ የመስኖ ምድብ/ብሎክ/ ዕቅድ ዝግጅት ላይ የብሎክ አባላትን ያግዛል፤
- ☞ የመስኖ ምድብ /ብሎክ/ ዕቅዱ በውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር በኩል ይጠቃለላል፡፡
- ☞ የቀበሌ አስተዳደሩ እቅዱን ከልሶ ለወረዳው የመስኖ ጽ/ቤት ያቀርባል፤
- ☞ የመስኖ አስተቃቀድ ሰነዱ ገላጭ እትም የአፈጻጸም ስትራቴጂውን ዋና ዋና ተግባራት በዝርዝር ያብራራል፤
- ☞ ዕቅዱ ተከልሶ እንዲፀድቅ ለዞኑ ይቀርባ፤

### የወረዳ መስኖ ማኔጅመንት ኮሚቴ (IMC)

- ☞ የወረዳ ግብርና ልማት የመስኖ ማኔጅመንት ኮሚቴን ያደራጃል፤
- ☞ የመስኖ ማኔጅመንት ኮሚቴ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ ላይ አተኩሮ የመስኖ ጽ/ቤት ይደግፋል፤
- ☞ የመስኖ ማኔጅመንት ኮሚቴ በመስኖ ወቅት ቢያንስ 4 ጊዜ ስብሰባ ይኖራል፤
- ☞ በሌሎች የመስኖ ልማት አገልግሎት ሰጪዎች ማካከል, የግብርና ግብዓት እና የምርት ገበያ ትስስር፣ የብድርና ቁጠባ ተቋማት፣ የምርምር ማዕከላት፣ ግብዓት አቅራቢዎች፣ የግብይት ማህበራት፣ የመስኖ ማህበራት፣ የአርሶ አደር ማህበራት፣ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ያስተባብራሉ፤
- ☞ የወረዳ የመስኖ አጠቃቀም ኮሚቴ እንደዚሁ ከሌሎች ድርጅቶች መካከል ትብብር እና ትስስር እንዲኖር ምናልባትም የተለየ ሀሳብ ለማዳበር ሚና ይኖራቸዋል፤

## 9.1. ለዕቅድ መረጃ ማሰባሰብ

- ☞ ከፍተኛ ጥራት ያለው ዕቅድ የሚዘጋጀው ከፍተኛ ጥራት ባለው ተገቢ መረጃ ላይ ተመስርቶ ነው፡፡
- ☞ በመስኖ አሁን ስላለው ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ የሚያካትተው፡-

- ☞ ምርት መሸጫዎች እና የግብርና ምርቶች የገበያ ዋጋ፣
- ☞ የመስኖ ልማት  ማህበረሰብ የህዝብ ጥሬ ዳታ፣
- ☞ የአግሮ ኢኮሎጂ መረጃ፣
- ☞ የሰብል አዘራር ዲዛይንና መጠን፣
- ☞ የክትትል ውጤቶች፣
- ☞ የመስኖ ልማት ተክኖሎጂ ፍላጎትና አቅርቦት፣
- ☞ የግብርና ምርቶች ክምችት ማመቻቸት፣
- ☞ ለአካባቢ/ቀበሌ/ የመስኖ ልማት መሳሪያዎች አቅርቦትና ሽያጭ ፣
- ☞ የተለያዩ ጥናቶች የግምገማ ውጤቶች፣
- ☞ በመስኖ ሥራ አካባቢዎች ያላቸውን ጥንካሬና እጥረት በተመለከተ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪዎችንና ሌሎች አጋር አካላትን መረዳት፤
- ☞ የመስኖ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች በመስኖ ኤክስቴንሽን የአቀራረብ ዘዴ ላይ ትኩረት ማድረግ፤
- ☞ ማንኛውም የኤክስቴንሽን ጅምሮች ወይም ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች፤
- ☞ የወረዳና ክልል ግብርና ጽ/ቤት/ ቢሮ የበጀት ምደባ መስፈርት፡፡

## 9.2. የወረዳ አስተቃቀድ አውደ ጥናት

- ☞ የአስተቃቀድ አውደ ጥናት ይደራጃል
- ☞ የወረዳ ባልደረባ እና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው አካላት በአውደ ጥናቱ መሳተፍ አለባቸው
- ☞ አውደ ጥናቱ 3 ስብሰባዎች አሉት
    - የአስተቃቀድ መረጃ ላይ በሚደረግ ትኩረት
    - ምርትን፣ ውጤትን፣ ተጽዕኖን ስለ ማፍለቅ
    - የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባራትን ልየታ

## 9.3. የወረዳ መስኖ ልማት ሥራ ዝርዝር የአስተቃቀድ ቅጽ

- ☞ ከወረዳ አስተቃቀድ አውደ ጥናት በኋላ የወረዳ ባለሙያዎች የወረዳ አስተቃቀድ ቅጽ ያሟላሉ (ከዚህ በታች እንደተመለከተው)፤
- ☞ በቅጹ ያለው ክፍል በወረዳ አስተቃቀድ አውደ ጥናት፤

- ☞ ገላጭ የሆነ ትርጉም ያለው የመስኖ አስተቃቀድ ሰነድ የአተገባበር ስትራቴጂው በዋና ዋና ተግባራት ላይ በዝርዝር እንዲዘጋጅ ያስፈልጋል፤
- ☞ ለክለሳና ለማስፀደቅ ዕቅዱ ለዞኑ የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ይቀርባል፡፡ ዓመታዊ የቀበሌ (ዕዝል 7) ፣ የወረዳ (ዕዝል 8) መስኖ አስተቃቀድ ተግባራት ቅጽ እና ዕዝል 9 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ አዘጋጃጀት ቅጽ ይመልከቱ፡፡

## 9.4. የዞኑን ዓመታዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ ማጠቃለል

- ☞ የወረዳ መስኖ ልማት ዕቅድን ለመደገፍ ዞኑ በወረዳዎች የተዘጋጁ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅዶችን ያጠቃልላል፤
- ☞ የመጽሄቶችን ትርዒቶችን፣ ሠርቶ ማሳያዎችን፣ የወረዳ ባለሙያ ስልጠናዎችን ያጠቃልላል፤ የተጠቃለለው ዕቅድ ለክልል ተልኮ ይፀድቃል፡፡
- ☞ የዞን መስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያና የግብርና ልማት አጋር አካላት ትስስር መድረክ
- ☞ የዞን መስኖ አገልግሎት ማስተባበሪያ የሚቋቋመው ተገቢነት ካላቸው አጋር አካላት ሲሆን የመስኖ ፐሮግራም አተገባበርን ያግዛል፤
- ☞ የዞን መስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ ዋና ሥራው ወደ ክልሉ ከመቅረቡ በፊት የወረዳ መስኖ ዕቅዶችን መከለስ እና የዞን ተግባራትን ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

## 9.5. የክልል መስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ (ISC)

- ☞ የክልል ኮሚቴ ሥራውንና የአርሶ አደር ማህበራትን ጨምሮ ከመስኖ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪዎች ጋር እንዴት ትስስር እንደፈጠሩ ይከልሳል፤
- ☞ ክልሉ በዋናነት ከዞን የቀረበውን የተጠቃለለ ዕቅድ አካቶ ተገቢ ያልሆኑ ስትራቴጂዎችን ወይም ቴክኖሎጂዎችን ለመከለስ ቁልፍ ሚና ይኖረዋል፤
- ☞ የክልል መስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ መነሻ ዕቅድንና አስተያየቶችን ያፀድቃል፡፡

## 9.6. የተጠቃለሉ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅዶችንና በጀትን ማስተካከል

- ☞ ማስተካከያዎቹ የሚከተሉት ዓይነቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡-
  - ተግባራትን መሠረዝ፣
  - ተጨማሪ ተግባራትን መጨመር፣
  - ከአስፈለገ ዝርዝር ተግባራትን ማስተካከል፡፡
- ☞ ማንኛውም የተደረገ ማስተካከያ ከውሃ ተጠቃሚ መረጃ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት

ማፈንገጥ የለበትም፤

☞ ከክልል የመስኖ ልማት አገልግሎት ማስተባበሪያ በቀረበ አስተያየት መሠረት የዞን ዕቅድ ይጠቃለላል፤

☞ የኤክስቴንሽን አስተቃቀድ የኮምፒዩተር ፕሮግራምን (ሶፍትዌር) በመጠቀም ሁሉም ጥሬ መረጃ ወደ ኮምፒዩተር ውስጥ ይገባል፤

☞ ጥሬ መረጃ በሚገባበት ጊዜ የዞን ባልደረባዎች (ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች) ትክክለኛ የምስጢር ቁልፍ ቁጥር ያለው ስለመሆኑ እያንዳንዱን የታቀደ ተግባር ይፈትሻሉ፤

☞ ጥሬ መረጃ ማስገባቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የዞን መምሪያዎች መነሻ ዕቅዱን ያሻሽላሉ ፤ የእያንዳንዱን ወረዳ የመጨረሻ እትም አባዝተው ያወጣሉ፤

☞ የፀደቀው የወረዳ ዕቅድ እትም ለትግበራ ወደ ሚፈለገው ወረዳ ይላካል።

## 9.7. የአሰልጣኞች ሙያዊ (ቴክኒክ) ስልጠናን ማካሄድ

☞ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅዶች እና ዕቅዶቹ የያዟቸው ተግባራት በወረዳ ባለሙያዎችና በመስኖ ልማት ወኪሎች ይተገበራሉ፤

☞ ሁለት ዓይነት መሪ ክህሎቶች አሉ።

- የመስኖ ቴክኖሎጂ ክህሎት፣
- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክህሎት፣

☞ አሠልጣኞች በቂ እና ተግባራዊ እውቀትና ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል፤

☞ በመስኖ ኤክስቴንሽን ለወረዳ ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል።

## 9.8. ወረዳ ላይ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና ማካሄድ

☞ የአሠልጣኞች ስልጠና በተሰጠበት ተመሳሳይ መንገድ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስልጠና በየአካባቢው ይታቀዳል፤

☞ የመስኖ ልማት ወኪሎች ዋና ተሳታፊዎች ናቸው፤

☞ ስልጠናዉ የሚያካትታቸው ምስል (ቪዲዮ)፣ፍሊፕ ቻርት፣እና ፖስተሮች (የሚለጠፉ ምስሎች) ዓመታዊ የኤክስቴንሽን ፕላን፤

☞ የመስኖ ልማት ወኪሎች ለውሃ ተጠቃሚዎች የሥራ ላይ ስልጠና ለመስጠት ሀላፊነት አለባቸው።

## 9.9. የአተገባበር ስትራቴጂ እና ክትትል

- ☞ ከዕቅዱ በመነሳት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን እንቅስቃሴዎችን መፈፀም እና በመስኖ ልማት ወኪሎች የኤክስቴንሽን የውሎ ማስታዎሻ ላይ የተመዘገቡ ተግባራትን መከታተል ለተሳካ የኤክስቴንሽን አፈጻጸም ቁልፍ ተግባር ነው፡፡
- ☞ በአተገባበር ወቅት የተሰባሰቡ ጥሬ መረጃዎችን መከታተል ለዕቅዱ ሂደት አስፈላጊው አካል መሆኑን ማገናዘብ ይገባል፡፡

## 9.10. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን መገምገም

- ☞ ግምገማው የሚያካትተው በአተገባበር ወቅት የተመዘገቡ የክትትል መረጃዎችን መተንተንን ነው፡፡
- ☞ ከእያንዳንዱ የትግበራ ወቅት ግምገማ የሚካሄደው፡-
  - ግቦች እየተሳኩ ስለመሆኑ ለማጣራት፣
  - ግቦች ተገቢ ስለመሆናቸው ለማጣራት፣
  - ማንኛውንም የተለየ ጥንካሬ ለመለየት፣
  - ድክመቶች የነበሩ ስለመሆኑ ለመለየት ነው፡፡

## 9.11. ዓመታዊ የበጀት ግምት ሪፖርት ማዘጋጀት

- ☞ የወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች በኩል ቅድሚያ በጀት ማዘጋጀት፤
- ☞ እነኝህን በቅድሚያ ለማስጸደቅ ተግባር ለወረዳ አስተዳደር ይላካል፤
- ☞ በመጨረሻም የተገመተው በጀት እንዲፀድቅ ይደረጋል፤ ገንዘቡም በተቀመጠው ውል/ዝርዝር/ መሠረት ይመደባል፡፡

ክፍል 9

## ስርዓተ-ፆታን ያማከለ የመስኖ ኤክስቴንሽን ተግባራትን በመለየት ስለማቀድ

- የመስኖ ኤክስቴንሽን ተግባራት ሲታቀድ የሴቶች ጉዳይ ተለይቶ አይታቀድም፣ ትኩረትም አያገኙም።
- በተለያየ ደረጃ ያሉ የሥርዓተ-ፆታ ባለሙያዎች የኤክስቴንሽን ዕቅድ ሲከለስም ሆነ ሲፀድቅ የስርዓ-ፆታ ጉዳዮች በዕቅዶቹ እንዲካተቱ ያለመካተትልና ያለማድረግ ችግር ይታያል።
- የመስኖ ተግባራት ዕቅድ ሲታቀድ ነባር እና የተሻለ የሥርዓተ-ፆታ መዋቅሮች (የሴቶች ማህበር፣ የሴቶች ልማት ቡድን) እና የሴቶች ጉዳዮችን የሚከታተሉ ተቋማትን የማሳተፍ ስራ አይሰራም።

## እንዴት ውጤታማ ማድረግ ይቻላል?

- በተለያየ ደረጃ ያሉ ሁሉም ባለሙያዎች በተቀናጀ መልኩ ወንዶች እና ሴቶች በተመለከተ እኩል ማየት የሚችሉበት ዘዴ የሚያስችል አቅም እንዲኖራቸው ማድረግ እና የመስኖ ኤክስቴንሽን አቅም ሲከለስ ከሥርዓተ-ፆታ አንፃር በማቆራኘት ከዕቅድ ጀምሮ እስከ ገምጋሚ ባለሙያ በሁሉም ደረጃ እኩል የወንዶች እና የሴቶች ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ ታሳቢ ማድረግ የሚያስችለውን አቅም እንዲኖረው ማድረግ ማረጋገጥ።

## የሚያስገኘው ጥቅም:-

- በሁሉም ደረጃ ላይ የሚገኙ ባለሙያዎች ያለውን የመሪነት ቦታ ክፍተት በመረዳት ሥርዓተ-ፆታን ያማከለ እና ምላሽ ሰጪ ዕቅድ ለማዘጋጀት እና ለመተባበር የሚያስችል የተለያዩ አቅም እና ክህሎት እንዲኖርራቸው ያስችላቸዋል። ሴቶችና ወንዶችን በሚመለከት በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ በማድረግ ዘላቂ፣ የተሻሻለ የመስኖ ቴክኖሎጂ ትግበራን ማሳካት ይቻላል።

# ምዕራፍ-10 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የክትትል፣ግምገማና መማማር

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአነስተኛ እና የቤተሰብ መስኖ እና የማህበረሰብ ኩሬ በመስኖ አውታሮች የሚከናወነውን የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን እንቅስቃሴዎች ወይም ተግባራት የክትትልና ግምገማ መሣሪያዎችንና አሰራሮችንና ቴክኒኮችን ነው፡፡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ክትትልና ግምገማ መሣሪያዎች ተጽዕኖዎች ወይም ውጤቶች መለኪያ የአገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል ይጠቅማሉ፡፡ ይህም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች እርካታና ውጤቶች ላይ ሪፖርት ለማቅረብና፣ ውጤቶቹን ተመረኩዞ የተግባር ማሻሻያና መመሪያ ለመስጠት ያገለግላል፡፡፡ ከበርካታ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግምገማ ገጽታዎች ባሻገር የግምገማ ተሞክሮዎችን ለማሻሻል እንደዚሁ ስትራቴጂዎችን ግልጽ ያደርጋል፡፡ የሚያጠቃልለው የቀበሌ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የግምገማ አቅም የማሳደግ ጠቀሜታንና በጎ ተፅዕኖን መቀመርና፣ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራሞች አገልግሎቶችና ውጤታማ ልማት በማሻሻል ረገድ ውጤትን ለማስፋትና ለማሰራጨት  አፅንኦት በመስጠት ነው፡፡

## 10.1 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል አስፈላጊነት

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል ማድረግ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራሞቹ የሚተገበሩት ከዓላማና ግቦች አኳያ መሆኑን ለማረጋገጥ ያግዛል፡፡ ይህም ትክክለኛውን ሥራ እየሠራን ስለመሆኑ፣ በትክክል እየሠራን ስለመሆኑ፣ እንዴት እየተሰራ ስለመሆኑ እና መቼና ምን መሰራት እንዳለበት የሚሉ ጥያቄዎችን ይመልሳል፡፡ የመስኖ ልማት ሠራተኞች፣ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተቆጣጣሪ አካላት፣ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የስራ ክፍሎች መረጃን መሠረት በማድረግ በግብዓትና እንቅስቃሴዎች የድጋፍ ጣልቃ ገብነት ዙሪያ ወቅታዊ መረጃዎችን በማሰባሰብ የመጣውን ለውጥ ወይም የተመዘገበውን እድገት በዘላቂነት ለማስቀጠል ክትትልን ይጠቀማሉ፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች በአጠቃላይ የሀብትና የሂደት ጥርጊያ መንገድን ያመቻቻሉ፡፡ ለምሳሌ፡- የስብሰባዎች፣ ሠርቶ ማሳያዎች፣ የመስክ ቀናት፣ ጉብኝታዊ የልምድ ልውውጥ ወ.ዘ.ተ መኖራቸውን ለማረጋገጥ ይጠቅማል፡፡



የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት፣ የኤክስቴንሽን ቡድን/ዩኒት/፣ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የባለሙያዎች ቡድን እና ሱፐርቫይዘሮች የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትልና ግምገማ ያካሂዳሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ እነዚህ ቡድኖች/ዩኒቶች የሴቶችና ወንዶች ተሳታፊ ቁጥርን፣ የተከናወኑ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን እንቅስቃሴዎች ዓይነትን፣ የመስኖ ሰብል አመራረትን፣ የሰብል እርሻ የጊዜ ሰሌዳን (ካላንደር)፣ የመስኖ ግብዓት ፍላጎትን፣ የግብዓት ክፍፍልን፣ ሊለማ የሚችል የመስኖ መሬት መጠንን፣ የለማ የመስኖ መሬት መጠንን፣ የገበያ መረጃን፣ በሂደት ላይ ያሉ እና እየመጡ ያሉ የአርሶ/አርብቶ አደሮች የመስኖ ስልጠና ፍላጎቶችን ያካተተ በርካታ አጠቃላይ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ላይ ወቅታዊ መረጃ ያሰባስባሉ፡፡ ይሁንና ለተለያዩ የፕሮግራም መሻሻልና ለሠራተኞች አስተዳደር ዓላማ ለአርሶ/አርብቶ አደር ትክክለኛ የሆነ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ሙሉ የሆነ የክትትል መረጃ ሊኖራቸው አይችልም፡፡

የፕሮግራም አፈጻጸም ግምገማና የተጽዕኖ ግምገማ የተገናኙ ቢሆኑም የተለያዩ ዘዴዎችንና የጥንካሬ ደረጃዎች አሏቸው፡፡ የክትትል አግባብነት ያላቸው መግለጫዎችን ለመስጠት በዚህም ውጤትን ለመገምገም በፕሮግራሙ መስመር ወይም አቅጣጫ ለእድገት አመላካቾች ጥርጊያ መንገድ ይከፍታል፡፡ ለስኬታማና ውጤታማ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል እና ግምገማ ለማድረግ 10 መሠረታዊ መርሆዎችን መከተል ይኖርብናል፡፡ እነርሱም፡-

- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል ቀላል መሆን አለበት፡- የተዘበራረቀና ውስብስብ የሆነ የክትትል ሲስተም በራሱ ውጤት አልባ ነው፡፡

- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል ወቅታዊ (በወቅቱ/በጊዜው) መሆን አለበት፡ - ትክክለኛውን ሰዓት መጠቀም ዋነኛው ጉዳይ ሲሆን በዚህም የስኬትን እድል ለመጨመር በመስኖ ኤክስቴንሽን ተገቢ ለውጥ በፍጥነት ማምጣት ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- የሠርቶ ማሳያ ቦታ መረጣ፣ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት፣ ሠርቶ ማሳያ፣ የመስክ ቀን ወዘተ ወቅታዊነትን ይጠይቃሉ

- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል አግባብነት ያለው መሆን አለበት፡- ክትትል ከተቀመጡ ግቦች ጋር የተመጣጠነ፣ ጠቃሚ መረጃዎችን የሚያፈልቅ መሆን አለበት፡፡

- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል መረጃ ታማኝ እና በመረጃ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡- ተቆጣጣሪዎች፣ ተመራማሪዎች፣ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በክትትል ግኝቶች ላይ የሚመረኮዙት መረጃዎች በታማኝነትና ምክንያታዊ ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በሠርቶ ማሳያ ቦታዎች መረጃ ማሰባሰብ፣ ጠቃሚ የሆነ የቴክኖሎጂ ግብረ መልስ፣ ተሞክሮዎችን ወደ ሌላ ማስተዋወቅ ወዘተ የሚቻላው የሚሰበሰበው መረጃ ታማኝ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል ጥረቶች አሳታፊ መሆን አለባቸው፡- ይህ የሚያጠቃልለው በመስኖ ኤክስቴንሽን ሥራዎች የሚመለከታቸው አጋር አካላት ያካተተ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ለምሳሌ፡-አርሶ/አርብቶ አደሮች ሴቶችና ወጣቶች፣ የመስኖ

ልማት ሰራተኞች ፣ባለሙያዎች ወ.ዘ.ተ.

- ☞ የመስኖ ኤክቴንሽን ክትትል ሁኔታዎችን ያገናዘበ መሆን አለበት፡- ይህ በተፈጥሮ ተደጋጋሚ የሆነና ጊዜውን ሙሉ በመደበኛነት የሚቀጥል ነው፡፡

- ☞ የመስኖ ኤክቴንሽን ክትትል የድርጊት መርህን የተከተለ መሆን አለበት፡- ይህ የተግባራዊ እውነታ አቀራረብ ዘዴን ከምንም በላይ ለመስኖ ኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች መስፈርቶችን ግምት ውስጥ ያስገባ አሠራርን መከተል አለበት፡፡

- ☞ የመስኖ ኤክቴንሽን ክትትል ፖሊሲ/ውሳኔ ሰጪዎችን መርህ የተከተለ መሆን አለበት፡- የክትትል ቡድን የክትትል አሰራርን ለመንደፍና ሥራ ላይ ለማዋል የፖሊሲ ውሳኔ ሰጪዎች መስፈርቶችን መጠበቅ አለበት፡፡

- ☞ የመስኖ ኤክቴንሽን ክትትል ቡድን የተለዩ ድርጊቶችን ያመለክታል ፡- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል በመረጃ ማሰባሰብና ትንተና ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን ችግሮችን የሚመረምር እና ተግባራዊ አማራጭ መፍትሄዎች ላይም ሀሳብ ያቀርባል፡፡ ለምሳሌ፡- በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ደረጃ፣ የአውታር ዲዛይን፣ የግብዓት አቅርቦት፣ ግብይት ወ.ዘ.ተ… --

## 10.2. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግምገማ አስፈላጊነት

ግምገማ ማለት አዲስ ጽንሰ ሀሳብ ሳይሆን መደበኛ በሆነ ባልሆነ መልኩ ሁላችንም እያካሄድነው ያለ ተግባር ነው፡፡ ግምገማ የተወሰኑ ተቀባይነት ያላቸው መለኪያዎች የተገኙና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው ጥያቄዎችን ለመመለስ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ሥራዎችን ወይም ውጤቶችን እንዲሁም የፕሮግራምና ፕሮጀክት ውጤታማ ተጽዕኖዎችን በአሰራር የምንዳስስበት ሂደት ነው፡፡ ይህ የሚያመለክተው የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ግልፅ፣ ሊለኩ የሚችሉ ግቦች መኖር ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡

አስቀድመው በታወቁ ወይም በተወሰኑ ግቦች ላይ በመመስረትም ሆነ ያልታሰቡ ቅጽበታዊ አፍታዎች ላይ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድና ለማሻሻል የግምገማ ውጤቶች ጠቃሚ ናቸው፡፡ መደበኛ የሆኑ ወይም ያልሆኑና ግምገማዎች ቀጣይነት ያላቸው ሁለት ጫፎች ያሏቸውን ሀላፊነት ሊያስተዋውቁ ይችላሉ፡፡ በአንደኛው ጫፍ መደበኛ ያልሆኑ ግምገማዎች ውሳኔ ለመስጠት በአሰራር ያልተመሩ፣ በመስፈርትና በማስረጃ ላይ ያልተመሠረቱ በመሆናቸው ግልጽ ያልሆኑና ብዙ ጊዜ ግለሰባዊ ውሳኔዎች ናቸው፡፡ እነዚህም አድልኦ እና አሳሳች ወይም ወደ የተሳሳተ መንገድ የሚመሩ ናቸው፡፡ በሁለተኛው ጫፍ መደበኛ ግምገማዎች ሲሆኑ በአሰራር የሚመሩ፣ ስለ ፕሮግራሙ ተገቢነት፣ ውጤታማነት፣ ቅልጥፍና ወይም ተጽዕኖዎች ውሳኔ ለመስጠት ግልጽ የሆኑ መስፈርቶችንና ማስረጃዎችን የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ስትራቴጂዎችን ለማቀድ ለመከለስና ግኝቶችን የሚያፀድቀው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሩ እና ውሳኔ ሰጪ አካል ነው፡፡

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግምገማ የድጋፍ ተሳትፎ ውጤታማነት ማለትም

የኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ፣ የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ስልጠና፣ የቴክኖሎጂ ፓኬጅ፣ ትምህርታዊ ጉብኝቶች፣ ፕሮጀክቶች ወይም ግቡን ለማሳካት ያለው ፖሊሲ ላይ ያተኩራል፡፡ ለአርሶ/አርብቶ አደሩ የሚወጣውን ወጪን እና የመስኖ ልማት አገልግሎት መስጠትን፣ ወ.ዘ.ተ. አካቶ የሀብት ውጤታማነት ገቢ ወጪ ትንተና የድጋፍ ጣልቃገብነት በሚኖርበት ጊዜ፤

ፕሮግራሞች፣ የፖሊሲዎችና ተሞክሮዎች ለተለያዩ የታለመላቸው ቡድኖች (ለምሳሌ፡ ☞ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት ወይም አባል የሆኑና ያልሆኑ ወ.ዘ.ተ. የበለጠ ውጤታማ ይሆናሉ፡፡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግምገማ እንደዚሁ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች የአገልግሎቱን ጥራት ምን ያህል እንደተገነዘቡ ወይም አዳዲስ መረጃ ወይም ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ ያላቸውን እውቅና ይለካል፡፡ ስለሆነም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግምገማ ሁለቱንም ማለትም ጥበባዊና ሳይንሳዊ ነው፡፡ ጥበባዊ ግምገማ በፕሮግራም ወይም በፖሊሲ የድጋፍ ተሳትፎ ላይ ዓላማንና ተመልካች ወይም አድማጭ ልየታን፣ ተገቢ ዕቅድን፣ መረጃ ማብራራትን ያካትታል፡፡ ሳይንሳዊ ግምገማ ስለውጤትና ተጽዕኖ በአሰራር መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ይተነትናል፡፡

## 10.3. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግምገማ ተግዳሮቶች

ለኤክስቴንሽን አገልግሎት በማሳ ደረጃ የተለዩ ተጽዕኖዎችን ለመለካት/ለመለየት ከባድና ውስብስብ ነው፡፡ ምክንያቱም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አፈጻጸምን የበርካታ ጉዳዮች ውህድና ተሳትፎ ስለሚኖርበት ነው፡፡ ለምሳሌ የመስኖ መሬት ይዞታ ስርዓት መተግበርና መልሶ ማከፋፈል፣ የመስኖ ግብዓት አቅርቦት በወቅቱ መገኘት ዋጋ ወይም መጠንና ጥራት፣ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ጥንካሬና አገልግሎት አሰጣጥ፣ የአርሶ አደሮች የግንዛቤ ደረጃ፣ የገበያ መሠረተ ልማቶች፣ የመስኖ ልማት ሠራተኞች እና የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ተነሳሽነት ወዘተ ናቸው፡፡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የድጋፍ ተሳትፎ ግምገማ ለውጥ ለማምጣት በታለመ እንቅስቃሴ (ለምሳሌ፡ - የጓሮ አትክልት ልማት ሠርቶ ማሳያ እና በሚፈለገው ውጤት ማለትም እያደገ የመጣ የጓሮ አትክልትን መመገብ በቤተሰብ አባላት ላይ ያመጣው የተመጣጠነ ምግብ መሻሻል) መካከል ያለውን የምክንያትና ውጤት ግንኙነትን መለየት መቻል አለበት፡ ፡ ይህን የምክንያትና ውጤት ግንኙነት መረዳቱ የተጽዕኖ መረጃን ለመተንተን ጥሩ የግምገማ ዕቅድና የስታትስቲክ እውቀትን ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ የመማሪያ ሂደት ሆኖ እንዲያገለግል የኤክስቴንሽን ግምገማ ሊዋቀር ይገባል፡፡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግምገማ በኤክስቴንሽን የድጋፍ ተሳትፎ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና የአቀራረብ ዘዴ ደረጃ ላይ እውነተኛውን ውሳኔ አሰጣጥ ለማሳወቅ የሚታመን ማስረጃ ለመስጠት ብቻ የሚጠቅም ነው፡፡ የምክንያትና ውጤት ግንኙነት የሙከራ ወይም ሙከራ ነክ የምርምር ዕቅድ ምናልባት የሚፈልግ ሲሆን በዚህም የሙከራ መደቦች የተለዩ አያያዞችን ይቀበላሉ፤ በሌላ በኩል የማወዳደሪያው መደብ የተሻለ አያያዝ ያልተደረገላቸውን ይቀበላል፡፡ የማወዳደሪያ መደብ ጥቅሙ ገምጋሚው ለአያያዝ ውጤት ብዙ አማራጭ መግለጫዎችን እንዳይቀበል ያስችለዋል፡፡ ስለዚህ በሳይንሳዊ ምርምሮች ማወዳደር አስፈላጊ ነው፡፡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽንን በሚመለከት የመስኖ አገልግሎትን የሚቀበሉ አርሶ አደሮችና እኩል ቁጥር ባለው ቡድን የኤክስቴንሽን አገልግሎትን የማይቀበሉ አርሶ/አርብቶ አደሮች ጋር ማወዳደር በደንብ የተደገፈ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ነው፡፡

ይሁንና የመጣው ለውጥ በእውነትም በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የድጋፍ ተሳትፎ አማካኝነት ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ይህን የግምገማ ጥናት ከመምራት አኳያ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና ፖሊሲ አውጭዎች መሠረታዊውን የምርምር ዲዛይኖችን፣ ጥልቅ መረጃዎችን ማሰባሰብ እና ስታትስቲካዊ ፍተሻዎችን መረዳት አለባቸው፡፡ ሆኖም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግምገማ ውጤቶች ለድጋፍ ተሳትፎ መሻሻል የሚጠቅም ስለመሆኑ በማይለወጥ አኳኋን አያረጋግጡም፡፡ በዚህም ፖሊሲ አውጭዎች ከአማካሪዎች፣ ከሥራ ጓደኞች፣ ከአርሶ/አርብቶ አደር ድርጅቶች፣ ፍላጎት ካላቸው ቡድኖች ወይም ከመገናኛ ብዙሀን በመረጃ ማመሳከሪያ ስለ መስኖ ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የግምገማ ውጤት ጥቅም ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ በርካታ ምክንያቶችን ሊመለከቱ ይችላሉ፡፡

## 10.4. የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለውጥን መለካት

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎቶችና ፕሮግራሞች ገምጋሚዎች የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችና አግባቦችን፣ በተግባር ላይ የማዋል ርዝመት፣ የግምገማ ዓላማ፣ አቅርቦት ውስንነቶች ላይ በመመስረት ልዩ ልዩ ቅንጅታዊ እና ድርጅታዊ የአቀራረብ ዘዴዎች መምረጥ ይችላሉ፡፡ ከፕሮግራም ቀድሞና በኋላ ግምገማ ፕሮግራሙ በተሳታፊዎች ዘንድ የነበረውን ማንኛውንም በጎ ተፅኖ/ፋይዳ ወይም ጉዳት መግለጽ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ከፕሮግራም ቀድሞ ወይም በኋላ ዳሰሳ ጥናት ሁለቱ ወካይ የግምገማ ጥያቄዎችን በመጠቀ፤- የሥልጠና ተሳታፊ ሆነው በመስኖ የሚያለሙ አርሶ/አርብቶ አደሮች ካልተሳተፉት ይልቅ የተሟላ የመስኖ ፓኬጆችን ተቀብለው ሥራ ላይ አውለዋልን? በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሥልጠና ተሳታፊ የሆኑ አርሶ/አርሶ አደሮች ካልተሳተፉት ይልቅ ከፍተኛ የተጣራ ገቢ አግኝተዋልን? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችል ሆናል፡፡

### 10.4.1 የኤክስቴንሽን አፈጻጸም አመላካቾች

የስኬት ደረጃን ለመወሰን ግቦች አመላካቾችን በመጠቀም መለካት ይኖርባቸዋል፡፡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል ማለት የእነዚህ አመላካቾች የምዝገባ ሂደት ሲሆን ግምገማ ማለት የተመዘገቡትን አመላካቾች መተንተንና ወደፊት አፈጻጸምን እንዴት መሻሻል እንደሚቻል መወሰን ነው፡፡ የክትትልና ግምገማ መሣሪያዎችን መጠቀም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራሞች ሥራ ላይ መዋል ዕቅድን የተከተለ እና የአርሶ/አርብቶ አደሮችን ፍላጎት ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡ ውጤታማ ክትትልና ግምገማ በሰዓቱ መወሰንና መተግበር እንዲችሉ ትክክለኛው መረጃ በትክክለኛው ሰዓትና በትክክለኛው ይዞታና አቀራረብ (format) ለትክክለኛው ሰው ከደረሰ ተገቢና ትክክለኛ መረጃ ይሰጣል፡፡

የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አፈጻጸም አመላካቾች በመስኖ ኤክስቴንሽን እንቅስቃሴ ሥራ ላይ የመዋል ሂደት ላይ ክትትል የተደረገባቸው የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፋይዳ/በጎ ተጽዕኖዎችን፣ ውጤቶችን፣ ምርቶችን፣ እና ግብዓቶችን ይለካሉ፡፡ በመጨረሻ አመላካቾች የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፋይዳ/በጎ ተጽዕኖ ስኬትን ለመገምገም ይጠቅማሉ፡፡ የተደራጀ

መረጃ የታለሙ ግቦች ስኬትንና የሚገመቱ ችግሮችን ለመለየት በመስኖ ኤክስቴንሽን የድጋፍ ጣልቃገብነት ፋይዳ/በጎ ተጽዕኖዎች፣ ውጤቶች፣ ምርቶችና ግብዓቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ግልጽ ያደርጋል፡፡ ልዩ ልዩ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትልና ግምገማ አመላካቾች አሉ፡፡ ይሁንና ከዚህ በታች የተመለከቱት የበለጠ የጋራ የሆኑ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትልና ግምገማ አመላካቾች ናቸው፡፡

## 10.4.2 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፋይዳ ግምገማና አመላካቾች

- አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና እና አሰራሮችን ማላመድ:- እነዚህ የመስኖ ኤክሰቴንሽን አመላካቾች የሚያሳዩት አርሶ/አርብቶ አደሩ ምርትና ምርታማነትን በማንኛውም መልኩ ለማሻሻል እንዲማር፣ ግንዘቤ እንዲኖረውና በአዲስ መንገድ ሥራ ላይ እንዲያውል የእውቀት፣ ክህሎት እና የለውጥ መሻሻልን ያሳያል፡፡ ለምሳሌ:- የምርት መጠንንና ጥራትን ማሻሻል፣ ከምርት በኋላ ወ.ዘ.ተ…

- ወጪን መቀነስ:-ይህ አመላካች የሚለካው የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ቴክኖሎጂ ሥራ ላይ በመዋሉ ምክንያት በተሳታፊዎች ወይም የመስኖ ተጠቃሚዎች ዘንድ የተቆጠበ ገንዘብን ነው፡፡ ወጪ ሲባል ጊዜን፣ ጉልበትን እና ሌሎችም የሀብት ዓይነቶች ሊሆን ይችላል፡፡

- ቁጠባ:- ከወጪ ቅነሳ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ይህ አመላካች መጠነ ቁጠባን ወይም ከመስኖ ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በመማር የመስኖ ልማትና ሌሎች ተሞክሮዎች በሥራ ላይ በማዋል ረገድ የጨመረ ቁጠባን ይለያል፡፡

- ገቢን መጨመር:- ይህ አመላካች በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የድጋፍ ጣልቃ ገብነት ምክንያት ተጠቃሚዎች ወይም ተሳታፊዎች (በግለሰብ ወይም በቤተሰብ ደረጃ) ከፕሮግራሙ በፊትና በኋላ ያገኙትን ገቢ ያወዳድራል፡፡ ለምሳሌ:-የተሟላ ፓኬጅን ሥራ ላይ በማዋሉ ምናልባት የአርሶ አደሩ ገቢ ጨምሮ ሊሆን ይችላል፤ ማለትም በሄክታር ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ ቲማቲም፣ ድንች ወይም ሌላ ዓይነት የምርጥ ዘር መጠቀም፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያን ሥራ ላይ ማዋልና እሴት የመጨመር ተሞክሮ ወ.ዘ.ተ በመስኖ ኤክስቴንሽን መረጃ ወይም ስልጠና በማግኘት ምክንያት ሊሆን ይቸላል፡፡

- ምርታማነትን መጨመር :- ይህ አመላካች ከመስኖ ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ወይም ከሠርቶ ማሳያ በመማር ተመሳሳይ በሆነ የማሳ መጠን ወይም የማምረቻ መሣሪያዎች አዲስ ተሞክሮን ሥራ ላይ በማዋል የጨመረውን ምርታማነት በኮምፒዩተር በመታገዝ ምጣኔ ብታዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ እሴትን መለካት ነው፡፡ ለምሳሌ:- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አርሶ/አርብቶ አደሮች አዲስ ቴክኖሎጂን እንዴት እንደሚጠቀሙ ያስተምራል፡፡ አዲስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የተገኘ ትርፍ ሲቀነስ ቴክኖሎጂ የተገዛበት ዋጋ ከምርታማነት መጨመር ጋር እኩል ይሆናል፡፡

- **እሴትን መጨመር:-** ይህ አመላካች የሚያሳየው በመስኖ ሰብል ምርት ሂደት ከወጣው ወጪ ባሻገር የተገኘ ተጨማሪ ትርፍን ወይም እሴትን ነው፡፡ ለምሳሌ:- የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የአትክልትና ፍራፍሬ አምራች አርሶ አደሮችን ምርጥ ዘር እንዲጠቀሙ ማስተማር በጥራት አምርተው እሴት እንዲጨምሩ ያስችላቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የተመረተውን ምርት ተመራጭና የመሻጫ ዋጋምው ከፍ እንዲል በማድርግ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ገቢ ከመጨመር አኳያ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

- **የካፒታል ዋጋ አማራጭ መልካም አጋጣሚዎች:-** የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራሞች ያለውን ካፒታል (መሬት፣ጉልበት እና ውሃ) በተለያዩ ወይም የበለጠ ቀልጣፋ መንገድን በመጠቀም ተጠቃሚዎች እንዴት ማስተካከል ብዙ ገንዘብ እንደሚያገኙ ማስተማር ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ:- መሬት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ሰብሎች ማምረት ያስችላል፡፡ ከፍተኛ ዋጋ ካላቸው ሰብሎች የሚገኘውን ገቢ ዝቅተኛ ዋጋ ካላቸው ሰብሎች ጋር በማወዳደር የኤክስቴንሽን ፕሮግራም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን በመገመት አርሶ/አርብቶ አደሩ እንዲገነዘበውና እንዲደግፋቸው በማድረግ ወደ አዲሶቹ ከፍተኛ ዋጋ ወደሚሰጡ ሰብሎች እንዲቀየር ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ምናልባትም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙ የገበያ መረጃን ይሰጣል፣ የአዋጪነት ስሌት ላይ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ያግዛል፡፡

- **የመክፈል አቅምና ፈቃደኝነት:-** አርሶ/አርብቶ አደሮች አዲስ ቴክኖሎጂና አሰራርን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን፣ እውቀትና ክህሎትን ተቀብሎ ሥራ ላይ ማዋልን እና ምጣኔ ሃብታዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ እሴትን ከመረዳት የሚመጣ ነው፡፡ የተወሰነ እቃ (ቁሳቁስ) ወይም አገልግሎት ምናልባት ምጣኔ ሃብታዊ/ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንደሚኖራቸው የሚታሰበው ለምርቱ ወይም አገልግሎቱን ከመግዛት ፍላጎታቸው በፊት ሲታሰብ ከነበረው የተለመደው ደንብ በልጦ ሲገኝ ነው፡፡ የመስኖ ምርት በገበያ ላይ የበለጠ ውጤታማ ሆኖ የሚሸጥ ከሆነ በመስኖ ኤክስቴንሽን ስልጠና ወይም ድጋፍ አማካኝነት እሴት የተጨመረበት ምርት ወይም አዲስ ገቢ እና ትርፋማነት ደረጃ ላይ ደረሰ ማለት ሲሆን ለመክፈል ያላቸው ፍላጎት የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎቱ ዋጋ እንደሆነ ሊታሰብ ይችላል፡፡ በአጭሩ አንድ አርሶ/አረብቶ አደር የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ስልጠናና ምክር አግኝቶ የአንድን ቴክኖሎጂ አገልግሎት ተረድቶ ፍላጎት አሳደረ ወይም ለመክፈል ፍቃደኛ ሆነ ማለት የመክፈል አቅሙ ተረጋገጠ ማለት አይደለም፡፡ የመግዛት አቅም ማለት ክፍያን ፈፅሞ መውሰድ ወይም የራስ ማድረግ ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን እንቅስቃሴዎች ክትትል የሚካሄደው በተግባር ሂደት ላይ ሲሆን ግምገማ ደግሞ ብዙውን ጊዜ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ነው፡፡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል መጀመሪያ የሚመጣ ነው፡፡ ምክንያቱም መረጃ ሳይሰበሰብ ተገቢ የሆነ ግምገማ ሊካሄድ አይችልም፡፡ ይሁንና የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል ሙሉ ጥቅም ሊሰጥ የሚችለው የተሰበሰበው መረጃ ትምህርት እንዲሰጥ ሲቃኝ ወይም ሲከለስ ብቻ ነው፡፡ ይህ ግምገማ መሆኑ ነው፡፡ ለመስኖ ኤክስቴንሽን ዕቅድ መረጃ ከሁለቱም ማለትም ከግምገማና ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች የመረጃ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የሚመጣ ሲሆን ከእነዚህ አንደኛው

የመረጃ ምንጭ ከሌለ ወደ ዕቅድ ጥራት ደረጃ ውስንነት ይወስደናል፡፡ በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ ሂደት የወረዳዎችን አፈጻጸም ለማሻሻል ያግዙ ዘንድ ክትትልና ግምገማ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ የመስኖ እንቅስቃሴዎች የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትልና ግምገማ በመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እንዲካሄዱ የሚፈለጉ የውስጥ ግምገማ ሂደቶች ናቸው፡፡ ውጤታማ ተሳትፎአዊ የመስኖ ኤክስቴንሽንን ለማረጋገጥ ጠቃሚ የሆኑ ሁለት ዓይነት ክትትልና ግምገማዎች አሉ፡፡ እነርሱም፡ - የሂደት እና የውጤት ዳሰሳ/ግመታ/ በመባል ይታወቃሉ፡፡

## 10.4.3 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሂደት ዳሰሳ

የሂደት ዳሰሳ ግመታ ብዙውን ጊዜ የሚካሄደው በተሳትፎአዊ መስኖ ልማት አመራር ቅድመ ልየታ ደረጃ ሂደት ላይ ሲሆን ይህም በመስኖ አውታር በተግባር ላይ መዋል/ አተገባበር/ እና የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን እንቅስቃሴዎችና ቴክኖሎጂን ተቀብሎ ሥራ ላይ ስለማዋል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ በአጠቃላይ ሂደቱ በተፈጥሮ ወሳኝነት ያለው ሲሆን ግን የጋራ መሆንም ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- በሥራ ዕቅድ ሂደት ላይ በቴክኖሎጂ መቀበልና ሥራ ላይ ማዋል የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎችና የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ስለ እውነተኛው የአፈጻጸም ስኬት ማወቅ ሲፈልጉ ለማለት ነው፡፡ ይህ የሂደት ዳሰሳ ክትትልና ግምገማ የሚከናወነው የአሰራር ወይም ቴክኒክ ኦዲት በማካሄድ ነው፡፡ እነዚህም፡-

- ☞ የመስኖ አውታር ልየታ ዳሰሳ እና የምክረ ሀሳብ ሰነድ፤
- ☞ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች መረጃ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት፤
- ☞ ዓመታዊ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ዕቅድ፤
- ☞ ሠርቶ ማሳያዎች እና የውሃ ተጠቃሚ ስልጠና መዝገብ፤
- ☞ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል ሠልጣኞች ምዝገባ እና የተመራቂዎች ሰነድ፤
- ☞ ወርሀዊ የሥራ መርሀ ግብር እና የመስኖ ልማት ሠራተኞች የኤክስቴንሽን የዕለት መመዝገቢያ ማስታዎሻ ደብተር፤
- ☞ የክትትል እና ድጋፍ ሪፖርቶች ናቸዉ፡፡
- ☞ የሂደት ጥንካሬ፡- የሚከተሉት በክትትልና ግምገማ ሂደት ጥንካሬዎች ላይ ጥቂት ነጥቦች ናቸው፡፡
- ☞ ወደ ሚፈለጉና የማይፈለጉ ውጤቶች በሚያመራ ሂደት ላይ የተገኘ እውቀትን መሰረት በማደረግ ወደ ፊት የመስኖ ሰብል አመራረት ቴክኖሎጂን ተቀብሎ ሥራ ላይ በማዋል ላይ አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- ☞ ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትና ተገቢነት ላላቸው አጋር አካላት በአውታር ደረጃ ምን እየተከናወነ እንዳለ ማብራራትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ዕቅድን መከለስአስፈላጊ ነዉ፡፡
- ☞ የሂደት ክትትል በጋራ ከተከናወነ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዋና

ዓላማዎች፣ ግቦች እና ዓላማዎችን በቀላሉ ለመረዳትና ማጠናከር ይችላል፡፡

☞ የቴክኒክ እና አሰራር ኦዲት፦ የቴክኒክ/አሰራር ኦዲት ዓላማ በአነስተኛ እና ዝቅተኛ መስኖ አውታሮች የሚከናወኑ ሁሉም የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን እንቅስቃሴዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ለመከታተል ይረዳል፡፡ በዚህ ረገድ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና የመስኖ ልማት ሠራተኞች በየ 15 ቀኑ የቴክኒክ እና አሰራር ኦዲት ያደርጋሉ፡፡

☞ የመስኖ እንቅስቃሴዎች እንዴት እንደታቀዱ፤

☞ እንዴት በተግባር ላይ እንደዋሉና እንደተተገበሩ፤

☞ የመስኖ ልማት ሰራተኞች፣ ተመራማሪዎች፣ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትልን እንደ መስኖ ባህሪዎችን ማሻሻል፡፡

## የቴክኒክ/አሰራር ኦዲት 2 ዋና ዓላማዎች አሉት፦

☞ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን የአቀራረብ ዘዴ ሂደትን በሚመለከት በውሃ ተጠቃሚዎች፣ አርሶ/አርብቶ አደር ተኮር ቡድን ወይም የመስኖ ልማት ሠራተኞች መካከል ማንኛውንም አለመረዳቶችና አለመግባባቶች እና እርግጠኛ ያልሆኑ ጉዳዩችን መለየት

☞ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እና የመስኖ ልማት ሠራተኞች የተመደቡበትን ሀላፊነት እየተወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡

የቴክኒክ እና አሰራር ኦዲት የመስክ ማስታወሻ ዝርዝር (ቼክሊስት) የአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ አውታሮች ተግባር ላይ መዋል የጥራት አሻራን ለማግኘት ሲባል የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችንና የመስኖ ልማት ሠራተኞችን ለማገዝ የተነደፈ ነው፡፡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ባለሙያ ወይም የመስኖ ልማት ሰራተኛ በተለያዩ የመስኖ አውታር በተግባር ላይ መዋል ትክክለኛና አጠቃላይ ስዕል ለማግኘት ማንኛውንም ሌላ ምርመራ ለመጨመር ነጻ ናቸው፡፡ የሚከተለው በየ15 ቀኑ እንዲካሄድ የሚፈለግ

የቴክኒክ እና አሰራር ኦዲት ማጠቃለያ ነው፡፡

## ሠንጠረዥ- 12፡-የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ክትትል

| አመላካች | የአመላካች ማረጋገጫ | ለወደፊት መሻሻል የቀረቡ አስተያየቶችና ሀሳቦች |
|---|---|---|
| የመስኖ አውታሩ የግብርና ልማት ዕቅድ አለው? | የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን እንቅስቃሴዎች ወርሃዊ የሥራ ዕቅድን መሠረት ያደረጉ ናቸው? | |
| | ይህ ከታለሙ የውሃ ተጠቃሚዎች፣ የጥቃቅን መስኖ እና የማህበረሰብ ኩሬ አባወራ/እማወራ ቤተሰቦች ፍላጎት ጋር የተስማማ ነው? | |
| | የአነስተኛ መስኖ፣ የማህበረሰብ ኩሬ እና በቤተሰብ ደረጃ የጥቃቅን መስኖ ማሳ ከመነሻ የአከባቢ ተስማሚነት ዳሰሳ/ኢ.አይ.ኤ (EIA) ጋር የተስማማ ነው? | |
| | የመስኖ እንቅስቃሴዎች ሥርዓተ ጾታን ያካተተ እና ያማከለ ነው ወይ? | |
| | የግብርና ልማት ዕቅድ የወርሀዊ ስብሰባዎች ቃለ ጉባኤ ግልባጭ/ኮፒ አለው? | |
| ለውሃ ተጠቃሚዎችና የቤተሰብ ጥቃቅን መስኖ እና የማህበረሰብ ኩሬ ተጠቃሚዎች የስልጠና ሁኔታዎች | በአነስተኛ መስኖ፣ የተሟላ ፓኬጅ፣ የመስኖ እሴት ሰንሰለት ላይ ምን ያህል የስልጠና ጊዜ ታቅደው ተጠናቀቁ? | |
| | በመስኖ አውታሮች (ሰብሎች፣ የመስኖ አመራርት) ምን ያህል የስልጠና ታቅደው ተጠናቀቁ? | |
| | ከምርት በኂላ ምን ያህል የስልጠናዎች ታቅደው ተጠናቀቁ? | |
| | በአሠራርና ጥገና ምን ያህል የስልጠና ታቅደው ተጠናቀቀ? | |
| የሰለጠኑ አርሶ/ አርብቶ አደሮች | የተመዘገቡ ወንድና ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁጥር | |
| | 90% በሆኑ የስልጠና ጊዜያቶች የስልጠና ሞጁሎችን ያጠናቀቁ ወንድና ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁጥር | |
| | ከ70 - 80% በሆኑ የስልጠና ጊዜያቶች የስልጠና ሞጁሎችን ያጠናቀቁ ወንድና ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁጥር | |
| | ከ70 % በታች በሆኑ የተሟላ ፓኬጅ ስልጠና ያጠናቀቁ ወንድና ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁጥር | |
| | ወንድና ሴት ያጠናቀቁና የተመረቁ አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁጥር | |

| | | |
|---|---|---|
| የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ሥራዎች በተግባር ላይ መዋል | በአነስተኛ መስኖ/በቤተሰብ ደረጃ ጥቃቅን መስኖ እና በማህበረሰብ ኩሬ መስኖ ማሳዎች ምን ዓይነት ችግሮች አጋጠሙ? እና በመስኖ ልማት ሠራተኞች በኩል ምን ዓይነት መፍትሄዎች ተሰጡ? | |
| | በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል ምን ዓይነት ችግሮች አጋጠሙ? እና በመስኖ ልማት ሠራተኞች በኩል ምን ዓይነት መፍትሄዎች ተሰጡ? | |
| | በግብዓት ስርጭትና በግብይት ሂደት ምን ዓይነት ችግሮች አጋጠሙ? እና በመስኖ ልማት ሠራተኞች በኩል ምን ዓይነት መፍትሄዎች ተሰጡ? | |
| | በችግሮች ላይ በመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ኮሚቴ እና አባልት ባልሆኑት ምን ዓይነት የግል አስተያየቶች ቀረቡ? | |
| | በአነስተኛ መስኖ፣ በማህበረሰብ ኩሬ እና በቤተሰብ ደረጃ በጥቃቅን መስኖ ማሳዎች የአርሶ/አርብቶ አደሮች እና አጋር አካላት የአርሶ/አርብቶ አደሮች የመስክ ቀን ወይም ጉብኝት የተዘጋጀ ቁጥር እና የተሳተፉ ወንድና ሴት ጠቅላላ ድምር አመላካች | |
| ግንዛቤ | የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ግንዛቤ አገልግሎት ያገኙ ወንድና ሴት አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁጥር | |
| ጉብኝት | በሳምንት/በወር በመስኖ ልማት ሠራተኞች/ባለሙያዎች የተጎበኙ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ቁጥር | |
| የአርሶ አደሮች ስልጠና | በመስኖ ርዕሶች የሰለጠኑ ወንድና ሴት አርሶ አደሮች ቁጥር፦ ለምሳሌ የተሟላ ፓኬጅ | |
| የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ኮሚቴ | ከመስኖ ልማት ሠራተኞች፣ ተጠቃሚዎች፣ ባለሙያዎች ወ.ዘ.ተ. የተካሄዱ ስብሰባዎች ቁጥር የተላለፉ ውሳኔዎች ዓይነትና ብዛት | |
| የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል መደበኛ ስልጠና | በሳምንት/ወር የስልጠና ቀናት ብዛትና መደበኛነቱ | |
| ሠርቶ ማሳያ | በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል፣ በማሳ ላይ፣ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ የተካሄደ ሠርቶ ማሳያ ቁጥር | |
| የመስክ ቀን | በአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ የተዘጋጀ የአርሶ/አርብቶ አደር የመስክ ቀን ቁጥር | |
| ቁጥጥሮች/ሥራን ያካተተ ድጋፍ | በአማካይ በሳምንት/በወር በልማት ሠራተኞች/በሥራ ፈጠራ ድጋፍ ላይ የተደረገ ቁጥጥር ብዛት | |
| ምርምር፣ ኤክስቴንሽን፣ አርሶ/ አርብቶ አደሮች ግንኙነት | በሩብ ዓመት/በዓመት/ የተዘጋጀ የምርምር፣ ኤክስቴንሽን አርሶ/አርብቶ አደር ትስስር ወርክሾፕ ቁጥር | |

## 10.4.4 የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ውጤት/Out come/ ዳሰሳ

የውጤት ዳሰሳ ግመታ እያንዳንዱ የአነስተኛ፣ የማህበረሰብ ኩሬ እና የጥቃቅን መስኖ አውታር ከተጠናቀቀ በኂላ እንዲካሄድ የሚፈለግ ሲሆን ዓላማውም በአነስተኛና ጥቃቅን መስኖ ግንባታዎችና በጓሮ ዙሪያ ግብርና አዳዲስ የፈለቁና ሠርቶ ማሳያ በተሠራባቸው ተስማሚ ቴክኖሎጂዎች ጠቃሚነታቸውንና ውጤታማነታቸውን፣ የመስኖ አውታር አመራርን፣ የተሻሻሉ የሰብል ዝርያዎች ልማትን እና የውሃ አመራርን ለመዳሰስና ለመገመት ነው፡፡ ይህ የውጤት ዳሰሳ ግመታ የሚከናወነው የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አቀራረብ ዘዴ በተግባር ላይ መዋልንና በመሠረታዊነት የሚፈለገው ዉጤት መገኘቱን ለማወቅ ነው፡፡ ውጤት የአጠቃላይ ድምር ሲሆን ነገር ግን ምናልባት ግኝቶች የወደፊት የመስኖ ልማት ስራን ለማሻሻል ጥቅም ላይ ከዋሉ ሊለዋወጥ ይችላል፡፡

ከላይ የተመለከትነው የሂደት አመላካች የሚያሳየው የሁኔታዎችን አካሄድ ብቻ እንጂ በጥልቀት የተከናወኑትን አይደለም፡፡ የተውጣጡ ወይም የተዋሃዱ አመላካቾች የሚዘጋጁት ሁኔታዎችንና የእነርሱን ዉጤት ወይም ምርት ለመረዳት ነው፡፡ የተመረጡ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን ውጤታማነት አመላካቾች አማካይ የሂሳብ ስሌት ማለትም የግንዛቤ አመላካች (የልማት ሠራተኞችን ማወቅ)፣ የጉብኝት አመላካች (በወር-2 ጊዜ የተካሄደ ጉብኝት ቁጥር) ፣ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር አመላካች (በአርሶ/አርብቶ አደር ማሳ ላይ ስብሰባ ማካሄድ) እና መደበኛ አመላካች (በተመሳሳይ ቀን ጉብኝት) የሁኔታን ተጽዕኖን ማሳየት ይችላል፡፡ ከዚህ በታች የተመለከቱት ጥቂት ወሳኝ የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን በጎ ተጽዕኖ/ውጤት ግምገማ አመላካቾች ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ-13፡-የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ክትትል አመላካቾች

| የመስኖ ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች የብቃት ክትትል አመላካቾች | |
|---|---|
